አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብዕ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ላይ ያለው ተጽዕኖ

# (በሰባተኛ ክፍል ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)

በ

እታገኝ ገደፋው ጌታሁን

መጋቢት 2016 ዓ.ም.

# መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ላይ ያለው ተጽዕኖ (በሰባተኛ ክፍል ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብዕ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህ ረምረቃ መርሀ ግብር


በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት


በእታገኝ ገደፋው ጌታሁን

የጥናቱ አማካሪ ዶክተር ጌታቸው እንዳላማው


አዲስ አበባ

ግንቦት 2016 ዓ.ም

# አበርክቶ

ይህ ጥናት በማያልቅ ፍቅሩና መልካምነቱ ከጎኔ ሆኖ በስራዬ እንድበረታ ላደረገኝ ውድ ባለቤቴ መ/ር ተሻገር ሉሌ እንዲሁም ገና በጨቅላ እድሜያቸው ድካሜን ለተጋሩኝ ለምወዳቸው ልጆቼ ለባህራን ተሻገር እና ኤማሁስ ተሻገር ይሁንልኝ!

# ምስጋና

በመጀመሪያ ደረጃ ይህን ጥናት ጀምሬ እንድጨርስ ጸጋውን ሁሉ ላበዛልኝ ለድንግል ማሪያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር፣ ምስጋናና አምልኮት ለዘለአለም ይግባው፡፡በመቀጠል እንደ አባትም እንደ ባለሞያም ሆነው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለጥናታዊ ጽሁፌ ገንቢ አስተያየት በመስጠት ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ በተጨማሪም በመረጥኩት የጥናት ርዕስ ዙሪያ ጠቃሚ መረጃዎችን እያበረከቱልኝ ስራዬን በከፍተኛ ተነሳሽነት እንድሰራ አቅም ለሆኑኝ ዶክተር አለማየሁ ተክለ ማርያም ክብርና ሞገስ ይስጥልኝ፡፡ በጥናቴ ሂደትም የሚያጋጥሙኝን ችግሮች በትጋት እንድወጣ ሀሳብ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ መምህሬ ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ ያለኝ አክብሮት የላቀ ነው፡፡ በነበረኝ የትምህርት ቆይታ እንደ ጓደኛና አማካሪ ሆኖ ጠቃሚ ምክሮችን ሲለግሰኝ ለቆየው ወንድሜ ደክተር አማረ ተሾመ ላቅ ያለ ምስጋና አለኝ፡፡ ትምህርቴን በምማርበት ጊዜም ሆነ ጥናቴን በማካሂድበት ወቅት ያጋጠመኝ የነበረውን የገንዘብ፣ የጊዜ፣ ቤተሰብ ወዘተ. ችግሮች ማለፍ የቻልኩት በዋናነት በባለቤቴ መ/ር ተሻገር ሉሌ እና በአጎቴ ወርቅነህ መኮነን ልዩ ድጋፍ መሆኑን ለአፍታም የምዘነጋው ባለመሆኑ ውድ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ እልፍ ነው፡፡ እንዲሁም ወጪዬን በከፊል በመሸፈን ለተባበረኝ ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ሌላው የምርምር ስራ በማካሂድበት ወቅት በቦታ ርቀትና በጊዜ ጥበት ምክንያት ስራዬን ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ችግሮችን ያለምንም መሰልቸት እየቀረፈች ለስኬት እስከበቃሁበት ቀን ድረስ ከጎኔ ላልተለየችኝ እህቴ መሰረት አዲሱ መውደዴ ወደር የለውም፡፡ በመጨረሻም ትምህርት ቤቶችን በማመቻቸት፣ተማሪዎችን በማዘጋጀት፣ ግብዓቶችን በማቅረብና ትምህርቱን በማቀላጠፍ ለተባበሩኝ ለቪክትሪና አልፋ መስማት ለተሳናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት መምህራን ለመ/ር ሞላ፣ ለመ/ርት የክቴ እና ለመ/ርት ብርሃኔ ምስጋናየ ይድረሳቸው እያልኩ አስካሁን የጠቀስኳቸውን ሁሉ ባለውለታዎቼን የሰጠኝ ልዑል እግዚአብሄርን በድጋሜ አመስግኜ ሀሳቤን ቋጨሁ ፡፡

# አህጽሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት ዋናኛ ዓላማ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ከማሻሻል አንጻር ያለውን ተጽዕኖ መመርመር ነው። ጥናቱ በአንድ የሙከራ ቡድን ንድፍ* (Single Group Experimental Design) *ላይ በመመስረት የተከናወነ ሲሆን ይህ የምርምር ንድፍም የጥናት ናሙናን በመምረጥ ሂደት የተጠኚዎች ቁጥር ለሁለት ቡድን ማለትም ለጥብቅ* (Control) *ለሙከራ* (Exprmental) *ሳይበቃ ሲቀር የሚመረጥ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር ከሚገኙ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች መካከል በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት ሲሆን በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የክፍል ደረጃዎች መካከል ለጥናቱ የተመረጠው ክፍል ሰባተኛ ነው። ትምህርት ቤቱንና የክፍል ደረጃውን በመምረጥ ረገድ አላማ ተኮር ናሙና* (purposive Sampling) *ተግባራዊ ተደርጓል። በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት ተማሪዎች በጠቅላይ ናሙና* (Comprehensive Sampling) *የተመረጡ ሲሆን በዚህም በክፍል ደረጃው የሚማሩ ሁሉም ተማሪዎች (ሰባቱም) በጥናቱ ተካተዋል። እነዚህ ተማሪዎች በቀጥታ በጥናቱ እንዲሳተፉ የተደረገበት ዋናው ምክንያት ቁጥራቸው ውስንና ከተጠቀሰው በላይ ባለመሆኑ ነው።ለጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ተግባር ላይ የዋሉት ፈተና፣ የጽሑፍ መጠይቅና የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። ፈተናው ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ሲሆን ዋነኛ አላማውም ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊትና በኋላ ያላቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን ለማወቅ ነው። የጽሁፍ መጠይቁም በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ትግበራ ወቅት የሚሞላ ሲሆን አላማው ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊትና በኋላ የነበራቸው የመጻፍ ክሂል ትምህርት የመማር ፍላጎት ምን ያህል ጉልህ ልዩነት እንዳሳየ ማረጋገጥ ነው። ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ ያገለገለው የቡድን ተኮር ውይይት ሲሆን አላማው ደግሞ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ ለተሰበሰቡት መረጃዎች ማጠናከሪያ ሀሳብ ማስገኘት ነው። በዚህም መሰረት የመጻፍ ክሂል ፈተናውና የጽሁፍ መጠይቁ በቅድመና ድህረ ትምህርት ትግበራው ላይ ለተጠኚዎች ቀርበው መረጃ የተሰበሰበባቸው ሲሆን የተገኘው ውጤትም በጥንድ ናሙና ቲ- ቴስት* (Paird sample t-test) *መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተሰልቶ* ( $P< 0.05$) *የሆነ የጉልህነት መለያ ውጤት ተገኝቷል። በአንጻሩ በቡድን ተኮር ውይይቱ የተሰበሰበው መረጃም በአይነታዊ የመረጃ*

*መተንተኛ ዘዴ ተተንትኖ በፈተናውና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውን የሚደግፍ ውጤት አስገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበው ከተተነተኑት መረጃዎች የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ መኖሩንና ተጽዕኖውም አዎንታዊ መሆኑን ነው፡፡*

# የይዘት ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

አበርክቶ ---------------------------------------------------------------------------------------------- i

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------------------- ii

አህጽሮተ ጥናት ------------------------------------------------------------------------------------ iii

የይዘት ማውጫ ------------------------------------------------------------------------------------ v

የሰንጠረዥ ማውጫ ---------------------------------------------------------------------------------- x

የአባሪ ማውጫ ------------------------------------------------------------------------------------ xii

የምስል ማውጫ ------------------------------------------------------------------------------------ xiv

**ምዕራፍ አንድ**

1.1. የጥናቱ ዳራ ---------------------------------------------------------------------------------1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት-------------------------------------------------------------------11

1.4. የጥናቱ አላማ -------------------------------------------------------------------------- 19

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ----------------------------------------------------------------------- 19

1.6. የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------- 20

1.7. የጥናቱ ውሱንነት ---------------------------------------------------------------------- 21

1.8. የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ተግባራዊ ፍቺ ---------------------------------------------- 23

**ምዕራፍ ሁለት**

የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት --------------------------------------------------------------- 25

2.1. የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች ከመጻፍ ክሂል ትምህርት አንጻር ሲቃኙ----------- 25

2.1.1. የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ------------------------------------------ 25

2.1.2. የግንዛቤ እድገት ንድፈ ሀሳብ ------------------------------------------------- 25

2.1.3. የተግባቦታዊ ንድፈ ሀሳብ ------------------------------------------------------------------ 26

2.2. የመጻፍ ክሂል ምንነት -------------------------------------------------------------------------- 27

2.2.1. የመጻፍ ክሂልን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የማስተማር

አስፈላጊነት ---------------------------------------------------------------------------- 28

2.2.2. መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት

ያለው ተግዳሮት ----------------------------------------------------------------------- 31

2.3. የመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ ምንነት ---------------------------------------------- 37

2.3.1. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት መስማት ለተሳናቸው

ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ---------------------------------------------- 40

2.4. የመማር ፍላጎት ምንነትና መገለጫዎች ---------------------------------------------- 53

2.4.1 ፍላጎት በትምህርት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ --------------------------------------- 54

2.5. የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ ------------------------------------------------------- 56

2.6. የጥናቱ ግንዛቤያዊ ማሕቀፍ ------------------------------------------------------------ 57

2.7. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ ------------------------------------------------------------------ 59

## ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ንድፍና ዘዴ -------------------------------------------------------------------------- 61

3.1. የጥናቱ ንድፍ ------------------------------------------------------------------------------- 61

3.2. የጥናቱ ዘዴ ------------------------------------------------------------------------------------ 61

3.2.1 የንሞና ዘዴ ---------------------------------------------------------------------------------- 61

3.2.1.1. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ------------------------------------------------------- 62

3.2.1.2. የክፍል ደረጃና የተጠኚ ተማሪዎች አመራረጥ ----------------------------------- 63

3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ------------------------------------------------------- 64

3.2.2.1 ፈተና -------------------------------------------------------------------------------- 65

3.2.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ -------------------------------------------------------------------- 69

3.2.2.3 የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ---------------------------------------------- 70

3.3. የናሙና ጥናት -------------------------------------------------------------------------- 71

3.3.1.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት -------------------------------------- 71

3.3.1.1. የፈተናዎች ትክክለኛነት ------------------------------------------------------- 72

3.3.1.2. የጽሁፍ መጠይቅ ትክክለኛነት -------------------------------------------------- 74

3.3.1.3. የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ትክክለኛነት ---------------------------- 75

3.3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነት --------------------------------- 75

3.3.2.1. የፈተናዎች አስተማማኝነት ----------------------------------------------------- 76

3.3.2.2. የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነት ---------------------------------------------- 76

3.3.3. ከናሙና ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች --------------------------------------------- 77

3.4. የማስተማር ትግበራ ---------------------------------------------------------------------- 82

3.5. የማስተማሪያ ይዘቶችና ተግባራት አዘገጃጀት ------------------------------------------ 86

3.6. የጥናቱ የአሰራር ቅደም ተከተል---------------------------------------------------------- 87

3.7. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ----------------------------------------------------------------- 91

3.8. የጥናቱ ተለዋዋጮች --------------------------------------------------------------------- 92

3.9. የምርምር ስነምግባራዊ ሁኔታዎች ------------------------------------------------------ 92

## ምዕራፍ አራት

የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ------------------------------------------------------------- 94

4.1. ዋና ጥናት------------------------------------------------------------------------------- 94

4.1.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና--------------------------------------------------------------- 94

4.1.1.1 የመጠናዊ መረጃዎች የአስተማማኝነት ደረጃ -------------------------------- 95

4.1.1.2 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ፓራሜትሪካዊ ስታትስቲክስ ፍተሻ -------------- 98

4.1.1.3. በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች

ውጤት ትንተና ---------------------------------------------------------------- 101

4.1.1.4. የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤቶች ትንተና ------ 111

4.1.1.5. የዓይነታዊ መረጃዎች ውጤትት ትንተና ---------------------------------- 112

4.1.1.5.1. የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ውጤት ትንተና--------------- 112

4.1.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ -------------------------------------------------------- 119

4.1.2.1. ከንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች አንጻር ------------------------------------ 120

4.1.2.1.1. አረፍተ ነገር መጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ---------------------------- 120

4.1.2.1.2. አረፍተ ነገር እንደገና የማቀናበር ንዑስ የመጻፍ ክሂል ---------- 120

4.1.2.1.3. ጅምር ሀሳቦችን የመጨረስ ንዑስ የመጻፍ ክሂል -------------------- 121

4.1.2.1.4. ስርዓተ ነጥቦችን የመጠቀም ንዑስ የመጻፍ ክሂል ----------------- 122

4.1.2.1.5. ድርሰት የመጻፍ ንዑስ ክሂል ------------------------------------------ 123

4.1.2.2. ከጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር ----------------------------------- 124

4.1.2.3. ከተማሪዎች የመማር ፍላጎት አንጻር ------------------------------------ 125

**ምዕራፍ አምስት**

**ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ፣ የመፍትሄ ሀሳቦችና ወደፊት ሊጠኑ የሚገቡ የትኩረት አቅጣጫዎች** ------------------------------------------------------------ 127

5.1. ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------ 127

5.2 መደምደሚያ --------------------------------------------------------------------- 129

5.3. የመፍትሄ ሀሳቦች ---------------------------------------------------------------- 132

5.4. ወደፊት ሊጠኑ የሚገቡ የትኩረት አቅጣጫዎች -------------------------------- 134

ዋቢ ጽሁፎች ------------------------------------------------------------------------------ 137

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

ሰንጠረዥ4.1. የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና የአራሚዎች

የስምምነት ደረጃ (በክሮንባኽ አልፋ ስሌት) ---------------------------------- 96

ሰንጠረዥ4.2. የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ

የአስተማማኝነት ደረጃ ( በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ ---------------- 97

ሰንጠረዥ4.3. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የውጤት ስርጭት

ወጥነነት (Normality) ------------------------------------------------------------ 99

ሰንጠረዥ4.4. የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የውጤት ስርጭት

ወጥነነት (Normality) ---------------------------------------------------------- 100

ሰንጠረዥ4.5. ጥቅልና ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች ትንተና -----------------101

ሰንጠረዥ4.6. አረፍተ ነገሮችን የመጻፍ ንዑስ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር -----------102

ሰንጠረዥ4.7. አረፍተ ነገሮችን የማቀናበር ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት

ትንተና ንጽጽር ---------------------------------------------------------------- 103

ሰንጠረዥ4.8. ጅምር ሀሳቦችን የመጨረስ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት ትንተና

ንጽጽር ---------------------------------------------------------------------- 104

ሰንጠረዥ4.9. ስርአተ ነጥቦችን የመጠቀም ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት

ትንተና ንጽጽር -------------------------------------------------------------- 106

ሰንጠረዥ4.10. ድርሰት የመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት

ትንተና ንጽጽር --------------------------------------------------------------- 107

ሰንጠረዥ4.11 የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ጥቅል የመጻፍ

ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር ---------------------------------------------110

ሰንጠረዥ4.12. የጽሁፍ መጠይቅ ውጤቶች ትንተና ንጽጽር------------------------------112

## የአባሪ ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

አባሪ ሀ፦ ለናሙናና ለዋና ጥናቱ የቀረበ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና --------------147

አባሪ ለ፦ በቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ

ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች የቀረበ የቅድመና

ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ (ናሙና ጥናት) --------------------------------152

አባሪ መ፦ በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ

ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች ተሻሻሎ

የቀረበ የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ (ዋና ጥናት) -----------155

አባሪ ሠ፦ በቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ

ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች የቀረበ

የቡድን ተኮር ውይይት(ናሙና ጥናት) ------------------------------------------- 159

አባሪ ረ፦ በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ

ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች

ተሻሽሎ የቀረበ የቡድን ተኮር ውይይት (ዋና ጥናት) --------------------------160

አባሪ ሰ፦ የናሙናና የዋና ጥናቱን የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ

ክሂል ፈተናዎች ለማረም ተግባር ላይ የዋለው

የJacobs et.al (1981) እና የHeaton (1988) መስፈርት ------------------------------162

አባሪ ሸ፦ የናሙናና የዋና ጥናቱን የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ

ክሂል ፈተናዎች ለማረም ተግባር ላይ የዋለው የChrstopher Gordon

(2001) የመገምገሚያ ሞዴል ከ Elizabeth (2009፡31) ------------------------------164

አባሪ ቀ፦ በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለተተኳሪው የክፍል

ደረጃ (7ኛክፍል) ተጠኚ ተማሪዎችን ለምታስተምር ወይም

ለሚያስተምር መምህር(ርት) የተዘጋጀ የስልጠና መመሪያ ---------------------168

አባሪ በ፦ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በመማሪያ ክፍል ውስጥ

ተግባራዊ የማድረጊያ መርህ -------------------------------------------------------176

አባሪ ተ፦ ተጠኚ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለማስተማር

የተዘጋጁ የጽህፈት ትምህርት ተግባራት --------------------------------------- 178

አባሪ ቸ፦ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ የአጠቃላይና

የንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች (የናሙና ጥናት) ------------------------------ 218

አባሪ ኀ፦ በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ከተጠኚ ተማሪዎች በጽሁፍ

መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች (የናሙና ጥናት) ------------------------------------- 220

አባሪ ነ፦ ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች

ላይ ያስመዘገቡት የአጠቃላይና  የንዑሳን የመጻፍ ክሂል

ውጤቶች (የዋና ጥናት) --------------------------------------------------------------- 221

አባሪ ኘ፦ በቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች

(የዋና ጥናት) ---------------------------------------------------------------------- 224

# የምስል ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

ምስል አንድ፦ የመማር ፍላጎት፣ ማስተማሪያ ዘዴና ውጤት ያላቸው ዝምድና ----------- 55

ምስል ሁለት፦ የጥናቱ አተገባበር ንድፍ ----------------------------------------------------------- 57

ምስል ሶስት፦ የሙከራ ጥናቱ ቅደም ተከተላዊ ተግባራት ------------------------------------- 90

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ተቀዳሚ አላማ ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ እንዲሁም የስነልሳንና የሥነ ጽሁፍ እውቀት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካትም በመማር ማስተማሩ ሂደት በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከተጠቀሱት መሰረታዊ ክሂሎች መካከል የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ስለሆነው የመጻፍ ክሂል ብንመለከት ክሂሉ ካለው ውስጣዊ ውስብስብ ባህሪና ውጫዊ ተግዳሮቶች አኳያ የትምህርት ሂደቱ ከባድና አስቸጋሪ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ ይህንንም ምሁራን ለክሂሉ ብያኔ በሰጡበት ወቅት በጽሁፋቸው ካሰፈሩት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ Byrne (1996) መጻፍ ሀሳብን በትዕምርት በመወከል ወረቀት ላይ የማስፈር ሂደት ብቻ ሳይሆን ከድምፅ ወካይ ፊደላት ድምር ያለፈና ትርጉም ባላቸውና በጥንቃቄ በተደራጁ መዋቅሮች አማካኝነት መልዕክትን ለማስተላለፍና ተራክቦን ለመመስረት የሚከወን እንደሆነና በመማር ማስተማር ሂደትም ከሌሎች ክሂሎች በተለየ ሁኔታ በቀላሉ የማይለመድና ከፍተኛ ድካምን የሚጠይቅ መሆኑን በመግለጽ ውስብስብነቱን አመላክተዋል፡፡ በተመሳሳይ መጻፍ አካላዊና አዕምሯዊ ቅንጅትን የሚጠይቅና እንደ ይዘት፣ መዋቅር፣ የቃላት ምርጫ፣ የሀሳብ አደረጃጀት (አንድነት፣ ግጥምጥምነት፣ ተከታታይነት) የመሳሰሉትን በርካታ አላባውያን በውሰጡ አካቶ የያዘ ከመሆኑ በተጨማሪ በአተገባበር ሂደቱም ማቀድ፣ ማደራጀት፣ ማርቀቅና መከለስ በተባሉ ቅደም ተከተላዊ ቅንጅቶች የሚመራ መሆኑ በአጭር ጊዜና በቀላሉ የሚጨበጥ እንዳይሆን እንዳደረገው Nunan (1989)፣ Byrne (1988) እና Richard and Rodgers (2001) ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ምሁራን ስለመጻፍ ክሂል ትምህርት ውስብስብ ባህሪይ አስተያየቶችን ይሰንዝሩ እንጂ ሂደቱን ለማቅለል በጥናት ተፈትሸው ተግባር ላይ እየዋሉ ያሉ የማስተማሪያ ብልሃቶች መበራከታቸውን ከጥናቶች መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ ከማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች አንጻር የሚያጋጥመውን ችግር ለመቅረፍ በየዘመኑ አዳዲስ አቀራረቦች ፈልቀው ሲሰራባቸው ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል ሂደት ተኮር፣ ውጤት ተኮርና ዘውግ ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች በዋናነት የሚጠቀሱ እንደሆኑ Nunan (1989)፣ Raims (1983)፣ Richard and Rodgers (2001)፣ Brookes and Grundy (1990) ያስረዳሉ፡፡ የእያንዳንዱን አቀራረብ ባህሪይ ጠቅለል በማድረግ ቀጥሎ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

የመጀመሪያው ውጤት ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ Nunan (1989) እንደሚገልጹት አቀራረቡ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየና አሁንም በተወሰነ መልኩ ተግባር ላይ እየዋለ ያለ ልማዳዊና ነባር ክንውኖችን ያካተተ ሲሆን፣ዋነኛ ዓላማውም ተማሪዎች በቋንቋው መዋቅር ወይም ህግጋት ላይ ተመስርተው የመጻፍ ክሂል ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ማስቻል ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ የትምህርቱ ዓላማ ከግብ መድረሱ የሚረጋገጠው ተማሪዎች በሚጽፉት የመጨረሻ ድርሰት ትክክለኛነት ነው፡፡ በመሆኑም በትምህርቱ ሂደት ለሚፈጠሩ ስህተቶች የእርምት ዕድል ብዙም አይሰጥም፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች ሞዴል ጽሁፍን መሰረት አድርገው ከስህተት የፀዱ ቃላትን፣ ዐረፍተ ነገሮችን፣ አንቀፆችን፣ ስረዓተ ነጥቦችን ወ.ዘ.ተ አደራጅተው አቻ ጽሁፍ ሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ የአቀራረቡ አበይት ተግባራት ናቸው (Richard and Rodgers 2001፣ Hedge 1988 and Raimes 1983)፡፡ ውጤት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማሻሻል ከሚረዱ የመጻፍ ተግባራት ይልቅ በቋንቋው ቅርጽና ሰዋስዋዊ ህግጋት ላይ ባተኮሩ ይዘቶች መጠመዱ፣ የመማር ማስተማር ክንውኑም ቢሆን በመምህሩ የበላይነት የሚመራ መሆኑ ወ.ዘ.ተ በደካማ ጎን እንዲተች አድርጎታል፡፡ በመሆኑም አቀራረቡ ቀስበቀስ በሂደት ተኮር እንዲተካ ሆኗል፡፡

ሂደታዊ አቀራረብ በውጤት ተኮር ይነሱ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ አዲስ መልክ ይዞ የመጣ ነው፡፡በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች በስተመጨረሻ ከሚያዘጋጁት ጽሑፍ ይልቅ ጽሁፉን ለማቀነባበር በሚያልፉባቸው ሂደቶች ላይ ይተኮራል፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ምን ጻፉ? ሳይሆን እንዴት ጻፉ? የሚለው ጥያቄ እንዲመለስ ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም የአቀራረቡ ዋነኛ አላማ ትክክለኛ የሆነ የፅህፈት ስራ ማስገኘት ሳይሆን ተማሪዎች በልምምዱ ወቅት የሚሰሯቸውን ስህተቶች በሂደት ቀንሰው ራሳቸውን የቻሉ ጸሀፊዎችና ገምጋሚዎች እንዲሆኑ ማድረግ እንደሆነ Ferris (2003) ያስረዳሉ፡፡ ሂደታዊ አቀራረብ ከውጤታዊ አቀራረብ አንጻር ሲታይ የቋንቋውን ቅርፅና መዋቅር ከጠበቁ የጽሁፍ ውጤቶች ይልቅ ወደዚያ ሊያደርሱ በሚችሉ ሂደቶች ላይ የሚያተኩር መሆኑና ተማሪዎችን ከመምህሩ ጣልቃ ገብነት አላቆ ራሳቸውን ችለው የመጻፍ ልምምድ እንዲያደረጉ እድል መስጠቱ በበርካቶች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደረገ ቢሆንም በአንጻሩ ተማሪዎች በስተመጨረሻ በሚጽፉት ድርሰትና ሰዋስዋዊ ጉዳዮች ላይ ምንም ትኩረት አለማድረጉ በሌሎች ወገኖችም ዘንድ ትችት እንዲነሳበት ሆኗል (Nunan 1989፣ Raimes 1983፣ Seow 2002 ፣ Richard and Rodgers 2001) ።

ሶስተኛው አቀራረብ ዘውግ ተኮር ሲሆን በአብዛኛው ከውጤታዊ አቀራረብ ጋር በሚያመሳስሉት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ Nunan (1989)፣ Richard and Rodgers (2001) እና Raimes (1983) እንደሚሉት አቀራረቡ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ስኬታማ የሚሆነው ተግባራት ከማህበራዊ አውዶች ጋር ተዋህደው መቅረብ ሲችሉ እንደሆነ ያምናል፡፡ በመሆኑም በቋንቋው ማህበራዊ አጠቃቀም ላይ የተመሰረቱ ይዘቶችንና ክንውኖችን ወደ መማሪያ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ እያገናዘቡ እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ከማህበራዊ አውድ ጋር አስተሳስሮ በማስተማር ረገድ አቀራረቡ ያለው አቋም የሚያስመሰግነው መሆኑ ቢታወቅም የተማሪዎችን የአፍልቆት ሚና በማሳነስ ብዙውን ነገር ከውጪው አለም እንዲቀዱ የሚያበረታቱ አካሄዶች የሚታዩበት መሆኑ ደግሞ እንደሌሎች አቀራረቦች ሁሉ ትችት እንዲነሳበት እንዳደረገው Nunan (1989) Richards (1990) እና Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ሶስቱ አበይት የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች በተለያዩ ጊዜያት በተነሱ ስነ-ትምህርታዊ አስተሳሰቦች ላይ ተመስርተው ተግባር ላይ የዋሉ እንደመሆናቸው መጠን በአተገባበራቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ በዚህም በትምህርት ሂደቱ ላይ ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን እየተመዘነ ምሁራዊ ትችት እየተሰነዘረባቸው እንደሚገኝ ከድርሳናት መመልከት ይቻላል (Nunan 1989፣ Hedge 1988፣ Raimes 1983፣ Richard and Rodgers 2001)። ይህ ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት አንድና ብቸኛ መንገድ አለመኖሩን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ McLaughlin (1991)፣ Pincas (1982) እና Hillocks (1986) በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ ማስተማሪያ አቀራረቦች ላይ ባደረጓቸው ጥናቶች አንድን ቋንቋ በማስተማር ረገድ የበለጠና የተሻለ የሚባል ብቸኛ የማስተማሪያ ዘዴ አለመኖሩንና በአንጻሩ የቋንቋ ትምህርት ሂደቱን በተሻለ መልኩ ለማከናወን ቅንጅታዊ የማስተማሪያ ስልትን መከተል ተገቢ መሆኑን የሰጡት ትንታኔም ይህንን ሀሳብ ያጠናክረዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም Harmer (1996) የትኞቹም የማስተማሪያ ዘዴዎች ቢሆኑ በተናጠል ሲተገበሩ ድክመት ያለባቸው በመሆናቸው ከየዘዴዎቹ ጠንካራ ጎን በመወሰድ ሚዛኑን የጠበቀ ቅንጅታዊ ስልት ፈጥሮ ማስተማር ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል ይመክራሉ፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድም አሁን ላይ እየተለመደ የመጣና ለበርካታ ቅንጅታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች መገኘት ምክንያት እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የማስተማሪያ ዘዴዎችን አቀናጅቶ በማስተማር ረገድ ተግባር ላይ እየዋሉ ካሉት ዘዴዎች መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ (Intractive WritingTeaching Mthod) አንዱ ሲሆን ከማህበረ ባህላዊ

(ግንባታውያን) የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ ጋር ተጋርቶ ያለውና ቀደም ሲል ይሰራባቸው በነበሩት ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል አቀራረቦች ቅንጅት ላይ ተቃኝተው በሚተገበሩ የማስተማሪያ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ እንደሆነ ድርሳናት ያስረዳሉ (Brown 2001፣ McCarrier and Pinnell 1994፣ ግርማ 1990 )።

መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በውጤታዊና ሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘውጎች ላይ ተመስርቶ ሲቀርብ ለምሳሌ በውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት ይሰጠው እንደነበረው በሞዴል ጽሁፎች ላይ መመስረት፣ በጽሁፍ ሂደት ስለሰዋስው ስርኣት አጠቃቀም መጨነቅና ለትክክለኛ ውጤት መጻፍ ወ.ዘ.ተ የሚሉ አስተሳሰቦችን በማስቀጠልና በሂደት ተኮር አቀራረብም ይሰራበት እንደነበረው "ሂደታዊ መጻፍ ለተግባቦታዊ ችሎታ" በሚለው መርህ መሰረትነት የመጻፍ ትምህርት ልምምዱ ተማሪዎችን የተግባሩ መሪ ተዋንያን በማድረግ ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ማርቀቅ፣ ማደራጀት፣ መከለስና አርትኦት መስጠት በተባሉት ሂደታዊ ክንውኖች ላይ እንዲያተኩር በማድረግ መሆኑን McCarrier and Pinnell (1994)፣ Hillocks (1986)፣ Hussni (2014)፣ Button, Johnson, Furguson (1996)፣ Fountas, McCarrier and Pinnell (2000)፣ Tammie (2003)፣ Salah (2010) ፣ግርማ (1990) በጥናቶቻቸው ካሰፈሯቸው ሀሳቦች መረዳት ይቻላል፡፡ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የውጤታዊና ሂደታዊ አቀራረቦች ቅንጅት ከመሆኑም ባሻገር የመጻፍ ክሂል ትምህርት ተግባር ከመምህራንና ተማሪዎች የጋራ ተራክቦ አንጻር ተሳልጦ መቅረብ እንዳለበት የሚያምንም ጭምር ነው፡፡ ይህም ዘዴው አሁን ካለው ዘመናዊው የቋንቋ አስተምሮ ጋር አዎንታዊ የሆነ ትስስር እንዲኖረው ያደረገ መሆኑን McCarrier and Pinnell (1994)፣ Fountas.et.al (2000) ያስረዳሉ፡፡

መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በየትኛውም የዕድሜ ክልልና የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ቋንቋ መስማት የሚችሉ ተማሪዎችን ለማስተማር ከማገልገሉም ባሻገር መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ተመራጭ የማስተማሪያ መንገድ እንደሆነ በጥናት ፈትሸው የገለጹ ምሁራን Wolbers (2008) ፣ Wolbers, Dostal, and Stephenson (2012) Wolbers, Dostal and Graham (2016)፣ Elizabeth (2009)፣ Dostal and Wolbers (2014) ፣ Flo and Bill (2009) ያስረዳሉ፡፡ በእርግጥ የማስተማሪያ ዘዴው ከዘመናዊ የቋንቋ የትምህርት አቀራረብ እሳቤዎች መምጣት ጋር ተያይዞ ከ1980ዎቹ ወዲህ ባለው ጊዜ በማስተማሪያነት ማገልገል እንደጀመረ Brown (2001) McCarrier and Pinnell (1994) ቢገልጹም መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ሆኖ በልዩ አቀራረብ ማገልገል

የጀመረው ግን በ1991 ዓ.ም በኦሃዮ ዩኒቨርስቲ ባሉ መምህራን እንደሆነ Elizabeth (2009) በጥናታቸው ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላም የማስተማሪያ ዘዴውን ፋይዳ መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎችና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ጋር በማያያዝ በተለያየ መንገድ ያጠኑ ተመራማሪዎች ያሉ ሲሆን Elizabeth (2009)፣ Wolbers (2008)፣ Flo and Bill (2009)፣ Wolbers.et.al (2012)፣ Wolbers.et.al (2016) ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ አጥኚዎች መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና የመረመሩበት መንገድ የተለያየ ቢሆንም እንኳን በግኝቶቻቸው ካሰፈሯቸው ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው ዘዴው ከትንንሽ እስከ ትልልቅ የሚደርሱ የቋንቋ መዋቅሮችን (ከድምጽ እስከ አንቀጽ) ለማስተማር ማገዙን፣ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የቋንቋ ችሎታ እንዲሁም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የመስማት ችግር ባላቸው ተማሪዎች ዘንድ ማለትም ሙሉ በሙሉ በማይሰሙ (Deaf) እና በከፊል በሚሰሙ (Hard of Hearing) የተማከለ የትምህርት ሁኔታ እንዲኖር ማስቻሉን፣ እንዲሁም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የክፍል ደረጃ (ከመዋዕለ ህጻናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም) ያሉ ተማሪዎችን ለማስተማር ምቹ መሆኑን አሳይተዋል (Elizabeth 2009፣ Wolbers 2008፣ Flo and Bill 2009፣ Wolbers.et.al 2012፣ Wolbers.et.al 2016)።

በተጨማሪም Wolbers (2008)፣ Flo and Bill (2009)፣ Wolbers.et.al (2012)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Wolbers.et.al (2016) መስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርት በሂደትና በውጤት ላይ ባተኮረ ተግባራዊ ልምምድ እንዲሁም በመምህራንና በተማሪዎች የጋራ ተራክቦ መቃኘት እንዳለበት በጽኑ ከማመኑ ባሻገር ለሌሎች ተጓዳኝ ክሂሎች ማለትም ለማዳመጥ፣ ለመናገርና ለማንበብ መዳበር የጎላ ሚና ያለውና ተማሪዎችን እለት በእለት በሚከናወኑና በሚመዘኑ ልምምዶች ውስጥ እንዲያልፉ የሚያደርግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተለይ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ማዳመጥን ከሚሹት ይልቅ እይታንና ተግባራዊ ተሳትፎን በሚያጎሉ ተግባራት ላይ በማተኮር በትምህርቱ ሂደት የሚገጥማቸውን የተረድኦት ችግር ለመቅረፍ አማራጭ የማስተማሪያ ስልቶችን ለመተግበር ዘዴው ምቹ መሆኑን Wolbers (2008) እና Elizabeth (2009) ይናገራሉ፡፡

ሌላው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ሆኖ ሲቀርብ ለየት ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል በዋናነት የሚነሳው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመለማመጃነት ለሚቀርቡት ለእያንዳንዱ የጽህፈት ተግባራት እይታዊ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመጠቀም የሚያስገድድ መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ቃላትን እንዲጽፉና ፍቺዎቻቸውን እንዲገነዘቡ ያለመ የጽህፈት ትምህርት በመስተጋብራዊ ዘዴ ሲቀርብ የቃላት ካርታና ውህድ ስዕሎችን፣ አስረጅ ሞዴሎችን፣ አገናኝ ፅንስሀሳቦች ወይም Elizabeth (2009) በእንግሊዝኛው አጠራር ‘’Knowledge modell of vocabulary acquisition” የሚሉትን ስልት መምህራን እንዲጠቀሙ ይጋብዛል፡፡መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የጽሁፍ ሀሳብን ለመረዳት ከምልክት ቋንቋ ገለጻ ይልቅ እይታዊ መሳሪያዎችን የሚፈልጉ እንደመሆናቸው መጠን ከመጻፊያ መሳሪያዎች ጀምሮ ትኩረታቸውን የሚስቡ ቀለማትን መጠቀም፣ በቪዲዮ የተቀረጹ አስረጂ ተግባራትን ማቅረብና ተማሪዎች የተመለከቱትን ድርጊት ወደ ሀሳብ በመለወጥ አረፍተ ነገር እንዲጽፉና እንዲያደራጁ ማድረግ በመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡ በእጅ የሚገጣጠሙ የፊደላት ገበታን ተጠቅሞ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን ተማሪዎች እንዲጽፉ ማስቻል የመስተጋብራዊ ዘዴ ትግበራ አካል ነው፡፡

በተጨማሪም Brown (2001)፣ McCarrier and Pinnell፣ (1994)፣ ግርማ (1990) እንደሚሉት መስማት የሚችሉ ተማሪዎች ለማስተማር በመስተጋብራዊ ዘዴ የሚቀርብ የጽህፈት ትምህርት ማቀድ፣ማደራጀት፣ መጻፍ፣ አርትኦት ማድረግ፣ መከለስና ማሳተም የተባሉ የትግበራ ደረጃዎችን ይከተላል፡፡ በአንጻሩ ግን የማስተማሪያ ዘዴው መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ማስተማሪያነት ሲውል የጽህፈት ትምህርት ተግባራት በአደረጃጀታቸው ከፍ ብለውና የተማሪዎቹን የመማር ሁኔታ ያገናዘቡ አጋዥ መሳሪያዎች አካተው ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ የጽህፈት ትምህርት ተግባር ደረጃዎች ስድስት ሲሆኑ Wolbers (2008) እና Williams (2011) ‘’POSTER’’ ወይም ‘’POWTER’’ ይሉታል። ምህጻሩ ሲብራራም ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መጻፍ (መግለጽ)፣ መተርጎም፣ አርትኦት ማድረግና መከለስ ናቸው፡፡ የWolbers (2008) እና Williams (2011) ‘’POSTER’’ ወይም ‘’POWTER’’ የጽህፈት ትምህርት ደረጃን ከላይ በBrown (2001)፣ McCarrier and Pinnell፣ (1994)፣ ግርማ (1990) ከቀረበው ጋር ለየት የሚያደርገው መተርጎም የተባለውን ትግበራ እንደ አንድ እርከን ማካተት መቻሉ ነው፡፡ መተርጎም በልምምዱ ሂደት ተማሪዎች ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በምልክት ቋንቋ አማካኝነት የሚያደርጉት የሃሳብ ልውውጥ ሲሆን በስራቸው ላይ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡

መስተጋብራዊ ዘዴ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለን ጤናማ የመማር ማስተማር ግንኙነት ባስጠበቀ መልኩ ተማሪ መራሽ የትምህርት ሂደት እንዲጎለብት የሚያበረታታና መምህራንም ከተለመደው የግምገማ አስራር ወጣ ብለው ግለማህደረ ምዘና (Portfolio) የቅድመ ምዘና ተግባር ንድፍ (Rubrics) ግለ ግምገማ መከታተያ ቅጽ (Self assesment cheek list) የመሳሰሉትን ግብኣቶች አዘጋጅተው በመተግበር ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲማማሩ፣ እንዲገማገሙ እንዲሁም ያሉበትን ወቅታዊ ደረጃ አውቀው ለቀጣዩ የትምህርት ክንውን ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ የሚያበረታታ ነው፡፡ እንደዚሁም መምህራንና ተማሪዎች ተግባርን እኩል የሚጋሩበት በመሆኑም የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜትና የመማር ፍላጎት በእጅጉ እንዲጨምር የሚያደርግ እንደሆነ Flo and Bill (2009) በጽሁፋቸው በስፋት ይተነትናሉ፡፡

Wolbers (2008) ፣Wolbers.et.al (2012)፣ Sheilla (2011) እንደሚሉት የመጻፍ ክሂልን በመማር ሂደት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከሌሎች መስማት ከሚችሉት ተማሪዎች በላቀ ሁኔታ የአጻጻፍ ስርዓት አጠባበቅ ክፍተቶችን ያሳያሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ አረፍተ ነገሮችን በመመስረት ሂደት ባለቤትን፣ ግስንና ተሳቢን የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው ሁኔታ አስማምቶ አለመጻፍ፣ቃላትን በማዋቀር ረገድም የጊዜ፣ የቁጥር፣ የጾታ አመልካች ምዕላዶችን በትክክለኛው ቦታቸው አስማማቶ ያለመጻፍና ከሰዋስው ስርዓት አጠቃቀም ያፈነገጡ አገላለጾችን መጠቀም በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን በተጨማሪም ስርኣተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው አለመገልገል፣ ፊደላትን በትክክለኛው ቅርጻቸው አለመጻፍና ሀሳብን የማደራጀት ችግሮች በስፋት አሉባቸው፡፡

እነዚህ የመጻፍ ክሂል ችግሮች እንግሊዝኛ ቋንቋን መሰረት አድርገው በተጠኑ ጥናቶች ይገለጹ እንጂ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን በሚማሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ላይም በተመሳሳይ እንዳለ ተተኳሪ ተማሪዎችን በማስተማር የረጅም ጊዜ ልምድ ካላቸው መምህራን ጋር ከተደረገ ኢ- መደበኛ ውይይት፣ ከተመራማሪዋ ምልከታና ከአማርኛ ምዘና ውጤታቸው መረዳት ተችሏል፡፡ እንደ Hinkel (2011) አገላለጽ ደግሞ አንድ ጽሁፍ አገልግሎት መስጠት የሚችለው ከእነዚህ ስህተቶች የጸዳ ሆኖ ሲቀርብ በመሆኑ ተተኳሪ ተማሪዎቹ ካለባቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ውስንነት ተሻሽለው ወደ ትክክለኛው የጽሁፍ ስራ አስኪመጡ ድረስ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ሊሆን እንደሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በተለየ የመማሪያ ክፍል አውድም (በልዩ[1]) ሆነ ከሌሎችመስማት ከሚችሉት ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው (አካቶ[2]) ሲማሩ ትምህርቱ የሚቀርብበት መንገድ ከመማር ሁኔታቸው ጋር የሚጣጣም ካልሆነ በውጤታቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ ሊፈጠር እንደሚችል Elizabeth (2009)፣ Wolbers (2008)፣ እና Flo and Bill (2009) ያስረዳሉ፡፡ እንደ ተመራማሪዎቹ ገለጻ ተማሪዎቹ በየትኛውም የትምህርት አውድ ቢገኙ ማለትም በልዩ የመማሪያ ክፍልና መስማት ከሚችሉት ጋር ተቀላቅለው ሲማሩ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ለእያንዳንዱ የትምህርት ተግባር አማራጭ የማስተማሪያና የመመዘኛ ስልቶችን፣ ተጨማሪ ልምምዶችንና መሳሪያዎችን ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ለእነዚህ ተማሪዎች የሚቀርበው የመጻፍ ክሂል ትምህርት በቅድመ ቋንቋ ለመዳ እድሜቸው ሊያዳብሩ ያልቻሉትን የቋንቋ ችሎታ ክፍተት ሊሞላ በሚችል መልኩ መሆን ስላለበት ነው፡፡ እንደሚታወቀው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ባላቸው የአኗኗር ዘይቤ ምክንያት ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች ያላቸው የተጋልጦ መጠን ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት በቅድመ ትምህርት ዕድሜያቸው ሊያዳብሩት የሚገባቸውን የቋንቋ ችሎታ ሳይዙ ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደቱ ላይ በርካታ ተግዳሮቶች እንዲያጋጥማቸው እድል ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎቹ የሚቀርበው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ቀድመው በሚናገሩትና በሚያውቁት ቋንቋ ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑና እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተደርጎ ስለማይቆጠር ትምህርቱ የሚቀርብበት መንገድ በተቻለ መጠን የመማር ሁኔታቸውንና የሚማሩትን ቋንቋ ደረጃ (የአፍ መፍቻ ወይም የሁለተኛ) ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል (Wolbers 200)፣ Wolbers.et.al 2016 እና Flo and Bill 2009)፡፡

እንደተመራማሪዎቹ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተስማሚነት ችግር ከተማሪዎች ውጤት ባሻገር የመማር ፍላጎታቸውንም በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡ ድርሳናት እንደሚያስረዱት የመማር ፍላጎት ከትምህርት ውጤት የተጋመደ ነው፡፡ ጥሩ የሆነ የመማር ፍላጎት በሌለበት ጥሩ የሆነ የትምህርት ውጤት እንደዚሁም ስኬታማውጤት ባልተገኘበት ትምህርት ደስታ ያለበት መማርን መጠበቅ አዳጋች ነው፡፡

---

[1] መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መስማት ከሚችሉ ተማሪዎች ተለይተው የሚማሩበትን የመማሪያ ክፍል አውድን ይወክላል (Exclusive Class)

[2] መስማት የተሳናቸውና መስማት የሚችሉ ተማሪዎች በጋራ የሚማሩበትን የመማሪያ ክፍል ተጋርቶ ያመለክታል (Inclusive Class)

ምክንያቱም ፍላጎት አንድና ነጠላ ከሆነ የስነ ልቦና ሀሳብነት ፍቺው በዘለለ ሂደታዊ በሆነ መልኩ በግለሰቦች ዘንድ ያለን እምቅ ሀይል የመጠቀምና ያለመጠቀም ግፊት በመሆኑ ነው (Folling and Hartinger 1998)።

የፍላጎት ጽንሰ ሀሳብ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በስነ ልቦና ትምህርት ትኩረት ከተሰጣቸው ሀሳቦች አንዱ የነበረ ሲሆን ከመገለጫ መንገዱ አንጻር ሲገለጽም ውስጣዊ (ነባራዊ) እና ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል Harp and Mayer (1997)፣ Frick (1992) ያስረዳሉ፡፡ ሁኔታዊ ፍላጎት በአካባቢያዊ አነሳሽ ምክንያት ማለትም ሳቢና ማራኪነት ሳቢያ ሊፈጠር የሚችል ነው፡፡ ነባራዊ ፍላጎት ደግሞ በነገሮች ላይ በሚኖር የረጅም ጊዜ ምልከታና ግንዛቤ የሚመጣ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ስሜት ነው፡፡ በተመሳሳይ ፍላጎትን ከአፈጣጠሩ አንጻር ተመልክተው Dewey (1913) ቀጥተኛና ኢ- ቀጥተኛ ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል የገለጹ ሲሆን ቀጥተኛ ፍላጎት በድርጊትና በውጤት መካከል ሊኖር በሚገባ ግንኙነት ውስጥ የማይከሰት ወይም በቅጽበታዊ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚታይ የአሁናዊ ስሜት እንደሆነና ኢ-ቀጥተኛ ፍላጎት ደግሞ በተቃራኒው በሂደትና በውጤት ላይ በመመስረት የሚመጣ ዝግመታዊ የመሻት መጠን መሆኑን ያብራራሉ፡፡ ይሁንና ፍላጎትን ሁሉም ምሁራን በተለያዩ ስያሜዎች ይግለጹት እንጂ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚለያይ አለመሆኑን ከብያኔቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

የፍላጎት ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔን በማብራራት ረገድ ምሁራን የሚሰነዝሯቸው ሀሳቦች በአገላለጽ ይለያዩ እንጂ በሚያተኩሩባቸው ይዘቶች ላይ ግን የጎላ ልዩነት አይታይም፡፡ በመሆኑም ፍላጎት ከብዙ ምሁራን አተያይ አንጻር ጠቅለል ብሎ ሲገለጽ በውጫዊ ተነሳስቶ የሚፈጠር ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) ፍላጎት እና በአእምሮ ውስጥ ከሚኖር ግለሰባዊ ግንዛቤ አኳያ የሚፈጠር ውስጣዊ (ነባራዊ) ፍላጎት በመባል ይታወቃል፡፡ ፍላጎት ከማህበራዊነት፣ ከግለሰባዊነት፣ ከስነ ትምህርት ወዘተ. ጋር ባለው ጥብቅ ቁርኝት ይጠናል እንዲሁም ይተነተናል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ፍላጎት የተመረመረው ከማስተማሪያ ዘዴ አንጻር እንደመሆኑ መጠን ድርሳናትን በማጣቀስ ጥቂት ሀሳቦችን ለማነሳት ይሞከራል፡፡ Harp and Mayer (1997) እንደሚሉት ትምህርታዊ ፍላጎት ውስጣዊ (ነባራዊ) እና ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) ተብለው በተጠቀሱት ሁለት የፍላጎት ገጽታዎች ይገለጻል፡፡ ሁኔታዊ ፍላጎት ከትምህርት ተግባራት፣ ከማስተማሪያ ዘዴዎችና ግብዓቶች፣ ከትምህርት ቤት ሁኔታዎችና በአጠቃላይ ከአካባቢ ጋር በተገናኘ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት የሚኖራቸው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ስሜት ሲሆን ውስጣዊ (ነባራዊ)

ፍላጎት ደግሞ ካለምንም ውጫዊ ግፊትና አነሳሽ ምክንያት ማለትም የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ ግብዓቶች ወዘተ. ተማሪዎች ወደፊት እንዲሆኑ ከሚያልሙት ነገርና ከማንነታቸው ጋር በተቆራኘ መልኩ ለነገሮች በሚሰጡት ዋጋ ወይም ግለሰባዊ አተያይ ላይ ተመስርቶ የሚንጸባረቅ ስሜት ነው (Harp and Mayer 1997)። ከዚህም በመነሳት ፍላጎት በሰዎች ግላዊ ማንነትና በአካባቢያቸው በሚያደርጉት መስተጋብር የሚፈጠር የመሻት ክስተትና መጠን ነው ማለት ይቻላል። ስነ ትምህርታዊ ፍላጎት ምንጩ ምንም ይሁን ምን በተማሪዎች ውጤት ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ Hidi and Berndorff (1998)፣ Andreas (1999) Sauer (2012) Barbara and Judith (2002)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በሚወዱት የማስተማሪያ ዘዴ ማስተማርና በተግባራትም ላይ የሚመርጧቸውን ግብዓቶች ማለትም መጻህፍትን፣ ማስተማሪያ ቁሶችን ወዘተ. በማቅረብ ማለማመድ የመማር ፍላጎታቸውን ከፍ ከማድረጉ ጎን ለጎን በውጤታቸው እንዲልቁም ከፍተኛ ሚና አለው። እንደ ምሁሩ ምልከታ በአብዛኛው በመምህራን የበላይነትና ብቸኛ ተግባሪነት ከሚመራ የመማር ማስተማር ሂደት ይልቅ በተማሪዎች የእርስ በእርስ መስተጋብር የዳበረ አቀራረብ በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ውጤታቸው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው። በእርግጥ የጋራ መስተጋብር ሲባል በተማሪዎች መካከል ያለውን ብቻ ማለት አይደለም በአንጻሩ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለ ስነ ትምህርታዊ ቅርርብንም የሚያካትት ነው። በጥቅሉ የማስተማሪያ ዘዴ፣ በመማር ፍላጎት የመማር ፍላጎት ደግሞ በትምህርት ውጤት ላይ ኖራቸው አንዳቸው በሌላኛው ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ካቀረቡት ሀሳብ መረዳት ይቻላል። በተለይ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በማስተማር ረገድ የመማር ፍላጎታቸውን በሚጨምሩ፣በራስ የመተማመን ስሜታቸውን በሚገነቡና ችሎታቸውን በሚያሻሽሉ የትምህርት አቀራረቦች ላይ ብርቱ ስራ መስራት ይጠበቃል።

እስካሁን መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርትን እንዴት ቢማሩ ችሎታቸው ሊሻሻል ይችላል? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ረገድ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን ትኩረት አድርገው የተካሄዱ የውጪ ሀገር ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል (Wolbers 2008 ፣ Wolbers, Dostal, and Stephenson 2012፣ Wolbers, Dostal and Graham 2016፣ Elizabeth 2009፣ Dostal and Wolbers 2014 ፣ Flo and Bill 2009) ። ለዚህ

ጥናትም መነሻ ሆኑት እነዚህ ምርምሮች የደረሱበት ውጤት በብዛኛው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ መስተጋብራዊ ዘዴ በባህሪው በእርስ በእርስ ቅንጅታዊ ተራክቦ ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ መጠን ከፍተኛ የተማሪ ቁጥር ባለበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ በተሳካ ሁኔታ መተግበር ውጤታማ ላያደርግ እንደሚችል ስጋታቸውን ያስቀመጡ ምሁራንም አሉ (Flo and Bill 2009)። ይህም ጥናት በእንግሊዝኛ ቋንቋ በተካሄዱት ምርምሮች መነሻነት የመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን ፋይዳ በሀገራችን ባሉ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት አንጻር በፍትነታዊ ዘዴ መርምሮ ውጤት ላይ ደርሷል፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የተመረጠው ትምህርት ቤት አልፋ ሲሆን ይህም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ስር ከሚገኙ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አምስት የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤቶች መካከል አንደኛው ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ተመረጠበት ምክንያትና መንገድ በምዕራፍ ሶስት በስፋት ቀርቧል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የመጻፍ ክሂል ትምህርትን በመማር ሂደት በተማሪዎች ዘንድ ለሚስተዋሉ ችግሮች በምንጭነት ከሚጠቀሱት መካከል አንደኛው ከተማሪዎች ስነ ልቦና፣ ስነ ልሳንና ግንዛቤ ጋር የሚያያዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ክሂሉ በውስጡ ከሚይዛቸው እንደ ይዘት፣ ሰዋስው፣ ቃላት፣ አገባብ፣ ግጥምጥምነት፣ ተለጣጣቂነት ወ.ዘ.ተ ከተባሉ አላባውያን አንጻር ሊገለጽ እንደሚችል Byrne (1988) ያስረዳሉ፡፡ ሶስተኛው የችግር ምንጭ እንደዚሁ ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ካለመጠቀም የተነሳ የሚመጣ እንደሆነ Ferris and Roberts (2001)፣ Kaplan and Grabe (1996) እና Aragon, Claudia, Mira, Dalia, Rodriguez, Cloria (2013) ይተነትናሉ፡፡ በዚህ ሀሳብ ላይ Norrish (1983) Brown (2001) እና Richard and Rodgers (2001) ተመሳሳይ አቋም አላቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Rumsey (1998) ለመጻፍ ክሂል አለማደግ በየክፍል ደረጃው በሚዘጋጁ መርሃ ትምህርቶች ውስጥ መጻፍን ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶችና ክንውኖች ተግባር ተኮርነታቸው ዝቅተኛ መሆናቸው እንደሆነ በምክንያትነት ያነሳሉ፡፡

Aragon.et.al (2013) እንደሚሉት የመጻፍ ክሂል ትምህርት አላማ ሁሉንም ተማሪዎች የተካኑ ጸሀፍት እንዲሆኑ ማድረግ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ በአንጻሩ በደረጃቸው መጠን ሀሳባቸውን በጽሁፍ መግለጽ እንዲችሉ ማስቻል ነው፡፡ ይሁንና የበርካታ ተማሪዎች ችግር የሆነው

ከንግግር ባሻገር ሀሳባቸውን በትክክል በጽሁፍ መግለጽ አለመቻል ነው፡፡ ይህም ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ በሚማሩ ተማሪዎች ዘንድ በስፋት ይስተዋላል፡፡ እንደ ምሁራኑ ገለጻ ችግሩን ለመቀነስ አንዳንድ ሀገሮች በዩኒቨርስቲዎቻቸው የመጻፍ ክሂል ኮርሶችን ከውሳኔ ሰጪ ፈተናዎች ውጪ (በትምህርት ማጠናቀቂያ የሚሰጡ ጥቅል ፈተናዎች) ተማሪዎች ደጋግመው እንዲማሩ እስከማድረግ ደርሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ ችግሩ የሚጀምረው ገና ከታችኞቹ የክፍል ደረጃዎች በመሆኑ ይህም ብዙም ለውጥ እንዳላመጣና የችግሩ ባለቤቶች የትኞቹ እንደሆኑ ለይቶ ለመፈረጅ በማይቻልበት ሁኔታ በአፍ ፈቶችም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዘንድ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ክሂሉ ዝቅ ብሎ ይታያል፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች የችግሩን ግዝፈት በዚህ መጠን ይግለጹት እንጂ የመጻፍ ክሂልን በመማር ሂደት ታላሚውን ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ከሚማሩት ይልቅ አፍ ፈቶች የተሻሉ እንደሆኑ ደግሞ የገለጹ ምሁራንም አሉ (Kroll 1993፣ Hinkel 2011)።

ለመጻፍ ክሂል ትምህርት አለማደግ በተግዳሮትነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች እንደየቋንቋዎች ባህሪይ፣ የተማሪዎች የመማር ሁኔታ፣ የሀገሮች የትምህርት አቀራረብ ስርዓት ወ.ዘ.ተ አኳያ በብዙ መልኩ ሊተነተኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ ችግሮቹ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ብቻም የሚታዩ አይደሉም፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብና በተማሪዎች ውጤት ዙሪያ የተጠኑ በርካታ ሀገራዊ ጥናቶችን ብንመለከት እንኳን በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ላይ የሰዋስው ህግጋትን የመጠበቅ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ የመገልገል፣ ሀሳቦችን የማቀናበርና ጥሩ የቋንቋ አገላለጽን ተጠቅመው ሀሳባቸውን የመግለጽ ችግሮች በእጅጉ እንደሚታይባቸው በስፋት ያስረዳሉ፡፡ ይህንን የተማሪዎች የመጻፍ ችግር በጽሁፋቸው ከገለጹት ምሁራን መካከል በቀዳሚነት ባየ (2000፡xxvi) የተናገሩትን ብንመለከት ‹‹በየደረጃው እየተመረቁ የሚወጡት ተማሪዎች ተራ ዘገባ (ሪፖርት) ለማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት እንደሌላቸው ነው››፡፡ በተመሳሳይ ሰለሞን (1987) አለማየሁ (2007)፣ አማረ (2010) እንዳለ (1992)፣ ክፍሌ (1986) የሽጥላ (2008) እና ግርማ (1990) በጥናታቸው ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለቁጥር አዳጋች የሆኑ የቋንቋ አጠቃቀሞችንና የአገባብ ስህተቶችን (ለምሳሌ የፊደላት አጣጣል የጾታ አለመስማማት፣ የመደብ አለመጣጣም፣ የቁጥር አለመመጣጠን፣ የጽንሰ ሀሳብና የቃላት አለቦታቸው መግባት) የመሳሰሉት ችግሮችን እንደሚፈጽሙ የጠቆሙት ሀሳብ ለአብነት የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

እነዚህ የሀገር ውስጥ ጥናቶች የመጻፍ ክሂል ያለበትን የእድገት ደረጃ ከተለያዩ መልኮች አንጻር መርምረው ዝቅተኛነቱን ይግለጹ እንጂ ለእድገቱ ማነቆ የሚሆኑ ነገሮችን በማቃለልና በማስወገድ ትምህርቱን ካለበት ደረጃ ከፍ ማድረግ እንደሚቻል በውጤታቸው አሳይተዋል፡፡ ከጥናቶች መረዳት የተቻለው የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ትምህርቱ ከማስተማሪያ ዘዴዎች፣ ከመመዘኛ ስልቶች፣ ከይዘት አቀራረቦች፣ ከዕቀዳ ዓይነቶችና ከሌሎች አተገባበሮች አንጻር በጥናት ቢፈተሽ ክሂሉን ሊያጎለብቱ የሚችሉ አዳዲስ አስተሳሰቦችንና ግኝቶችን ማምጣት የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንደ አጠቃላይ በክሂሉ ዙሪያ ሊሰሩ የሚገቡ ተጨማሪ ጥናቶች ማስፈለጋቸውን የሚያስገነዝብና በአነሳሽ ምክንያትነት የሚታይ ነው፡፡

ከፍ ሲል የመጻፍ ክሂል አሁን ያለበት የዕድገት ሁኔታ ምን እንደሚመስልና በእድገቱም ላይ እንቅፋት ሆነው የሚጠቀሱ ጉዳዮችን ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ ይሁንና የዚህ ጥናት ዋና ርዕሰ ጉዳይ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብን ከመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴና መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች አንጻር መመርመር እንደመሆኑ መጠን ቀጥሎ የሚቀርቡት ሀሳቦች ደግሞ በዚህ ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል ችሎታ መስማት በሚችሉ አፍ ፈቶችም ሆነ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ዘንድ ያለው የዕድገት ደረጃ ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱን ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ከላይ ተገልጿል፡፡ ችግሩ መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች አንጻር ሲታይም በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዘንድ ከሚታየው በላይ ገዝፎ እንደሚገኝ Wolbers.et.al. (2016) ፣ Hpelin (2017)፣ Almayehu (2003)፣ Anne Gray (2003) ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ደግሞ አንደኛው ልጆቹ ለመደበኛው ጽህፈት የሚያግዛቸውን ቋንቋ በቅድመ ትምህርት ዕድሜያቸው አዳብረው (በአንድ ቋንቋ አፍ ፈተውና መናገር ችለው) አለመምጣታቸው ሲሆን ሁለተኛውም ለተግባቦታቸው በሚያውሉት የምልክት ቋንቋ አጠቃቀምና በሚጽፉበት ቋንቋ (ለትምህርትነት በቀረበላቸው ቋንቋ) የአጻጻፍ ስርዓት መካከል ብዙ ተዛምዶ አለመኖሩ ነው፡፡

በተጨማሪም Deginesh (2016) Carrington and Robinson (2006)ንን ጠቅሰው በጥናታቸው እንዳነሱት በየትኛውም የትምህርት አውድና የክፍል ደረጃ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸው የመጻፍ ክሂል ችግሮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸው ውሱንነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በስፋት እንደሚታየው እነዚህ ተማሪዎች ሲጽፉ ከሚገኙበት የእድሜ ክልልና ከሚማሩበት የክፍል ደረጃ በታች ነው፡፡ ይህም የሆነበት አንደኛው

ምክንያት የሚማሩትን ቋንቋ የንግግር ቅርጽ ከአለማወቅ የሚመጣ እንደሆነ Deginesh (2016) ይገልጻሉ፡፡ ድርሳናት እንደሚያስረዱትም የዳበረ የንግግር ቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ ለጥሩ የጽሁፍ ቅርጽ መገኘት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ለንግግር ተግባቦት የሚያውሉት የምልክት ቋንቋ በአይነቱ የተለየ እንደመሆኑ መጠን በምልክት ቋንቋውና በታላሚው ቋንቋ የአጻጻፍ ስርዓት አጠቃቀም መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ ካልተቻለ ችግሩን መቀነስ አይቻልም Deginesh (2016)፡፡

Almayehu (2003)፣ Anne Gray (2003)፣ Deginesh (2016) በጽሁፋቸው ካቀረቡት ሀሳብም ሆነ ተመራማሪዋ አማርኛ ቋንቋን መሰረት አድርጋ በትምህርት ቤቶች በመዘዋወር በግንባር ከተመለከተችው መረዳት እንደተቻለው መስማት በሚችሉ ተማሪዎች ዘንድ ያለው የንግግር ቋንቋ አጠቃቀም የታላሚውን ቋንቋ የጽሁፍ ስርዓት የሚደግፈው ሲሆን በአንጻሩ ግን መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በሚገለገሉበት የምልክት ቋንቋና በታላሚው ቋንቋ የጽሁፍ ስርዓት መካከል ሰፊ የሆነ የአጠቃቀም ልዩነት በመኖሩ የተነሳ የትምህርት ሂደቱን ከባድ ሲያደርግባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይ በቋንቋው ምዕላዶች፣ ቃላት፣ሀረጋትና አረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓቱ ላይ የምልክት ቋንቋው አጠቃቀም ጣልቃ እየገባ የሰዋስው ህግጋትን እንዲጥሱና ስህተት የሆኑ አገላለጾችን እንዲጠቀሙ ተጽእኖ ሲያሳድርባቸው መመልከት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በምልክት ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያለው የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት በጽሁፍ ወቅት እንዳለው ለባለቤት፣ ለተሳቢና ለግስ ቅደም ተከተል መጠበቅ ትኩረት አይሰጥም፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት ደግሞ ባለቤት+ ተሳቢ+ ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ) እንደሆነ ጌታሁን (1990) ያስረዳሉ፡፡ የአጻጻፍ ስርዓቱም ይህንን ቅርጽ ይከተላል፡፡ በተጨማሪም ቃላትን ለተለያዩ ሰዋስዋዊ ተግባራት መግለጫነት ለማዋል ሲታሰብ ለምሳሌ ለጊዜ፣ ለጾታ፣ ለቁጥር ወዘተ. የምስረታና የዕርባታ ምዕላዶችን አስማምቶ መጠቀም በጽሁፍ ወቅት ሊጠበቅ የሚገባ ሌላው ህግ እንደሆነ ጌታሁን (1990) አክለው ይገልጻሉ፡፡ ይሁንና በተገለጸው መልኩ የቃላትን ቅርጽ እየለዋወጡ ለተለያየ ተግባር የማዋሉ ሂደት ከምልክት ቋንቋው አጠቃቀምና ከአማርኛ ቋንቋ የጽሁፍ ስርዓት አንጻር ሲታይ ሰፊ ልዩነት ይታይበታል፡፡ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች ዘንድ ለሚታየው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ውስንነትም አንዱ በምልክት ቋንቋውና በጽሁፍ ስርዓቱ መካከል ያለው የአጠቃቀም ልዩነት ሆኖ መጠቀስ የቻለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ Byrne (1988) በጽህፈት ሂደት ለቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ ለዐረፍተ ነገሮች አገነባብ፣ ለሀሳብ አደረጃጀትና ሌሎች የስዋሰው

ስርዓቶች መከበር የንግግር ክሂል ችሎታ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የሰነዘሩት አስተያየት ሀሳቡን ያጠናክረዋል፡፡

ሌላው Wolbers.et.al (2012) Anne Gray (2003) Elizabeth (2009) እና Wolbers (2008) በጥናታቸው መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ መቀነስ ምክንያት ይሆናል ብለው በጋራ ያነሱት ሀሳብ የማህበራዊ መስተጋብር ውስንነትን ነው፡፡ በቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች በተለይ በማህበረ ባህል (ግንባታውያን) እሳቤ መሰረት የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ በእጅጉ የሚዳብረው በማህበራዊ መስተጋብር እንደሆነ በስፋት ይታወቃል፡፡ይሁን እንጂ በአብዛኞች መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ዘንድ እንደሚታየው ከመደበኛው ትምህርት አውድ ውጪ በሚኖራቸው ማህበራዊ መስተጋብር የመጻፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል ጥረት አይደረግም፡፡ Anne Gray (2003) እንደሚሉት የተማሪዎች ማህበራዊ መስተጋብር ዝቅተኛ በሚሆንበት አጋጣሚ ማለትም በምልክት ቋንቋ ብቻ በሚጠቀሙበት ጊዜ ለጽሁፍ የሚያግዟቸውን ተጨማሪ ልምዶችና የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓቶች እንዳያውቁ ይገደዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም በክሂሉ የመጠቀም ፍላጎታቸው እየቀነሰና የመርሳት ዕድላቸውም እየሰፋ ስለሚሄድ ከራሳቸው አልፎ በማህበራዊ ህይወታቸውም ጭምር አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲደርስባቸው እድል ይፈጥራል፡፡ ምክንያቱም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በእለት ተዕለት ህይወታቸው ተራክቦ የሚያደርጉት ከማይሰሙ አልያም የምልክት ቋንቋን በወጉ ከማያውቁ የሚሰሙ ቤተሰቦቻቸው፣ ጓደኞቻቸውና ከሰፊው ማህበረሰብ ጋር እንደመሆኑ መጠን የመጻፍ ክሂልን አማራጭ ተግባቦታዊ መሳሪያ አድረገው እስካልተጠቀሙ ድረስ ተግባቦታዊ ወሰናቸው በእጅጉ የጠበበ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም Anne Gray (2003)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማዳከም ረገድ ትልቁን ቦታ የሚይዘው የትምህርት አቀራረብ ስርዓቱ እንደሆነ Elizabeth (2009) ፣ Wolbers (2008) እና Wolbers.et.al (2012) ያስረዳሉ፡፡ ምሁራኑ በብዙ ሀገራት ካለው ተሞክሮ በመነሳት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የሚማሩበት የትምህርት ስርዓት ጠቅላይና መስማት ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር የጋራ በሚያደርጋቸው አንድ አይነት መርሃ ትምህርት፣መማሪያ መጽሀፍ፣ መማሪያ ክፍል (በአብዛኛው) የተቃኘ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ይሁንና ችግሩ ያለው ተማሪዎች በዚህ አይነቱ ስርዓት መማራቸው ላይ ሳይሆን በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚካተቱ የማስተማሪያ ይዘቶች፣ለማስተማሪያና ለመመዘኛነት የሚመረጡ ዘዴዎች እንዲሁም ትምህርቱን ለማሳለጥ የሚቀርቡ የትምህርት መሳሪያዎች የብዙሃን ተማሪዎችን እንጂ

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመማር ሁኔታና ፍላጎት ያገናዘቡ ባለመሆናቸው ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሁለቱም የመማሪያ ክፍል አውድ (በልዩና በአካቶ) በሚማሩ ተማሪዎች ዘንድ ችግሩን እያባባሰውና ተማሪዎች በክሂሉ መጠቀም በማይችሉበት ደረጃ እንዲደርሱ እያደረገ ያለ መሆኑን Elizabeth (2009)፣ Wolbers (2008) እና Dostal and Wolbers (2014) ይገልጻሉ፡፡

በእርግጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ በላቀ ሁኔታ ስህተቶችን ይሰራሉ ይባል እንጂ ትምህርቱ ፍላጎታቸውን ባማከለ ሁኔታ ከቀረበላቸውና ተጨማሪ ማህበራዊ ድጋፍ ከተደረገላቸው መስማት ከሚችሉት ተማሪዎች ጋር ተመጣጣኝ በሚባል ደረጃ ችሎታቸውን ማበልጸግ እንደሚችሉና ብቁ ጸሀፊ ብቻም ሳይሆን አንባቢ እንደሚሆኑ ጭምር Sheilla (2011) በጥናታቸው ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ለእነዚህ ተማሪዎች በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ቀንሶ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ መሰራት ያለባቸው በርካታ ተግባራት ያሉ ቢሆንም በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ጥናት ማካሄድ ደግሞ አንዱና ዋነኛው እንደሆነ የዚህ ጥናት አቅራቢ ታምናለች፡፡ ይሁንና እስካሁን በተረገው ፍተሻ ክሂሉን ልዩ የመማር ፍላጎት ከሌላቸው ተማሪዎች አንጻር እንጂ ከተተኳሪ ተማሪዎችና ከአማርኛ ቋንቋ ጋር አያይዘው የመረመሩ የሀገር ውስጥ ጥናቶች አልተገኙም፡፡ ይህ ደግሞ ለጉዳዩ ብዙ ትኩረት እንዳልተሰጠው የሚያመለክት ነው፡፡ Tesfaye (2014) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባጠኑት ጥናት ላይ ካሰፈሩት ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለውም ይህንኑ ነው፡፡ አጥኚው እንደሚሉት በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ በርካታ የሚባሉ ትምህርታዊ ምክክሮች ሲደረጉ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ትኩረታቸው ለጥቅል ትምህርቱና ለብዙሃን ተማሪዎች እንጂ መስማት ለማይችሉ ተማሪዎች አይደለም፡፡ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች ላይ የተከናወኑ በርካታ ምርምሮችን ስንመለከት እንኳን ትኩረታቸው በምልክት ቋንቋ አጠቃቀም፣ በልዩ ወይም በአካቶ የመማሪያ ክፍል አውድ በሚሰጠው የመማር ማስተማር መርሃ ግብር ውጤታማነት ግምገማና በሌሎች ዘውጎች ላይ እንጂ ከመጻፍ ትምህርት አቀራረብም ሆነ ከውጤት ማሻሻያዎች ጋር ተያይዘው ስነትምህርታዊ ድጋፍ ሊሰጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እንዳልሆኑ Tesfaye (2014) ይተነትናሉ፡፡

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ሲታሰብም የመነሻ ሀሳቦችንበማፈላለግ ሂደት ከእንግሊዝኛና ከምልክት ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አንጻር ተጠንተው መስማት በተሳናቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ዙሪያ ውስን ማብራሪያ መስጠት የቻሉት የAlmayehu (2003)፣ የTesfaye (2014) እና የGirma (2008) ጥናቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡እነዚህ ጥናቶች ከአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልና ከመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ኖሯቸው ባይጠኑም

በሀገራችን ያሉ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ደረጃ በተወሰነ መልኩ የገለጹ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ውስጥም በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ ለአብነት Tesfaye (2014) በጥናታቸው ያሰፈሩትን ሀሳብ ብንመለከት እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ያላቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል የሚባሉት ሳይቀሩ የመጻፍና የማንበብ ክሂል አቅማቸው ሲመዘን በአራተኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ ከሚጠበቀው ጋር እኩል ሆኖ የሚታይ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ተመራማሪው መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች ዘንድ ያለውን የመጻፍ ክሂል ክፍተት በጠቆሙበት ወቅት ለችግሩ ስር መስደድ ዋናው ምክንያት ነው ያሉትም የትምህርት አሰጣጡን ሲሆን በተለይ በትምህርቱ አቀራረብ ተስማሚነት ዙሪያ የሚከናወኑ ችግር ፈቺ ምርምሮች ውስን መሆናቸው ደግሞ ችግሩን እያባባሰው እንደሄደ በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡

በአንጻሩ በውጪ ሀገራት ያለውን ተሞክሮ ስንመለከት በየደረጃው የሚማሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት በማሳደግ ረገድ በርካታ ምርምሮች እየተከናወኑ እንዳሉ ለዚህ ጥናት ዋቢ ሆነው ቀጥለው ከቀረቡት ድርሳናት መረዳት ይቻላል፡፡ የመጻፍ ክሂል ትምህርትንም በአቀራረቡ የተሻለ አድርጎ ተማሪዎችን ለጥሩ ውጤት ማብቃት እንዲቻል የማስተማሪያ ዘዴዎችም በጥናት ተሞክረዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የዚህ ጥናት አብይ ጉዳይ የሆነው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ አንዱ ሲሆን እንግሊዝኛ ቋንቋን ከማስተማር አንጻርም ጥሩ ውጤት እንደተገኘበት በተመራማሪዎች እየተገለጸ ይገኛል (Wolber 2008፣ Dostal and Wolbers 2014፣ Elizabeth 2009፣ Wolbers.et.al 2012፣ Wolbers.et.al 2016 እና Flo and Bill 2009)። መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ውስንነት በመቅረፍ ረገድ ያለውን ሚና በተመለከተም ከዚህ ቀደም በአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ስር የቀረበ ጥናት አልተገኘም፡፡ ከዚህ በተለየ ርዕሰ ጉዳይ ግን "በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብራዊ ስልት ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት "በሚል አቀራረብ ግርማ (1990) ጥናት አካሂደው ነበር፡፡ ይህም ጥናት መስማት በሚችሉና አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በውጤቱም የማስተማሪያ ዘዴው የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ሚናው የላቀ እንደሆነ ያመላከተ ነው፡፡

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ ተመስርተው የመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴን ውጤታማነት መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት አኳያ ከመረመሩት ጥናቶች በመነሳት ይህንን ጥናት ለማካሄድ ምክንያት የሆኑት አበይት ጉዳዮች ጠቅለል ብለው ሲገለጹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ውሱንነት ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን የተግባቦት ችግር ለመቅረፍ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ቢታመንም በአጠቃቀም ደረጃ በተማሪዎች ላይ እየታየ ያለው ችግር ግን ከፍተኛ መሆኑን ያመለከቱ ጥናቶች መኖራቸው (Tesfaye 2014 ፣ Almayehu 2003 እና Girma 2008)።
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሻሻል ረገድ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ጥቅም እንዳለው ያመለከቱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥናቶች ቢኖሩም ዘዴውን ከአማርኛ ቋንቋ፣ በሀገራችን ካለው የትምህርት አሰጣጥ ስርዓትና ከተተኳሪ ተማሪዎች አንጻር የመረመሩ ጥናቶች ያልተገኙ በመሆኑ ቢጠና ለመማር ማስተማሩ መዳበር አስፈላጊ ግብዓትን ይሰጣል የሚል እምነት መኖሩ፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በሚጽፉበት ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ የሰዋስው አጠቃቀም ስህተቶች፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት አጠቃቀምና የሀሳብ አደረጃጀት ችግሮችን በከፍተኛ ሁኔታ ሲፈጽሙ መገኘታቸውና በአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችም ላይ የሚያስመዘግቡት ውጤት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱ በትምህርት አቀራረቡና በተተኳሪ ተማሪዎች የመማር ሁኔታ መካከል ችግር እንዳለ የሚጠቁም መሆኑ፡፡ (መምህር ባህሩ፣ መምህርት አገርነሽና መምህርት ከበቡሽ የግል ውይይት፤ ህዳር 2008 ዓ.ም. እንዲሁም በተመራማሪዋ የተደረገ ኢመደበኛ ዳሰሳዊ ጥናት)
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከምልክት ቋንቋ ባለፈ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ጽሁፍን ለተግባቦት ሲመርጡት ካለመታየታቸው በተጨማሪ እንዲጽፉ ሲደረጉም የመሰላቸት ስሜት ሲፈጠርባቸው መስተዋሉ ወይም ለመማር ያላቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ መታየቱ፡፡ (መምህር ፈይሳ፣ መምህርት ብርሃኔ፣ መምህርት ከበቡሽ የግል ውይይት፤ ህዳር 2008 ዓ.ም.)

- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች በተለያዩ አውዶች በሚቀርቡ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ላይ እንደሚሰሙ ተማሪዎች ሲሳተፉ አለመታየታቸው ብቻም ሳይሆን እድሉ ሲሰጣቸው ላለመጠቀም ሲሸሹና ሲፈሩ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ በክሂሉ ላይ ትልቅ ክፍተት እንዳለባቸው የሚያሳይ በመሆኑ የችግሩን ምንጭ ለማወቅም ሆነ መፍትሄ ለመስጠት ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፡፡ (መምህርት ሰዓዳ፣ መምህር ቢኒያም፣ መምህርት መአዛ፣ መምህርት ገንዘብ  የግል ውይይት፤ ህዳር 2008 ዓ.ም. እንዲሁም የተመራማሪዋ ምልከታ)

ከላይ እንደተገለጸው ከTesfaye (2014)፣ ከAlmayehu (2003) እና ከGirma (2008) ጥናቶች፣ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ አማርኛ ቋንቋን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች በማስተማር የረጅም ጊዜ ልምድ ካላቸው መምህራንና ከተመራማሪዋ የግል ምልከታ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው ተማሪዎቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በመጻፍ ክሂል ችሎታቸው ላይ ከፍተኛ ችግር አለባቸው፡፡ በዚህም ይህ ጥናት የተጠቀሱትን ችግሮች መነሻ በማድረግ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ያሻሽለው ይሆናል ያለውን መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በሙከራዊ ምርምር በመፈተሽ ቀጥሎ ለቀረቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ሞክሯል፡፡

- መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል?
- መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ መስተጋብራዊ የማስተማር ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና በመማር ፍላጎታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

1. መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ያለው ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ ለመርሃ

ትምህርትና ለመማሪያ መጽሃፍ አዘጋጆች ጠቃሚ የሆነ ስነ ትምህርታዊ መረጃ ይሰጣል፡፡

2. የመጻፍ ክሂልን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ለሚያስተምሩ መምህራን በትምህርቱ ሂደት ከሚከተሏቸው ዘዴዎች በተጨማሪ መስተጋብራዊ ዘዴንም በመጠቀም የተማሪዎቻቸውን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ማሳደግ እንዲችሉ ያግዛል፡፡
3. ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለሚደረጉ ተጨማሪ ምርምሮች መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት አብይ አላማ መስተጋብራዊ የማስተማር ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና በመማር ፍላጎታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ በአዲስ አበባ መስተዳደር ስር መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ከሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች መካከል በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት የተካሄደ ሲሆን በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከልም ጥናቱ የተመለከተው በ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በ7ኛ ክፍል የሚማሩትን ነው፡፡ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲመረጡ የተደረገበት ምክንያት ትምህርቱን አስመልክቶ የሚቀርቡ ተግባራትን ሀላፊነት ወስዶ በመተግበር ረገድ በዕድሜም ሆነ በአስተሳሰብ ከክፍል ደረጃው በታች ካሉት ሌሎች ተማሪዎች የተሻሉ ይሆናሉ የሚል ግምት በመኖሩ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከክፍል ደረጃው በላይ የሚማሩት የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በክልላዊ ፈተና ላይ የሚሳተፉ እንደመሆናቸው ለጥናቱ ትኩረት ላይሰጡት ይችላሉ የሚል ስጋት ስላለ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ከተጠቀሰው ውጪ ያሉትን ሌሎች የክፍል ደረጃዎች አልተመለከተም፡፡ በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚመማሩት ተማሪዎች ሰባት ሲሆኑ ካላቸው የቁጥር ውስንነት የተነሳም ሁሉም በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎቹን በአንድ ቡድን አደራጅቶ ከማጥናት ባለፈ ከሌላ ቡድን ወይም ትምህርት ቤት ጋር እያነጻጸሩ ትንታኔ መስጠት የጥናቱ ትኩረት አይደለም፡፡

ሌላው ጥናቱ የመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴን ፋይዳ ለማረጋገጥ ያለመ እንደመሆኑ መጠን የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ በዘዴው የአቀራረብ መርሆች ላይ ተመስርተው በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ከተተኳሪው የማስተማሪያ ዘዴና ከተመረጠው ክሂል ውጪ ያሉ ሌሎች አቀራረቦችና ተጓዳኝ ክሂሎች በጥናቱ አልተዳሰሱም፡፡ በጥናቱ ሂደት የተተገበረው

የመጻፍ ክሂል ትምህርት በተመረጠው የክፍል ደረጃ (7ኛ ክፍል) እያገለገለ ባለው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችንና ተግባራትን መሰረት ያደረገ ሲሆን በዋናነትም በመጻፍ ክሂል ንዑሳን ክሂሎች ማለትም ሆሄያትንና ቃላትን በመጻፍ፣አረፍተ ነገሮችን በመገንባትና በማደራጀት፣ ጅምር ሀሳቦችን በማጠናቀቅ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው በመጠቀም፣ አንቀጽና ድርሰቶችን በመጻፍ ልምምዶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ዓብይ ምክንያት በተመራማሪዋ ምልከታና በናሙና ጥናቱ ትግበራ ላይ በነበረው የትምህርት አቀራረብ የተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ችግር ልቆ የታየው ሆሄያትን በትክክለኛ ቅርጻቸው አለመጻፍ፣ ትርጉም ሰጪ ቃላትን አለመመስረት፣ አረፍተ ነገሮችን በትክክለኛ የሰዋስው ቅርጻቸው አለማዋቀር፣ አንቀጾችን አለማደራጀትና ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው አለመጠቀም፣ እንዲሁም የድርሰት ሀሳብን አለማደራጀት ላይ በመሆኑ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማም ችግርን መለየት ብቻ ሳይሆን ለችግሩ መፍትሄ መፈለግ እንደመሆኑ መጠን መማር ማስተማሩን በተመረጡ የመጻፍ ክሂል ተግባራት ላይ አድርጎ ማቅረቡ በጥቂቱም ቢሆን ረብ ያለው ውጤት ያስገኛል የሚል እምነት አለ፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውሱንነት

ይህ ጥናት ከናሙና አወሳሰድ፣ ከማስተማሪያ ግብዓቶችና ከቀደምት ጥናቶች አንጻር የሚነሱ ውሱንነቶች አሉበት፡፡ ከናሙና አወሳሰድ አንጻር ያለውን ውሱንነት አስቀድመን ብንመለከት የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች ልዩ እገዛን የሚሹና መስማት ተሳናቸው እንደመሆናቸው በትምህርት ቤቶች ያላቸው ቁጥር መስማት ከሚችሉት ተማሪዎች አንጻር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ በትምህርት ሚንስተር ውስጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ተመራማሪዋ ካገኘችው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሀገራችን ባለው የትምህርት መርሃ ግብር በልዩም ሆነ በአካቶ የሚማሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው ምን ያህል ቁጥር እንዳላቸው ለማወቅ ተመራማሪዋ በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውራ ለመመልከትና በስልክም ጭምር መረጃዎችን ለማግኘት ጥረት አድርጋለች፡፡ ለምሳሌ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በተደራጀ ሁኔታ ያስተምራሉ በተባሉ የተለያዩ የክፍለ ሀገር አካባቢዎች በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ክልል ወ.ዘ.ተ ስልክ በመደወል እየተተገበረ ስላለው የመማር ማስተማር ሁኔታ መረዳት ተችሏል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ተተኳሪ ተማሪዎችን በልዩም ሆነ በአካቶ የትምህርት መርሃ ግብር ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶች ይኑሩ እንጂ በየክፍል ደረጃዎች

ተማሪዎችን በበቂ ቁጥር አግኝቶ ለማስተማር ፈታኝ ጉዳዮች ያሉ መሆናቸውን በትምህርት ቤቶቹ ካሉ ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡

ይህንን ጥናት በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ ካሉ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች መካከል በአንዱ ለማካሄድ የተቻለበት ዋነኛ ምክንያትም ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ተያይዞ ሊያጋጥም የሚችለውን ችግር በተወሰነ መልኩም ቢሆን መቅረፍ ይቻላል የሚል እምነት በመኖሩ ነው፡፡ በዚህም በአዲስ አበባ ካሉት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለጥናቱ ማከናወኛ የሆነውን ትምህርት ቤት በመምረጥ ሂደት ቅድመ ዳሰሳዎች ተደርገው የነበረ ሲሆን ለጥናቱ መሳካት በብዙ መልኩ የተሻሉ ሆነው በተገኙት ሁለት ትምህርት ቤቶች የናሙናና የዋና ጥናቱን ማካሄድ ተችሏል፡፡ እነዚህ መስማት የተሳናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤቶች ቪክትሪ እና አልፋ ሲሆኑ በልዩ (Exclusive) የመማሪያ ክፍል ተማሪዎችን ተቀብለው የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ ከያዟቸው የተማሪዎች ቁጥርና በምልክት ቋንቋ ከሰለጠኑ መምህራን አንጻር ሲታዩም የተሻሉ የሚባሉ ናቸው፡፡ ይሁንና ለዚህ ጥናት በተመረጠው የክፍል ደረጃ (ሰባተኛ ክፍል) የሚማሩት ተማሪዎች ብዛታቸው ሰባት ብቻ መሆኑ ሁሉንም ተማሪዎች አጠቃሎ ለማጥናት አስገዳጅ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህም ጥናቱ ውሱንነት እንዲኖረው ያደረገ ነው፡፡ ምክንያቱም የአንድን ጥናት ውጤት አስተማማኝነት ከሚያጎናጽፉ ወሳኝ ጉዳዮች መካከል የጥናት ናሙና ወካይ መሆን እንደሆነ ስለሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በነጠላ ቡድን የጥናት ንድፍ (Single group experimental design) ላይ ተመስርቶ መካሄዱ ምንም እንኳን ከተጠኚዎች ዳራዊ ማንነት ጋር ተያይዞ ባጋጠመ ችግር ምክንያት መሆኑ ቢታመንም ከምርምር መስኪያ ባህሪያቶች አንጻር ሲመዘን ግን ውሱንነት አለበት ማለት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው በጥናቱ ሂደት ያጋጠመው ችግር የማስተማሪያ ግብዓቶች እጥረት ነው፡፡ በጥናቱ የተለያዩ ክፍሎች እንደተገለጸው በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚቀርብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ደጋፊ የሆኑ እይታዊና ተዳሳሽ መሳሪያዎችን ይፈልጋል፡፡ እይታዊ መሳሪያዎች ሲባል ለምሳሌ ስዕሎች፣ ፎቶዎች፣ቀለማት፣ቪዲዮዎችና የመሳሰሉት የሚጠቃለሉበት ሲሆን ተዳሳሽ መሳሪያዎች ደግሞ ተማሪዎች ሆሄያትን፣ ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን ሲጽፉ በእጃቸው እየፈቱ የሚገጣጥሟቸውን ዘመናዊ የጽህፈት መለማመጃ መሳሪያዎችን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህና ሌሎች ያልተጠቀሱ የማስተማሪያ ቁሶች የትምህርቱን ሂደት በማቀላጠፍ ረገድ ያላቸው አዎንታዊ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ቢታመንም አግኝቶ ለመጠቀም የተደረገው ጥረት ግን ጥናቱን ፈታኝ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይሁን እንጂ ችግሩን ለመቅረፍ በተመራማሪዋና

ዘዴውን በምትተገብረው መምህርት በቀላሉ መሰራት የሚቻሉትን በራስ በማዘጋጀት ከአቅም በላይ የሆኑትን ደግሞ ገንዘብ መድቦ ከባለሞያዎች በመግዛት (ከፊደል ጥሩ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ማዕከል) ጥናቱን ማካሄድ ተችሏል፡፡

ሌላው የቀደምት ጥናቶች ውስንነት ነው፡፡ በአነሳሽ ምክንያቱ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት አጥኚ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ችግር ምን ያህል እንደሆነ መረዳት የቻለችው በውጪ ሀገር በእንግሊዝኛ ቋንቋ በተካሄዱ ጥናቶች ላይ ካደረገችው ንባብና በትምህርት ቤቶች ተዘዋውራ ካካሄደችው ኢ- መደበኛ የዳሰሳ ጥናት ነው፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች የተገኘውን መነሻ ሀሳብ በመያዝ ሀገራችን ባሉ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ዙሪያ የተካሄዱ ምርምሮች መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ብርቱ ፍተሻ ቢደረግም ምንም ዓይነት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ይዞት ከተነሳው ርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሀገራዊ የምርምር ስራዎችን ማግኘት ባለመቻሉ ያጋጠመውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት ብዙ ጊዜን ወስዷል፡፡ በተለይ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በሀገራችን ካለው የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ጋር አዛምዶ ከማቅረብና ከተተኳሪ ተማሪዎቹ የመማር ሁኔታና ከታላሚው ቋንቋ ባህሪ አንጻር አስማምቶ ለመተግበር የተደረገው ጥረት የጥናቱን ሂደት ከባድና ውሱንነት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡

## 1.7. የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ተግባራዊ ፍቺ

- ቅድመ ልደታዊ መስማት መሳን፦ በዚህ ጥናት ውስጥ ቅድመ ልደታዊ መስማት መሳን የተባለው ልጆች በእናታቸው ማሕጸን ሳሉ የሚገጥማቸው የመስማት ችግር ወይም በተፈጥሮ መስማት የተሳናቸው ሆነው የመወለዳቸውን ሁኔታ ነው፡፡
- ድህረ ልደታዊ መስማት መሳን፦ ልጆች በጤና ከተወለዱ በኋላ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የሚገጥማቸውን የመስማት ችግር ይመለከታል፡፡
- ተረድኦት፦ እንደዚህ ጥናት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎች ዘንድ የሚኖር የሀሳብ ተቀብሎትን ይገልጻል፡፡ ግለ ምዘና፦ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚገመግሙበት መንገድ፡፡
- ግለ ማህደረ ተግባር፦ የእያንዳንዱ ተማሪን የባህሪ ለውጥ መዝግቦ ለመከታተል የሚጠቅም ሰነድ ማለት ነው፡፡

- ቅድመ ምዘና ተግባር ንድፍ፦ ተማሪዎች ከመመዘናቸው በፊት ስለሚመዘኑበት የቋንቋ ይዘት፤ስለሚጠበቅባቸው ተግባር፤ምዘናው ስለሚይዘው ነጥብና አጠቃላይ ሁኔታዎች የሚገልጽ ነው፡፡
- የቋንቋ አላባዎች፦ ቋንቋን በማስተማር ሂደት በትምህርትነት የሚቀርቡ ክሂሎች ለምሳሌ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ናቸው፡፡
- የልዩ ትምህርት፦ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ተለይተው የሚማሩበት የትምህርት መርሃ ግብር ወይም መማሪያ ክፍል አውድ ማለት ሲሆን መስማት ካለመቻላቸው ጋር ተያይዞ ሊሰጠው የሚችል ሌላ ትርጓሜ የለውም፡፡
- የአካቶ ትምህርት፦ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩበት የትምህርት መርሃ ግብር ወይም የመማሪያ ክፍል አውድ ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 2.1. የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች ከመጻፍ ክሂል ትምህርት አንጻር ሲቃኙ

### 2.1.1. የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ (Social Construction Theory)

ይህ ንድፈ ሀሳብ Vygotsky በ1978 ያፈለቁት ሲሆን ትምህርት ወይም እውቀት በግል ብቻ ከሚደረግ ጥረት በቀላሉ የሚገኝ ሳይሆን በማህበራዊ አውዶችም ላይ በመመስረት ሊገነባና ሊበለጽግ የሚችል መሆኑን ያመላከተ ስነትምህርታዊ እሳቤ ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች፣የግለሰቦች ተራክቦ (መስተጋብር) በትምህርት ሂደት ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ማለትም የሰው ልጅ የሚማረው ከማህበረ-ባህል ጋር በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት ሲሆን ትምህርትና የእውቀት ደረጃም የተለያዩ ሂደቶችን ተራ በተራ በመከወን የሚያድጉ ናቸው፡፡ በእርግጥ ይህ ንድፈ ሀሳብ ሁለተኛ ቋንቋን ለሚማሩ ተማሪዎችም ሆነ በመጻፍ ክሂል ትምህርት አውድ ውስጥ አሁን ድረስ ተቀባይነት ያለው እንደሆነ Cazden (1996) ካሰፈሩት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ ማህበረ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እሳቤ የመጻፍ ክሂል ትምህርት መመስረት ያለበት ተማሪዎች በየግላቸው በሚያከናውኗቸው ተግባራት ላይ ተመርኩዘው በሚያመጡት የመጨረሻ ውጤት ላይ ብቻ ሳይሆን ከጓደኞቻቸው ጋር በሚያደርጉት ሂደታዊ መስተጋብር ጭምር ነው፡፡ ይህም የመጻፍ ክሂል ትምህርት ቅንጅታዊ ዘዴን ተከትሎ መቅረብ እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ይህም ጥናት የተከተለው የማህበረ ግንባታውያንን እሳቤ ሲሆን ንድፈ ሀሳቡን መነሻ ለማድረግ ምክንያት የሆነው ዓብይ ጉዳይ ደግሞ በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል በንዑስ ርዕስ 2.2.7.ተብራርቷል፡፡

### 2.1.2. የግንዛቤ ድገት ንድፈ ሀሳብ (Cognitive Development Theory)

በግንዛቤያዊ እድገት ንደፈ ሀሳብ አተያይ ቋንቋን በመማር ሂደት ተማሪዎች ቀድሞ ከሚያውቁትና በአእምሯቸው ከተዋቀረው መረጃ ውጭ የሚያገኙትን አዲስ መረጃ ዝም ብለው አይቀበሉትም፡፡ ስለ አዲሱ መረጃ አእምሯቸው ትንታኔን ሲያገኝ ከቀደመው መረጃ ጋር አገናዝቦ ያዛምደዋል (Slavin1990)፡፡ ይህ ሀሳብ ደግሞ ከPiaget እሳቤ ጋር ተጋርቶ ያሳያል፡፡

እንደ Piaget አተያይ መማር በቅድመ እውቀትና በማህበራዊ ተራክቦ ጥምረት የሚገኝ የአእምሯዊ (Cogntive) እድገት ነው፡፡ ይህ ሀሳብ በአንድ በኩልም ከVygotsky የግንባታዊ ንድፈ ሀሳብ ዋነኛ መርህ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በግንዛቤ እድገት ንድፈ ሀሳብ በእውቀትና በክህሎት ማደግ ቀድሞ በአእምሮ ውስጥ ከነበረው ችሎታ በተጨማሪ ከአካባቢ ጋር መጣመርን ግድ ይላል (Slavin 1990)፡፡ አእምሯዊ ቅድመ እውቀትን ከአካባቢ ጋር በማስተሳሰር የመማር እሳቤ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች በርካታ ሲሆኑ ለምሳሌ ቀደም ሲል የነበረን የመረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፣ ስህተትን አገናዝቦ ለማረምና እንደዚሁም የተጓደለ መረጃ ካለ ለማሟላት ያግዛል፡፡ በግንዛቤ እድገት ንድፈ ሀሳብ አተያይ ጽሁፍ የጥልቅ እሳቤ፣ የመረዳትና የግንዛቤ ውጤት ሲሆን ይህም ተማሪዎች እንዲያቅዱ፣ የራሳቸውን ሀሳብ እንዲያፈልቁ፣እንዲያደራጁ፣ እንዲጽፉና እንዲከልሱ የማድረግ ሂደት ነው፡፡

Ronald (2008) እንደሚሉት በግንዛቤ እድገት ንድፈ ሀሳብ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን የተሳካ ለማድረግ የተለያዩ ሞዴሎች ቀርበው ትችትና ድጋፍን አስተናግደዋል፡፡ እነዚህ ሞዴሎች ሲገመገሙም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የሚያልፉባቸውን ሂደቶች ባገናዘበ መልኩ እንደነበር Ronald (2008) አክለው ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው ሞዴል የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ በሚያልፍባቸው ደረጃዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን እነዚህም ማቀድ፣ ማደራጀት፣ ማብራራትና መከለስ የሚሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው የእውቀትን ማሳወቅ ሞዴል ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የእውቀት ሽግግር ሞዴል ይባላል፡፡ በእነዚህ ሞዴሎች የመጻፍ ክሂል ትምህርቱን ለማሻሻል በተለያየ ጊዜ በምሁራን የፈለቁና ለትግበራውም የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ ናቸው፡፡

### 2.1.3. የተግባቦታዊ ንድፈ ሀሳብ (Communication Theory)

ተግባቦታዊ ንድፈ ሀሳብ Scudder በተባለው ምሁር አፍላቂነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀው በ1980ዎቹ በእንግሊዝ ሀገር ሲሆን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተያይዞ መተግበር የጀመረው ደግሞ በ1982 Roberet በተባለ ግለሰብ እንደነበር John (2004) ያስረዳሉ፡፡ ከእርሱ በመቀበልም የተለያዩ ተመራማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ሲተገብሩትና በጥናትም ሲመረምሩት ቆይተዋል፡፡ በዚህ ረገድ ሚናቸውን ሲወጡ ከነበሩት ምሁራን መካከል Rchards እና Rodgers በዋናነት የሚጠቀሱ እንደሆኑ John (2004) ይገልጻሉ፡፡ በተግባቦታዊ ንድፈ ሀሳብ እይታ በማንኛውም የመጻፍ ክሂል ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በተግባቦታዊ ሂደቶች ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው ከመደረጉ ባሻገር ለማህበራዊ

ዲስኩሮችም ትልቅ ቦታ እንዲሰጥ ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት የመጻፍ ልምምድ ከክፍል ውጪ በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ሊያጋጥሚቸው በሚችሉ እውነታዎች ላይ ይመሰረታል (Paul 2013)። በአጠቃላይ እስካሁን የተመለከትናቸው የመማር ንድፈ ሀሳቦች ለመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ማለት ይቻላል ትምህርቱ ከተማሪዎች ቅድመ እውቀት ወይም አእምሮታዊ ችሎታና ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር እንዴት ተጋምዶ መሰጠት እንዳለበትና ከመምህራን የበላይ ተግባሪነት ይልቅ በተማሪዎች የሚመራ የትምህርት ባህል በምን መልኩ መለመድ እንዳለበት አቅጣጫ የሚያመለክቱ ከመሆናቸው በተጨማሪ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ መምህራን የቋንቋ ችሎታን በውጤት (በቁጥር) ከመግለጽ ይልቅ በተማሪዎች የተግባቦት ብቃት መመዘን እንዲችሉ ግንዛቤ የሚፈጠሩ ናቸው፡፡

## 2.2. የመጻፍ ክሂል ምንነት

የመጻፍ ክሂልን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔዎች ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ ለአብነትም Brown (2001) የመጻፍ ክሂል የድምፅ ወካይ ምልክቶች ድምር ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ተግባራዊ ሂደቶች ጥምር ውጤት የሆነና ማቀድ፣የማርቀቅ፣መከለስና ማረም የተባሉ ቅደም ተከተሎችን ተግባራዊ በማድረግ ስነ-ትምህርታዊ ሂደትን ተከትሎ የሚዳብር እንደሆነ የገለጹ ሲሆን White and Arndt (1991) እንደዚሁ መጻፍ ሆሄያትን ጠንቅቆ ማወቅና መለየትን፣ የአጻጻፍ ህግጋትን መረዳትን፣ሰዋስውን በተገቢ መጠቀምን፣ የተደራሲያንን ማንነት ማወቅን፣ የአጻጻፍ ምርጫ ማድረግን፣ይዘት ማደራጀትን ወ.ዘ.ተ የተባሉ ንዑሳን ክሂሎችን የሚፈልግ የማሰብ ውጤት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Byrne (1988) እና Raimes (1983) ፅህፈት የሰው ልጅ ሀሳቡን፣ እውቀቱን፣ እምነቱን፣ ደስታውንና ሀዘኑን ወዘተ. በፊደል ምልክትነት ቀርጾ ወደ ሌላው ለማስተላለፍ የሚጠቅም የቋንቋ መኪል መሆኑን ሲገልፁ Nunan (1989) እና Harmer (1996) ደግሞ ጽህፈት በትዕምርቶች የመወከል ሂደት ብቻም ሳይሆን አእምሮንና የአካል እንቅስቃሴን በማቀናጀት የአፃፃፍ ስልትን፣ የአወቃቀር ስርዓትን፣ የቃላት ምርጫን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ አንድነትን፣ ግጥምጥምነትን የሚጠይቅና ሌሎች በርካታ ተግባራት የሚከናወኑበት ውስብስብ አእምሮዊ ስራ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.2.1. የመጸፍ ክሂልን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የማስተማር አስፈላጊነት

የመፃፍ ክሂል ትምህርት ጥቅምን መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች አኳያ ከመመልከታችን አስቀድመን ስለ አካል ጉዳትና በውስጡም ስለሚካተተው መስማት መሳን ጥቂት ሀሳቦችን ማንሳት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ አጭር ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል የሚል እምነት አለ፡፡

Tewodros (2014) አለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ማህበር በ2005 ዓ.ም ያወጣውን ዘገባ በመጥቀስ እንደገለጹት 10% የሚሆኑት የአለማችን ህዝቦች አካል ጉዳተኛ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ መስማት የተሳናቸው ሰዎች መጠን በቁጥር ሲሰላ ደግሞ ወደ 360 ሚሊዩን የሚጠጋ ሆኖ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት (WHO) በቅርቡ በ2019 ካወጣው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በአለማችን በአሁኑ ወቅት 15% የሚሆነው ህዝብ አካል ያለበት ሲሆን ከዚህም ውስጥ 466 ሚሊዮኑ መስማት መሳን ያለባቸው ናቸው፡፡ ይሁንና በሁለቱ ጊዜ ከወጣው መረጃ መረዳት የሚቻለው መስማት የተሳናቸው ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ ማለቱን ነው፡፡ ወደ ሀገራችን ኢትዩጵያ ስንመጣም በ2007 ዓ.ም ከተደረገው የቤትና የህዝብ ቆጠራ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው 805,492 አካል ጉዳተኞች ሲኖሩ ከእነዚህም መካከል ሙሉ በሙሉ መስማት የማይችሉት (Deaf) 27,288 ከፊል የመስማት መሳን አለባቸው (Hard of hearing) የሚባሉት ደግሞ 37,632 እንደሆኑ Tewodros (2014) ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ይህ ቁጥር አስተማማኝነት ያለው ነው ብሎ መደምደም እንደማይቻልና ችግሩ ከዚህ በላይ በሆነ ቁጥር ሊገለጽ እንደሚችል የገለጹት አጥኚው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአካል ጉዳተኝነት መጠን በውል መታወቅ ያልቻለው አንድም ጉዳቱ ከተሰጠው የተሳሳተ ግንዛቤና አሉታዊ አመለካከት ሳቢያ ሲሆን በተለይ ወላጆች የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆቻቸውን በተመለከተ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ካለመሆናቸው የመጣ እንደሆነ ስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

እነዚህ ግለሰቦች በትምህርት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ብንመለከት እንኳን ትምህርት ሚኒስትር በ2012 ያወጣውን መረጃ ዋቢ አድርገው Tewodros (2014) እንደገለጹት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ካሉት ጥቅል ተማሪዎች ውስጥ አካል ጉዳተኞች 3.2% ብቻ የሚሸፍኑ ሲሆን ከጥቅል የአካል ጉዳተኞች ቁጥር አንጻር ሲሰላ በእጅጉ ዝቅ ያለ ወይም 96.8% የሚሆኑት የሀገሪቱ ህጻናት የትምህርት ዕድል አለማግኘታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

መስማት የመሳን ሁኔታ በአለምላይና በሀገራችን ከሚኖሩ ህዝቦች አንጻር ሲታይ ምን ያህሉን ቁጥር እንደሚሸፍን ባጭሩ ለመግለጽ የተሞከረ ቢሆንም መስማት መሳን እንዴት ይከሰታል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ስለሚያስፈልግ ጥቂት ሀሳቦችን ማነሳት ጠቃሚ ነው፡፡ መስማት ከሚለው የቃል ስያሜ ውክልና ብንጀምር መስማት ተለይተው ከሚታወቁ ከአምስቱ የስሜት ህዋሳቶች መካከል በጆሮ የሚከናወንና በአካባቢ ያሉ ድምጾችን ለይቶ እስከ መረዳትና ምላሽ እስከመስጠት ድረስ ያለውን ሂደት የሚወክል ነው፡፡ በተቃራኒው መስማት መሳን ደግሞ አንድን ድምጽ ሰምቶና ተረድቶ ትክክለኛ ምላሽ አለመስጠት ወይም ጭራሹንም ድምፁን አለመለየት ነው፡፡ የመስማት መሳን በአካባቢያዊ የድምፅ ብክለት ችግር ለምሳሌ ከፍተኛ ድምጽ ባላቸው የማሽንና የተሽከርካሪ ጩኸቶች፣ ከመጠን አልፈው በሚለቀቁ የሙዚቃ ድምጾች፣ በዘር ሀረግ፣ በተለያዩ በሽታዎች፣ በአልኮል መጠጥና ከትክክለኛ የመወለጃ ቀን ቀድሞ በሚከሰት ውልደት (ከ9 ወር ቀድሞ)፣ መድሃኒቶችን ያለ አግባብ ከመጠቀም የሚከሰት የህክምና ስህተት፣ በጆሮ አካባቢ በሚደርሱ አካላዊ ግጭቶች ወዘተ ሊከሰት ይችላል (Mohammed 2013)።

በተለይ ከዘር ሀረግ (ከእናት አባት) ጤና ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን የመስማት መሳንን Christen, Lori and Nicholas, (2013) አሜሪካን መሰረት በማድረግ የወጣን አንድ ጥናት ዋቢ አድርገው ሲገልጹ በሀገሪቱ በየአመቱ ከሚወለዱት ህፃናት ውስጥ 12,000 የሚሆኑት መስማት የተሳናቸው ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል 50% የሚሆኑት ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው በተስተላልፎ የሚያጋጥማቸው ናቸው፡፡

ከላይ የጥናቱ አንዱ ትኩረት ስለሆነው መስማት የመሳን ስርጭታዊ ዳራና መከሰቻ ምክንያቶች ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ሌላው መነሳት ያለበት ሀሳብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ያለው አስፈላጊነት ነው፡፡

ከብያኔው መረዳት መረዳት እንደተቻለው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለሁሉም አይነት ሰዎች እንዲሁም ተማሪዎች (መስማት ለሚችሉትም ሆነ ለተሳናቸው) የሚኖረው አዎንታዊ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ የመጻፍ ትምህርት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር ብቻ ተገድበው እንዳይገልጹ አማራጭ መንገድ የሚሆናቸውን ችሎታ የሚጨብጡበት ከመሆኑም ባሻገር ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ለመከታተልና ወደ ፊትም በሚሰማሩበት የስራ መስክ ስኬታማ ሆነው ለመቀጠል የሚያስችላቸውን አቅም የሚገነቡበት እንደሆነ Keys (2000)፣ Hedge (1988) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Troxka (1990) እና Hyland (2003) የመጻፍ ክሂል በተግባቦታዊ

መሳሪያነቱ የተገኘን እውቀት ለሌሎች ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መረጃን ቀርሶ ማቆያ መንገድ መሆኑን በመግለጽ በመደበኛው ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ተሰቶት መቅረብ እንደሚገባው ይመክራሉ፡፡ በተመሳሳይ Heaton (1991) የመጻፍ ክሂልን መማር ሌሎች ተጓዳኝ ክሂሎችን ለማዳበር ከማገዙም ባሻገር በራሱ በመጻፍ ክሂል ውስጥ ያሉ ንዑሳን ክሂሎችን ማለትም የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት ምርጫ፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም፣ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ችሎታ አልቆ ለማምጣት እንደሚያስችል ያስገነዝባሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች አኳያ ብቻ ሲታይም እስካሁን ከተጠቀሱት ሀሳቦች ብዙም የተለየ አይሆንም፡፡ ነገር ግን የአስፈላጊነት መጠኑ ከፍና ዝቅ የሚልበት ሁኔታ እንዳለ ድርሳናት ከሚያነሷቸው ሀሳቦችና በተማሪዎች ዘንድ በተጨባጭ ከሚታየው እውነታ መረዳት ይቻላል፡፡ እንደሚታወቀው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በእለት ተዕለት ህይወታቸው ተራክቦ የሚያደርጉት ከማይሰሙ አልያም የምልክት ቋንቋን በወጉ ከማያውቁ የሚሰሙ ቤተሰቦቻቸው፣ ጓደኞቻቸውና ከሰፊው ማህበረሰብ ጋር ነው፡፡ከእነዚህ ሁኔታዎች ጋር ተስማምተው ግንኙነታቸውን ለማስቀጠል ደግሞ የተለያዩ አማራጭ የተግባቦት መንገዶችን መጠቀም መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም አንደኛው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ነው፡፡ ምንም እንኳን በጽሁፍ የሚከናወን ተግባቦት መማርን የሚጠይቅ ቢሆንም ከሌሎች የመግባቢያ መንገዶች በተለየ በቦታና በጊዜ ያልተገደበ መጠነ ሰፊ ማህበራዊ ተራክቦን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ተመራጭ እንደሚያደርገው ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ Wolbers (2008) እንደሚሉት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የፅሁፍ ቋንቋን ባወቁ መጠን ቴክኖሎጂ ባመጣቸው መሳሪያዎች የመገልገል እድላቸው እጅግ የሰፋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከዘመኑ ጋር አብረው እንዲዘምኑ ብቻ ሳይሆን ስለአለምና ስለ ሌሎች ነገሮች ሊኖራቸው የሚገባውን እውቀት በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምርላቸዋል፡፡ በቦታና በዘመን ከሚርቋቸው አካላት ጋር ለመተዋወቅና ግለሰባዊም ሆነ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ለማስፋት የመጻፍ ክሂል ትምህርት እንደሚያስፈልጋቸው ተመራማሪዋ ያብራራሉ፡፡

ይሁንና የመጻፍ ክሂል ትምህርት መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ሲቀርብ በሁለተኛ ቋንቋነት እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምምድ ጊዜ ከአካባቢያቸው ያገኙት የቀደመ እውቀት የሌላቸው በመሆኑ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ በርካታ ችግሮች ሲገጥሟቸው ይስተዋላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የጽሁፍ ስርዓት ብቻ ሳይሆን ለንግግር አጠቃቀሙም አዲስ ከመሆናቸው የተነሳ እንዲያውቁ የሚፈለገው በሁለቱ

አውዶች ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ክህሎት ነው (Wolbers 2008፣ Elizabeth 2009)፡፡ ይህ ደግሞ ሂደቱን የበለጠ ከባድ ያደርገዋል፡፡ በእርግጥ መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ጋር በተገኛኘ ሊዘረዘሩ የሚችሉ በርካታ ተግዳሮቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የትምህርቱ አቀራረብ፣ የምልክት ቋንቋ ጣልቃ ገብነት፣ ለትምህርቱ የሚኖራቸው ፍላጎት፣ የማህበረሰባዊ ድጋፍ ማነስ  የመሳሰሉት ችግሮች በስፋት ከሚታዩት መካከል ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ትምህርቱ የሚሰጥበት ዓላማ እንደ ሁሉም ተማሪዎች የቃላትንና የሰዋስው ህግጋትን እንዲያውቁ፣እንደተገኙበት አውድም እራሳቸውን እንዲገልጹ፣በምልክት ቋንቋ ለመግለጽ አዳጋች ሊሆኑባቸው የሚችሉ አሻሚ ጽንሰሀሳቦች በቀላሉ እንዲያብራሩ፣ እንደ የስራ ማመልከቻዎች፣ ደብዳቤዎች፣የግል ማስታወሻዎች ወ.ዘ.ተ ያሉ የግል ፍላጎታቸውን የሚገልጹባቸው መጻጽፎችን ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ እንዲያረቁ፣ ምናባዊ እይታቸውን በማስፋት የፈጠራ ታሪኮችን እንዲጽፉና በተጻፉ ስራዎችም ላይ የራሳቸውን ሂስ ለማቅረብ የሚያስችል አቅምን እንዲያጎለብቱ፣በአመክንዮ የተደራጁ ሀሳቦችን እንዲፈጥሩና ብሎም ለሌሎች እንዲያጋሩ፣ በአጠቃላይ ከጥሩ ጸሃፊያን እኩል ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን ስብዕና ይዘው እንዲገኙ ማስቻል በመሆኑ ለታለመለት ግብ እንዲደርሱ  በተቻለ መጠን በመማር ሁኔታዎቻቸው ዙሪያ ትልቅ ስራ መስራት ይገባል (Sheilla 2011፣ Anne Gray 2003)፡፡

መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በትምህርትነት መቅረቡ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግድ የሚሆንበትም እውነታ እንዳለ በርካቶች የሚስማሙ ቢሆንም ክሂሉን አሳድጎ በተገለጸው ሁኔታ ተማሪዎችን ተጠቃሚ በማድረጉ ረገድ ግን በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ዘንድ ጥረት ሲደረግ አይስተዋልም፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎች ዘንድ እየታየ ላለው የቋንቋ አጠቃቀም ውሱንነት መባባስ አይነተኛ ተጽዕኖ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የክሂሉን አስፈላጊነት በሚገባ ተረድተው፣ ወደውና ፈቅደው እንዲማሩ ግንዛቤ የማስጨበጡ ስራ ከልምምዱ ጎን ለጎን በየዕለቱ በመምህራን ሊተገበር የሚገባ መሆኑን የጥናቱ አቅራቢ በጽኑ ታምናለች፡፡

### 2.2.2. መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ያለው ተግዳሮት

የመጻፍ ክሂል ትምህርት ችግሮችን ከመስማት መሳን ጋር አያይዘን ከመመልከታችን በፊት እንደአጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ተግዳሮቶች ናቸው እየተባሉ በተለያዩ ምሁራን

የሚገለጹ ጉዳዮችን መዳሰስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንደ Byrne (1988) ገለጻ የመጻፍ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች በላቀ ሁኔታ በመማር ማስተማር ሂደቱ በርካታ ችግሮች ያጋጥሙታል፡፡ ለእነዚህ ችግሮች መከሰት እንደምክንያት ከጠቀሷቸው መካከል አንዱ ክሂሉ በውስጡ የሚይዛቸው አላባውያን ወይም የሚከተላቸው ስርዓቶች ማለትም ይዘት፣ የአጻጻፍ ስልት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት ምርጫ፣ ስርዓተ ነጥብ፣ የሀሳብ አንድነት፣ ግጥምጥምነት፣ ተከታታይነትና የመሳሰሉት መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ አክለውም በጸሀፊው ዘንድ የሚፈጠሩ የስነልሳናዊ ችግር (Linguistic problem)፣ ስነ ልቦናዊ ችግር (Psychological problem) እና ግንዛቤያዊ ችግር (cognitive problem) ሌሎች ህጸጾች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

የእነዚህን ችግሮች ባህሪ በተናጠል ስንመለከት ለምሳሌ ስነልሳናዊ ችግር አብዛኛውን ጊዜ የአንድን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ወይም ህግጋት በመለየት ሂደት ሊያጋጥም የሚችለውን የባህሪይ ውስብስብነት የሚመለከት ነው፡፡ Byrne (1988) እንደሚገልጹት መጻፍን በአፍልቆት የክሂል ዘርፍነት ከሚታወቀው ከንግግር ጋር ብናነጻጽረው የመልእክት አስተላላፊውን የስዋሰው ችሎታ በመፈተን ይታወቃል፡፡ በትምህርትነት በሚቀርቡበት ጊዜም ያላቸው የባህሪ ክብደት በአንጻሩ የተለያየ ነው፡፡ ንግግር በባህሪው ተፈጥሯዊ መግባቢያ እንደመሆኑ መጠን ቋንቋው በሚነገርበት አካባቢ ያደገ አንድ ጤናማ ሰው በክሂሉ መገልገል ይችላል፡፡ ክሂሉን በመልመድ ሂደትም ሊያጋጥሙ በሚችሉ የቃላት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ችግሮች ማስተካከያ ወይም ማብራሪያ ከአድማጭ እያገኘ ችሎታውን የሚያጎለብትበት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ በተጨማሪም በንግግር ጊዜ በተናጋሪዎች የሚፈጠሩ የስዋሰው ስህተቶችን ባሉበት ተቀብሎ ተግባቦቱን ማስቀጠል የተለመደ ነው፡፡ በፅህፈት የሚመሰረተው ግንኙት ግን እንደ ቃላዊ ተግባቦት ባለመሆኑ በሀሳብ አቀባዮና በተቀባዩ መካከል ሊፈጠር የሚችለውን ተግባቦታዊ ችግር መቅረፊያ ቅጽበታዊ አጋዥ መንገድ ባለመኖሩ ግንኙነቱን ከባድ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ላልተሟሉና ስዋሰዋዊ ስርዓታቸውን ላልጠበቁ ውቅሮች አለመፈጠር ተጠንቅቆ የታሸና የተደራጀ ሀሳብን በተገቢ ቅንብር ለማቅረብ መጣር ከአንድ ተናጋሪ በበለጠ ከፀሀፊ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ሀሳብም Richards (1990) ይስማማሉ፡፡

ይሁን እንጂ በሁለቱ ክሂሎች ዘንድ ያለው የባህርይ ክብደት ልዩነት እንዳለ ሆኖ አንደኛው ለሌላኛው መጎልበት አስተዋፅኦ እንዳላቸውም Byrne (1988) ይናገራሉ፡፡ በፅህፈት ስርዓት ለምሳሌ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የዐረፍተ ነገሮች አገነባብ፣የሀሳብ አደረጃጀትና ሌሎች የስዋሰው ስርዓቶች ቋንቋን በማወቅ መጠን የሚወሰኑ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ በንግግር ለተግባቦት

ያልተገለገሉበትን ቋንቋ ከመፃፍ ይልቅ በሚናገሩት ቋንቋ መጻፍ በአንፃሩ የቀለለ እንደሆነ ያሳያል፡፡

እውነታውን መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመማር ሁኔታ አኳያ ስንመዝነው ደግሞ አሉታዊነቱ የጎላ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም፡፡ እነዚህ ልጆች እንዲፅፉ በሚደረጉበት ቋንቋ መናገር ባለመቻላቸው ወይም ታላሚውን ቋንቋ በቅድመ ትምህርት ዕድሜያቸው ባለመልመዳቸው ምክንያት በሚፅፉበት ጊዜ ለበርካታ ስዋሰዋዊ ስህተቶች የመጋለጣቸው ዕድል ሰፊ እንደሆነ Anne Gray (2003) ካቀረቡት ሀሳብም ሆነ በተማሪዎች ዘንድ በተጨባጭ ከሚታየው መረዳት ይቻላል፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደትም ወደ ታለመው ግብ እስኪደርሱ ድረስ ከሌሎች ተማሪዎች የላቀ እገዛ የሚያስፈልጋቸውም ይህንኑ ችግር ለማቃለል ሲባል ነው፡፡

ሁለተኛው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ችግር ስነልቦናዊ ሲሆን ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በሚጽፉበት ወቅት ስህተትን እፈጽም ይሆን? በሚል ስጋት የተነሳ የሚያጋጥማቸውን ውስጣዊ ጭንቀት የሚያመለክት ነው (Byrne1988)፡፡ በእርግጥ  እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ ብዙ ጊዜ የሚመነጨው ለስህተት ከሚሰጥ ተገቢ ያልሆነ አሉታዊ አመለካከት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዘመናዊ በሆነውና በአዲሱ የትምህርት እሳቤ መሰረት በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚያጋጥሙ ስህተቶች የትምህረቱ አንድ አካል ተደርገው የሚቆጠሩና እንደ መማሪያም ጭምር የሚያገለግሉ እንደሆኑ ካለመረዳት የሚመጣን የተማሪዎች ስነልቦናዊ ጭንቀት ለማስወገድ መምህራን የላቀ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሶስተኛው ግንዛቤያዊ ችግር ሲሆን ይህም በታላሚው ቋንቋ ከሚኖር የችሎታ ውሱንነት አኳያ የሚከሰት እንደሆነ Byrne (1988) ይገልጻሉ፡፡ ውሱንነት ሲባል ለምሳሌ ተማሪዎች በሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ስለሚያካትቱት ሀሳብ እጥረት ሲያጋጥማቸው፣ሀሳባቸውን ለመግለጽ ሲነሱም በቋንቋው የመጠቀም ብቃት ሲያንሳቸውና የአደረጃጀት ችግሮች ሲፈትኗቸው የሚስተዋል ነው፡፡

በሌላ በኩል ግርማ (1990) Ede (1992)ን ዋቢ አድረገው እንደገለጹት የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ከባድ እንዲሆን ያደረገው ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ለክሂሉ የሚሰጠው ጥበባዊ ግምት ነው፡፡ይህም በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ክሂሉ በልምምድ የሚገኝ ሳይሆን ከውልደት ጋር ተያይዞ ለጥቂቶች ብቻ እንደሚሰጥ ጸጋ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ይህ ዓይነቱ የተሳሳተ ግምት ደግሞ ተማሪዎች በክሂሉ ላይ በጎ አመለካከት እንዳይኖራቸው ስለሚያደርግ በተዘዋዋሪም ቢሆን

የመማር ማስተማር ሂደቱ  እንዲገታ ያደርገዋል፡፡ በመማር ላይ የሚኖር አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ አመለካከት በራሱ ደግሞ በተማሪዎች ውጤት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል አለመሆኑን የሚናገሩ ምሁራን አሉ (Brand 1989)፡፡ ስለሆነም ትምህርቱ ግቡን እንዲመታ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ተነሳሽነት ለመጨመር ከፍተኛ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

በተጨማሪ Byrne (1996) ፣ Nunan (1989)፣ Richards (1990) የመጻፍ ክሂልን ትምህርትን ውስብስብ እንዲሆን ያደረገው የሚቀርብበት መንገድ እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡ ይህ ሲባል ለምሳሌ በአንድ የክፍል ደረጃ  ጽህፈትን ለማስተማር ታስቦ የሚዘጋጅ እቅድ በይዘቱ፣በመተግበሪያና በምዘና ዘዴው፣ በማስተማሪያ መሳሪያውና በሌሎች የክንውን ንድፎቹ ከተማሪዎች የመማር ሁኔታ፣ ባህላዊ ዳራ፣ እድሜ፣ የክፍል ደረጃ ወዘተ. ጋር የተጣጣመና ሂደቱን በማቅለል ለተሻለ ውጤት የሚያበቃ ሊሆን ይገባል፡፡ ይሁን እንጅ አፈጻጸሙ ከእውነታው ውጭ እየሆነ ለበርካታ ዘመናት ክሂሉ እየተፈራ መቀጠሉን የተጠቀሱት ምሁራን ገልጸዋል፡፡ እውነታው በታላሚው ቋንቋ ጽህፈትን በማስተማር ረገድ እንደሚንጸባረቅም በጥናታቸው ከገለጹት መካከል ሰለሞን (1987)፣ ግርማ (1990)፣ አለማየሁ (2007)፣ የሽጥላ (2008) ይጠቀሳሉ፡፡ ክሂሉን ለማሻሻል እየተባለ በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ በየጊዜው በምሁራን የሚካሄዱ ምርምሮች የችግሩ አንድ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ከፍ ሲል የመጻፍ ትምህርት ተግዳሮት ክሂሉ ካለው ተፈጥሯዊ ባህሪና በተማሪዎች በኩል ከሚኖር የስነልቦናና የአቅም ችግር ሊመነጭ እንደሚችል በስፋት ተገልጿል፡፡ ሀሳቡን መነሻ ለማድረግ የተፈለገበት ዋናው ምክንያትም ገዥነቱ ለሁሉም ዓይነት ተማሪዎች(መስማት ለተሳናቸው እና ለሚሰሙት) መሆኑ ስለታመነበት ነው፡፡ ይሁንና የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ችግር ከሚሰሙ ተማሪዎች እኩል ከሚጋሩትም በላይ ነው፡፡ ከመማር ሁኔታቸው ወይም መንገዳቸው ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሟቸው ችግሮችም በርካታ ናቸው፡፡ በእርግጥ ለችግሮቻቸው ምንጭ ሆነው የሚነሱ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በምዕራፍ አንድ በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ በስፋት ተነስቷል፡፡ ለምሳሌ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የምልክት ቋንቋ ጣልቃ ገብነት፣ ማህበራዊ ተሳትፎ ውስንነት በዋናነት ተጠቅሰዋል (Wolbers 2008፣ Dostal and Wolbers 2014፣ Elizabeth 2009 እና Wolbers.et.al 2012)።

በተመሳሳይ Graham, Bowers, Wolbers, Dostal (2013) መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል ዋነኛው የምልክት ቋንቋ ጣልቃ ገብነት መሆኑን በስፋት የገለጹበት ሁኔታም አለ፡፡ ተመራማሪዎቹ እንደሚሉት መስማት ለሚችልም ሆነ ለተሳነው አንድ ተማሪ የሚቀርብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ክብደትና ቅለት ከሚወሰንባቸው ምክንያቶች አንዱ ተማሪው በታላሚው ቋንቋ የሚኖረው የንግግር ችሎታ ነው፡፡ ማለትም ተማሪው የሚጽፍበት ቋንቋ ቀድሞ አፍ የፈታበት ወይም የሚናገርበት ከሆነ በቋንቋው ሊኖረው የሚችለው የቀደመ እውቀት ሂደቱን የበለጠ ቀላል ያደርግለታል፡፡ ምክንያቱም የሚናገርበትና የሚጽፍበት ቋንቋ አንድ እንደመሆኑ መጠን አፍራሽ የሆነ ልዩነት እንብዛም ባለመኖሩ ነው፡፡ በተቃራኒው ግን የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚቀርብ ከሆነ በሂደቱ በርካታ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ Graham.et.al (2013) ያብራራሉ፡፡ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋለው ችግርም ከዚሁ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ለእነዚህ ልጆች የመጀመሪያ ቋንቋቸው ተደርጎ የሚወሰደው የምልክት ቋንቋ ሲሆን በአወቃቀር ረገድም ለየት ያለ ባህሪ ያለው ነው፡፡ የምልክት ቋንቋ እንደሌሎች ቋንቋዎች ተፈጥሯዊ ድምጽን በመጠቀም በንግግር የሚቀርብ ሳይሆን በአካላዊ እንቅስቃሴዎች፣በፊት ገጽታ አጋዥነት፣ በከናፍራዊ ንባብና በሌሎች መንገዶች የሚታጀብ ነው፡፡ ይህ አይነቱ አገላለጽ ደግሞ ቅጽበታዊ የሆነ ተግባቦትን ከማቀላጠፍ ባለፈ ጽህፈትን በመማር ሂደት የሚያበረክተው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ብዙም አይደለም፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው በምልክት ቋንቋ አጠቃቀም ወቅት በአካላዊ እንቅስቃሴዎች ታግዘው ከሚቀርቡ በርካታ አገላለጾች መካከል የቦታ፣ የቁጥርና የጾታ አመልካቾች እንዲሁም የተጋነኑ ስሜቶች (ደስታ፣ሀዘን፣አግራሞት፣አድናቆት ወዘተ.) በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ Graham.et.al (2013) እንደሚሉት እነዚህ አገላለጾች ደግሞ በምልክት ቋንቋው ስርዓት የጽሁፍ ውክልና ያልተሰጣቸው በመሆኑ ህያው ሆነው የሚቆዩት በምልክት የተግባቦት አውድ ነው፡፡ ሽግግርም የሌላቸው በመሆኑ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን ሲማሩ ቃላትና አረፍተ ነገሮችን በትክክለኛው ቅርጻቸው አዋቅረው አንቀጽን ወይም ድርሰት ለመጻፍ ሲሞክሩ በከፍተኛ ሁኔታ ሲቸገሩ ይታያሉ፡፡

ሌላው መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ላይ ችግር ሆኖ የሚነሳው የመስማት መሳን መከሰቻ ጊዜ እንደሆነ ከSheilla (2011)፣ Christen.et.al (2013) እና ከAlmyehu (2003) ጥናቶች መረዳት ይቻላል፡፡ ምሁራኑ እንደሚሉት መስማት መሳን በሁለት የዕድሜ

ክልሎች ከመከሰቱ ጋር ተያይዞ ቅድመ ልደታዊ (Pre-Born Deaf) እና ድህረ ልደታዊ (Post-Born Deaf) ተብሎ ይከፈላል፡፡ ቅድመ ልደታዊ የመስማት መሳን ከውልደት በፊት በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰት ሲሆን ድህረ ልደታዊ የመስማት መሳን ደግሞ ህፃናት በጤና ከተወለዱ በኂላ በተለያዩ ምክንያቶች ተጠቅተው የሚያጋጥማቸውን የመስማት መሳን ሁኔታን ይመለከታል፡፡ ይሁንና በሁለቱ የዕድሜ እርከኖች መካከል የሚከሰተው ጉዳት የኂላ ኂላ በባለቤቱ ላይ የሚያሳርፈው አሉታዊ ጫና ተመሳሳይ እንደሆነ ቢታመንም ቋንቋን ከመማር (ከመልመድ) ሂደት አንጻር ሲታይ ግን አንደኛው ከሌላኛው የተሻለ አጋጣሚ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ይናገራሉ ፡፡

በተለይ Sheilla (2011) በድህረና ቅድመ ልደት ወቅት የሚከሰተው የመስማት መሳን ችግር በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ መካከል መበላለጥ እንዲኖር ያደርጋል የሚለውን መደምደሚያ ለመስጠት መነሻ ያደረጉት ቋንቋን የመማርና የመልመድ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች ለቋንቋ መልመድ ምክንያት ይሆናሉ ብለው ያቀረቧቸውን ሀሳቦች ሲሆን ከእነዚህ መካከልም ለቋንቋ ለመዳ አካባቢያዊ መስተጋብር ወሳኝ መሆኑን የሚተነትነውን የKrashin’s (2003) የለመዳ ትውረት እና የVygotsky’s ማህበረ ባህላዊ ትውረት በአስረጂነት ያቀርባሉ፡፡

በእርግጥ በየትኛውም ደረጃ ያለና የተከሰተ የመስማት መሳን ሁኔታ የሰዎችን የማወቅና የመረዳት አቅምን ሊገድብ እንደማይችል የWolbers (2008)፣ Sheilla (2011)፣ Christen.et.al (2013) ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ጉዳዩን በአዎንታዊ ተቀብሎ የልጆቹን ፍላጎት ያማከ ድጋፍና ማበረታቻ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ማበረታቻው ደግሞ ከቤተሰብና ከአካባቢ እስከ ትምህርት ቤት ተጠናክሮ የሚቀጥል ሊሆን ይገባል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት መላክ ብቻ ሳይሆን ከመምህሮቻቸው ጋር ዕለት በዕለት እየተገናኙ ለውጣቸውን መከታተል፣ የስነልቦና አማካሪዎችን ማገናኘት፣ ለማህበራዊ ተራክቦ ማጋለጥና በቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲገለገሉና ስለአለም እንዲያውቁ እድል መፍጠር፣ ተግባቦታዊ ችግራቸውን ለመቅረፍም የምልክት ቋንቋን መማርና እንዲጽፉ ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ትምህርት ቤቶችም ልጆቹ የልዩ ፍላጎት ተጠቃሚ እንደመሆናቸው መጠን በዘርፉ ልምድ ባላቸው ባለሞያዎችና ተረጓሚዎች እንዲማሩ ማድረግ፣ የድምፅ ማጉያ ዘዴዎችን አጋዥ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን መጠቀም፣ በምልክት ቋንቋ እንዲገለገሉ ግብዓቶችን ማዘጋጀት፣ የተመቻቸ የክፍል ውስጥ አቀማመጥ እንዲኖር ማድረግ፣ በምስልና በድምፅ የተደገፉ መረጃዎችን ማቅረብ እንደሚገባቸው Sheilla (2011)፣ እና Christen.et.al (2013) በጽሁፋቸው ይገልጻሉ፡፡

ሌላው ከጽሁፍ ውጪ መስማት የማይችሉ ልጆች መግባባት የሚችሉት በድምፅ ወይም በተለያዩ መመሪያዎች (manual means) እና ሁለቱንም በመቀላቀል ነው፡፡ በድምፅ ሲባል ከናፍራዊ ንበትን (Lip Reading) ተጠቅሞ በመናገር ሲሆን መመሪያ (manual) ደግሞ በተለያዩ አካላዊ ምልክቶች የሚደረግ ተግባቦታዊ መግለጫን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም እነዚህን መንገዶች በመጠቀምና ጥቅል የመግባቢያ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ የልጆቹን የተግባቦት አቅም ማሳደግ እንደዚሁም ከቋንቋ ጋር በተገናኘ የሚገጥማቸውን ችግር መቀነስ እንደሚቻልም የተጠቀሱት ምሁራን አክለው ያስረዳሉ፡፡

## 2.3. የመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ ምንነት

እንደ Brown (2001) ገለጻ መስተጋብራዊነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከስነ ትምህርታዊ አንድምታው አንጻር ሲገለጽ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለን የእርስ በእርስ ግንኙነትና ቅንጅታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አቀራረብን የሚያመለክት ነው፡፡ መስተጋብራዊነት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አካላት መካከል የሚካሄድ የሀሳብ፣ የስሜት፣የእውቀት ወ.ዘ.ተ ልውውጥን የሚወክል ሲሆን ውጤቱም የጋራ ውሳኔን የሚያከብር ነው፡፡ መስተጋብራዊነት ከመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴነቱ አኳያ ሲገለጽ ደግሞ ቅንጅታዊ አቀራረብን፣ ቅቡልነትን፣ተነሳሽነትን፣ አቃጂነትና ሀላፊነት መውሰድን ወ.ዘ.ተ የተባሉ መርሆዎችን በመከተል የሚተገበር እንደሆነ Rachell (2013) Brown (2001) እና Hussni (2014) ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ ቅቡልነት ለእውነተኛ የቋንቋ ተግባቦት መፈጠር ከሰዋስው ግድፈት ይልቅ ለሚተላለፈው መልዕክት ዋጋ መስጠትን የሚመለከት ሲሆን ተነሳሽነት ለትምህርቱ መቀልጠፍ ማበረታቻ መስጠትን፣ አቃጂነት ትምህርቱ ለሚያልፍባቸው ሂደቶች የተግባር ንድፍ ማዘጋጀትንና ሀላፊነት መውሰድ ደግሞ ከስህተት መማር እንዳለ በማመን ሙከራን የትምህርቱ አንድ አካል አድርጎ መንዝን የሚመለከት እንደሆነ Brown (2001) ይገልጻሉ፡፡

መስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ጥቅም ላይ እንዴት እንደሚውል ከመመልከታችን አስቀድሞ አጀማመሩ ምን እደሚመስል መጠቆም ያስፈልጋል፡፡ ከድርሳናት መረዳት እንደተቻለው ቀደም ባሉት ዘመናት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይሰጥ የነበረው ራሱን ችሎ እንደ አንድ የትምህርት ክፍል ሳይሆን ሰዋስውንና ሌሎች የቋንቋውን ክፍሎች ለማስተማር ሲባል እንደነበር ነው፡፡ መምህራንን አሰልጥኖና ክሂሉ ላይ ያተኮሩ ይዘቶችን አዘጋጅቶ እንደ አንድ ክፍል ትምህርት መስጠት የተጀመረው በቅርቡ እንደሆነ Kroll (1993)

ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጅ ክሂሉን በራሱ ነጥሎ በማስተማሩ ረገድ ከማስተማሪያ ስነ ዘዴው፣ ከይዘቶቹ አመራረጥና አደረጃጀት፣ ከምዘና አሰጣጡ፣ ከመምህራን የማስተማር ብቃትና አመለካከት፣ ከተማሪዎች የመማር ፍላጎት ወዘተ. አንፃር በርካታ ችግሮች አጋጥመውና እያጋጠሙም እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ (Kroll 1993፣ Richard and Rodgers 2001)፡፡

ምንም እንኳን ከእንከን የጸዳ ትክክለኛና ተመራጭ ነው ተብሎ የተረጋገጠለት አንድ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ ባይኖርም ብዙዎች የተስማሙባቸውና ተግባር ላይ እየዋሉ ያሉት ውጤት ተኮር፣ሂደት ተኮር እና ዘውግ ተኮር አቀራረብ እንደሆኑ (Nunan 1989፣ Raimes 1983፣ Richard and Rodgers 2001) ያስረዳሉ፡፡

ውጤት ተኮር አቀራረብ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሲስጥ የቆየና አሁንም በተወሰነ መልኩ ተግባር ላይ እየዋለ ያለ ልማዳዊና ነባር ክንውኖችን ያካተተ ነው፡፡ አቀራረቡ በጥሩ ሁኔታ ተጽፈዋል ተብለው በሚታመንባቸው ሞዴል ጽሁፎች መሰረትነት ተማሪዎች ተመሳሳይ ጽሁፍ እንዲጽፉ የሚጋብዝ ሲሆን ለሰዋስዋዊ ችሎታ ትልቅ ግምት የሚሰጥ በመሆኑም ልምምዱ በቋንቋው ቅርፅና ህግጋት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህ አቀራረብ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ የሚወሰነው በስተመጨረሻ በሚያቀርቡት የፅህፈት ሰራ ሲሆን ከስህተት የፀዱ ቃላትን፣ ዐረፍተ ነገሮችን፣ አንቀፆችን፣ ስረዓተ ነጥቦችን ወዘተ. አደራጅተው እንዲፅፉ ያልማል (Richards 1990፣ Hedge 1988፣ Raimes 1983)።

እንደ Kroll (1993)፣ Pincas (1982) ገለፃ አቀራረቡ ሶስት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም ውስን ፅህፈት፣ መሪ ፅህፈትና ነፃ ጽህፈት ናቸው፡፡ የእያንዳንዳቸውን ባህሪ ባጭሩ ስንመለከተ ውስን ፅህፈት /Cntrolled Writing/ አላማው ተማሪዎች ከስህተት የፀዳ ፅሁፍን እንዲያዘጋጁ ማድረግ በመሆኑ ብዙ ማሰብንና ማፍለቅን በማይጠይቁ እንደ ባዶ ቦታዎችን መሙላት፣ ቅደም ተከተላቸው የተፋሱ ቃላትን አስተካክሎ አረፍተ ነገርን መመስረት፣ በስንጠረዥ የቀረቡ ግሶችን ከቁጥር፣ ከጊዜ፣ ከፆታ አንፃር መለወጥና በመሳሰሉት ቀለል ባሉ ተግባራት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በአንፃሩ ደረጃው የጽሁፍ ችሎታቸው በዝቅተኛ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ጠቃሚ ተደርጎ እንደሚታሰብም ሙህራኑ ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል መሪ ፅህፈትን ብንመለከት በውስን ፅህፈት ተማሪዎች ከገነቡት የዐ.ነገር አፃፃፍ ችሎታ በተጨማሪ ወደ ነፃ ፅህፈት የሚያሸጋግራቸውን ልምድ የሚያዳብሩበት ነው፡፡ በእርግጥ

በውስን ፅህፈት ተማሪዎች በሞዴል ፅሁፍ ቁጥጥር ስር ከመሆናቸው የተነሳ የሚፈፅሙት ስህተት በመሪ የፅህፈት ደረጃ ከሚፈፅሙት ጋር በአንፃሩ ሲታይ ያነሰ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ደግሞ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች እንብዛም ባልተገደቡና ግለ ገለፃን በማይከለክሉ ለምሳሌ፦ ጅምር ሀሳቦችን በራስ አገላለጽ መጨረስ! ወዘተ. በሚሉ ተግባራት ላይ ትኩረት ስለሚደረግ ነው (Nunan1989)፡፡ ሶስተኛው ነፃፅህፈት /Free-wrting/ ሲሆን በአብዛኛው በመምህሩ በሚሰጡ ርዕሶች ላይ ተማሪዎች ለስዋሰው ህግጋት ብዙም ሳይጨነቁ አስቀድመው ሀሳባቸውን በወረቀት ላይ በነፃነት ካሰፈሩ በኋላ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ተግባራቸው (አርትኦታቸው) ደግሞ በስተመጨረሻ ይምጣ ብሎ የሚያምን ነው (Raimes 1983 ፣ Byrne 1988)፡፡

ሂደት ተኮር አቀራረብ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ማገልገል የጀመረው ከ1970ዎቹ ወዲህ ሲሆን አላማውም በውጤት ተኮር አቀራረብ ላይ ይነሱ የነበሩ ችግሮችን አስወግዶ አዲስ እምርታን ማምጣት ነው፡፡ ስለሆነም ትኩረቱ ተማሪዎች በስተመጨረሻ የሚያቀርቡትን ትክክለኛ የሆነ የፅህፈት ሥራ ማስገኘት ሳይሆን በልምምዱ ወቅት የሚሰሯቸውን ስህተቶች በሂደት ቀንሰው ራሳቸውን የቻሉ አርታኢዎች  እንዲሆኑ ማድረግና የቋንቋውን ቅርፅና መዋቅር ከጠበቁ የጽሁፍ ውጤቶች ይልቅ ወደዚያ ሊያደርሱ በሚችሉ ሂደቶች ላይ በመሆኑ ከውጤታዊ አቀራረብ ጋር ሲነፃፀርም በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎችን ስኬታማ ያደረጋል ተብሎ በምሁራን ዘንድ የሚታመን ነው (Nunan 1989፣ Seow 2002፣ Ferris 2003)፡፡

ከሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ በኋላ የመጣው "ጀነር" ተኮር አቀራረብ ሲሆን ሰዋስዋዊ ህግጋቶችን ከማህበረሰቡ የቋንቋ አጠቃቀም ጋር አዋህዶ ማስተማር ላይ ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ ባህሪውም ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር በከፊል እንዲመሳሰል አድርጎታል፡፡
ከላይ የተጠቀሱት የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች ፍጹም ጥሩ ወይም መጥፎ ናቸው ተብለው ሊፈረጁ እንደማይችሉ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ ውጤት ተኮር አቀራረብ ለትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት መስጠቱ የሚበረታታ ቢሆንም በውጤት ላይ ብቻ ከማተኮሩ የተነሳ ሂደታዊ ተግባራትን መዘንጋቱና የመምህሩን የበላይነት ሚና ያጎላ መሆኑ እንዲተች አድርጎታል፡፡ በአንጻሩ ሂደታዊ አቀራረብ በውጤት ተኮር ላይ የሚታየውን የተማሪዎች ጥገኝነት በመግታት በክፍል ውስጥ በመካከላቸው ተባብሮ የመስራት ባህል እንዲኖርና በተለያዩ የሂደቱ ደረጃዎች ውስጥ እንዲያልፉ የሚያበረታታ መሆኑ ቢያስመሰግነውም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማላቅ ሲል ነጻ ጽህፈትን እንደ ዋና ተግባር

መውሰዱና ለቋንቋው የሰዋስው ህግጋት የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆኑ ትችት ውስጥ አስገብቶታል፡፡

ዘውግ ተኮር አቀራረብም እንደዚሁ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከእነማህበራዊ አውዱ ተማሪዎች እንዲረዱ ማድረጉ ጥሩ ጎኑ ሆኖ ሳለ የተማሪዎችን የአፍልቆት፣ የተሳታፊነት ሚና የሚያሳንስ መሆኑ በድክመት እንዲነሳ ሆኗል (Nunan 1989፣ Richard and Rodgers 2001 እና Raimes 1983)፡፡

በመሆኑም የመጻፍ ትምህርት ሂደቱን በተሻለ መልኩ ለማከናወን የሁሉንም አቀራረቦች መሰረት ያደረገ የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር ጠቃሚ አስተሳሰብ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህንንም በቋንቋ ማስተማሪያ ትውረቶችና ዘዴዎች ላይ ከተደረጉ ጥናቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡ለምሳሌ McLaughlin (1991) የሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ቲዎሪዎችንና ዘዴዎችን ባህሪና አቀራረብ በጥልቀት በመመርመር ቋንቋን በማስተማር ረገድ ጥሩና ብቸኛ መንገድ ተብሎ የሚወሰን እንደሌለና ትምህርቱን የተሻለ አድርጎ ለማቅረብ ግን ከየዘዴዎቹ መምህራን ጠቃሚ ስልቶችን በመምረጥ ማስተማር እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ Harmer (1996)፣ Mc.Carrier እና Pinnell (1994) እንዲሁም Raimes (1983) ይጋሩታል፡፡

ይህ አይነቱ አካሄድም በተለያዩ ሀገራትና ቋንቋዎች በስፋት እየተሰራበትና ጥሩ ውጤት እያመጣ ያለ እንደሆነ በጥናቶች ላይ ከተደረገው ዳሰሳ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦችን አቀናጅቶ በማስተማር ረገድ ተግባር ላይ እየዋሉ ካሉ የማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል መስተጋብራዊ ዘዴ አንዱ ነው፡፡ የዚህን የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነት በተመለከተ መስማት ከሚችሉ ተማሪዎች አኳያ በጥናት ፈትሸው ማብራሪያ የሰጡ የተለያዩ የውጪ ሀገር ምርምሮች ቢኖሩም ከአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አንጻር ግን ግርማ በ(1990) ካካሄዱት በስተቀር ሌሎች ጥናቶችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ የዚህ ጥናት አብይ ጉዳይ ደግሞ መስተጋብራዊ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴን /Intractive Writing Teaching Mthod) መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች አንጻር መመርመር እንደመሆኑ መጠን በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተካሄዱ የውጪ ሀገር የጥናት ውጤቶችንና ድርሳናት የሚያነሷቸው ሀሳቦችን ዋቢ በማድረግ ቀጥሎ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

### 2. 3.1. በመስተጋብራዊ ዘዴ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ማስተማር

በዳራው ላይ እንደተገለጸው የውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት በሞዴል ጽሁፎች አማካኝነት በሰዋስው ስርዓት አጠባበቃቸው፣ በቃላት ቅንብራቸው ወዘተ. አቻ የሆኑ ጽሁፎችን በማስገኘት

ትክክለኛነት /Accuracy/ እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ በአንጻሩ ሂደት ተኮር ደግሞ ከጽሁፍ ትክክለኛነት ይልቅ በርዕቱነት /Fluncy/ ላይ በማተኮር ተማሪዎችን በአቻ ጽሁፍ ጥናት ሳይሆን ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ማርቀቅ፣ መከለስ ወዘተ. በተባሉ ልምምዶች የሚያሳትፍ መሆኑን Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ደግሞ የውጤታዊና የሂደታዊ አቀራረቦች ቅንጅትን የተከተለ እንደመሆኑ መጠን ለፅሁፍ ትክክለኛነት /Accuracy/ እና ርዕቱነት /Fluncy/ መዳበር እድል የሚሰጥ መሆኑን Brown (2001) Mc.Carrier and Pinnell (1994) ይገላጻሉ፡፡ ወይም በሌላ አገላለጽ እንደ ውጤታዊ አቀራረብ የቋንቋውን ቅርፅ መሠረት አድርጎ በሚከናወን የተማሪዎች የመጨረሻ የፅሁፍ ላይ ያልተገደበና እንደ ሂደታዊም ይህንን ያልዘነጋ ነገር ግን ሁለቱንም አቀራረቦች እንዳስፈላጊነታቸው አዋህዶ መተግበር በሚቻልበት ሁኔታ የቀረበ ዘዴ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዘዴው የመጀመሪያና የሁለተኛ ቋንቋቸውን የሚማሩ ተማሪዎችን ለማስተማር ከማገልገሉም ባሻገር መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሳደግ ጥቅም እንዳለው በጥናት ፈትሸው ያረጋገጡ ምሁራን Wolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Elizabeth (2009) እና Wolbers.et.al (2012) ያስረዳሉ፡፡

እንደ Elizabeth (2009) ገለጻ መስተጋብራዊ ዘዴ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ ሆኖ ማገልገል የጀመረው እ.ኤ.አ ከ1991 ዓ.ም ወዲህ በኦሀዩ ዩኒቨርስቲ በሚያስተምሩ መምህራን ሲሆን የመማር ማስተማር ሂደቱን በማዘመን ረገድ ባለው ተቀባይነት ምክንያት የተለያዩ ቋንቋዎችን ለማስተማር እየተሰራበት ያለና በምርምሩም በኩል የበርካታ ተመራማሪዎችን ትኩረት እየሳበ የመጣ ነው፡፡ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር እንደሚያገለግል ድርሳናት ቢያመለክቱም መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ሲቀርብ ግን በሁለት አብይ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡

የመጀመሪያው ትኩረት የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ውጤታዊና ሂደታዊ (ቅንጅታዊ) ሆኖ በሚቀርብባቸው መርሆዎችና ዝኩሮች[3] ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትምህርቱን (ልምምዱን) ቀልጣፋ በማድረግ የታቀደውን አላማ ለማሳካት የጀርባ አጥንት ሆነው በሚያግዙ የመምህር ተማሪ ግንኙነቶች ላይ ነው፡፡

---

[3]ዝኩሮች የሚለው ቃል ከዚህ ጥናት አንጻር ሲገለጽ በመጻፍ ትምህርት ሂደት ሊተኮርባቸው የሚገቡ የተግባራት አይነቶችን ይመለክታል፡፡

እነዚህ ሁለቱ የማስተማሪያ ዘዴው መገለጫ ባህሪያቶች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ብቻ ሳይሆን ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት በእጅጉ ለማሳደግ የሚያስችሉ የጽህፈት ተግባራት ማሕቀፎች መሆናቸውን ዘዴውን ካጠኑ ምሁራን ከWolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Elizabeth (2009)፣ Wolbers.et.al (2012) መረዳት ይቻላል፡፡ ምሁራኑ እንደሚሉት ዘዴው በተግባራት አቀራረቡ ተማሪዎችን ዕለት በዕለት በሚከናወኑና በሚመዘኑ ልምምዶች ውስጥ እንዲያልፉ የሚያደርግ፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ለመተግበር ምቹ የሆነና በእርስ በርስ ተደጋግፎ ሊዳብር የሚችል የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜትና የመማር ፍላጎት የሚያበለጽግ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ የፅህፈት ተግባሩ በአብዛኛው የሚከናወነው በተማሪዎች ሲሆን መምህሩ ደግሞ የአመቻችነት ሚናውን ይወጣል፡፡ ስለሚፅፉት ነገር ተማሪዎች ለመምህራቸው ያሳውቃሉ እንጅ መምህሩ ርዕስ ወስኖ እንዲሰጣቸው አይጠበቅበትም፡፡ በዚህ መልኩ ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉት መስተጋብር የፅህፈት ችሎታቸውን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተጓዳኝ ክሂሎታቸውንም ሊያዳብርላቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ይህንንም Fountas.et.al. (2000) መስተጋብራዊ ዘዴ ተማሪዎች የመጻፍ ክህሎታቸውን ከማንብና ከንግግር (መስማት ለተሳናቸው ሲሆን ደግሞ ከምልክት ቋንቋ) ጋር እንዲያገናኙ የሚጠቅማቸው እንደሆነ ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

እንደ Mc.Carrier and Pinnell (1994፡149-170) ገለፃ አቀራረቡ ተማሪዎችና መምህራን ተግባርን እኩል የሚጋሩበትና ስለሂደቱ በጋራ የሚወስኑበት ከመሆኑ የተነሳም ''Sharing pen'' እየተባለ ይጠራል፡፡ ሌላው ዘዴው በየትኛውም የክፍል ደረጃ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርሱ የጽህፈት ችሎታዎችን ለማስጨበጥ ውጤታማ መሆኑን (Wolbers 2008) አክለው ያስረዳሉ፡፡ ምላሾች ምቹ በመሆኑ የእያንዳንዱን ተማሪ አቅም ለይቶ ለመደገፍም ሆነ ለማበረታታት ሰፊ እድል ይሰጣል፡፡

ሌላው አቀራረቡ ተመሳሳይ ወይም የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች አንድ ላይ በማቧደን አልያም ለይቶ በማስተማር በመካከላቸው ሊኖር የሚችለውን ልዩነት በማጥበብ ረገድ ተመራጭ ቢሆንም አንዳንዴ ግን በርካታ የተማሪ ቁጥር ባለበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ በቀላሉ መተግባር አመቺ እንዳልሆነ Flo and Bill (2009) ያሳስባሉ፡፡

የማስተማሪያ ዘዴው ተማሪዎች የታለመው የትምህርት ግብ ላይ እስኪ ደርሱ ድረስ በበርካታ የልምምድ ደረጃዎች ስር እንዲያልፉ እድልን የሚሰጥ፣ ምዘናውም ሂደትን መሰረት ያደረገ፣

የማቀድ፣ የማርቀቅ፣ የመከለስ፣ የመገምገምና የማጠቃለል ጊዜ ተግባራትም ያሉትና በተጨማሪም የተማሪዎችን የዕለት ተዕለት ለውጥ መከታተያ ግለ ማህደር ምዘና (ፖርትፎሊዩ) ለማደራጀትም ምቹ እንደሆነ Flo and Bill (2009)፣ Wolbers (2008) ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ መስተጋብራዊ የማስተማር ዘዴን በተለያዩ ጊዜያትና የክፍል ደረጃዎች በተደጋጋሚ በሙከራ ጥናት ፈትሸው ውጤታማነቱን ከመሰከሩት የWolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Wolbers.et.al (2012) እና Wolbers.et.al (2016) ጥናት የምንረዳው መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የምናስተምረው የመጻፍ ክሂል ትምህርት በቅድመ ቋንቋ ለመዳ እድሜቸው ሊያዳብሩ ያልቻሉትን የቋንቋ ችሎታ ክፍተት ሊሞላ በሚችል መልኩ በመሆኑ መስማት ለሚችሉት ተማሪዎች ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ሲነፃፀር በበርካታ ፍች ወካይ ስዕላዊ መግለጫዎች የታገዘ ሊሆን የተገባ መሆኑን ነው፡፡

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ሲማሩ እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው ከመሆኑም ባሻገር ልዩ ትኩረት(ድጋፍ) እሚሹ እንደመሆናቸው መጠን ችግሩ ተደራርቦ በትምህርታቸው ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ለሚማሯቸው እያንዳንዱ ቃላት ተጨማሪ ስዕላዊና መግለጫዎችና ባለ ብዙ አማራጭ ጽንሰ ሀሳባዊ ፍቺ ያስፈልጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ “ዛፍ” የሚለውን ቃል ተናጠላዊም ሆነ አገባባዊ ፍቺ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች አስተምሮ ማለፍ ከሌሎቹ ተማሪዎች አንፃር ሲመዘን ያን ያህል ቀላል አይሆንም፡፡ ምናልባትም ስዕሉን ስሎ ቅጠሉን፣ ግንዱን፣ ቅርጫፎቹን ወዘተ. እያመለከቱ በምልክት ቋንቋ ታግዞ ትርጉም መስጠትንና አረፍተ ነገር መመስረትን ይጠይቃል፡፡ ጽህፈትን ለማከናወን ደግሞ ከቃል ትርጉም ወይም ከዚህ መሰል ተግባር መጀመር አስፈላጊ መሆኑ መዘንጋት እንደሌለበት Flo and Bill (2009) ይስማማሉ፡፡መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን ከሌሎች በበለጠ እንዲመረጥ ካስቻሉት ምክንያቶች ዋነኛው ከተማሪዎች የመማር ሁኔታ አንጻር ሂደቱን ሊያቀሉ የሚችሉ የተለያዩ አማራጭ የማስተማሪያ ስልቶችን አጣምሮ ለመተግበር ምቹ መሆኑ እንደሆነም አጥኚዎች ይናገራሉ፡፡ እስካሁን መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ባጭሩ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይሁንና በዚህ ዘዴ የሚቀርብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ምን? ምን? ደረጃዎችን ማለፍ እንዳለበትና መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በማስተማሩ ረገድም በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራት እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው

ማብራራት ስለሚያስፈልግ የማስተማሪያ ዘዴውንበጥናታቸው ፈትሸው ትንታኔ የሰጡ የተለያዩ ምሁራን ያቀረቧቸውን ሀሳቦች በማቀናጀት ቀጥሎ በቀረበው መልኩ ለመግለጽ ይሞከራል፡፡

Wolbers (2008) እና Williams (2011) ዘዴው በተግባር ሲውል ተማሪዎች ''POSTER'' ወይም ''POWTER''ምህጻሩ ሲብራራም ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መጻፍ (መግለጽ)፣ መተርጎም፣ አርትኦት ማድረግና መከለስ በተባሉ ስድስት ደረጃዎች ውስጥ ማለፍ እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡

*ሀ.ማቀድ*

ፅህፈትን በማስተማር ሂደት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ተማሪዎችም ቢሆኑ በዚህ ደረጃ ስለሚፅፉት ነገር ርዕስ የሚመረጡበትና ርዕሳቸውን ሊያጎሉላቸው የሚችሉላቸውን ጠቃሚ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስቡበት እንዲሁም ለጽሁፍ ተግባሩ እራሳቸውን የሚያዘጋጁበት እንደሆነ ይታወቃል (Oshima and Houghu 1981 እና Harmer 2004:4-6)፡፡ ይሁን እንጂ ተግባሩ መስማት በተሳናቸውና በሚችሉት ተማሪዎች ዘንድ እኩል ቀለለ ላይሆን ይችላል፡፡ Flo and Bill (2009) ሲገልጹም አንድን ርዕስ መርጦ በስሩ ስለሚመጡ ሀሳቦች ማቀድና አስተዋጽኦ መንደፍ ከፊደል (ሆሄያት) ልየታና ያለችግር ከአረፍተ ነገሮች ግንባታ በኋላ የሚመጣ ተግባር ነው፡፡ በየትኛውም የክፍል ደረጃ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከፊደል ልየታ ጀምሮ ዐረፍተ ነገሮችን እስከ ማዋቀር ድረስ ከፍተኛ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ይህንን ችግር ለመለየትም ሆነ ለመፍታት መምህራን የተለያዩ ተግባራን ሊያከናውኑ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በእያንዳንዱ ተማሪ የተመረጠውን ርዕስ እየዞሩ አልያም ጽሁፋቸውን ሰብስቦ በማንበብ ወይም ሠሌዳ ላይ በመፃፍ ትክክለኛነታቸውን ማሳየት፣ ከመሰሎቻቸውም ሆነ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ጥንድ ሆነው በርዕሶቻቸው ላይ በወረቀት አሊያም በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አስተያየት እንዲለዋወጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን ይበልጥ ያጠናክርላቸዋል፡፡

ቀጥሎ በርዕሶቻቸው ስር ስለሚያነሷቸው ሀሳቦች አንድ በአንድ እየዘረዘሩ እንዲፅፉ እድሉን መስጠትና የፃፉትን ገምግሞ ምግበ ምላሽ መስጠት ይጠበቃል፡፡ እንደ ምሁራኑ አነጋገር ተማሪዎቹ ለሚፅፉት ዝርዝር ነገር ሀሳብ ማፍለቁ ያን ያህል ቀላል ላይሆን ስለሚችል መምህሩ መሪ ሀሳቦችን ሊሰጥ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ስለ "ስፖርት" ሊፅፉ ቢሆን ከስፖርት ዓይነቶች የትኛውን እንደሚመርጡ? ለምሳሌ እግር ኳስ፣ ሩጫ፣ ዋና ወዘተ. ዝርዝር ሀሳቦችን በሠንጠረዥ መልክ መምህሩ በመጻፍ ሊያስመርጣቸው ይችላል፡፡ አንዱን ከመረጡ በኋላም ሌሎች መሪ ሀሳቦችን እንደገና በመጻፍ ዝርዝሮችን ደግሞ እነሱ እንዲፅፉ ያደርጋል፡፡የእግር

ኳስ ስፖርትን የመረጡ ቢሆን የስፖርት አይነቱን ለመከወን የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ምን እንደሆኑና እነዚያንም ማሊያ፣ ጫማ፣ ሜዳ፣ ወዘተ. እያሉ እንዲዘረዝሩ ቢደረግ፣ በተጨማሪም ከታዋቂ እግር ኳስ ተጫዋቾች የሚያደንቁትን እንዲገልፁ መሪ ጥያቄ ቢሰጣቸው የሚጽፉበትን ርዕስ ጉዳይ እያስፋፉት ይሄዳሉ፡፡ የተደራጀና ትርጉም ያለው ፅሁፍም እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በሀሳብ ነደፋቸው ወቅት የቃላት ፍቺ ሊፈትናቸው ይችላል፡፡ እንግዳ ሆነው ለሚከብዷቸው ቃላት መምህሩ ተመሳሳይ፣ ተቃራኒና አውዳዊ ፍቺ እየሰጠ በቻርት መልክ ሊያሳውቃቸው ይገባል፡፡ ወይም የማያውቁትን አዲስ ቃል በሌላ መልኩ ከሚያውቁት ፍቺ ጋር በማዛመድ አልያም በማቃረን ማሳየት ወይም እንደተመራማሪዎች አጠራር (Buld Concept Vocabulary Webs or Chat model) መጠቀም እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡ በአውድ ሲባል ደግሞ እንግዳ ቃላቱን የሚሸከሙ ዐረፍተ ነገሮችን በመመስረት አልያም አንቀጽ በማዋቀር የቃላቱን ትርጉም ከሀተታው እንዲረዱና በገባቸው መጠን በራሳቸው ዐረፍተ ነገሮችን እንዲመሰረቱ ማድረግ ሂደቱን ቀላል ያደረገዋል፡፡

ሌላው አዳዲስ ቃላትን ከሌሎች እውቀቶቻቸው ጋር በማዛመድ ምሳሌዎችን በመስጠት፣ መዝገበ ቃላዊ ፍቺያቸውን በማጣቀሻ መጻህፍት አማካኝነት ማሳወቅ ወይም በአጥኚዎች አገላለጽ (Knowledge Model of Vocabulary Acquisition) የተባለውን ስልት በመተግበር ሂደቱን ቀላል ማድረግ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ከተባለው ውጭ የተማሪዎችን የተረድኦት ሁኔታ እየተመለከተ መምህሩ በራሱ ፈጥሮ የሚጠቀማቸው ስልቶች ትምህርቱን እንደሚያቀላጥፉት ይታመናል፡፡ የድጋፍ አሰጣጡም የአንድ ለአንድ (One to one Support) የተከተለ መሆን እንዳለበት (Flob and Bill 2009) ያስረዳሉ፡፡

እንደ Dostal and Wolbers (2014) ገለጻም ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርዕስ ሲመርጡ መነሻ ሀሳብ የሚያገኙበትን መንገድና ምንጮችን ማመቻቸት ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች እንደ ሌሎቹ "ርዕስ መርጣችሁ በዚህን ያህል ቃል የሚያልቅ አንቀጽ ጻፉ!" በሚል ትዕዛዝ የሚጽፉ አይደሉም፡፡ በሚያከናውኑት እያንዳንዱ ተግባር ምሪት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለሆነም ርዕስ እንዲመርጡ የሚያግዟቸውን ሞዴል ፅሁፎች፣ በእይታ የተደገፉ ምስሎችንና ሀሳቦችን ቀድሞ ማቅረብ ይገባል፡፡ እንደ Raimes (1983፣7) እና Button.et.al (1996:445) ገለጻ መስተጋብራዊ ዘዴ የውጤትና ሂደት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ቅይጥ እንደመሆኑ በአተገባበር ሂደቱ ላይም በሞዴል ጽሁፎች የሚጀምር፣ በማስተማሪያ መሳሪያነት ደግሞ የስዕል ወረቀቶችን በዓይነት በቀለም የሚጠቀም፣ ማርከሮችን፣ መቅረጸ ድምጾችን፣ የተቆራረጡና መለጠፍ የሚችሉ የሆሄያትና የቃላት ከርዶችን፣ ነጭ ሰሌዳ፣ መጠቆሚያ ቀስት፣ ሰንጠረዦችን

ወዘተ.የሚፈልግ ነው፡፡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ሲዉል ደግሞ ከዚህ በላቀ ሁኔታ ተጠናክሮ መቅረብ እንደሚገባው ከሀሳቡ መረዳት አያዳግትም፡፡

**ለ.ማደራጀት**

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ግልጽ ባለ መልኩ ወደ ጽሁፍ እንዲቀይሩት የሚረዳቸውን የድረጊት ማህቀፍ የሚነድፉበትና ለትግበራው የሚዘጋጁበት እንደሆነ Wolbers (2008) እና Williams (2011) ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሲባል ለጽሁፍ ስራቸው የሰበሰቧቸው ፍሬ ሀሳቦች በዝተው እንዳያስቸግሩና የጽሁፉን አቅጣጭ እንዳያስቱ እንደጠቃሚነት ደረጃቸው የሚመርጡበት ነው፡፡ ስለሆነም በማደራጀት ሂደት ተማሪዎች ርዕሴን ያጎሉልኛል የሚሏቸውን ሀሳቦች እንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል የሚያዋቅሩበት ነው፡፡

**መ.መግለጽ፣ መጻፍ**

ደረጃው በሁሉም አይነት ተማሪዎች ዘንድ ለሚከናወን የፅህፈት ትምህርት በተመረጠ አንድ ርዕስ ላይ የተሰሰበቡ መረጃዎች በመጀመሪያ ረቂቅነት የሚተነተኑበት ነው (Smoke1987:70)። በሂደቱ የሚከናወኑት ተግባራት አድማስ  ግን እንደ ተማሪዎቹ የመማር ሁኔታ የተለያዩ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መጻፍን ሲማሩ በየደረጃው የሚያጋጥማቸው ችግርና ሊደረግላቸው የሚገባ እገዛ ፈረጀ ብዙ ነው፡፡ በዚህ ደረጃም የፅህፈት ልምምድን ሲያደርጉ ከስነዘዴው ጋር ተዋህደው ሊተገበሩ የሚችሉ ስልቶች አሉ፡፡ እነዚህ ስልቶች እንደሚፃፈው የፁሁፍ አይነት የተለያዩ

ናቸው ፡፡ እንደሚታወቀው መምህራን ቃላትን፣ ዐረፍተ ነገሮችን፣ አንቀፆችንና ሰፋፊ ሀተታዎችን (ድርሰትን) ሲያጽፉ የሚጠቀሟቸው መንገዶች አንድ አይነት አይሆኑም፡፡

Flo and Bill (2009፣17-18) Vaughn, Boss and Chumm (2003)ን በመጥቀስ ሲገልጹ ለምሳሌ ተማሪዎች አንቀጽን የሚጽፉ ቢሆን  "PLEASE Strategy"ን መጠቀም ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ የእንግሊዝኛው አገላለጽ በአማርኛ ትርጉሙ ሲብራራም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

P= Pick topic, audience and paragraph type

- በመጀመሪያ ደረጃ የሚጽፉበትን ርዕስ፣ ተደራሲያቸውንና የሚፅፉትን የአንቀጽ አይነት መለየት አለባቸው፡፡

L= List Information about the Topic

- በርዕሱ ስር ተካታች የሆኑ ሀሳቦችን መሰብሰብና መንደፍ ያስፈልጋል፡፡

E= Evaluate whether the list is complete and determine how to order the itmes into  the list.

- የተነደፉት ሀሳቦች ቅደም ተከታላቸውን ስለመያዛቸውና በቂ ስለመሆናቸው መገምገም ይጠበቅባቸዋል፡፡

A= Activate your Writing by starting with atopic sentence

- ሀይለቃልን (መሪ ሀሳብን) በማስቀደም የጽሁፍ ስራውን መጀመር ያስፈልጋል፡፡

S= Supporting details in sentences using items form list

- ደጋፊ ሀሳቦችን በመጠቀም የፀሁፉን ጭብጥ ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

E= End with Strong concluding sentence & evalute the paragraph by Revising& editing

- ጽሁፉን በጠንካራ የመደምደሚያ ዐረፍተ ነገር መቋጨትና የክለሳ ስራ ማከናወን ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ሰፋፊ ሀተታዎችን (ድርሰትን) ወይም /Essay/ እንዲፅፉ በሚደረጉበት ወቅት ደግሞ “TREE Strategy” እና “DEFENDS Strategy” የተባለውን ስልት ተጠቅመው መምህራን እንዲያለማምዷቸው Flo & Bill (2009፣17-18) አስተያየታቸውን በጽሁፋቸው ይገልጻሉ፡፡ለአብነት የ“TREE Strategy” የእንግሊዝኛ አገላለጽ በአማርኛ ትርጉሙ ሲብራራ

T= Write topic sentence

- ሀይለቃል (መሪ ዐ.ነገር) መፃፍ

R= Think of reasons to support atopic

- ርዕሱን የሚደግፉ አመክንዮችን ማሠብ

E= Examine your reasons

- የአመክንዮቹን አሳማኝነት መገምገም

E= Think of ending or conclusion

- ስለመደምደሚያ ሀሳቦች ማሰላሰል

እንደ ተመራማሪዎቹ እምነት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የማስተማሪያ ስልቶች በልምምዱ ወቅት መምህራን በመርህነት ሊጠቀሟቸው የሚገቡ ቢሆንም ለእያንዳንዱ መርህ ተግባራዊነት ግን እንደተማሪዎች የተረድኦት ሁኔታ ተጨማሪ ገለፃዎች፤ እርማቶችና ምግበ ምላሾች የማይቀሩና አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ጽሁፍን ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶችን በምልክት ቋንቋ ከመግለጽ በዘለለ በእይታ ወይም በስዕል አስደግፎ ማስረዳት የተሻለ ይሆናል፡፡ በእርግጥ በስዕል ሊገለፁ በማይችሉ ፅንስ-ሀሳቦች ላይ እንዲፅፉ የሚደረግበት ወቅት ይኖር ይሆናል፡፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ አሻሚ ፅንስ ሀሳቦችን ተጨባጭ አድርጎ ለማቅረብ ከምልክት ቋንቋው ጋር

ተሳልጠው በሰሌዳ ላይ ተብራርተው  በመምህሩ የሚቀርቡ ገለፃዎች በቀላሉ የሚዘነጉ አይደሉም፡፡

**ሰ.መተርጎም**

በትርጎማ የጽህፈት ደረጃ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ ውጭ እንዳይወጡ ወይም ይዘታቸውን ለቀው ስላልተፈለገ ነገር ሲጽፉ እንዳይገኙ መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ስራ እየተመለከተ በምልክት ቋንቋቸውም ሆነ ሌላ መንገድ ተጠቅሞ በመተርጎም ግንዛቤ የሚያስጨብጥበት ነው፡፡ ይህም የመጻፍ ክሂልን ከማንበብ፣ ከንግግር (ከምልክት ቋንቋ) ጋር አገናኝቶ የማስተማር አንዱ የመስተጋብራዊ ዘዴ ጠንካራ ጎን መገለጫ መሆኑን Wolbers (2008) ያስረዳሉ፡፡

**ረ. አርትኦት ማድረግ**

በአርትኦት የጽህፈት ደረጃ በመጀመሪያ ረቂቅ የቀረበው ፅሁፍ ከሰዋሰው ህግጋት አጠባበቁ፣ ከሀሳብ አደረጃጀቱ፣ ከይዘት ግልፅነቱ፣ ከተደራሲያን ሁኔታና ከሌሎች መሰል ስርዓቶች አንፃር ትክክለኛነቱ ምን ያህል እንደሆነ? የሚገመገምበት ነው፡፡ ደረጃው ተማሪዎች በጥንድም ይሁን በግል የፃፉትን ጽሁፍ ደጋግመው እንዲያነቡ ዕድል ስለሚፈጥርላቸው የውስጣቸውን የጽሁፍ ችሎታ /inner voice/ ለማውጣት ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ ደረጃ መምህሩ የሚሰጠው እርማትና ምግበ ምላሽ ተማሪዎች በራሳቸው አልያም በጓደኞቻቸው ከሚያከናውኑት የእርስ በእርስ ተመጋገቦ ተከትሎ እንጅ ቀድሞ መምጣት እንደሌለበትና እንዲሁም ምግበ ምላሹ ጽሁፋዊ ሲሆን ደግሞ ተማሪዎችን የበለጠ ሊያበረታ እንደሚችል Wolbers (2008) እና Williams (2011) ይመክራሉ፡፡

**ሸ. መከለስ**

በአርትኦቱ ወቅት ተገምግመው ችግር ያለባቸው ሀሳቦች የሚወገዱበት አልያም ማስተካከያ የሚደረግባቸው በዚህ ደረጃ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የሰዋስው አጠቃቀም ችግር ስለሚታይባቸውና የምልክት ቋንቋውም ይህንን በግልጽ ስለማያሳያቸው መምህራን አስፈላጊውን እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡ ሰዋስውን በማስተማርና በማረም ረገድም ከንጥል መዋቅራዊ ቅንጣቶች ይልቅ በጥቅል ቅርጽ ላይ ማተኮር እንደሚገባ Dostal and Wolbers (2014) እና Flo and Bill (2009) ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም የምልክት ቋንቋ ሀሳብን እንጂ የሰዋስው ህግጋትን ካለማሳየቱም በተጨማሪ አንዳንዴ እንደ እጆች እንቅስቃሴና አቀጣጫም ሁኔታ የተለዩ ትርጓሜ ሊያመጣ ስለሚችል ነው፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች አንቀጽን ሲጽፉ በሚመሠርቷቸው በርካታ አረፍተ ነገሮች ውስጥ በሚፈጥሯቸው የፆታ፣ ቁጥር ባለቤት ወዘተ. አመልካች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ላይ ብዙ እንዲጨነቁ ከማድረግ ስለ አጠቃላይ የአረፍተረፍተ ነገር ግንባታቸውና የሀሳብ አደረጃጀታቸው ማበረታቻ መስጠት ይገባል፡፡ ጥቃቅን የሆኑና ችላ የማይባሉ ሰዋስዋዊ ስህተቶች በሂደቱ ይቃናሉና ነው፡፡

ሌላው የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት ትምህርቱን ቀላልና ተጨባጭ ለማድረግ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑ በርካታ ልምምዶች አሉ፡፡ ልምምዱ ደግሞ ምናልባት ተማሪዎችን እንዳያሰለቻቸው ከትምህርት ቤት ውጭ እንደ የእለት ውሎ ማስታወሻ /diary/ የስልክ የጽሁፍ መልክት፣ የድህረ ገጽ ውይይቶች /Chat/ የጋዜጣ አምዶች ወዘተ. ባሉ ተጨማሪ አውዶች ውስጥ ራሳቸውን አስገብተው ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ መምህራን እድሉን ሊፈጥሩላቸው ይገባል፡፡ ይህ ዓይነቱ ተግባር ደግሞ በጽሁፍ ሂደት የሰዋስው ስህተትን በመቀነስ ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው kroll (1993) የገለጹትን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡

የተማሪዎችን ጽሁፍ መገምገምና ውጤት መስጠት የመምህራን የቀን ተቀን ሀላፊነት ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ አቅጣጫውን ይስትና ስነ-ትምህርታዊ ውድቀትን ያስከትላል፡፡ በተለይ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ችሎታ በመመዘን ሂደት መምህራን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ Elizabeth (2009) እንደሚሉትም በየክፍል ደረጃውና በየእድሜ እርከናቸው የሚጠበቅባቸው ችሎታ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በእኩል ተመዝኖ የሚቀመጥ ባይሆን ይመረጣል፡፡ ይህ ሲባል የተለዩ የመመዘኛ ዘዴ ይዘርጋላቸው ማለት ሳይሆን ያላቸውን የመማር ሁኔታ ታሳቢ ባደረጉ አማራጭ የመለከያ ስልቶች ውስጥ ይለፉ ለማለት ታስቦ ነው፡፡ የፅሁፍ ስራቸውን በማረም ሂደትም በጽሁፍ ከሚሰጥ ምግበ ምላሽ ባለፈ የአንድ ለአንድ ቃለ ምልልስና ውይይት ማካሄድ ትምህርቱን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ የመምህራን ግምገማም ትኩረት ማድረግ ያለበት በጥቅል መግባቢያዎች ላይ፣ሀሳባቸውን ለመደገፍ ባቀረቧቸው ማሳመኛዎችና በይዘት አደረጃጀታቸው ላይ ቢሆን ይደገፋል፡፡ Wolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014) እና Flo and Bill (2009) እንደሚሉት ተማሪዎች ወደ ፁሁፍ ሥራቸው ከመግባታቸው በፊትም የመገምገሚያ መስፈርት **/Rubrics/** ማዘጋጀትና የተዘጋጀውን መስፈርት ለተማሪዎች በግልፅ በማቅረብ በጽሁፍ ሥራቸው ወቅት መምህሩ ምን ምን ነገሮችን እንደሚመለከት? ቀድመው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ብዙ የተለመደ ባይሆንም ጠቃሚነቱ ግን በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ስለሚመዘኑበት መስፈርት ፣ርዕሰ ጉዳይ ጥልቅ መረጃ ቀድመው አውቁ ማለት ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ከማገዙም

በላይ እራሳቸውን ለትምህርቱ ብቁ እንዲያደርጉና ሀላፊነት እንዲወስዱ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል፡፡

በአጠቃላይ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ ትምህርቱ ሂደታዊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ባለሞያዎች እንደሚሉት መሰማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ትምህርትን ገና ሲጀምሩ ትግል የሚያደርጉት መፃፍ በመቻል አለመቻላቸው ላይ ሳይሆን እንዲሰሩ የታዘዙት የጽሁፍ ስራ ምን እንደሆነ መረዳቱ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው የሚከናወኑ ልምምዶች ሁኔታቸውን ባገናዘቡና ሂደቱን ሊያቀሉ በሚችሉ ማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች፣ ስልቶችና አጋዥ መሳሪያዎች ሊሞሉ ይገባል፡፡

በአንጻሩ ለየንዑስ ትምህርት ክፍሉ ተስማሚ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች ተግባራዊ በመሆንና ባለመሆናቸው ሳቢያ ስነ-ትምህርታዊ ውድቀት ሲከሰት ይስተዋላል፡፡ በዚህ ረገድ ለሚመጣው ውጤት ደግሞ ከፍተኛውን ድርሻ ከሚወስዱት መካከል መምህራን ተቀዳሚዎች ናቸው፡፡ በማስተማር ሂደት የሁሉም መምህራን አላማ መሆን ያለበት የመማር ማስተማሩን ሁኔታ ምቹ ማድረግ፣ የተማሪዎችን የተሰበጣጠረ ፍላጎት አጣጥሞና የእውቀት ክፍተታቸውን በተለያዩ መልኩ ሞልቶ ወደ ስኬት ማምጣት ነው፡፡ በተለይ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች መጻፍንም ሆነ ሌሎች የትምህርት ክፍሎችን በማስተማሩ ሂደት የመምህራን ብቃትና ዝግጁነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚገባ ጥናቶች ያሳያሉ (Adrienne Anne 2012)፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ትኩረት ካለመስጠት የተነሳ የተማሪዎችን የመማር ችግር የሚቀንስ በሙያው የሰለጠነ መምህር አለማፍራት፣ አበረታች የትምህርት አቅድን ነድፎ ምቹ የመማሪያ አውድን መፍጠር አለመቻልና ሌሎች በርካታ ችግሮች መኖራቸውን በሀገራችንም ሆነ በውጭው አለም ከሚታዩ ነባራዊ እውነታዎች መታዘብ ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል በ2012 በአሜሪካ ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በሚያስተምሩ 42 መምህራን ላይ የናሙና ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ በዚህም ከ42 መምህራን መካከል 26% የሚሆኑት በባህሪ አስተዳደር፣ 36% የሚሆኑት በተለያዩ የአካል ጉዳቶች ላይና 44% ያህሉ ደግሞ ከየትኛውም የአካል ጉደት ጋር ግንኙነት በሌለው ዘርፍ የተመረቁ መሆናቸውን Adrienne Anne (2012) ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ ጥናት መረዳት የሚቻለው የመስማት መሳን ላለባቸው ተማሪዎች የሚመደቡ መምህራን የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ያማከለ ስልጠና ያልወሰዱና በዚህም ምክንያት በተማሪዎች ላይ ለሚፈጠረው ስነ-ትምህርታዊ ውድቀት አሻራቸው ደምቆ የሚታይ መሆኑን ነው፡፡ አድገዋል

በተባሉ ሀገሮች እንኳን ለጉዳዩ እየተሰጠ ያለው ትኩረት ይህንን ያህል ዝቅተኛ ከሆነ በሀገራችን ያለውን እውነታ መገመቱ የሚያዳግት አይሆንም፡፡

በተመሳሳይ Christen et,al (2013) መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች በትምህርት፣ በቋንቋ፣ በማህበራዊና በሌሎች ስሜቶቻቸው ላይ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ ያላቸውን ጉዳዮች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

- **ተጣምሮ ያለመስራት፦** አብዛኛውን ጊዜ እንደሚስተዋለው የተማሪዎቹን ሁለንተናዊ ችግር ተገንዝቦ ክፍተታቸውን በመሙላት ለስኬት የሚያበቁ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ሆነ ማህበረሰቦች ሲተጉ አይታዩም፡፡ በተቃራኒው ጉዳቱ ከፈጣሪ እንደወረደ ቁጣ ተደርጎ ስለሚታሰብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ከመስራት ይልቅ ማራቅና ማግለል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይህ አመለካከት በቤተሰብ የሚገታ ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤት ባሉ ተማሪዎች፣ መምህራንና ሌሎች አካላት የሚንፀባረቅ ነው፡፡
- **የመርሃ ትምህርቱና የግምገማ ሂደቶች፦** እነዚህ ተማሪዎች ከሌሎች የተለየ የሚማሩበት የራሳቸው ስርዓተትምህርት ባይነደፍላቸውም በመርሃ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የመማር ሁኔታቸውን ያገናዘበ የትምህርት ይዘት፣ የማስተማሪያ ዘዴና ስልት፣ተስማሚ መመዘኛና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ያካተተ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በአንፃሩ ተማሪዎቹ ካላቸው የቁጥር ውስንነት ጋር ተያይዞ ለዝግጅቱ ትኩረት የማይሰጠው ከሆነ አሉታዊ ጫናው እየተባባሰ እንደሚሄድ አጥኝዎቹ ይገልፃሉ፡፡
- **የችግሩ ቅድመትና የተወሰዱ መፍትሄዎች፦** ልጆቹ ከተወለዱ ከ0-5 ዓመት ባለው ጊዜ ጉዳቱ ከታወቀ ቋንቋን ለማለማመድም ሆነ ሌሎች ድጋፎችን ለመስጠት ምቹ ይሆናል፡፡ ይህንን ማድረግ ከተቻለ ደግሞ በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ላይ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች መቀነስ ይችላል፡፡
- **የተሳሳቱ ግምቶች፦** ከፍሲል እንደተጠቆመው ወላጆች፣መምህራንና ማህበረሰቡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ዝቅ አድርገው ሲመለከቱ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ የልጆቹን ስነልቦናዊ ጫና ያባብሰዋል፡፡ ይህንን አስመልክቶ Neorgious (1999) እንደሚገልጹት የልጆችና የወላጆች የግንኙነት ሁኔታ በብዙ መልኩ በትምህርት አቀባበል ላይም ሆነ በአፍላ የእድሜ ዘመናቸው ሊገነቡት በሚችሉት በራስ የመተማመን ስሜታቸው ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ወላጆች በልጆቻቸው ጉዳይ ከቤት እስከ ትምህርት ቤት ባለው አውድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተጣምረው መስራት

ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአብነት ያህል የልጆቻቸውን ዕለታዊ ለውጥና መሻሻል መከታተል፣ በትምህርት ቤት እቅዶችና ልዩ ልዩ ተግባራት ላይ መሳተፍ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው ተግባቦት እንዲዳብር በራስ የመተማመን ስሜታቸውን መገንባትና የመግባቢያ መንገዶችን ማለማመድ (ማስተማር)፣ አስፈላጊ የትምህርት መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና ሌሎች በርካታ ድጋፎችን እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ Neorgious (1999) በገለጻቸው መስማት አለመቻል ለሌሎች ችግሮች ያጋልጣል እንጂ በራሱ ችግር እንዳይደለ ያስረዳሉ፡፡በመማር ማስተማሩ ሂደትም እነዚህ ተማሪዎች ለሚያስመዘግቡት ዝቅተኛ ውጤት ምክንያቱ መስማት ባለመቻላቸው በሚመጣ የብቃት ማነስ ሳይሆን ከፍላጎታቸው ጋር የሚጣጣም የትምህርት ስርዓት ሳይዘረጋላቸው ሲቀርና በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ውጭ በሚኖራቸው ማህበራዊ መስተጋብር ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያበረታቱ ሁኔታዎች ባለመኖራቸው የተነሳ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ ማህበራዊ መስተጋብር በተለይ ለተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ መዳበር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው Deginesh (2016) Almayehu (2003) Jonsun.et.al (1989)ን እና Strong (1995)ን ዋቢ አድርገው ይገልጻሉ፡፡ ይህም የቋንቋ ተግባቦት የሚበለጽገው በትምህርት ከሚገኝ ክህሎት ባለፈ ከአካባቢ ጋር በሚደረግ ማህበራዊ ተረክቦ በመሆኑ ነው፡፡

እንደ ምሁሩ ገለጻ የቤተሰብ ሁኔታም ከተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ አንጻር የሚኖረው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በምሳሌ ሲያብራሩም 90% የሚሆኑት መስማት የተሳናቸው ልጆች የሚወለዱት መስማት ከሚችሉ ወላጆች ነው፡፡መስማት ከማይችሉ ወላጆች የሚወለዱት ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለውን የተግባቦት ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ሚዛኑ ወደ አንዱ ያደላ ነው፡፡ ከማይሰሙት የሚወለዱት ልጆች በምልክት ቋንቋም ሆነ በፅሁፍ የመግባባት እድላቸው ሰፊ ሲሆን በአንፃሩ ተምረውም ሆነ ሳይማሩ ከሚሰሙት ወላጆች የሚወለዱት ግን የተግባቦት መጠናቸው የቀነሰ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍና ልጆቻቸውን ለመርዳት ደግሞ ወላጆች የምልክት ቋንቋን መማር፣ ከባለሞያዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ማገናኘትና ለማህበራዊ ተረክቦ እንዲጋለጡ ማበረታታት እንደሚጠበቅባቸው ያሳስባሉ፡፡

በሌላ በኩል Almayehu (2003) እንደሚያስረዱት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤትም ይሁን የሚያስተምሯቸው መምህራን ወይም የሚያማክሯቸው ባለሞያዎች ለተማሪዎች ስኬት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች ለመስማት የሚያግዛቸውን ቴክኖሎጂ ቀመስ መሳሪያዎችን፣ ምቹ የመማሪያ

ክፍሎችን ማዘጋጀትና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ስለልጆቹ ሁኔታ አውቆ እንዲረዳቸው ግንዛቤ መፍጠር፣ መርሃ ትምህርቱና የመማር ማስተማር ሂደቱ ከልጆች የመማር ሁኔታ ጋር መጣጣሙን መገምገም፣ የልጆችን አካላዊና ስነልቦናዊ ችግር ቀርቦ በመረዳት የመማር ተነሳሽነታቸውን ሊያበለፅጉ የሚችሉና ለውጤት የሚያበቁ መምህራንና አማካሪ ባለሞያዎችን መቅጠር እንዲሁም ሌሎች በርካታ ድጋፎችን እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

የመምህራን የማስተማር ስልትንም ብንመለከት መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ትምህርትን ይሁን ሌሎች የቋንቋውን ክሂሎች በማስተማር ረገድ ሊጠቀሙት የሚገባው መንገድ የመማር ሁኔታቸውን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የማስተማሪያ መንገዶች የትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ ዋነኛ መሳሪያዎች እንደ መሆናቸው መጠን ለእነዚህ ተማሪዎች የሚዘጋጅ አንድን ትምህርትም አቅም በፈቀደው መጠን ለተረድኦት በሚቀላቸውና ለፍላጎታቸው በቀረበ ሁኔታ በአማራጭ ስልቶች አለዝቦ ማቅረብ ያስፈልጋል (Almayehu 2003)፡፡

## 2.4. የመማር ፍላጎት ምንነትና መገለጫዎች

የፍላጎት ጽንሰ ሀሳብ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በስነ ልቦና ትምህርት ትኩረት ከተሰጣቸው ሀሳቦች አንዱ ነበር፡፡ የጽንሰ ሀሳቡን ምንነት በተመለከተም ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ Dewey (1913) በጥናታቸው ያሰፈሩትን ሀሳብ ዋቢ በማድረግ Folling እና Hartinger (1998) ፍላጎት አንድና ነጠላ የሆነ የስነ ልቦና ሀሳብ ብቻ ሳይሆን ሂደታዊ በሆነ መልኩ በግለሰቦች ዘንድ ያለን እምቅ ሀይል የመጠቀም ግፊት እንደሆነ የገለጹ ሲሆን Joseph (2010) ደግሞ የግንዛቤ እድገት እና የማህበረ ግንባታውያንን ንድፈ ሀሳብ መነሻ በማድረግ ፍላጎት ከግለሰባዊ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ቅድመ እውቀትና ከማህበረ ባህል ጋር ጥብቅ ተዛምዶ ያለው ዘውግ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Dewey (1913) የፍላጎትን ጽንሰ ሀሳባዊ ምንነት ከሰው ልጅ ስብዕና ግንባታ ጋር በማያያዝ እራስን የማወቂያ፣ የመገንቢያ፣ የማብቂያና ማህበራዊነትን መመስረቻ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ፍላጎት ከመገለጫ መንገዱ አንጻር ሲገለጽ ደግሞ ውስጣዊ (ነባራዊ) እና ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) ፍላጎት ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል Harp& Mayer (1997)፣ Frick (1992) ያስረዳሉ፡፡ ሁኔታዊ ፍላጎት በአካባቢያዊ አነሳሽ ምክንያት ማለትም ሳቢና ማራኪነት ሳቢያ ሊፈጠር የሚችል ሲሆን ነባራዊ ፍላጎት ደግሞ በነገሮች ላይ በሚኖር የረጅም ጊዜ ምልከታና ግንዛቤ የሚመጣ


አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ስሜት ነው፡፡ በተመሳሳይ ፍላጎትን ከአፈጣጠሩ አንጻር ተመልክተው Dewey (1913) ቀጥተኛና ኢ- ቀጥተኛ ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል የገለጹ ሲሆን ቀጥተኛ ፍላጎት በድርጊትና በውጤት መካከል ሊኖር በሚገባ ግንኙነት ውስጥ የማይከሰት ወይም በቅጽበታዊ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚታይ የአሁናዊ ስሜት እንደሆነና ኢ-ቀጥተኛ ፍላጎት ደግሞ በተቃራኒው በሂደትና በውጤት ላይ በመመስረት የሚመጣ ዝግመታዊ የመሻት መጠን መሆኑን ያብራራሉ፡፡የፍላጎት ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔን በማብራራት ረገድ ምሁራን የሚሰነዝሯቸው ሀሳቦች በአገላለጽ ይለያዩ እንጂ በሚመሰረቱባቸው ይዘቶች ላይ ግን የጎላ ልዩነት አይታይም፡፡ በመሆኑም ፍላጎት ከብዙ ምሁራን አተያይ አንጻር ጠቅለል ብሎ ሲገለጽ በውጫዊ ተነሳስቶ የሚፈጠር ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) ፍላጎት እና በአእምሮ ውስጥ ከሚኖር ግለሰባዊ ግንዛቤ አኳያ የሚፈጠር ውስጣዊ (ነባራዊ) ፍላጎት በመባል ይታወቃል፡፡ ፍላጎት ከማህበራዊነት፣ ከግለሰባዊነት፣ ከስነ ትምህርት ወዘተ. ጋር ባለው ጥብቅ ቁርኝት ይጠናል እንዲሁም ይተነተናል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ፍላጎት የተመረመረው ከተማሪዎችና ከማስተማሪያ ዘዴ አንጻር እንደመሆኑ መጠን ድርሳናትን በማጣቀስ ጥቂት ሀሳቦችን ለማነሳት ይሞከራል፡፡ Harp and Mayer (1997) እንደሚሉት ትምህርታዊ ፍላጎት ውስጣዊ (ነባራዊ) እና ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) ተብለው በተጠቀሱት ሁለት የፍላጎት ገጽታዎች ይገለጻል፡፡ ሁኔታዊ ፍላጎት ከትምህርት ተግባራት፣ ከማስተማሪያ ዘዴዎችና ግብዓቶች፣ ከትምህርት ቤት ሁኔታዎችና በአጠቃላይ ከአካባቢ ጋር በተገናኘ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት የሚኖራቸው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ስሜት ሲሆን ውስጣዊ (ነባራዊ) ፍላጎት ደግሞ ካለምንም ውጫዊ ግፊትና አነሳሽ ምክንያት ማለትም የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ ግብዓቶች ወዘተ. ተማሪዎች ወደፊት እንዲሆኑ ከሚያልሙት ነገርና ከማንነታቸው ጋር በተቆራኘ መልኩ ለነገሮች በሚሰጡት ዋጋ ወይም ግለሰባዊ አተያይ ላይ ተመስርቶ የሚንጸባረቅ ስሜት ነው (Harp and Mayer 1997)፡፡ ከዚህም በመነሳት ፍላጎት በሰዎች ግላዊ ማንነትና በአካባቢያቸው በሚያደርጉት መስተጋብር የሚፈጠር የመሻት ክስተትና መጠን ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.4.1 ፍላጎት በትምህርት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ስነ ትምህርታዊ ፍላጎት ምንጩ ምንም ይሁን ምን በተማሪዎች ውጤት ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ አለ፡፡ ለምሳሌ Sauer (2012) Barbara and Judith (2002)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በሚወዱት የማስተማሪያ ዘዴ ማስተማርና በተግባራትም ላይ የሚመርጧቸውን ግብዓቶች

ማለትም መጻህፍትን፣ማስተማሪያ ቁሶችን ወዘተ. በማቅረብ ማለማመድ የመማር ፍላጎታቸውን ከፍ ከማድረጉ ጎን ለጎን በውጤታቸው እንዲልቁም ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ እንደምሁሩ ምልከታ በአብዛኛው በመምህራን የበላይነትና ብቸኛ ተግባሪነት ከሚመራ የመማር ማስተማር ሂደት ይልቅ በተማሪዎች የእርስ በእርስ መስተጋብር የዳበረ አቀራረብ በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ውጤታቸው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ በእርግጥ የጋራ መስተጋብር ሲባል በተማሪዎች መካከል ያለውን ብቻ ማለት አይደለም በአንጻሩ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለ ስነ ትምህርታዊ ቅርርብም በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ውጤት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር Hidi and Berndorff (1998) የተለያዩ ጥናቶችን በመጠቀም ያብራራሉ፡፡በጥቅሉ በማስተማሪያ ዘዴ፣ በመማር ፍላጎትና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን የእርስ በእርስ ተጽዕኖ ከሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ምስል አንድ፡- የመማር ፍላጎት፣ ማስተማሪያ ዘዴና ውጤት ያላቸው ግንኙነት




Andreas (1999)፡፡

ከስዕላዊ መግለጫው መመልከት የሚቻለው የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ፣ በመማር ፍላጎት፣ የመማር ፍላጎት እንደዚሁ በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ መደራረሳቸውን ነው፡፡ ሌላው የመማር ፍላጎት ከትምህርት አቀራረብና ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል በሀሳብ ደረጃ መግለጽ ብዙም ከባድ አይሆንም፡፡ ነገር ግን በምርምር ስራ ውስጥ እንደ አንድ ተላውጦ ሲጠናና ወደልኬታው ሲመጣ ግን ከጉዳዩ ኢ-ተጨባጭነት አኳያ ሂደቱ ቀላል እንዳልሆነ Harp and Mayer (1997) ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ጽንሰ ሀሳቡን ሊገልጹ የሚችሉ ስሜት ተሸካሚ ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን በመጠይቆች ውስጥ ተጠንቅቆ መቅረጽ

ከተመራማሪው የሚጠበቅ ትልቅ ተግባር ነው፡፡ በሌላ በኩል Hidi and Berndorff (1998) እንደሚሉት የመማር ፍላጎትን በመለካት ረገድ መገለጫ መንገዶቹ ላይ ማተኮር እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ የተማሪዎች የትኩረት መጠን፣ለትምህርቱ ያላቸው የመሳብ ልቀት፣ የሚያሳዩት የደስታ ስሜት፣ በትምህርቱ ሂደት የሚኖራቸው ተነሳሽነትና ተሳትፎ በዋናነት መለኪያውን ለማዘጋጀት መነሻ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍም በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ ሲዘጋጅ ከላይ በተዘረዘሩት መነሻ ሀሳቦች ላይ ትኩረቱን አድረጓል፡፡

## 2.5. የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ


የዚህ ጥናት አብይ ጉዳይ የሆነው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከየትኛው የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ ይነሳል? ወይም የትኛውን ይከተላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በተተኳሪው የማስተማሪያ ዘዴው ዙሪያ የተጻፉ ጽሁፎችንና የተካሄዱ ጥናቶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በዚህም ዘዴው የሚከተለው የቋንቋ ንድፈ ሀሳብ የማህበረ ባህላዊ (የግንባታውያን) የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ የማስተማር ትውረት ቋንቋ በሰው ልጆች ያላሰለሰ ማህበዊና ባህላዊ ግንኙነት ወይም ተጋልጦ የሚዳብር መሆኑን የሚያምን ነው፡፡ ማህበራዊ ግንኙነትም በትምህርት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እንዳለው ንድፈ ሀሳቡ ያመለክታል፡፡ የዚህ ሀሳብ ዋና አቀንቃኝ የሆኑት Vygotsky’s, Bruner እና Rogoffን ዋቢ በማድረግ Habibullah, Rafique, Shumaila, Ali& Illahi (2018) እንደሚሉት ልጆች ቋንቋን መማር የሚችሉት ተፈጥሮ በለገሰቻቸው አቅም ብቻ ሳይሆን ወላጆች፣ ማህበረሰቦችና መምህራን በሚያደርጉላቸው እገዛ ነው፡፡ ወይም መማር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ በሚኖር መስተጋብራዊ ግብአት አማካይነት የሚገነባ ሂደት ነው፡፡ እነዚህ ምሁራን የልጆችን የቋንቋ ለመዳ ብቻቸውን የሚያውቁት፣ በሌሎች እርዳታ የሚያውቁትና ጭራሹንም ባሉበት የዕድሜ ክልል የማያውቁት በማለት በሶስት ዞኖች (Zone of Proxima Development) ይገልጹታል:: የቤተሰብ፣ የማህበረሰቦችና የመምህራን ድርሻም በእነዚህ በተጠቀሱት ዞኖች መካከል ጣልቃ እየገቡ ክፍተታቸውን መሙላት ነው:: በማህበረ ባህላዊ (ግንባታውያን) ንድፈ ሀሳብ አተያይ ተፈጥሯዊው የሰው ልጅ የመማር ልምድ የሚያድገው በማህበራዊነት ነው፡፡ ወይም የህፃናት ቀጣይ ብቃታቸው የሚዳብረው በአካባቢያቸው ከሚያገኙት ግብአት ሲሆን ውጫዊው አለም ደግሞ ለአእምሯዊ እድገታቸው እንደሞዴል ነው፡፡ በግንባታውያን አቀንቃኞች ዘንድ መማር የሚጎለብተው ውስጣዊ ፍላጎትን የሚያሳድጉ ሁነቶች ሲኖሩና በተለይ ደግሞ ተማሪዎች

**በአካባቢያቸው ከሚገኙ የማህበረሰብ አባላትና ጓደኞቻቸው ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር እንደሆነ ይታመናል** Habibullah.et.al. (2018)።

**በአንጻሩም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴም እውቀት ከመምህራን ወደተማሪዎች በቀላሉ የሚተላለፍ ሳይሆን ተማሪዎች አእምሯቸውን በመጠቀም በአካባቢያቸው ከሚያገኟቸው ሰዎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር የሚያዳብሩት እንደሆነ የሚያምን መሆኑ የማህበረ ባህላዊ (ግንባታውያን) ንድፈ ሀሳብ መርህ ተጋርቶ ያለው ነው፡፡**

## 2.6. የጥናቱ ግንዛቤያዊ ማሕቀፍ

**ምስል ሁለት፡- የጥናቱ አተገባበር ንድፍ**




McLaughlin,B.(1991፡165) *በቋንቋ ንድፈ ሀሳቦች ክለሳቸው ውስጥ ባቀረቡት ጽሁፍ መነሻነት ከጥናቱ ትኩረትና አላማ አንጻር ተቀናጅቶ የተዘጋጀ፡፡*

**በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚመራ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ዘዴው በሚከተላቸው አላባዎች ላይ ተመስርቶ የቀረበ ሲሆን እንደሆነ በመስኩ ላይ**

የተደረጉ ጥናቶች ይገልፃሉ (Mc.Carrier and Pinnell 1994፣ Hussni 2014)፡፡ ከላይ ምስላዊ በሆነ መልኩ የቀረበው ገለጻ የሚያመለክተውም McLaughlin (1991፡165) የተለያዩ የመማር ትውረቶችን መነሻ በማድረግ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ የተሻለና ብቸኛ የሚባል የማስተማሪያ ዘዴ ባለመኖሩ ዘዴዎችን በተናጠል ከመተግበር ይልቅ አቀናጅቶ መጠቀም ውጤታማ እንደሚያደርግ በገለጹበት ወቅት በአስረጅነት ካቀረቡት ሞዴል ጋር በከፊል የተዛመደ ጥናቱ ሂደታዊ ንድፍ ነው፡፡ በዚህ ሞዴል መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ሆኖ ሲቀርብ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ዘርዘር ባለ ሁኔታ መግለጽ አመቺ ባይሆንም ጠቅለል ባለ መልኩ ግን በጥናቱ ሂደት የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበሩ ከመነሻው እስከ ፍጻሜው ድረስ  ምን አይነት ገጽታ እንዳለው ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

በመሆኑም ጥናቱ በአንድ ነጠላ ቡድን ላይ የተካሄደ በመሆኑ ተሳታፊ ተማሪዎች ያለ ተነጻጻሪ ቡድን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ እንደሚታወቀው መስተጋብራዊ ዘዴ የውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ቅንጅት እንደመሆኑ መጠን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ትግበራው ያተኮረው በሁለቱ አቀራረቦች መርሆ ላይ ነው፡፡ በቀስቶቹ ለማመላከት እንደተሞከረው የጽህፈት ልምምዱ የሚጀምረው ለአዲሱ ትምህርት መነሻና ማጠናከሪያ ከሚሆን ግብዓት (ሞዴል ጽሁፍ) ሲሆን በዚህም የተማሪዎች የሰዋስው ስርዓት አጠቃቀምንና የአጻጻፍ ብልሃቶች (ቴክኒክ) መሻሻሎች ተጠባቂ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መግለጽ፣ መተርጎም፣ መከለስ፣ አርትኦት ማድረግና ማሳተም የተባሉ የጽህፈት ደረጃዎችን ተከትሎ በመተግበር ተማሪዎች በእያንዳንዱ ደረጃ የነበራቸው ንቁ ተሳትፎና ያሳዩት መሻሻል በየጊዜው ተመዝኖ ተሰንዷል፡፡ በመጨረሻም የጥናቱ ዋነኛ አላማ  መስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ በተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ መፈተሽ በመሆኑ በምስሉ ላይ በጥገኛ ተለዋዋጭነት በተዘረዘሩት የመጻፍ ክሂል ችሎታዎች ዓረፍተ ነገር መጻፍ፣ እንደገና ማቀናበር፣ ጅምር ሀሳቦችን ማጠናቀቅ፣ የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም፣ ድርሰት መጻፍ እንደዚሁም በውስጣዊ (ነባራዊ)  እና ሁኔታዊ (አካባቢያዊ) የመማር ፍላጎት ላይ ምን ያህል ለውጥ እንዳመጣ ተመርምሯል፡፡

## 2.7. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

ይህ ጥናት መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት በማሻሻል ረገድ የሚኖረውን ተጽዕኖ መመርመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምርምሮችን ለማግኘት ብዙ ተሞክሯል፡፡ ይሁንና ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ በትምህርት ክፍሉ "በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብራዊ ስልት (Intractive Approach) ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት" በሚል ርዕስ በግርማ (1990) የተሰራ አንድ ጥናት ቢገኝም በተተኳሪ ተማሪዎች ማንነት፣ በአጠናን ሂደት፣ በተለዋዋጮች ወሰንና ባልተጠቀሱ ሌሎች ንዑሳን ጉዳዮች ከዚህ ጥናት ጋር የተለየ ያደርገዋል፡፡ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ያለው ዝምድና በአንድ አይነት ቋንቋና የማስተማሪያ ዘዴ (መስተጋብራዊ ዘዴ) ውጤታማነት ፍተሻ ላይ ማተኮራቸው ብቻ ነው፡፡ በሌላ መልኩ በሰነባህርይ ትምህርት ክፍል መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመማር ሁኔታ በተለያዩ ደረጃዎች የዳሰሱ ጥናቶች የተገኙ ቢሆንም ይዘውት በተነሱት አላማ፣ በሚያሳኩት ግብና በቀረቡበት ቋንቋ ከዚህ ጥናት ጋር ፍጹም የተለዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከእንግሊዝኛ የቃላት ትምህርት ጋር በማያያዝ Girma (2008)፣ ከቅድመ ቋንቋ የተግባቦት ልምድ አኳያ Alemayehu (2003) ከምልክት ቋንቋና ንባብ ጋር በተገናኘ Tesfaye (2014)፣ እንዲሁም ከአካቶ የመማሪያ ክፍል የትምህርት አቀራረብ ውጤታማነት አንጻር Deginesh (2016) የሰሯቸው ጥናቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ምርምሮች ከዚህ ጥናት ጋር የሚለያቸው በርካታ ምክንያቶች ያሏቸው ቢሆንም የጥናቱን ሀሳብ በማበልጸግ ረገድ በመረጃ ምንጭነት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ግን ከፍተኛ ነው፡፡

ከውጪ የተገኙትን ስንመለከት ደግሞ የWolbers (2008) Dostal and Wolbers (2014) Elizabeth (2009)፣ Wolbers et,al (2016)፣ Wolbers et,al (2012) እና Flo and Bill (2009) ጥናቶች መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን ከመጻፍ ክሂል ትምህርትና መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመማር ሁኔታ አኳያ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሰረትነት በመመርመር ውጤታማነቱን ያረጋገጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ምንም እንኳን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ ተመስርተው ቢጠኑም መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው፣ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በተፈታሽ የማስተማሪያ ዘዴነት መምረጣቸው እንዲሁም በጥናቱ ሂደት በተገበሯቸው የማስተማሪያ ዘዴው መርሆዎች በአብዛኛው ከዚህ ጥናት ጋር

ያመሳስላቸዋል፡፡ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም ጥናቶች መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን ፋይዳ መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል አኳያ ሲመረምሩ በተጨማሪነት የፈተሹት ሌላ ተለዋዋጭ አለመኖሩ ከዚህ ጥናት ጋር የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ጥናት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቻ ሳይሆን የመማር ፍላጎታቸውንም በሁለተኛ ተለዋዋጭነት መፈተሽ ችሏል ፡፡ በአጠቃላይ በውጪ ቋንቋ በተካሄዱት ጥናቶችና በዚህ ጥናት መካከል ከፊል ልዩነቶች ቢኖሩም በአብዛኛው ግን ዝምድና ያላቸው በመሆኑ ለጥናቱ በሚጠቅም መልኩ በስፋት ተዳሰው ተግባር ላይ እንደዋሉ ከጽሁፉ ብዙ ክፍሎች መረዳት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መፈተሽ ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካትም በመረጃ አሰባሰብና አተናተን ሂደት መጠናዊ (Quantitative) የምርምር ዓይነትንና የአንድ ሙከራ ቡድን (ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና) ንድፍን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህ የምርምር ንድፍ ከአንድ የጥናት ቡድን ላይ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካኝነት መረጃን ሁለት ጊዜ በመሰብሰብ ንጽጽራዊ የውጤት ትንተና ለማካሄድ የሚያስችል ሲሆን አስፈላጊነቱም የጥናት ናሙናን በመምረጥ ሂደት በተለያዩ ምክንያቶች የተጠኚዎች ቁጥር ለሁለት ቡድን ማለትም ለጥብቅ (Control) ለሙከራ (Exprmental) ሳይበቃ ሲቀር የሚመረጥ እንደሆነ Marsden and Torgerson (2012፣587)፣ Robin (2009፣14)፣ Rick (2006፣ 152)፣ Graziano and Raulin (1998)፣ Campbell and Cook (2006)፣ Smith Robson (2010) ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም በአንድ ነጠላ ቡድን የተመደቡት ተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሳይማሩ አስቀድመው በተፈተኑት ቅድመ ፈተናና በሞሉት የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሁም በዘዴው ከተማሩ በኋላ በድጋሚ በወሰዱት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ያስመዘገቡት ውጤት በምን ያህል ደረጃ ልዩነት እንለ እንዳሳየ ተመርምሯል፡፡

## 3.2. የጥናቱ ዘዴ

### 3.2.1. የንሞና ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባር ላይ የዋሉት የናሙና ዓይነቶች ዓላማ ተኮር ናሙና (purposive Sampling) እና ጠቅላይ ናሙና (Comprehensive Sampling) ሲሆኑ ዘዴዎቹ እንዴትና ለምን ተግባር እንደተመረጡም ቀጥሎ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

### 3.2.1.1. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄድበትን ትምህርት ቤት ለመምረጥ አላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በዚህም በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ከሚያሰተምሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አልፋ፣ ቪክትሪ፣ መካኒሳ፣ ዳግማዊ ምኒልክና የካቲት አስራ ሁለት መካከል አልፋ መስማት የተሳናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት ተመርጧል።

ትምህርት ቤቱን ለመምረጥ ምክንያት ከሆኑት የመጀመሪያው የጥናቱን አካላይ ሊወክሉ የሚችሉ የናሙና አባላትን በተሻለ ቁጥር አግኝቶ ተፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ማስቻሉ ነው። ምክንያቱም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በልዩ የመማሪያ ክፍል ተቀብለው ከሚያስተምሩ የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤቶች ማለትም ቪክትሪ፣ መካኒሳ፣ የካቲት አስራ ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተለይ ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ ማግኘት የተቻለው የተማሪ ቁጥር ከአራት ያልበለጠ ነበር። በአንጻሩ በአልፋ መስማት ተሳናቸው ትምህርት ቤት ሰባት ተማሪዎች የተገኙ መሆኑ ትምህርት ቤቱን እንዲመረጥ አድርጎታል።

ሁለተኛው ደግሞ ተፈታሹን የማስተማሪያ ዘዴ በጥናቱ ላይ በተገቢው መንገድ መተግበር ይቻል ዘንድ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ፣ በምልክት ቋንቋ ጥሩ ክህሎት ያለውና መስማት የሚችል መምህር በማሟላት ረገድ ትምህርት ቤቱ ከሌሎች በተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ከላይ በተጠቀሱት አብዛኞቹ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን መስማት ተሳናቸው እና በቋንቋው ያልተመረቁ እንደነበሩ በተመራማሪዋ የዳሰሳ ጥናት መመልከት ተችሏል። በአንጻሩ ይህም ጥናት ፍትነታዊ እንደመሆኑ መጠን የማስተማሪያ ዘዴውን ለመተግበር በረዳት አጥኚነት በሚመረጡ መምህራን ብቃት ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል። በመሆኑም በትምህርት ቤቶቹ ላይ ከተደረገው የግምገማ ውጤት በመነሳት ከሌሎች ይልቅ አልፋ መስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት በብዙ መልኩ ለጥናቱ ምቹ ሆኖ በመገኘቱ እንዲመረጥ አስችሎታል። ሶስተኛው ምክንያት ጥናቱ የሚመለከተው በልዩ የመማሪያ ክፍል (Exclusive class) የሚማሩ ተማሪዎችን እንደመሆኑ መጠን ለትምህርቱ መቀልጠፍ የሚረዱ የማስተማሪያ ቁሶችን፣ ምቹ የመማሪያ ክፍል አውዶችንና አደረጃጀቶችን በከፊል ከማግኘት አኳያም አልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤት ተመራጭ በመሆኑ ነው።

### 3.2.1.2. የክፍል ደረጃና የተጠኚ ተማሪዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ማከናወኛ በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ የተመረጠው የክፍል ደረጃ ሰባተኛ ክፍል ሲሆን የተመረጠበት አንደኛው ምክንያትም በጥናቱ ሂደት ለተተገበሩት የጽህፈት ተግባራት ከቋንቋ ችሎታ፣ ከመረዳት አቅምና ከእድሜ ወዘተ. አኳያ ብቁ ይሆናሉ የሚል ግንዛቤ በመያዙ ነው። በእርግጥ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በየትኛውም የክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎችን ለማስተማር ምቹ መሆኑን በዘርፉ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን Wolbers (2008) Dostal and Wolbers (2014) Elizabeth (2009) Wolbers et,al (2016) ተናግረው እንደነበር ቀደም ባሉት ክፍሎች ተገልጿል። ይሁንና  ለጥናቱ ከተመደበለት ጊዜ አኳያ የማስተማሪያ ዘዴውን በመተግበር ረገድ ለሚቀርቡ የጽህፈት ተግባራት መቀልጠፍ በዚህ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች የተሻሉ ናቸው ተብሎ ታምኖበታል።

ሰባተኛ ክፍል የተመረጠበት ሌላኛው ምክንያት ደግሞ የክፍል ደረጃው ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር እንደ አማካይ መቆጠሩ ነው። እንደሚታወቀው ሰባተኛ ክፍል በስምንኛና በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች መካከል የሚገኝ ነው። የስምንተኛ ክፍል ደግሞ የክልላዊ ፈተና የሚሰጥበት በመሆኑ ተፈታኝ ተማሪዎች በጥናቱ ቢሳተፉ ለፈተናው ከሚያደርጉት ዝግጅት ጋር ጫና ፈጥሮ የጥናቱን ውጤት ሊያዛባው ይችላል የሚል ስጋት መኖሩ የክፍል ደረጃው እንዳይመረጥ አድርጎታል። ሶስተኛው ምክንያት በከተማ አስተዳደሩ ስር ካሉት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ከመዋለ ህጻናት እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያስተምር አልፋ መስማት ተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤት ነው። ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ የተገደቡ ናቸው። በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ወደ ሰባተኛ ክፍል በሚዘዋወሩበት ወቅት ሄደው የሚማሩት ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት በመሆኑ በተሻለ ቁጥር ተጠኚዎችን ለማግኘት ያስችላል በሚል የክፍል ደረጃው እንዲመረጥ አድርጎታል።

በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ የተማሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ ጠቅላይ የናሙና ዘዴ (Comprehensive Sampling) ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን የምርምሩን አይነት፣ የጥናቱን አካላዮች ብዛት፣ በየደረጃው ያሉትን መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የቁጥር ውስንነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚማሩትን ሰባት ተማሪዎች ወይም ሁሉንም በማሳተፍ ጥናቱ ተካሄዷል። ይህ ሲባል ግን በክፍል ደረጃው የተገኙት ተማሪዎች በሙሉ በጅምላ ተመርጠዋል ማለት አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ

ከመደረጋቸው በፊት ከዳራዊ ማንነታቸው ጋር በተገናኘ ሁኔታ ምናልባት የጥናቱን ውጤት ሊያዛቡ ይችላሉ ተብለው በሚታሰቡ ጉዳዮች ላይ የቅድመ ማጣራት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የተማሪዎች የመስማት መጠን (ከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የማይሰሙ)፣ ተደራራቢ ጉዳቶች (መስማት መሳንና የአእምሮ እድገት ውስንነት)፣ የመስማት መሳን መከሰቻ እድሜ (ቅድመ ወይም ድህረ ልደት) የመሳሰሉት ልዩነቶች በተመራማሪዋና በትምህርት ቤቱ አስተዳደር በኩል ተፈትሸዋል፡፡ ይሁንና ተጠኚዎች በብዙ መልኩ ተቀራራቢ ማንነት ያላቸው ሆነው በመገኘታቸውና ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ከተዘረዘሩት ውጪ ሌሎች የጤና እክሎች የሌሉባቸው መሆኑ ተረጋግጦ በክፍል ደረጃው የሚማሩት ሁሉም ተማሪዎች በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ይህንንም ቀጥሎ ከቀረበው ማስረጃ መመልከት ይቻላል፡፡

- **የጥናቱ ተሳታፊዎች ዳራዊ ማንነት**

| ተጠኚዎች | ዕድሜ | ጾታ | የመስማት መጠን (Degree of Hearing impairment) |
|---|---|---|---|
| 1 | 14 | ወ | ሙሉ በሙሉ መስማት መሳን |
| 2 | 17 | ሴ | ሙሉ በሙሉ መስማት መሳን |
| 3 | 15 | ወ | ሙሉ በሙሉ መስማት መሳን |
| 4 | 15 | ሴ | ሙሉ በሙሉ መስማት መሳን |
| 5 | 16 | ሴ | ሙሉ በሙሉ መስማት መሳን |
| 6 | 18 | ወ | ሙሉ በሙሉ መስማት መሳን |
| 7 | 17 | ወ | ከፊል መስማት መሳን |

በሰንጠረዡ ላይ ከቀረበው መግለጫ መረዳት እንደሚቻለው የሁሉም ተማሪዎች የመስማት መጠን በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኝ ነው፡፡ ይሁንና በከፊል ይሰማል በተባለው አንዱ ተጠኚ ላይ የነበረውን ጥርጣሬ ለማስወገድ የመስማት መጠኑን ለማረጋገጥ የድምጽ መለያ ምርመራዎች የተደርጉ ሲሆን ከሌሎቹ ተጠኚዎች የጎላ ልዩነት ባለማሳየቱ ምክንያት በጥናቱ ላይ እንዲሳተፍ ተደርጓል፡፡

### 3.2.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የምርምሩን አላማዎች ለማሳካት ተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተና፣ የጽሁፍ መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት ሲሆኑ በጥናቱም ሂደት እንዴት እንደተተገበሩ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

### 3.2.2.1. ፈተና

ፈተና ተማሪዎች አንድን ትምህርት ከመማራቸው በፊትም ይሁን ከተማሩ በኋላ በተናጠል አልያም በቡድን ያሳዩትን ብቃት ለመለካት የሚያገለግል እንደሆነ ያለው (2001፡189-190) ካስፈሩት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናትም አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ የዋለው ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ሲሆን የቅድመ ትምህርት ፈተናው ዋነኛ ዓላማ ተማሪዎች በተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት ያላቸው የመጻፍ ችሎታ በምን ያህል ደረጃ ላይ እንዳለ ለማረጋገጥ የቀረበና በአንጻሩ የድህረ ትምህርት ፈተናው ዓላማም ከልምምዱ በኋላ ተጠኚዎች በመጻፍ ክሂል ችሎታቸው ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቸውን ለመለየት ያገለገለ ነው፡፡

- **የፈተናው አዘገጃጀትና አተገባበር**

ፈተናው በተቻለ መጠን ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በቀረቡት የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና ተጠኚ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲቀርብ አጥኚዋ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች፡፡ በዚህም በተለይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በቀረቡ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ላይ በተወሰነ መልኩ የማሻሻያ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለአብነት ብናነሳ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት የመጻፍ ትምህርት ይዘቶች መካከል በተደጋጋሚ ትኩረት ከተሰጠባቸው ዋነኛው ድርሰት የመጻፍ ተግባራት ናቸው፡፡ እነዚህ የጽህፈት ተግባራት ሰፊ ሽፋን ተሰቷቸው ለልምምድ መቅረባቸው እንዲመጣ ከሚፈለገው የተማሪዎች የውጤት መሻሻል አኳያ አዎንታዊ ፋይዳ እንዳለው ቢታመንም እንደዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች የመማር ሁኔታና የቋንቋ ችሎታ ውስንነት ሲታይ ግን የትምህርት ሂደቱን ከባድና ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የጥናቱን ርዕስ በመወሰን ሂደት አጥኚዋ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች ተዘዋውራ ተማሪዎችን ለረጅም ጊዜ ካስተማሩ መምህራን ጋር ካደረገችው ውይይትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተመለከተችው እውነታ መረዳት እንደተቻለው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ችግር የሚጀምረው ፊደላትን ከመለየት ወይም ሆሄያትን በትክክለኛው ቅርጻቸው ከመጻፍ፣ ቃላትን ከመመስረትና አረፍተ ነገሮችን ከማዋቀር ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጡት የመጻፍ ክሂል ተግባራት የተደራጁት ይህንን የተማሪዎች ክፍተት ለመሙላት በሚያስችሉ መልኩ ሆሄያትን ከመልመድ አንስቶ ድርሰት እስከመጻፍ ወይም ከቀላል ወደ ከባድ በሚወስዱ ተግባራት ነው፡፡ በቅድመና ድህረ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች መሰረት ያደረጉትም

በማስተማሪያነት የቀረቡትን ይዘቶችና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለልምምድ ሲቀርቡ የነበሩ የመጻፍ ተግባራትን ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በተለይ በዚህ ጥናት እየተፈተሸ ባለው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የጽህፈት ትምህርቱ ሲቀርብ ተማሪዎችን በማለማመድ ረገድ ተግባራት ተከፋፍለው ከሚቀርቡባቸው የመጻፍ ስልቶች በውስን ጽህፈት፣ በመር ጽህፈትና በነጻ ጽህፈት የተቃኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም በተሰጡ ቃላት ሰዋስዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁና ፍቺ የሚሰጡ አረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ማድረግ፣ የተዘበራረቁ የአረፍተ ነገር ቅንብሮችን እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ማድረግ፣ ጅምር አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላትና ስርዓተ ነጥቦች በማሟላት አንቀጽ እንዲያጠናቅቁ ማድረግና በተመረጡ ርዕሶች አማካኝነት ድርሰት መጻፍ በፈተናው ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት ናቸው (አባሪ “ሀ” ን ይመልከቱ)፡፡

የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ በዚህ መልኩ ከተዘጋጁና ትክክለኛነታቸው ከተፈተሸ በኋላ ለናሙና ጥናቱ ተሳታፊዎች በቀጥታ ከመቅረባቸው በፊት ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና የሙከራ ጥናቱን ከምትተገበረው መምህርት ጋር ስምምነት መፈጸም ስለሚያስፈልግ የጋራ ውይይት ተደረጓል፡፡ መምህርቷም ለስራው ከመቅረቧ አስቀድሞ በማስተማሪያ ዘዴው ምንነት፣ በአተገባበር መርሆውና አጠቃላይ ባህሪው ላይ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራት ለሰባት ተከታታይ ቀናት በአጥኚዋ ስልጠና እንዲሰጣት ተደርጓል (አባሪ “ቀ” ን ይመልከቱ)፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ስራ የሆነው በናሙና ጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ማዘጋጀት ነበር፡፡ በአጠቃላይ ለጥናቱ ውጤት ታዓማኒነት እንቅፋት የሚሆኑ ልዩነቶች አለመኖራቸው ከተረጋገጠ በኋላ ፈተናዎቹን በሁለት የተለያዩ ጊዜያት እንዲፈተኗቸው ተደርጓል፡፡ ማለትም የመጻፍ ትምህርት ልምምዱ ከመከናወኑ ከሁለት ቀን በፊት ቅድመ ፈተናው እንዲሁም ትምህርቱ ሊጠናቀቅ ሶስት ቀናት ሲቀሩት ደግሞ ድህረ ፈተናው ቀርቦ ትግበራው ተጠናቋል፡፡ በፈተናው ወቅትም በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚማሩት ሁሉም ተማሪዎች (7ቱም) የተሳተፉ ሲሆን ተፈታኝ ተማሪዎችም ለፈተናው መተግበሪያ በተሰጣቸው ሁለት ሰዓት ውስጥ ስራቸውን አጠናቀው ወረቀታቸውን መልሰዋል፡፡ የቅድመውንም ሆነ ድህረ ፈተናዎቹን በመፈተን ረገድ የተሳተፉት መምህራን ሁለት ሲሆኑ እነዚህም በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ላይ አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩና የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ፈተናውን በሁለት መምህራን ማስፈተን ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት አንደኛው መምህር የምልክት ቋንቋ ክህሎት ችግር ያለበት በመሆኑ እንደ ረዳት ፈታኝ ሆኖ እንዲያገለግል በማሰብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ ፈተናውን እንዴት

መፈተን እንዳለባቸው ከአጥኚዋ ጋር ተወያይተው ግንዛቤ ያገኙና ሙያዊ ሀላፊነትም በፍቃዳቸው የተቀበሉ ጭምር ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉት የሁለቱ ፈተናዎች አተገባበር በቅደም ተከተል ጠቅለል ብሎ ሲገለጽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- በመጀመሪያ የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት ቅድመ ትምህርት ፈተና (T1) ለተጠኚ ተማሪዎች ተሰጣቸው፡፡ በHeaton (1988) እና በJacobs et.al (1981) የአስተራረም ስልትመሰረት ታርሞ ውጤቱም በሂሳባዊ ቀመር አማካዩና ልዩነቱ ተሰልቶ ተቀመጠ፡፡
- ቀጥሎ ተጠኚ ተማሪዎች ለሁለት ወር ( ስምንት ሳምንታት ያህል በአዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ (በመስተጋብራዊ ዘዴ) እንዲማሩና እንዲለማመዱ ተደረገ፡፡
- ተጠኚ ተማሪዎች በተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩና ከተለማመዱ በኋላ በመጨረሻው ሳምንት በቅድመ ትምህርቱ ወቅት የተፈተኑትን ፈተና በተመሳሳይ አቀራረብ ደግመው (T2) እንዲፈተኑ ተሰጣቸው፡፡ ውጤታቸውም በሂሳባዊ ቀመር አማካዩና ልዩነቱ ተሰልቶ ተቀመጠ፡፡
- በመጨረሻም የተጠኚ ተማሪዎቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ጋር በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የተነፃጸረ ሲሆን ንጽጽሩም ተማሪዎች ከራሳቸው ጋር ወይም በቅድመና በድህረ ፈተና ውጤታቸው መካከል ባሳዩት ልዩነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በዚህ መልኩ በተገኘው ውጤት መሰረትነት ተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ተረጋግጧል፡፡

- **የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ማረሚያ ሞዴል**

ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ወቅቶች የተፈተኗቸው ፈተናዎች በክፍል ደረጃው በሚያስተምሩና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በተሰጣቸው ሶስት መምህራን እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡ ለፈተናዎቹ እርማት መስፈርት ሆነው ያገለገሉትም የመፃፍ ክሂል ትምህርትን በመገምገም ረገድ በምሁራን ዘንድ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ከሚባሉት አላባዎች ውስጥ ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቋንቋ፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የአፃፃፍ ስርዓት አገባብና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ናቸው (Heaton 1988፣146፣ Jacobs et.al 1981)፡፡ የምሁራኑን

ሀሳብ መነሻ በማድረግ ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርቦ የነበረው ፈተና ከመቶ የታረመ ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩ አላባዎች በሚይዙት ነጠላ ውጤት ላይም ተመስርቶ ውጤቱ እንዲሰላ ተደርጓል (አባሪ “ሰ” ን ይመልከቱ)፡፡ በተጨማሪም Elizabeth (2009) ባካሄዱት ጥናት በተከተሉት የChrstopher Gordon (2001) የመገምገሚያ ሞዴል መሰረትም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የጽሁፍ ችሎታ በመመዘን ሂደት ግምት ውስጥ እንዲገቡ ከሚፈለጉ መርሆች መካከል ተማሪዎቹ የሚገኙበት የዕድሜ ክልልና የሚማሩበት የክፍል ደረጃ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ሞዴሉ እንደሚያሳየው በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃና ዕድሜ ከተማሪዎች የሚጠበቅ መጻፍ ችሎታ አለ፡፡ ይህም ፊደላትን ለይቶ ከመጻፍ ጀምሮ ሰፋፊ ድርሰቶችን አደራጅቶ እስከመተንተን ይደርሳል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ሊመዘኑና ውጤት ሊሰጣቸው የሚገባው በሞዴሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት ልክ እንደሆነ Elizabeth (2009) በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡

ይህም ጥናት ተመራማሪዋ ከተከተሉት የChrstopher Gordon (2001) የመገምገሚያ ሞዴል ውስጥ የነጻነት እድሜ /Independent age/ ከሚለው ጠቃሚ ሀሳቦችን በመውሰድ እርማቱ ተከናውኗል፡፡ በመገምገሚያ ሞዴሉ ውስጥ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች መካከል የነጻነት ጊዜ የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ መስፈርቱ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ደረጃ ከዚህ እስከዚህ በሚል የእድሜ ክልል ያልገደበ በመሆኑና በተለይ ከአስራ አራት አመት በላይ ለሆኑ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መገምገሚያ ሆኖ ማገልገል ስለሚችል ነው፡፡ በተጓዳኝ ተጠኚ ተማሪዎች ያሉበት የዕድሜ ክልል ሲፈተሽም በመስፈርቱ በተካተተው የዕድሜ እርከን ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው መስፈርቱን ለመጠቀም አስፈላጊ ሆኗል (አባሪ “ሸ” ን ይመልከቱ)፡፡ ለምሳሌ የተደራጁና ስርዓታቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፣ መሸጋገሪያ ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም አንቀጽ መጻፍ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው ተጠቅመው በተለያዩ ርዕሶች ድርሰቶችን መጻፍ፣ በተሰጣቸው ሆነ ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ምናባዊ ጽሁፍ መጻፍ ወዘተ. የሚሉት ተጠባቂ ችሎታዎች ለማረሚያነት በተመረጠው የነጻነት እድሜ /Independent age/ ሞዴል ውስጥ በመስፈርትነት የተቀመጡ ናቸው፡፡

ሌላው የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ በሚታረሙበት ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ የማረሚያ ምልክትና የውጤት አሰጣጥ ዘዴ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ይኸውም በአራሚዎች መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለማጥበብና ተመሳሳይ የአስተራረም ስልት ለማስፈን ይቻል ዘንድ ነው፡፡ የፈተና አስተራረም መመሪያውም ለእያንዳንዱ አራሚ ተባዝቶ ተሰጥቷል፡፡

#### 3.2.2.2. የጽሁፍ መጠይቅ

Dornyei (2007) እንደገለጹት የጽሁፍ መጠይቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቁጥር ካላቸው ተጠኚዎች ስነባህሪያዊ ሁኔታንና ሌሎችን ጉዳዮች አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋለበት ዋነኛ አላማም ተጠኚዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት ለትምህርቱ የነበራቸው ፍላጎት በዘዴው ከተማሩ በኋላ ካሳዩት ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል ልዩነት እንዳመጣ ለማረጋገጥ ነው፡፡ መጠይቁ በጥናቱ መግቢያ የተነሱትን መሪ ጥያቄዎች ለመመለስ በሚያስችል ሁኔታ ከምርምሩ አላማና መላምት ጋር የተዛመዱ፣ሁሉም ተጠያቂ አካላት በቀላሉ አንብበው በሚረዷቸው መልኩ ግልጽና አጭር ሆነው የቀረቡ፣ እንዲሁም ከተመራማሪዋ ግላዊ ስሜት ፀድተው ተጠያቂዎች ባላቸው መረጃ ላይ ተመስርተው ትክክለኛ ምላሽን እንዲሰጡ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን እንዲይዝ ጥረት የተደረገ ሲሆን በዓይታቸውም ዝግ (closed) ጥያቄዎችን አካቷል፡፡

መጠይቁ የLikert Scale ስልትን የተከተለ ሲሆን ይህም "መላሾች አንድ ጥያቄ ይቀርብላቸውና በዚያ ጉዳይ ላይ ያላቸውን አመለካከት፣ ባህሪይና እምነት ሊወክል ይችላል የሚሉትን ከተሰጧቸው አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ መልስ እንዲሰጡ የሚደረግበት መጠን አመልካች የጥያቄ አይነት ነው" (ያለው 2001፡164)፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የLikert Scale የአጠያየቅ ስልት ማለትም በጣም አስማማለሁ (4) አስማማለሁ (3) አልስማማም (2) እና በጣም አልስማማም (1) የሚሉት አቀራረቦች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

ጥያቄዎችን በአንድ ዓይነት መልክ ማለትም በዝግ (closed) ብቻ ወስኖ ለማቅረብ ምክንያት የሆነው ከናሙና ጥናቱ የተገኘው ተሞክሮ ነው፡፡ በናሙና ጥናቱ ትግበራ ወቅት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ዝግ (closed) እና ነፃ (open) ጥያቄዎችን ያካተተ ነበር፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም አንድን መረጃ የተለያዩ አቀራረቦችን ተጠቅሞ መሰብሰብ ከትክክለኛነት አንጻር የሚኖረውን አዎንታዊ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይሁንና በናሙና ጥናቱ ወቅት ጥያቄዎቹ በሁለት መንገድ ይቅረቡ እንጂ ከተጠኚዎች ምላሽ የተሰጠባቸው ግን ዝግ ጥያቄዎች (closed) ብቻ ነበሩ፡፡ እንደሚታወቀው ነጻ (open) ጥያቄዎች የመረጃ ሰጭዎችን ግላዊ አስተያየት ወይም አቋም ለማወቅ የሚቀርቡ እንደመሆናቸው መጠን ሰፋ ያሉ ሀሳቦችን እንዲያስገኙ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ እንዲሳካ ደግሞ የመረጃ ሰጪዎች ሀሳብን በጽሁፍ የመግለጽ ብቃትና ፍቃደኝነት ወሳኝ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ያጋጠመው ሁኔታም ከዚሁ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች መስማት የተሳናቸውና ሀሳባቸውን በታላሚው ቋንቋ በጽሁፍ በመግለጽ ረገድ ውስንነት ያለባቸው በመሆናቸው በናሙና ጥናቱ ወቅት በቀረቡ ነጻ ጥያቄዎች ላይ የሰጧቸው ምላሾች ለትንተና የሚበቁ አልነበሩም፡፡ ሁሉም መላሾች ማለት በሚያስደፍር መልኩ ለነጻ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ የለም ወይም በጽሁፍ ያሰፈሩት ሀሳብ ትርጉም አልባ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ተጠኚዎች በቀላሉ ተረድተዋቸው አጭር ምላሽ ሊሰጡባቸው የሚያስችሉና አንድ ዓይነት መንገድን የተከተሉ ዝግ (closed) ጥያቄዎችን ብቻ አዘጋጅቶ ለማቅረብ ምክንያት ሆኗል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የተሞላበትን ጊዜ በተመለከተ ከፈተናው ጋር በተመሳሳይ መልኩ ትምህርቱ ከመጀመሩ ሁለት ቀን አስቀድሞና በትምህርቱ ማጠናቀቂያ ሳምንት ሲሆን በዚህም ተጠኚ ተማሪዎች ካላቸው የቁጥር ውስንነት የተነሳም በጥናቱ የታቀፉት ሁሉም ተማሪዎች (7ቱም) መጠይቁን በመሙላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

መጠይቁ ሃያ ሶስት ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህም አንድን አላማ ለማሳካት በሁለት ዓይነት መንገድ ተከፋፍለው የቀረቡ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ አስራ አንዱ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ፍላጎት ከማስተማሪያ ዘዴው አንጻር ሊለኩ በአሉታዊና በአዎንታዊ መልክ የቀረቡ ሲሆኑ ቀጣዮቹ አስራ ሁለት ጥያቄዎች ደግሞ የክሂሉን አስፈላጊነት አስመልክቶ ተማሪዎች ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ በተመሳሳይ ቅርጽ የቀረቡ ናቸው (አባሪ"መ"ንይመልከቱ)፡፡ በጥቅሉ ግን በሁለቱም ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች አላማ አድርገው የተነሱት መስተጋብራዊ ዘዴ በተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት ላይ ያመጣው ለውጥ ካለ ማረጋገጥ ነው፡፡

#### 3.2.2.3. የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት

በዚህ ጥናት ውስጥ በደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ የዋለው ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆን ዋነኛ አላማውም ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በመጻፍ ክሂል ችሎታቸውና በመማር ፍላጎታቸው ላይ የመጣው ለውጥ ምን እንደሚመስል ተጨማሪና የማጠናከሪያ ሀሳቦችን ማስገኘት ነው፡፡ ውይይቱ ማስተማሪያ ዘዴውን በመተግበር ሂደት በተከናወኑ አብይ ተግባራት ወይም በዘዴው ስነ ትምህርታዊ ፋይዳ ላይ ባተኮሩ ሰባት (7) የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ሲሆን በልምምዱ ሂደትም ተማሪዎች አጋጥመውናል የሚሏቸውን ተሞክሮዎች በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ ጎናቸው የተነተኑበት ነው፡፡ የመወያያ ሀሳቦች አጠቃላይ ይዘትን በተመለከተም በምዕራፍ አራት

በትንተናው ክፍልና በአባሪ “መ” ላይ በዝርዝር የቀረበ በመሆኑ ማመሳከሪያ ይሆን ዘንድ ከዚያ መመልከት ይቻላል፡፡የውይይቱን አተገባበር ስንመለከት እያንዳንዱ የመወያያ ሀሳብ ለተማሪዎች ቀርቦ ምላሽ የተሰጠው ዘዴውን ከምትተገብረው መምህርት ውጪ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች አማርኛ ቋንቋን በምታስተምር አንዲት መምህርት አማካኝነት በምልክት ቋንቋ እየተተረጎመ ሲሆን ከተማሪዎች የሚሰነዘሩ ሀሳቦችም ለትንታኔ በሚያመቹ መልኩ ውይይቱን በምትመራው መምህርት በጽሁፍ ለመመዝገብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሌላው ከትግበራው በፊት በውይይቱ የማተኮሪያ ሀሳቦች፣ በአላማውና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በተመራማሪዋና በአወያይ መምህርቷ ዘንድ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር በማሰብ የሁለትዮሽ ውይይትም ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

## 3.3. የናሙና ጥናት

ዋናው ጥናት በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ልዩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመካሄዱ በፊት የናሙና ጥናት ቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ልዩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተደርጓል፡፡ የናሙና ጥናቱ ዋነኛ ዓላማዎች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በናሙና ጥናቱ ሂደት ተግባር ላይ የሚውሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኝነታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹን የአስተማማኝነት ደረጃን መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በሁለቱ ዓላማዎች ውስጥ የተገኙ ውጤቶችን ለማሳየት ይሞከራል፡፡

### 3.3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኝነት

ትክክለኛነትና አስተማማኝነት በአንድ የምርምር ስራ ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጧቸው ሊሰሩ ከሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች  መካከል ዋነኞቹ እንደሆኑ ያለው (2001) ያስረዳሉ:: ምክንያቱም ሁለቱም የአንድን ጥናት ውጤት ተቀባይነት የሚወሰኑ በመሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ትክክለኝነት አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመሰብሰብ የተፈለገውን መረጃ ለማስገኘት ያለው ዝግጁነት ምን ያህል እንደሆነ ወይም በታሰበው መንገድ የተሟላና ተገቢ መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችለውን ባህሪ ማሟላት አለሟሟላቱ የሚረጋገጥበት ነው፡፡ የመረጃ ትክክለኝነት በተለያዩ መንገዶች ሊፈተሽ እንደሚችል ያለው (2001) ካሰፈሩት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ይዘት ተኮር፣ መስፈርት ተኮር፣ ትውረት ተኮርና ግልብ ተኮር ትክክለኛነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዚህ የጥናት ሂደትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹን የትክክለኝነት ደረጃ ለማረጋገጥ ተግባር ላይ የዋሉት የመለኪያ መንገዶች ይዘት ተኮርና ግልብ ተኮር ትክክለኛነት ሲሆኑ መለኪያዎቹ የተመረጡበት ምክንያትም አንደኛ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ሲገመገሙ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን መሪ ጥያቄ ለመመለስ በሚያስችሉ መልኩ ስለመዘጋጀታቸውና እንዲሁም ሊለካ የተፈለገውን ባህሪ በትክክል ለመለካት የሚያስችል ይዘታዊ አቀራረብ  ስለመላበሳቸው ማረጋገጥ የፍተሻው ዋነኛው ትኩረት በመሆኑ ነው፡፡በግልብ ተኮር ትክክለኛነት እንዲፈተሽ የተደረገበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በተለይ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ በሆነው ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ወይም የመጻፍ ትምህርት ተግባራት ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት በማድረግ በተመራማሪዋ ከተዘጋጁት የማስተማሪያ ተግባራት ጋር ሲናበቡ ምን ያህል ሚዛናቸውን ጠብቀው እንደተዘጋጁ ማረጋገጥ ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት ነው፡፡በዚህም መሰረት በናሙና ጥናቱ ትግበራ ወቅት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በቀጥታ ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት ትክክለኝነታቸው በተለያዩ አካላት እንዲፈተሽ የተደረገ ሲሆን  በዋናነት የጥናቱ አማካሪዎች የሆኑት ሁለት መምህራን እንዲሁም ጥያቄዎቹን ከቋንቋና መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመማር ዘይቤ አኳያ ገምግመው ሙያዊ አስተያየታቸውን የሰጡ አንድ የቋንቋና ሁለት የስነ ባህሪይ መምህራን ተሳትፈዋል፡፡ በግምገማው ሂደት ትኩረት የተደረገባቸውን ነጥቦች እንደ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ዓይነት በሚከተለው መልኩ በአስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

#### 3.3.1.1. የፈተናዎች ትክክለኝነት

የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችን ትክክለኛነት ለማስጠበቅ በጥናቱ አማካሪዎች እንዲገመገም በተደረገበት ወቅት ከተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መካከል አንዱ ከናሙና ጥናቱ ትግበራ በፊት ሌላ ቅድመ ናሙና ጥናት በአቻ ትምህርት ቤትና ተማሪዎች ላይ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ ይህ አይነቱ አሰራር በናሙና ጥናቱ ትግበራ ወቅት ከተጠኚ ተማሪዎች ዳራዊ ማንነት ጋር ተያይዞ ሊያጋጥም የሚችልን የቋንቋ ግንዛቤ ክፍተት አስቀድሞ ሊሞላ እንደሚችል ስለታመነበት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የናሙና ጥናቱ ከሚካሄድባቸው ተማሪዎች ውጪ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ለሚማሩ መስማት የተሳናቸው የሰባተኛ (7ኛ) ክፍል ተማሪዎች ፈተናውን አቅርቦ በመፈተን የቅድመ ናሙና ጥናት ፍተሻ ተከናውኗል፡፡ በዚህም በናሙና ጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ዘንድ ቢቀርቡ ከባድ ሆነው

ላይመለሱ የሚችሉ የፈተናውን አንዳንድ ጥያቄዎች አስወግዶ በቀላል አቀራረብ መቀየር፣ ለእያንዳዱ ተግባር መሪ ምሳሌዎችና ማብራሪያዎችን ማቅረብ እንዲሁም የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን ተግባራት መለየት ተችሏል፡፡ መመሪያዎችን በተመለከተም ከተጠኚ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ውስንነት አንጻር ተመዝነው በአቀራረባቸው አሻሚና ከባድ ሆነው የተገኙ ስለነበሩ በእነዚያም ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ፈተናውን ለመስራት የተሰጠው አንድ ሰዓት ከተጠኚዎች የአተገባበር ሁኔታ አኳያ ሲገመገም በቂ ሆኖ አለመገኘቱና ተጨማሪ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ የታወቀው እንደዚሁ የቅድመ ናሙና ጥናቱን በማከናወን ሂደት ነው፡፡

ሌላው ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርትና የጥናቱን ማስተማሪያ ተግባራት መሰረት አድርገው ከመቅረባቸው አኳያ ተገምግመው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ የተከናወነውን ስራ ለአብነት ብንመለከት በመጀመሪያ ዙር ለአማካሪዎችም ሆነ ለሌሎች ገምጋሚዎች ቀርቦ አስተያየት የተሰጠበት የቅድመና ድህረ ትምህርቱ ፈተና ይዘት የተጠኚዎችን ጥቅል የመጻፍ ችሎታን ለመለካት በሚያስችል መልኩ በነጻ ጽህፈት ስልት ብቻ የተቃኙ ነበሩ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በዋነኛነት ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ወይም መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት የመጻፍ ክሂል ይዘቶች መካከል ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ለነጻ ጽህፈት ተግባራት በመሆኑና ያንንም ሚዛናዊ አድርጎ ለማቅረብ ካለ ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በነጻ ጽህፈት ስልት የሚቀርቡ ተግባራት በአብዛኛው የሚያተኩሩት በሰፋፊ የድርሰት ሀተታዎች ላይ ነው፡፡ ተማሪዎችም በተሰጣቸው ወይም ራሳቸው በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመስርተው ሀሳባቸውን ያለገደብ በስፋት እንዲገልጹ የሚጠበቀው በዚሁ ስልት ነው፡፡ ስልቱ የመጻፍ ነጻነትን በማጎናጸፍ ተማሪዎች ብዙ ሀሳብ እንዲያመነጩና እንዲጽፉ በማድረጉ ረገድ ያለው ፋይዳ ቀላል ባይባልም የዚህ ጥናት ተተኳሪ ለሆኑት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ብቻውን በፈተናነት ማቅረብ ግን ከተማሪዎች የመስራት አቅም አኳያ ሲታይ ችግር ሊያመጣ እንደሚችል በአስተያየት ሰጪዎች ሀሳብ ተሰንዝሮበታል፡፡ በመሆኑም ፈተናው በነጻ ጽህፈት ላይ ብቻ ሳያተኩር በውስን እና መር ጽህፈት ተግባራት ተቃኝቶ ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅቶ እንደገና እንዲዘጋጅ ተደረጓል፡፡

ሌላው የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ ባካተቷቸው ጥያቄዎች ወይም የጽህፈት ተግባራት ምንም ዓይነት ልዩነት ያላቸው አይደሉም፡፡ ይህንንም አስመልክቶ በገምጋሚዎች በኩል አዎንታዊና አሉታዊ አስተያየቶች የተሰጠ ሲሆን የተወሰኑት ገምጋሚዎች ፈተናዎቹ

ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ይዘው መቅረባቸው በጥያቄዎቹ ወይም በተግባራቱ መካከል ሊፈጠር የሚችልን ያለመመጣጠን ችግር ለምሳሌ የክብደትና ቅለት ደረጃ፣ የይዘት ወጥነት/ተመሳሳይነት ችግርን ሊያስወግድ ስለሚችል የቅድመ ትምህርት ፈተናው ዓይነቱን ሳይቀይር በድህረ ትምህርቱ ላይ ቢቀርብ የተሻለ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ በቅድመ ትምህርቱ ወቅት የቀረበውን ፈተና በድህረ ትምህርት ፈተናነት እንደገና ማቅረቡ ተማሪዎች ተረድተው ሳይሆን አስታውሰው ለሚሰጡት ምላሽ በር ይከፍታል የሚል ምክንያት ሰንዝረዋል፡፡ በገምጋሚዎች የተሰጡትን አስተያየቶች በግብዓትነት በመውሰድ ተመራማሪዋ የጥናቱን አላማ እንደገና በጥልቀት ፈትሻና እንዲሁም በአንድ የሙከራ ቡድን ንድፍ ላይ ተመስርተው ከተጠኑ ሌሎች ጥናቶች ልምድ በመውሰድ የመጀመሪያውን አስተያየት ተቀብላዋለች፡፡ በመሆኑም የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ተመሳሳይ ቅርጽና ይዘት ኖሯቸው እንዲቀርቡ ውሳኔ ላይ መድረስ የተቻለው ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ ነው፡፡

### 3.3.1.2. የጽሑፍ መጠይቅ ትክክለኝነት

የጽሑፍ መጠይቁን በመገምገም ሂደት የጥናቱ አማካሪና እንደዚሁ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ አስተያየታቸውን ሰጥተው የነበሩት ሁለቱ የስነ ባህሪይ ትምህርት ክፍል መምህራን ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ በመጀመሪያ ዙር ለገምጋሚዎች በተሰጠበት ጊዜ የነበረውን መልክ ለአብነት ብናነሳ አብዛኞቹ ጥያቄዎች በአሉታዊ የአጠያየቅ መንፈስ የቀረቡና አንዳንዶቹም የሀሳብ ድግግሞሽ የታየባቸው እንዲሁም በመመሪያዎች ያልተከፋፈሉ ነበሩ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የጽሑፍ መጠይቁን ትክክለኛነት በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሚያጓድሉ ስለሆኑ እንደገና ታርመው እንዲቀርቡ በገምጋሚዎች አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ሀ. የመጻፍ ክሂል ትምህርት መማር ደስ የሚለኝ በስዕላዊ መግለጫዎች ታግዞ ሲቀርብ ይደለም ለ. በመጻፍ ልምምድ ጊዜ በመምህሩን የሚሰጡ ተከታታይ ተግባራት ስለሚያደክሙኝ ትምህርቱን እንድጠላው አድርጎኛል፡፡ የሚሉ በርካታ አረፍተ ነገሮችን ግሶቻቸውን ወደ አዎንታዊ በመቀየር ለማስተካከል ተሞክረዋል፡፡ በዚህም መሰረት በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች አሉታዊ ብቻ ሳይሆኑ አዎንታዊ የአጠያየቅ መንፈስን ተላብሰው እንዲቀርቡ፣ የሀሳብ ድግግሞሽ ያለባቸው ጥያቄዎች ተወግደው በሌላ እንዲተኩና ሁሉም ጥያቄዎች ለአንድ አላማ የቀረቡ ቢሆንም እንኳን በመመሪያዎች ተከፋፍለው መቅረባቸው ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት በሁለት ክፍል ተዋቅረው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የጽሁፍ መጠይቁ በመጀመሪያ ረቂቁ ላይ ያካተታቸው ጥያቄዎች በመጠናቸው በረካታ የነበሩ ሲሆን ዝግ ጥያቄዎች 35 ነጻ ጥያቄዎች ደግሞ 6 ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች

ከጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የመስራት ሁኔታ አንጻር ሲገመገሙ ብዙና አሰልቺ ከመሆናቸው የተነሳ የሚፈለገውን መረጃ በታሰበው ያህል ላያስገኙ ስለሚችሉ የተጠኚዎችን የመስራት አቅም ባገናዘበ ሁኔታ ተመጥነው መቅረብ እንዳለባቸው በገምጋሚዎች አስተያየት ተሰንዝሮባቸዋል፡፡ ይህም ተገቢ መሆኑ በተመራማሪዋ ስለታመነበት የዝግ ጥያቄዎች መጠን ወደ 23 እና የነጻ ጥያቄዎች ደግሞ ወደ 2 ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡ ሌላው በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ የነበሩት ጥቂት ጥያቄዎች ረዘም ባለ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስልት የቀረቡ ነበሩ፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች በተጠኚዎች ዘንድ ምናልባት አሻሚነትን ሊፈጥሩ ስለሚችሉ በቀላሉ ተረድተዋቸው ሊመልሷቸው በሚችሏቸው መልኩ አጠር ባለ የአረፍተ ነገር አወቃቀርና ግልጽ በሆነ አገላለጽ እደገና ተስተካክለው ቢቀርቡ ጠቃሚ እንደሚሆን ከገምጋሚዎቹ ሀሳብ ተገኝቷል፡፡ ሀሳቡን መሰረት በማድረግም እንከን አለባቸው የተባሉትን ጥያቄዎች አሻሽሎ በመጻፍ የክለሳ ስራ ተከናውኗል፡፡

#### 3.3.1.3. የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ትክክለኝነት

የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናውና ጽሑፍ መጠይቁ ትክክለኝነት እንደተፈተሸ ሁሉ ለተማሪዎች የሚቀርበው የቡድን ተኮር ውይይት አስቀድሞ እንዲገመገም ተደርጓል፡፡ የቡድን ተኮር ውይይቱ ዋነኛ አላማ  በፈተናውና በጽሁፍ መጠይቁ ለተሰበሰበው መረጃ ማጠናከሪያ የሚሆን ሀሳብ ማስገኘት እንደመሆኑ መጠን በውስጡ ሊያካትታቸው የሚገቡ የመወያ ሀሰቦችም ይህንን አላማ ሊያሳኩ የሚችሉ ሊሆኑ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በውይይቱ ላይ የሚቀርቡት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ በምን ያህል መጠን ተገቢነቱ እንደተጠበቀ ፈተናውና የጽሁፍ መጠያቁን ለገመገሙት ምሁራን ቀርቦ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ አስተያየቶቹ በአብዛኛው ተመሳሳይ የሆኑና ጥያቄዎቹ ሊያስገኙት በሚፈለገው መረጃ ላይ ትኩረት ሰጥተው መዘጋጀት እንዳለባቸው የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በመጀመሪያው ዙር ከተዘጋጁት 10 የመወያያ ጥያቄዎች መካከል ያፈነገጠ ሀሳብ ያለባቸውና ለጥናቱ ረብ የለሽ መረጃን ሊያሰጡ የሚችሉ ናቸው የተባሉ ጥያቅዎችን በማስወገድ ከጥናቱ አላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን 5 ጥያቄዎች በመምረጥ የማሻሻያ ስራ ተከናውኗል፡፡

### 3.3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነት

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የአስተማማኝነት ደረጃ በመለካት ረገድ ተግባር ላይ የሚውሉ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም መካከል ወጥነት (Stability) ወይም ዳግም ፈተና (Test-retest)፣ የመለኪያ ይዘታዊ ወጥነት (Internal Consistency)፣ተመሳሳይ ይዘት

መለኪያዎች ወ.ዘ.ተ በስፋት የሚታወቁ እንደሆኑ ያለው (2001) ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና ዘዴዎቹን ጥቅም ላይ ለማዋል በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ዓይነትና በተገኘው መረጃ ባህሪ ላይ ተመስርቶ ከዘዴዎቹ መካከል ተገቢውን መምረጥ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት በጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በሆነው ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን ውጤቶች የአስተማማኝነት ደረጃ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

**3.3.2.1. የፈተናዎች አስተማማኝነት**

በናሙና ጥናቱ ተሳታፊ የነበሩት ስድስቱ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የተፈተኗቸው ፈተናዎች በሁለት አራሚዎች እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ የተገኘው ውጤትም በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ (Pearson Correlation Coefficient) የአስተማማኝነት ደረጃው እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም በቅድመ ፈተናው 0.952 በድህረ ፈተናው ደግሞ 0.994 የሆነ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ ከተገኘው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ላይ የቀረቡት የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች የአስተማማኝነት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡

**3.3.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ አስተማማኝነት**

በናሙና ጥናቱ ትግበራ ወቅት በቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቆቹ የተገኙት መረጃዎች ተገቢ የሆነ የማጣራት፣ የማደራጀትና ኮድ የማድረግ ስራ ተደርጎባቸው የአስተማማኝነት ደረጃቸው በSPSS እንዲፈተሽ ሆኗል፡፡ የመለኪያ ዘዴ ወጥነት /Stability/ ወይም ዳግም ፍተና /Test r-test / የሆነው የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (መገመቻ) /Pearson correlation Coefficient/ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህም በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ 0.602 በድህረ ትምህርት መጠይቁ ደግሞ 0.672 የሆነ ውጤት የተመዘገበ ሲሆን ይህም ለተጠኚዎች የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆቹ አስተማማኝነታቸው ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተማሪዎቹን ዝርዝር ምላሽ በተመለከተ (አባሪ "ነ" ይመልከቱ)፡፡

በአጠቃላይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን አስተማማኝነት ያረጋግጣል ተብሎ የታሰበው የናሙና ጥናት ሲደረግ የሚከተሉት አብይ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ገብተዋል፡፡

- ቅድመ ትምህርት ፈተናውን እና የጽሁፍ መጠይቁን ትምህርቱ ከመጀመሩ ከሁለት ቀን በፊት ተጠኚ ተማሪዎች እንዲፈተኑና እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

- ትምህርቱ በተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ባህሪይ ዙሪያ ለ7ቀን ስልጠና በተሰጣት አንድ መምህርት ለአምስት ሳምንታት (ለ15 ክፍለ ጊዜያት) ያህል ለተጠኚዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

- በትምህርቱ ማገባደጃም በይዘት፣ በዓይነትና በመጠን በቅድመ ትምህርቱ ወቅት ከተሰጠው ጋር አንድ አይነት የሆነ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ እንደገና እንዲፈተኑና እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ወይም በቅድመ ትምህርቱ ወቅት የተፈተኑትን ፈተናና የሞሉትን የጽሁፍ መጠይቅ በድጋሜ እንዲፈተኑና እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡
- ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹም ሆነ የጽሁፍ መጠይቁ ለተጠኚዎች ቀርቦ የተሞላው ዘዴውን ከምትተገብረው ውጪ በትምህርት ቤቱ ባሉ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በኩል ሲሆን ሂደቱ በተመደበለት ሰዓት፣ በመማሪያ ክፍል ሁኔታ፣ በምልክት ቋንቋ አተረጓጎምና በሌሎች አቀራረቦች የተነሳ ለተሳሳተ ውጤት እንዳይዳረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡
- ሁለቱም ፈተናዎች የታረሙት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በተሰጣቸውና የመጀመሪያ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም በአንድ አይነት የማረሚያ መስፈርት ነው፡፡
- በቅድመና በድህረ ፈተናዎች መካከል የሶስት ሳምንታት የጊዜ ልዩነት ተደርጓል፡፡ ይህም በአላስፈላጊ የጊዜ ርዝማኔና እጥረት ሳቢያ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ላይ ሊመጣ የሚችልን የአስተማማኝነት ችግር ይቀንሳል የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡

### 3.3.3. ከናሙና ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች

የናሙና ጥናቱ የተካሄደው በቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት ተተኳሪ በሆኑ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ዋነኛ ዓላማውም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ከማረጋገጥ ባሻገር የማስተማሪያ ዘዴውን በመተግበር ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ በዋናው ጥናት እንዳይደገሙ ለይቶ በማውጣት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው፡፡ በመሆኑም በናሙና ጥናቱ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መጠናዊ መረጃዎች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው ተጠኚዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታቸውና የመማር ፍላጎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት እንዳሳዩና እንዳላሳዩ በማረጋገጥ የተፈታሹን የማስተማሪያ ዘዴ የተጽዕኖ ደረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘውም መረጃ በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ

ዘዴ ተተንትኖ በተመሳሳይ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውን ውጤት የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በአጠቃላይ በናሙና ጥናቱ ከተከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና ከተደረሰባቸው ውጤቶች በመነሳት በማስተማሪያነት በተዘጋጁት ይዘቶችና ተግባራት አቀራረብ፣ በመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ እንዲሁም በትምህርቱ መተግበሪያ መሳሪያዎች ዝግጅትና በጊዜ አጠቃቀም ዙሪያ ተጨማሪ ማሻሻያዎች ለዋናው ጥናት እንደሚያስፈልጉ መረዳት ተችሏል፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት ሀሳቦችም ይህንን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

1. የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎችን ለመፈተን የተሰጠው ሁለት ሰዓት ከጥያቄዎቹ ይዘትና ተተኳሪ ተማሪዎቹ ካለባቸው የቋንቋ ውሱንነት አኳያ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው ተጠኚዎች ለእያንዳንዱ የፈተናው ተግባር ማብራሪያና ምሳሌ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ቃላትን መሰረት አድርገው ዓ. ነገር እንዲጽፉ ለማዘዝ ጥያቄውን የመሰለ ምሳሌ ያስፈልጋል፡፡

   ሀ. ጥያቄ- ተሸለመ

   መልስ- ዳንኤል በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ስላመጣ ተሸለመ፡፡

   - ነገዶ፣ ዝናብ፣ ሄደ ወዘተ. የሚሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ ተደርገዋል፡፡

   በእርግጥ እንዲህ አይነቱ ችግር በናሙና ጥናቱ ላይ ያጋጥም ይሆናል በሚል ስጋት በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በሚማሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ላይ የቅድመ ናሙና ጥናት ፍተሻ ተደርጎ እንደነበር በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረትም መሻሻያ ተደርጎ ነበር፡፡ ይሁንና ማሻሻያው በቂ ሆኖ አለመገኘቱ በናሙና ጥናቱ ታውቋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ለዋናው ጥናት በሚቀርቡት ፈተናዎች ላይ ተጨማሪ ሰዓት መስጠት እንደሚገባ በመገንዘብ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ሁለት ሰዓት ወደ ሁለት ሰዓት ከግማሽ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

2. በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ቢካተቱ ጠቃሚ መረጃን ሊያስገኙ የሚችሉና ነገር ግን በናሙና ጥናቱ ያልቀረቡ ሀሳቦች እንዳሉ ከተደረገው የናሙና ጥናት መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም በዋናው ጥናት በተለይ ከማስተማሪያ ዘዴው ጋር በተገናኘ ልምምዱ በሚካሄድበት ጊዜ ተማሪዎችን ያጋጠሟቸው የአተገባበር ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎች እንዲካተቱ የተሰራ ሲሆን በዚህም

በናሙና ጥናቱ ላይ ቀርበው የነበሩት አምስት የመወያያ ሀሳቦች ወደ ሰባት ከፍ እንዲሉ ተደርጓል፡፡ ለዚህም በአባሪ ረ ጥያቄ ቁጥር ስድስትና ሰባት ላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ሀሳቦች ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

- በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርታችሁን በተማራችሁበት ወቅት የገጠማችሁ ችግር ወይም መሻሻል አለበት የምትሉት ነገር አለ?
- በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራችሁ በመጻፍ ክሂል ችሎታችሁና

  በመማር ፍላጎታችሁ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

3. በጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ ከቀረቡ የጥያቄ አይነቶች መካከል ተጠኚዎች በጽህፈት ትምህርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲጽፉ የሚጋብዙ ሁለት ክፍት ጥያቄዎች (ቁጥር 24 እና 25) ነበሩ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ ቢሰጥባቸው ለጥናቱ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ቀላል ባይሆንም በናሙና ጥናቱ በቀረቡበት ወቅት ግን የተፈለገውን መረጃ ሊያስገኙ አልቻሉም፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት ከሚነሱት አንደኛው ተጠኚ ተማሪዎች ያለባቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ማነስ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በፈተናው ላይ እንደታየው ለመጠይቁ የተፈቀደው ሰዓት በቂ አለመሆኑ እንደሆነ አጥኚዋ አምናለች፡፡ በመሆኑም ችግሩን ለመቅረፍ በዋናው ጥናት ላይ ሁለቱ ክፍት ጥያቄዎች እንዳይካተቱ ማድረግና ለቀሩት ሃያ ሶስቱ ዝግ ጥያቄዎችም ተጠኚዎች የሚያስፈልጋቸውን ሰፊ ጊዜ ታሳቢ በማድረግ ተመጣጣኝ ሰዓት መመደብ እንደሚያስፈልግ ልምድ ስለተገኘ በጥያቄዎች አቀራረብና በመተግበሪያ ሰዓቱ ላይ ማሻሻያ ተደርጎ ዋናው ጥናት እንዲከናወን ሆኗል፡፡ በዋናው ጥናት ላይ እንዳይካተቱ የተደረጉት ሁለቱ ክፍት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡
   - ጥያቄ ቁጥር ሀያ ሶስት፦ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን መማራችሁ ለህይወታችሁ ጠቃሚ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? አስረዱ፡፡
   - ጥያቄ ቁጥር ሀያ አምስት፦ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን መማር የምትፈልጉት በምን አይነት መንገድ ሲቀርብላችሁ ነው?አብራሩ፡፡

4. የናሙና ጥናቱን ለማከናወን በተመራማሪዋ የተዘጋጁት የጽህፈት ማለማመጃ ተግባራት መሰረት ያደረጉት ለክፍል ደረጃው የቀረበውን መማሪያ መጽሃፍ እንደመሆኑ መጠን

የይዘት አደረጃጀታቸው የሚጀምረው አንቀጽና ሰፋ ያለ ድርሰት በመጻፍ ነው፡፡ በእርግጥ አካሄዱ በክፍል ደረጃው ለሚማሩት ሌሎች ተማሪዎች (መስማት ለሚችሉ) ብዙ ላይከብድ ይችላል፡፡ ይሁንና መስማት እንደተሳናቸው ዓይነት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ውስንነት ያለባቸው ተማሪዎችን ለማስተማር ሁኔታው ከባድ ሆኖ መገኘቱን ከናሙና ጥናቱ ትግበራና የደረጃ ማበልጸጊያ ተቋቁሞ ፈታኝ መምህራን አስተያየት መረዳት ተችሏል፡፡ በናሙና ጥናቱ ትግበራ ወቅት እንደተስተዋለው የተተኳሪ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ልምምዱ መጀመር ያለበት አንቀጽና ረዘም ያሉ ድርሰቶችን ከማጻፍ ይልቅ ዝቅተኛ ከሚባሉት ተግባራት ማለትም ከሆሄያት አጻጻፍ፣ ከቃላት ምስረታና ጽንሰ ሀሳባዊ ፍቺ፣ ከዐረፍተ ነገሮች ግንባታ፣ ከስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም፣ ከአንቀጽ አወቃቀር ይሆንና በሂደት ከፍ ወዳለው ድርሰት የመጻፍ ስራ ቢሸጋገር ተገቢ ይሆናል የሚል እምነት አለ፡፡ በቅድመና ድህረትምህርት ፈተናዎች ላይ የሚካተቱት የጥያቄ ይዘቶችም ድርሰት የመጻፍ ተግባርን በከፊል ቀንሰው ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት ንዑስ የመጻፍ ክሂሎች አንጻር ቢደራጁ የተጠኚዎች የመጻፍ ችሎታ ችግር ምን እንደሆነና ለመለየትና ለችግሩ መፍትሄ ለመፈለግ እንደሚቻል ከናሙና ጥናቱ ትግበራ ትምህርት ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ የናሙና ጥናቱ ሲካሄድ በማስተማሪያነት አገልግለው በነበሩት የጽህፈት መለማመጃ ተግባራትና ይዘቶች ላይ ማሻሻያዎች ተደርገው ለዋናው ጥናት ቀርበዋል፡፡

5. ለጥናቱ የተዘጋጁትን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ተግባራትን በተመለከተ ተጨማሪ ትምህርቶች ተገኝተዋል፡፡ ይሄውም በናሙና ጥናቱ ትግበራ ሂደት በነበሩት አምስት የትምህርት ሳምንታት ባጋጠመው የጊዜ እጥረት የተነሳ በማስተማሪያ ሞጁሉ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ይዘቶችና ተግባራት ለመሸፈን ሲባል በመምህርቷ ይደረግ የነበረው የተጣደፈ የትምህርት አፈጻጸም በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተጠኚ ተማሪዎችን የመስራት አቅምና የማስተማሪያ ዘዴውን ውጤታማነት ሊፈትን የሚችል መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ችግሩን ለመቅረፍ ሁለት የማሻሻያ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ አንደኛው በዋናው ጥናት የሚሰጠውን የትምህርት ጊዜ ከአምስት ሳምንት በሶስት ከፍ ማድረግ ወደ ስምንት ሳምንት ማድረስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን የጽህፈት ልምምድ በተመረጡ ይዘቶች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ናቸው፡፡ እነዚህ የተመረጡ ይዘቶች በውስን፣ መርና ነጻ ጽህፈት ተግባራት ላይ ያተኮሩና የትምህርቱን የቆይታ ጊዜ ከተማሪዎች የመስራት አቅም ጋር አጣጥሞ

ለመሄድ የሚያስችሉ ከመሆናቸው ባሻገር በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ውስጥ በተካተቱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን አንጻርም የተቃኙ ናቸው፡፡

6. በቡድን ተኮር ውይይት ትንተናው ላይ እንደታየው በተለያየ ቁጥር ተገልጸው የነበሩ ጥያቄዎች (ቁጥር 3 እና 4) ተዋህደው ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ እንደዚህ ሊሆን የቻለው በተመራማሪዋ የግንዛቤ ክፍተት ምክንያት አንድን ርዕሰ ነገር የሚመለከቱ ነገር ግን በሁለት የተለያዩ ክፍሎች የቀረቡ ጥያቄዎች በመገኘታቸው ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በአንዳንድ ጥያቄዎች ውስጥ የሀሳብ ድግግሞሽ መኖሩን በመሆኑ ተመሳሳይ ችግር በዋናው ጥናት እንዳያጋጥም በተቻለ መጠን በሌሎች ጥያቄዎችም ላይ ክለሳ በማድረግ ራሳቸው ችለው ሊመለሱ የሚችሉና ያልተደረቱ ግብ መቺ ጥያቄዎችን ማካተት እንደሚገባ ከተደረገው የናሙና ጥናት ትምህርት ተገኝቷል፡፡

7. ከመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች አኳያ ትምህርቶች ተቀስመዋል፡፡ በደረጃ ማበልጸጊያ ተቋቁሞ ላይ በፈታኞች ከተሰጡ አስተያየቶች ውስጥ አንዱ መጠናዊ መረጃዎች የተተነተኑበት ስልት አስፈላጊ መስፈርቶችን አሟልቶ አለመገኘቱ ነበር፡፡ ይኼውም በጥናቱ የመረጃ መተንተኛነት ጥቅም ላይ የዋለው ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ስልት አስፈላጊነቱ ቢታመንም ዘዴውን ለመጠቀም የሚያስችሉ ፈቃጅ ህጎችን ወይም የቅድመ ሁኔታ እሙኖችን አስቀድሞ መፈተሽ ይገባል፡፡ ይህንን በናሙና ጥናቱ ወቅት ማድረግ አልተቻለም ነበር፡፡ ነገር ግን በዋናው ጥናት ትንተና ሂደት በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት የመጠናዊ መረጃዎች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ከመተንተናቸው አስቀድሞ መተንተኛ ዘዴው የፓራሜትሪካዊ ስትስቲክስ እሙኖችን ሟማላት አለማሟላቱን ለማረጋገጥ የመረጃ ስርጭት ወጥነት (Normality) በኮልሞጎሮቨ-ሲሚርኖቨ (Kolmogorov-Smirnov) እና በሻፒሮ ዊልክ (Shapiro- Wilk) እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረትም የመተንተኛ ዘዴውን ለዚህ ጥናት ማዋል አስፈላጊና ተመራጭ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

8. ሌላው ከማስተማሪያ ግብዓቶች ጋር በተያያዘ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው መጠን ትምህርቱን በሚቀላቸው መንገድ ለማቅረብ በሚያስችሉና ለጥሩ ውጤት በሚያበቁ አቀራረቦች ላይ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ በናሙና ጥናቱ ትግበራ ሂደት ካጋጠመው ችግሮች መገንዘብ ተችሏል፡፡ የናሙና ጥናቱ በሚካሄድበት ቪክትሪ መስማት የተሳናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት ረዳት መምህርቷን ካጋጠሚት ችግሮች መካከል አንዱ የማስተማሪያ ቁሶችን

በሚያስፈልጉበት አግባብ አዘጋጅቶ አለመጠቀም ነው፡፡ እንደሚታወቀው ተጠኚዎች ካላቸው የመማር ሁኔታ አንጻር ለሚቀርብላቸው እያንዳንዱ ሀሳብ ገላጭ ምሳሌ፣ ስዕል፣ የሚዳሰስ ቁስ (Real Object)፣አካላዊ እንቅስቃሴና ሌሎች እይታዊ አስረጅዎችን ይፈልጋሉ፡፡ በመስተጋብራዊ ዘዴ የአተገባበር መርህ መሰረትም የእነዚህ ግብዓቶች መኖር ትምህርቱን የበለጠ እንደሚያቀላጥፈው ይታመናል፡፡ ምንም እንኳን ዋናው ጥናት በተካሄደበት አልፋ መስማት የተሳናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት የማስተማሪያ መሳሪያዎች አቅርቦት ችግር በከፊል የሚቀንስ ቢሆንም ትምህርቱን በተሟላ መንገድ ለማቅረብ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በራስ መንገድ ማዘጋጀት አልያም በግዥ መልክ ማቅረብ ግዴታ ይሆናል፡፡ ይህንን ሀላፊነት በዋናነት መወጣት ያለባት ደግሞ ተመራማሪዋ በመሆኗ ለተግባራት ማስፈጸሚያነት የሚውሉ ማስተማሪያ ቁሶችን በመግዛትና በራስዋ በማዘጋጀት በናሙና ጥናቱ ላይ አጋጥመው የነበሩ ችግሮች በዋናው ጥናት እንዳይደገሙ በተደረገው ቅድመ ዝግጅት ችግሩን ለማቃለል ተችሏል፡፡ በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አጠቃቀም ዙሪያም ዋናውን ጥናት ከምትተገብረው መምህርት ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

9. በአጠቃላይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ብቃት በመፈተሽ ሂደት የመረጃ የፈተናውና የጽሑፍ መጠይቁ የአስተማማኝነትና የትክክለኝነት ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑን ማረጋገጥ በመቻሉ መለኪያዎቹ ባሉበት ሁኔታ ለዋናው ጥናት ቢውሉ ችግር እንደማያመጡ ከናሙና ጥናቱና በደረጃ ማበልጸጊያ ተቋቁሞ ላይ ከተሰጠው አስተያየት መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 3.4. የማስተማር ትግበራ

በዚህ የዋና ጥናት ትግበራ ሂደት የማስተማር ስራው ለአምስት ሳምንታት ወይም ለአስራ አምስት ክፍለ ጊዜያት ተካሂዷል፡፡ የማስተማር ትግበራውን ለማካሄድም ተመራማሪዋ በዓላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተጠኚ ተማሪዎችንና ትምህርቱን የምትመራውን መምህርት መርጣ ማዘጋጀቷ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ እንደዚሁም የተመረጠችው መምህርት ወደ ማስተማር ትግበራው ከመግባቷ በፊት ስለምታስተምርበት የማስተማሪያ ዘዴ (ስለመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ) ሰፊ ግንዛቤ እንዲኖራት የሚያስችላትን ስልጠና በተመራማሪዋ በኩል ያገኘች ሲሆን ስልጠናውም የሁለት ሰዓት እርዝማኔ ያለውና ለሰባት ቀን ያህል የተከናወነ ነው፡፡ ስልጠናው የተሰጠበትን አላማና እንዲሁም ትኩረት የተደረገባቸውን መሰረታዊ ሀሳቦች

በተመለከተ በጥናቱ የመጨረሻ ክፍሎች በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል (አባሪ "ቀ"ን ይመልከቱ)። ከስልጠናው በኋላም መምህርቷ በምታስተምረው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ተግባራት ዙሪያ በቂ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራት ማድረግ ስለሚያስፈልግ በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ተቃኝቶ በተመራማሪዋ የተዘጋጀውን የማስተማሪያ ሞጁል ለሁለት ሳምንት ያህል ቀድማ እንድታነበውና እንዲተዘጋጅበት ተሰጥቷታል።

በመቀጠልም ለጥናቱ በተመረጠው አልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት የዋናው ጥናት የትግበራ ሂደት ተጀምሯል። ወይም ተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ እንዲማሩ ተደርጓል። በጥናቱ የተለያዩ ክፍሎች ለመጥቀስ እንደተሞከረው በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ሲታሰብ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ። ይሄውም የማስተማሪያ ዘዴው ቅንጅታዊ ባህሪ ነው። እንደሚታወቀው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የውጤትና የሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል አቀራረቦች ቅንጅታዊ ውጤት እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው የሚተገበሩ ተግባራት ሁሉ በሁለቱ የአቀራረብ መርሆዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህ የአተገባበር መርሆዎች ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በትምህርቱ ሂደት በሚከናወኑ የመጻፍ ክሂል ልምምዶች ላይ የሚገለጡ ናቸው። ለምሳሌ በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ አማካኝነት በአንድ የትምህርት እቅድ ሊተገበር የታሰበ የመጻፍ ክሂል ይዘት ቅድመ ጽህፈት፣ ጊዜ ጽህፈትና ድህረ ጽህፈት በተባሉት ደረጃዎች ምን ምን ተግባራት ሊከናወኑበት እንደሚገቡ እንዲሁም በየደረጃዎቹ የመምህሩና የተማሪዎች ሚና ምን መምሰል እንዳለበት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አጠቃቀምና የሌሎች ስነትምህርታዊ ጉዳዮች አፈጻጸም የሚወሰነው ዘዴው በሚከተላቸው መርሆዎች ላይ ነው።

በመሆኑም በቅድመ ጽህፈት ወቅት ተማሪዎችን በእለቱ ከሚማሩት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ማስተዋወቅ፣ የትምህርቱን አላማ በመንገር ተነሳሽነታቸውን መጨመር፣ በትምህርቱ ሂደትና ከትምህርቱ በኋላ ከእነሱ የሚጠበቀውን ሀላፊነት ማስረዳት፣ ስለሚሰሩት ተግባር ብቻ ሳይሆን የሰሩት ተግባር ስለሚመዘንበት መንገድና ስለሚኖረው ውጤት አስቀድሞ ማሳወቅ፣ ለልምምዳቸው መነሻ የሚሆኑ ሞዴል ጽሁፎችንና ምሳሌዎችን ማሳየት ከተቻለም በወረቀት አባዝቶ መስጠትና ሌሎች በርካታ ስራዎች በመምህሩና በተማሪዎች መተግበር ስላለባቸው በጥናቱ ሂደትም በየክፍለ ጊዜው ተከናውነዋል።

እንዲሁም በጊዜ ጽህፈት ወቅት ልምምዱ ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መግለጽ፣ መተርጎም፣ መከለስ፣ አርትኦት ማድረግ  በተባሉ የመጻፍ ትምህርት ደረጃዎች እንዲያልፍ ይደረጋል።

በዚህም እንደመስተጋብራዊ ዘዴ  መሰረተ-እሳቤ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራንና ተማሪዎች የሚኖራቸው የተግባር ተጋርቶ እኩል እንደመሆኑ መጠን በእያንዳንዱ ንዑስ የትምህርቱ ደረጃዎች በመምህርቷና በተማሪዎች፣ በተማሪዎች መካከል ማለትም በጥንድ፣ በቡድን እንዲሁም በጥቅል ሊኖሩ የሚገቡ የጋራ ትብብሮችና ግንኙነቶች ለትምህርቱ መቀልጠፍ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ መምህርቷ ይህንን በትኩረት እንድታመቻች ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው መጠን በልምምዱ ወቅት የሚከናወኑ ተግባራትን ተጨባጭ አድርጎ ለማቅረብና ሂደቱን ለማቅለል እንደ አስፈላጊነታቸው ሞዴሎችን፣ እይታዊ መሳሪያዎችን (ስዕሎች፣ ቻርቶች፣ ሰንጠረዦች)፣ በእጅ የሚዳሰሱ ቁሶችን (የሆሄያትና የቃላት መገጣጠሚያዎች)፣ አካላዊ መግለጫዎችን (ከድርጊት ወደ ጽሁፍ ሊቀየሩ የሚችሉ ቀለል ያሉ ጨዋታዎችና ታሪክ ነጋሪ ትዕይንቶች) ወ.ዘ.ተ በአጋዥነት በማቀረብ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ጥረት ተደርጓል፡፡

ሌላው ጊዜ ጽህፈት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሰፊው የሚለማመዱበት የመሆኑን ያህል በውስን ጽህፈት፣ በመርና በነጻ ጽህፈት መርሆዎች መሰረትነት ቅደም ተከተላቸው ያልተጠበቁ ሆሄያትን፣ በመነሻ ፊደላትና ስዕላዊ መግለጫዎች አማካኝነት ሊመሰረቱ የሚችሉ ቃላትን፣ ሀሳባቸው ተጓድሎ የቀረቡ ጽሁፎችን፣ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ያላሟሉ ሀሳቦችን፣ አወቃቀራቸውና አደረጃጀታቸው የተፋለሱ አረፍተ ነገሮችን፣ ተጀምረው ያላለቁ አጫጭር ታሪኮችንና ሙሉ ድርሰት ለመጻፍ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ቀለል ያሉ ርዕሶችን በተለያየ መልኩ ለተማሪዎች በማቅረብ በርካታ አሳታፊ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ሶስተኛው ድህረ የጽህፈት ደረጃ  ሲሆን ይህም ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ጊዜ ከተረዱት፣ ከተመለከቱት ነገር በመነሳት በየግላቸው፣ በጥንድና በቡድን አቅደው የጻፉትን ረቂቀ- ሀሳብ ከልሰውና አርመው በመጨረስ ለመምህራቸውና ለክፍል ጓደኞቻቸው በንባብ አቅርበው ምግበ ምላሽ የሚያገኙበት ነው፡፡ ይሁንና የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች  መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች እንደመሆናቸው መጠን በደረጃው ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራት የመማር ሁኔታቸውን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ በልምምዱ ሂደት ተማሪዎች በጻፉት ሀሳብ ላይ አስተያየት ሲቀበሉ ከነበሩባቸው መንገዶች አንዱ መምህርቷ ወረቀታቸውን በመሰብሰብ በስራቸው ላይ ለፈጸሟቸው የአጻጻፍ ግድፈቶችና ለነበሯቸው  ጠንካራ ጎኖች የማስተካከያና የማበረታቻ ሀሳቦችን በጽሁፍ አልያም በቃል(በምልክት ቋንቋ) አማካኝነት በምታደርገው ሰፊ የማስገንዘብ ስራ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ተማሪዎች የጻፉትን ሀሳብ በራሳቸው ለክፍሉ

ተማሪዎች እንዲያብራሩ ሲደረግ የተነሱበትን ርዕስና በጽሁፋቸው ውስጥ የተካተቱ ፍሬ ነገሮችን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ በምልክት ቋንቋ የታገዘ ገለጻ እንዲያደርጉና በዚህም ከጓደኞቻቸው ጋር አስተያየቶችን እንዲለዋወጡ በመምህርቷ የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡

የተማሪዎችን የተግባር ምዘና በተመለከተም የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ተሞክሯል፡፡ በጥናቱ የክለሳ ድርሳን ክፍል በስፋት እንደተነሳው በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በሚተገበር የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተማሪዎች የጽሁፍ ስራ የሚመዘነው በመምህቷ(ሩ) ብቸኛ ዘዋሪነት ሳይሆን በአብዛኛው በተማሪዎችም ጭምር በመሆኑ ከልምምዱ በፊት፣ በልምምዱ ወቅትና በኋላ ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው፣ በጥንድ፣ በቡድንና በጥቅል ይገመግማሉ፡፡ይሁን እንጂ የምዘናውን ሂደት በማመቻቸት ረገድ የመምህሩ(ቷ) ሚና ቀላል አይደለም፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች የጽሁፍ ስራቸውን ለመገምገም የሚያስፈልጋቸውን መስፈርት በማዘጋጀት ለእያንዳንዱ ተማሪ በወረቀት ማድረስ፣ መስፈርቱን እንዴትና መቼ መጠቀም እንዳለባቸው ማስረዳት፣ የመስፈርቱ ጽንሰ ሀሳብ ያልገባቸው ካሉ ማብራራት፣ ስራቸውን ገምግመው ከጨረሱ በኋላ ቀጣዩ ተግባራቸው ምን እንደሚሆን ማሳወቅ ወ.ዘ.ተ የመምህሩ(ቷ) ሀላፊነቶች በመሆናቸው በጥናቱ የማስተማር ትግበራ ወቅትም ትምህርቱን በምትመራው መምህርት የተከናወኑ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በመምህርቷ በቀረበላቸው መስፈርት አማካኝነት ስራቸውን ደጋግመው እየገመገሙ በመጻፍ ያጠናቀቁትን የመጨረሻ የጽሁፍ ስራ በመመዘን ምግበ ምላሽና ውጤት መስጠት እንዲሁም ተማሪዎች በልምምዱ ሂደት በየጊዜው በየግላቸው ከጻፉት ጽሁፍ በመነሳት ያሳዩትን መሻሻል ሊያስረዳ የሚችል ማህደረ ተግባር (ፖርትፎሊዮ) ማዘጋጀትና ስራቸውን በጥቅል መመዘን በመምህርቷ ከተሰሩ የምዘና ተግባራት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በተገለጸው መንገድ የመማር ማስተማር ሂደቱ ሲከናወን ከክፍለ ጊዜ ስርጭት አንጻር ያጋጠሙ ችግሮች ያሉ ቢሆንም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ለመፍታት ተችሏል፡፡ በተለይ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሳምንት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ሶስት ብቻ መሆኑ በማስተማሪያነት የቀረቡትን ሃያ ሁለት ተግባራት ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን በቂ አልነበረም፡፡ ይሁንና ተጠኚ ተማሪዎች ያላቸውን የመማር ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባትና እንዲሁም ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው የሚጠይቀውን ንዑስ የመጻፍ ክሎት ታሳቢ በማድረግ በሞጁሉ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች ለመሸፈን ከሚደረግ ሩጫ ይልቅ በተመረጡ ይዘቶች ላይ አተኩሮ ጥልቅ ልምምድ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑ በተመራማሪዋና ዘዴውን በምትተገብረው መምህርት ስለታመነበት

ለትግበራው የተመረጡ ይዘቶችን በሃያ ክፍለ ጊዜያት በመከፋፈል እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ሌላው ተጠኚ ተማሪዎች በጥናቱ ሊፈተሽ በታሰበው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ እየተማሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ በተመረጡ ስድስት ክፍለ ጊዜያት በተመራማሪዋ በኩል የክፍል ውስጥ ምልከታ የተደረገ ሲሆን ከትምህርቱ መጠናቀቀ በኂላም ተማሪዎች ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነውና የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተው የማስተማር ትግበራው ከፍጻሜ ደርሷል፡፡

## 3.5. የማስተማሪያ ይዘቶችና ተግባራት አዘገጃጀት

በዚህ ጥናት ሊፈተሽ ለታሰበው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ መተግበሪያ ሆነው የሚያገለግሉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችን፣ ክንውኖችን፣ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን፣ መመዘኛ ስልቶችንና ሌሎች ግብዓቶችን አስቀድሞ መምረጥና ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህንን ተግባር ማከናወን ደግሞ ለጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ተመጣጣኝ ተግባራትን ለማዘጋጀት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በዚህም መሰረት ይዘቶቹን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሀፉ ይወሰዱ? ወይስ በአዲስ መልክ ይዘጋጁ? የሚለውን ለመወሰን በተመረጠው የክፍል ደረጃ (7ኛ ክፍል) በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ላይ ፍተሻ ተደረገ ሲሆን የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫም በማስተማሪያ ዘዴው ላይ እንደመሆኑ መጠን በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር ያላቸው አመቺነት ተጠንቶ በከፊል ተስማሚ ሆነው በመገኘታቸው ከጥቂት ተጨማሪ ተግባራት ጋር ተዋቅረው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ሊፈተሽ ታቀደውን የማስተማሪያ ዘዴ ከማስተግበር አኳያ ምቹ ናቸው ሲባል ግን ሙሉ በሙሉ ከተጠኚ ተማሪዎች የመማር ሁኔታ አንጻር ተቃኝተው ቀርበዋል ወይም መሻሻል አያስፈልጋቸውም ለማለት ታስቦ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በአንጻሩ በመማሪያ መጽሀፉ ላይ በተደረገው ዳሰሳ ከተገኙት ክፍተቶች አንዱ የይዘቶችና የተግባራት አደረጃጀት ወይም መስመራዊነት ከተጠኚ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ አኳያ ተመጣጣኝ ሆኖ አለመቅረብ መሆኑ በተመራማሪዋ ስለታመነበት የማሻሻል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተመረጡት ይዘቶችና ተግባራት ከተጠኚ ተማሪዎች የመማር ሁኔታና ከመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር መርሆዎች አኳያ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተደማጭነት ወደ እይታዊና ድርጊታዊነት ተቀይረው ከተደራጁና በሞጁል መልክ በተመራማሪዋ ከተዘጋጁ በኂላ በቅድሚያ ለጥናቱ አማካሪዎችና በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቁ ግምገማ ላይ ለተሳተፉት ሁለት መምህራን እንዲገመገሙ

ተደርጓል፡፡ ቀጥሎም ከተሰጠው አስተያየት በመነሳት ማሻሻያ ተደርጎባቸው ትምህርቱን ለምታስተምረው መምህርት እንድታነበው ተሰጥቷታል፡፡

ለጥናቱ በማስተማሪያነት ከቀረቡት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ተግባራት መካከል ጥቂቶቹን ለአብነት ብናነሳ የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያትን በትክክለኛው ቅርጻቸው አሟልቶ መጻፍ፣ በወካይ ስዕሎችና የመነሻ ሆሄያት አማካኝነት ትርጉም ያላቸው ቃላትን መመስረትና በተመሰረቱት ቃላትም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን ማዋቀር፣ የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን በአውድና ከአውድ ውጪ ባለ አቀራረብ እንዲለዩ ለማስቻል ተግባራት ከቃላት ካርታና ሰንጠረዦች እንዲሁም አጫጭር ምንባቦች ጋር ተጣምረው በመጀመሪያዎቹ ሁለት የትምህርት ሳምንታት እንዲከናወኑ ሆነው ተካተዋል፡፡ ቀጥሎም በአወቃቀራቸው የተዛቡ አረፍተ ነገሮችን እንደገና በትክክለኛው መንገድ መጻፍ፣ በጅምር የቀሩ ሀሳቦችን በተገቢ ሀሳብ መሟላት፣ ስርዓተ ነጥቦችን በአረፍተ ነገሮችና በአንቀጾች ውስጥ በትክክል መጠቀም፣ በምክንያትና በውጤት የተሳሰሩ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፣ የአንቀጽ ማደራጃ ቢጋር ማዘጋጀት፣ ጅምር ታሪኮችን በተዛማጅ ሀሳብ ማጠናቀቅና አጫጭር ድርሰቶችን መጻፍ የሚሉ የትምህርቱ ይዘቶችና ተግባራት በመጨረሻዎቹ አምስት ሳምንታት እንዲተገበሩ ሆነው ተካተዋል፡፡

በጥቅሉ ሲታዩ የቀረቡት የማስተማሪያ ይዘቶችና ተግባራት ተማሪዎችን ከሀሳብ ጠባቂነት ወደ አፍላቂነት የሚያሸጋግሩ እንዲሆኑ በተቻለ መጠን ጥረት ተደርጓል፡፡ የመልመጃዎቹ ዓላማም ተማሪዎች በትምህርቱ መነሻ ላይ ሆሄያትን በመጻፍ፣ ቃላትና አረፍተ ነገሮችን በመገንባት ያገኙት ክህሎት አሳድገውና አስፍተው ቢጋር በማዘጋጀት የተሟላ መልእክት ያለው ተነባቢ ድርሰት በራሳቸው እንዲያዘጋጁ የሚያስችላቸውን ችሎታ እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ ለአላማው መሳካትም በልምምዱ ላይ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል (አባሪ “ተ” ን ይመልከቱ)፡፡

## 3.6. የጥናቱ የአሰራር ቅደም ተከተል

ይህንን ጥናት ከጅማሬው አንስቶ እስከፍጻሜው ለማድረስ የተለየዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የመጀመሪያው ተግባር ከጥናቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተዛማጅ ጽሑፎች በጥልቀት እንዲገመገሙ ማድረግ ሲሆን በዚህም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ለማስተማር አስፈላጊ ሆኖ የመመረጡ ምክንያት፣ የሚከተላቸው መርሆችና፣ የአተገባበር ሁኔታው እንዴት እንደሆነ ሙህራን ካቀረቧቸው ንድፈ ሀሳባዊ እይታዎችና ከቀደሙ ጥናቶች አኳያ ለማገናዘብ ተሞክሯል፡፡ ቀጥሎም ትልመ ጥናት ማዘጋጀትና ለአማካሪዎች ማስነበብ እንዲሁም አስተያየቶችን ተቀብሎ የማስተካከል ስራ ተከናውኗል፡፡

በመቀጠልም የትልመ ጥናቱን ስራ ለተቋቁሞ ማቅረብ ተችሏል፡፡ ከትልመ ጥናቱ ተቋቁሞ የተገኙ ግብዓቶችን መሰረት በማድረግም በጥናቱ ሀሳብ ላይ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ ለናሙና ጥናት መተግበሪያ የሚሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከስራዎቹ መካከል ዋና ዋናዎቹን ብናነሳ ለምሳሌ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ዝግጅት ማለትም የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቆችን ማዘጋጀት፣ የቡድን ተኮር ውይይት መወያያ ሀሳቦች ማጠናቀር እንዲሁም የተዘጋጁትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎችን ትክክለኛነት ለማስጠበቅ በጥናቱ አማካሪዎችና በሌሎች መምህራን የማስገምገምና ቅድመ ናሙና ጥናት ተግባራት ማከናወን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በመቀጠልም ለናሙና ጥናቱ በተመረጠው ቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት በመሄድ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ ጥናቱን ከምትተገብረው መምህርትና ከተጠኚ ተማሪዎች ጋር መተዋወቅና ፈቃድ የመጠየቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚያም በናሙና ጥናቱ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴውን ለምትተገብረው መምህርት ለ7 ተከታታይ ቀናት የቆየና የ2 ሰዓት ርዝማኔ ያለው የግንዛቤ መጨበጫ የሁለትዮሽ (በተመራማሪዋና በመምህረቷ) ውይይት የተደረገ ሲሆን ከውይይቱ በኋላም ተጠኚ ተማሪዎችን ለማስተማር ይረዳ ዘንድ በተመራማሪዋ ተዘጋጅተው የቀረቡትን የመጻፍ ክሂል ማለማመጃ ተግባራት ለመምህርቷ በመስጠት ለሁለት ሳምንት ያህል እንድታነበውና እንድትዘጋጅበት ተደርጓል፡፡ ይህም መምህርቷ ከማስተማሪያ ዘዴው ጋር በጥልቀት እንድትተዋወቅ አግዟታል፡፡


ከዚህ በኋላ የነበረው የናሙና ጥናት ማካሄድ ነበር፡፡ የናሙና ጥናቱ የተጀመረው ተጠኚ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ እንዲወስዱ ከተደረገ በኋላ ሲሆን ከየካቲት 18/6/2011 እስከ መጋቢት 28/7/2011 ዓ.ም. ድረስ ለአምስት ሳምንታት ያህል ቆይቷል፡፡ ከሶስት ሳምንታት የመጻፍ ክሂል ልምምድ ቆይታ በኋላም በቅድመ ትምህርቱ ተሰጥቶ የነበረውን ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ተጠኚዎች እንደገና እንዲፈተኑና እንዲሞሉ በማድረግ የናሙና ጥናቱ የመረጃ ስብሰባ ስራ ተጠናቋል፡፡ በመጨረሻም በናሙና ጥናቱ ሂደት በጽሁፍ መጠይቅ፣ በፈተናና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተደራጅተው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት (Paird Sample test) ተተንትነው፣ የዳግም ፍተና /Test r-test / በሆነው የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (መገመቻ) /Pearson correlation Coefficient/ ዘዴ አስተማማኝነታቸው ተረጋግጦና ውጤታቸው ተተርጉሞ የናሙና ጥናቱ ከፍጻሜ ደርሷል፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ትክክለኝነትና አስተማማኝነት በናሙና ጥናቱ አማካኝነት ከተረጋገጠ በኋላ የደረጃ ማበልጸጊያ ተቋቁሞ በማድረግ ለጥናቱ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን ማግኘት ተችሏል፡፡ በፈታኝ መምህራን የተሰጡ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግም የተለያዩ የመሻሻያ ስራዎች ተሰርተው ዋና ጥናቱ በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም ለስምንት ተከታታይ ሳምንታት ወይም ለሃያ ክፍለ ጊዜያት ያህል ተካሂዷል፡፡ ይሁንና ከጥናቱ ትግበራ በፊት የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ፍቃድ የመጠየቅ፣ ትምህርቱን ከምትተገብረው የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ጋር ስምምነት ማድረግና ተገቢውን ስልጠና የመስጠት እንዲሁም ከተጠኚ ተማሪዎች ጋር የመተዋወቅ ስራዎች በናሙና ጥናቱ ቅድመ ትግበራ ላይ እንደተደረገው በተመሳሳይ ሁኔታ ለዋና ጥናቱም አስቀድመው የተከናወኑ ናቸው፡፡

በዋና ጥናቱ ሂደትም ትምህርቱ ከመጀመሩ ከሁለት ቀን በፊት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለመፈተሽ የቅድመ ትምህርት ፈተና የተሰጠ ሲሆን በተመሳሳይ ተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦ ቅድመ ስልጠና በተሰጣቸው ሁለት የትምህርት ቤቱ የቋንቋ መምህራን ተጠኚዎች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ተተኳሪ ተማሪዎች በተፈታሹ መስተጋብራዊ  የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለስምንት ሳምንታት ያህል ተምረው ከጨረሱ በኋላ በመጨረሻዎቹ ሁለት ቀናት በትምህርቱ መጀመሪያ ተፈትነው የነበረውን ፈተናና ሞልተው የነበረውን የጽሁፍ መጠይቅ ቅድመ ትምህርት ፈተናውንና የጽሁፍ መጠይቁን ባስተገበሩት ሁለቱ መምህራን አማካኝነት በተመሳሳይ የአሰራር መርህ በድጋሚ እንዲፈተኑና እንዲሞሉ በማድረግ የመጠናዊ መረጃዎች ስብሰባ ስራው ተጠናቋል፡፡ በተጨማሪም ለጥናቱ በደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባር ላይ እንዲውል የተመረጠው የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት እንደዚሁ ከድህረ ትምህርቱ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ትግበራ በኋላ ዘዴውን ከምትተገብረው መምህርት ውጪ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች አማርኛ ቋንቋን በምታስተምርና በምልክት ቋንቋ ጥሩ ክህሎት ባላት አንድ መምህርት እንዲከናወን ተደርጎ የዋና ጥናቱ ትግበራ መጠናቀቅ ችሏል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት በሶስት አራሚዎች ከታረመ በኋላ መረጃዎቹ በተለያየ የአተናተን ስልት እንዲተነተኑ የተደረገ ሲሆን በቅድመና ድህረ ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መጠናዊ መረጃዎች ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ዘዴ እንዲሁም በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙት አይነታዊ መረጃዎች ደግሞ በገላጭ የመተንተኛ ስልት ተተንትነው

ቀርበዋል፡፡ ከትንተናዎቹ በመነሳትም በተገኙ ውጤቶች ላይ ማብራሪያ፣ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች የመስጠት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የሙከራ ጥናቱን አጠቃላይ የክንውን ሂደት ቀጥሎ በቀረበው ምስላዊ መግለጫ ባጭሩ መመልከት ይቻላል፡፡

ምስል ሶስት፦. የሙከራ ጥናቱ ቅደም ተከተላዊ ተግባራት



## 3.7. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተግባር ላይ የዋሉት ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆኑ በሁለቱ የመሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙትን መረጃዎች ለማጠናከርም የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት በአጋዥነት አገልግሏል፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለተሰበሰቡት መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች መጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን እያንዳንዳቸውም ለምንና እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ ቀጥሎ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

የዋና ጥናቱን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ሂደት በመጀመሪያ የተደረገው ሰባቱ ተጠኚ ተማሪዎች በየደረጃው የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችን እንዲፈተኑ ማድረግ ነበር፡፡ ፈተናዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላም በሶስት አራሚዎች አማካኝነት ከመቶ ታርመው በእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ መለያ ቁጥር መሰረትነት በቅደም ተከተላቸው ተለይተው እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ አላማ ተጠኚ ተማሪዎች በተፈታሹ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ ያላቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ቀደም ሲል ወይም በዘዴው ከመማራቸው በፊት ከነበራቸው ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል ለውጥ እንዳሳየ ማረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን አረፍተ ነገሮችን በመመስረትና በማቀናበር፣ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም፣ ጅምር ሀሳቦችን በማጠናቀቅ፣ እንዲሁም አጭር ድርሰት በመጻፍ ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች አንጻር ያስመዘገቡት ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የመተንተኛ ዘዴ ተሰልቶ ልዩነቱ እንዲነጻጸር ተደርጓል፡፡ በዚህም ገላጭና ድምዳሜያዊ ስታስቲክስ (Descriptive and Inferential Statistics) ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ይኸውም የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስትን /Repeated Measures SampleT-test/ በመጠቀም አማካይ ውጤት (mean score)፣ መደበኛ ልይይትና አንዱን ቡድን ከራሱ ውጤት ጋር ማነጻጸር (Paird Sample test) የተባሉ ስሌቶችን በመጠቀም እያንዳንዳቸው ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊትና በኋላ በቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተናው ላይ ጉልህ ልዩነት ማምጣት አለማምጣታቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ (አስተማማኝነት) በክሮንባኽ አልፋ ስልት ተመርምሯል፡፡

በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደዚሁ ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊትና በኋላ የነበራቸው የመማር ፍላጎት ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን ለማወቅ የሚያገለግሉ እንደመሆናቸው መጠን በቅድመና ድህረ ትምህርት

ፈተናዎቹ ላይ እንደተደረገው  በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ስልት ተተንትነው ተነጻጽረዋል፡፡ በተጨማሪም በፈተናውና በጽሁፍ መጠይቁ የተሰበሰቡት መጠናዊ መረጃዎች በተመረጠው የመተንተኛ ዘዴ (ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት) ከመተንተናቸው በፊት የፓራሜትሪካዊ ስትስቲክስ እሙኖችን በኮልሞጎሮቭ-ሲሚርኖቭ (Kolmogorov-Smirnov) እና በሻፒሮ ዊልክ (Shapiro-Wilk) ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ትንተና የተደረገው በቡድን ተኮር ውይይት በተገኘው ዓይነታዊ መረጃ ላይ ሲሆን ይህም በፈተናና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች ለማጠናከር ያገለገለ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው በጥናቱ ወቅት ስራ ላይ የዋለው ተጠኚ ተማሪዎች የድህረ ትምህርት ፈተና ከተፈተኑና የጽሁፍ መጠይቅ ከሞሉ በኋላ ሲሆን ውይይቱ የተሳተፉት በጥናቱ የታቀፉት ሰባቱም ተጠኚ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በመወያያነት የቀረቡት ሰባት ጥያቄዎችም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና የመጻፍ ችሎታ ከማስተማሪያ ዘዴው ጋር አያይዘው የዳሰሱ ሲሆኑ በአወያይ መምህርቷ አማካኝነት በምልክት ቋንቋ እየተተረጎሙ ለተጠኚዎች  ቀርበዋል፡፡ ከተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾችም ለትንተና እንዲያመቹ ተደርገው በቅደም ተከተል ከተደራጁ በኋላ በገላጭ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 3.8. የጥናቱ ተለዋዋጮች

በዚህ ጥናት ውስጥ በነጻ ተለዋዋጭነት የሚጠቀሰው መስተጋብራዊ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ሲሆን በጥገኛ ተለዋዋጭነት የሚጠቀሱት ደግሞ የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ናቸው፡፡ በጥገኛ ተለዋዋጩ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ስር ሌሎች ንዑሳን ተለዋዋጮች የሚገኙ ሲሆን እነሱም አረፍተ ነገሮችን መመስረትና እንደገና ማቀናበር፣ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም፣ ጅምር ሀሳቦችን ማጠናቀቅና አጭር ድርሰት መጻፍ የሚሉት ናቸው፡፡

## 3.9. የምርምር ስነ ምግባራዊ ሁኔታዎች

አንድ ጥናታዊ ስራ ሊከተላቸው የሚገቡ ስነ ምግባራዊ መርሆዎች አሉት፡፡ እነዚህም ስነምግባራዊ ህጎች አጥኚም ሆነ ተጠኚዎች ሊገጥማቸው ከሚችል ማንኛውም ስጋት እንደ ዋስትና በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ይህም ጥናት ተግባራዊ በተደረገበት ወቅት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን  ስነ-ምግባራዊነትን ለመከተል ሞክሯል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የዋና ጥናቱን በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት ለማካሄድ ስራ ከመጀመሩ በፊት ጥናቱን ህጋዊ ለማድረግ ተመራማሪዋ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የትብብር ደብዳቤ አጽፋለች፡፡ቀጥሎም ለጥናቱ ወደ ተመረጠው ትምህርት ቤት በማምራት ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ጋር በመወያየት ጥናቱን ማካሄድ እንዲቻል ፍቃድ አግኝታለች፡፡ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርም ትምህርቱን ከምትተገብረው የአማርኛ ቋንቋ መምህርትና ከተጠኚ ተማሪዎች ጋር ተመራማሪዋ የትውውቅና የውይይት ጊዜ እንዲኖራት ሰዓት በማመቻቸትና የጥናቱን ዓላማም ለሌሎች አካላት በማስረዳት ተገቢውን ትብብር እንዲደረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ሌላው ተጠኚ ተማሪዎች በጥናቱ ሂደት ለስምንት ሳምንታት ያህል የመጻፍ ክሂል ልምምድ እንደሚያደርጉና ይህም ለችሎታቸው መሻሻል ትልቅ ጥቅም እንደሚያስገኝላቸው ገለጻ ተደርጎላቸው ከስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያደርጉት በጎ ተሳትፎ ለጥናቱ ያለው ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን አውቀው በፈተናው፣ በጽሁፍ መጠይቁም ሆነ በቡድን ተኮር ውይይቱ የሚሰጡት መረጃ የሌላ አካል ተጽዕኖ ያላረፈበትና የራሳቸውን አቋም ብቻ የሚያንጸባርቁበት ሊሆን እንደሚገባው በዘዴው ተግባሪ መምህርቷ ተገልጾላቸው ቃል እንዲገቡ ተደረጓል፡፡ ይህም ሲሆን በፈተናው የሚያገኙት ውጤት በተመራማሪዋ በኩል በሚስጥር እንደሚያዝ በጽሁፍ መጠይቅ ላይ የሚገልጹት ሀሳብም እንደዚሁ ለጥናቱ ብቻ ተነቦ እንደሚወገድ ተነግሯቸዋል፡፡ ለዚህም ማረጋገጫ እንዲሆናቸው በፈተናውና በጽሁፍ መጠይቁ ወረቀት ላይ ማንነታቸውን የሚገልጽ ምንም አይነት ምልክት እንዳይጽፉ ስምምነት ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎች በጥናቱ ሂደት ሊወጧቸው የሚገባቸውን ሀላፊነቶች በዝርዝር እንዲያውቁ ከማድረግ ባሻገር ምርምሩን በሚያደርገው አካል በኩልም እንዲደረግላቸው የሚፈልጉት የትኛውም ነገር ካለ መጠየቅ እንደሚችሉ ተገልጾላቸው የዋና ጥናቱ ትግበራ የተጀመረ ሲሆን ሂደቱ እንዳይሰናከልም በተመራማሪዋና ትምህርቱን በምትተገብረው መምህርት መካከል ህጋዊ የስራ ስምምነት ተፈጽሟል፡፡በመጨረሻም መረጃዎቹ በተያዘላቸው ጊዜ ለተመራማሪዋ ደርሰው ከግላዊ ስሜትና ሀሳብ ነጻ በሆነ ሁኔታ ተተንትነውና ተብራርተው እንዲቀርቡ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1. ዋና ጥናት

ይህ ንዑስ ርዕስ ጥናቱ ይዟቸው ለተነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎችና አላማዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ መጠናዊና ዓይነታዊ መረጃዎች ተተንትነው የቀረቡበት ሲሆን ከዚህም ባሻገር መረጃዎቹ ከመተንተናቸው አስቀድሞ ስለሚተነተኑበት ዘዴ ለመወሰን መሟላት ስለሚገባቸው የቅድመ ሁኔታ እሙኖች ፍተሻ የተደረገበትና የመጠናዊ መረጃዎች አስተማማኝነት በድጋሜ ተሰልቶ የተገለጸበት ጭምር ነው፡፡

### 4.1.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና በመማር ፍላጎታቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖ መፈተሽ ሲሆን ይዞት የተነሳውን ዓላማም ሆነ ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጓል፡፡

- መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል?
- መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው?

በምዕራፍ አንድና ሶስት ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር ካሉት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች መካከል በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት በሚማሩ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በጥናቱ ቅደም ተከተላዊ አተገባበር ላይ እንደተጠቆመው በተመረጠው ትምህርት ቤት ጥናቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ፈቃድ የማግኘትና ከተጠኚ ተማሪዎች ጋር የመወያየት፣ ዘዴውን ለምትተገብረው መምህርት ስልጠና የመስጠት፣ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናውን እንዲሁም የጽሁፍ መጠይቁን ለሚያስተገብሩ መምህራን ስልጠና የመስጠት ወ.ዘ.ተ ስራዎች ተከናውነው የመጀመሪያውን ዙር መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመቀጠልም በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ እየተተገበረ ለስምንት ሳምንታት የቆየው የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተጠናቀቀው ተጠኚዎች በትምህርቱ መጀመሪያ የተፈተኑትን ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ በተመሳሳይ ሁኔታ በድጋሜ እንዲወስዱ ተደርጎ ነው፡፡ በመጨረሻም ተጠኚዎች በሁለቱ ዙር የተፈተኑት ፈተና በሶስት መምህራን የታረመ ሲሆን

የአራሚዎች የስምምነት ደረጃም በናሙና ጥናቱ ወቅት ከተደረገው በተጨማሪ በክሮንባኽ አልፋ ስሌት በድጋሚ እንዲፈተሽ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተጠኚዎችን የመማር ፍላጎት ለማወቅ በጽሁፍ መጠይቁ የተሰበሰቡት መረጃዎች በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ ተሰልተው አስተማማኝነታቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችና የጽሁፍ መጠይቆች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የትንተና ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ይሁንና መረጃዎቹን በተመረጠው የመተንተኛ ዘዴ ለመተንተን በቅድመ ሁኔታ እሙኖች ላይ ቀድሞ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ ፍተሻው የቅድመ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡ በዚህም የጥናቱ መረጃዎች የመተንተኛ ዘዴው ያስቀመጣቸውን እሙኖች ያልጣሱ ሆነው በመገኘታቸው ትንተና በተመረጠው ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ላይ ተመስርቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

#### 4.1.1.1. የመጠናዊ መረጃዎች የአስተማማኝነት ደረጃ

በዚህ ጥናት ውስጥ በመጠናዊ መረጃነት የሚታወቁት በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ በፈተናዎቹ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ስንመለከት ከጥቅል የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤትና ከንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር ተዘርዝረው የተተነተኑ ሲሆን እነዚህም አረፍተ ነገር መጻፍ፣ አረፍተ ነገር ማዋቀር፣ ጅምር ሀሳብ መጨረስ፣ ስርዓተ ነጥብ መጠቀምና ድርሰት መጻፍ በሚሉት አላባውያን ተከፋፍለው የቀረቡ ናቸው፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ የተሰበሰቡት ደግሞ በአቀራረባቸው የተለያየ መልክ ይኑራቸው እንጂ አላማቸው የተጠኚ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎት መለካት እንደመሆኑ መጠን በንዑሳን ተለዋዋጮች ሳይከፋፈሉ በአንድ ሰንጠረዥ ተጠቃለው የተተነተኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊትና በኋላ በፈተናዎቹ ያስመዘገቧቸው የመጻፍ ክሂል ውጤቶችና በጽሁፍ መጠይቁ አማካኝነት ተነጻጽረው ልዩነታቸው የተገለጸባቸው የትንተና ክፍሎች ወደፊት በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከዚያ አስቀድሞ ግን የአራሚዎች የስምምነት (የአስተማማኝነት) ደረጃ እና የፓራሜትራዊ ስታትስቲክስ እሙኖች የተፈተሹባቸውን ሰንጠረዦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.1. የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ (በክሮንባኽ አልፋ ስሌት)**

| የመለኪያ ዓይነቶች | ቅድመ ትምህር ፈተና | ድህረ ትምህርት ፈተና |
|---|---|---|
| አረፍተ ነገር መጻፍ | 0.935 | 0.975 |
| አረፍተ ነገር እንደገና ማቀናበር | 0.870 | 0.975 |
| ጅምር ሀሳችን አጠናቆ መጻፍ | 0.930 | 0.949 |
| ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም መጻፍ | 0.914 | 0.956 |
| ድርሰት መጻፍ | 0.758 | 0.994 |
| ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት/ችሎታ | 0.991 | 0.993 |

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው አራሚ አንድ፣ አራሚ ሁለትና አራሚ ሶስት በቅድመ ትምህርት ፈተናው በእያንዳንዱ ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች እርማት ላይ ያሳዩት የስምምነት ደረጃ በክሮንባኽ አልፋ ስሌት  በቅደም ተከተል ሲገለጽ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ላይ አረፍተ ነገር በመጻፍ 0.935፣ አረፍተ ነገር በማደራጀት በማቀናበር 0.870፣ ጅምር ሀሳብ በመጨረስ 0.930፣ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም 0.914፣ ድርሰት በመጻፍ 0.758 የሆኑ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን በድህረ ፈተናው ደግሞ  አረፍተ ነገር በመጻፍ 0.975፣ አረፍተ ነገር በማቀናበር 0.975፣ ጅምር ሀሳብ በመጨረስ 0.949፣ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም 0.956፣ ድርሰት በመጻፍ 0.994 እንደዚሁም በቅድመ ትምህርት ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት 0.991 እና በድህረ ትምህርት ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት 0.993 ያህል አሃዞች ተገኝተዋል፡፡ ይህም ውጤት ሶስቱ አራሚዎች ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናውን ባረሙበት ወቅት ለእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ በሰጡት ውጤት ላይ እንብዛም ልዩነት ያላሳዩ መሆኑን የሚያስገነዝብ ወይም በመካከላቸው ጠንካራ ተዛምዶ እንዳለ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይኸውም አራሚዎቹ ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት እኩል የሆነ አልያም አንዱ የሰጠው ውጤት ሲጨምር ወይም ሲቀንስ በተመሳሳይ የሌላኛውም የሚጨምርና የሚቀንስ ሆኖ የተገኘበት ሁኔታ ተንጸባርቋል፡፡

ይህ አይነቱ የውጤት አሰጣጥ ደግሞ ሶስቱ አራሚዎች በማረሚያ መስፈርቱና ከተማሪዎች በሚጠበቀው ምላሽ ዙሪያ ጠንካራ የሆነ የጋራ ግንዛቤና ስምምነት ያላቸው መሆኑን የሚጠቁም ከመሆኑም ባሻገር በሁሉም ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎችና በጥቅል መጻፍ ክሂል የተመዘገቡት የክሮንባኽ አልፋ ውጤቶች ከ0.07 በላይ ሆነው መገኘታቸው በሶስቱ አራሚዎች መካከል ያለው የስምምነት ደረጃ አስተማማኝ እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 4.2 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የአስተማማኝነት ደረጃ (በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ)**

| የጽሁፍ መጠይቅ | ጥያቄዎች | የናሙና ብዛት | **P.Correlation.Coff.**( የፒርሰን ተዛምዶ) | Sig.Level |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ- ትምህርት የመማር ፍላጎት | 22 | 7 | 0.659** | 0.000 |
| ድህረ- ትምህርት የመማር ፍላጎት | 22 | 7 | 0.702** | 0.000 |

*(**) The correlation coefficient is significant at (0.05) level*

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቆች ተጠኚ ተማሪዎች በሰጧቸው ምላሾች መካከል ተዛምዶ መኖሩን ነው፡፡ ይህም በቅድመ የጽሁፍ መጠይቁ 0.659 በድህረ ትምህርት መጠይቁ ደግሞ 0.702 ያህል ውጤት ተገኝቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተጠኚዎች በሁለት ዙር በሰጧቸው ምላሾች መካከል ዝምድና መኖሩን ነው፡፡ ወይም በሌላ አገላለጽ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ፍላጎታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማወቅ በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ወቅት የቀረቡት መጠይቆች 68.05% ያህል በአስተማማኝነት (በወጥነት) ደረጃ የተፈለገውን ባህሪ ለመለካት የቻሉ ሲሆን የስህተት ይሁንታቸው ደግሞ 31.95% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በእርግጥ አስተማማኝነትን በመፈተሽ ሂደት የሚገኘውን ውጤት ከመወሰኛ ነጥቡ የሚያሳንሱ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ Cohen (2000 ፣106) ያለው (2001፣221) ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም የተጠኚዎች ባህሪ አንዱ ሲሆን ይህም በብዙ መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡፡ የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎችም መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው መጠን ካላቸው ዳራዊ ማንነት የተነሳ ማለትም ካለባቸው ቋንቋ ችሎታ ውስንነት አኳያ መጠይቆችን በመሙላትና በማስሞላት በምልክት ቋንቋ የሚደረግላቸውን ትርጉምም ሆነ በጽሁፍ ያለ ሀሳብን ለመረዳት በሚደረገው ጥረት እንዲሁም በሌሎች ተያያዥ ነገሮች ሳቢያ በሚሰጧቸው ምላሾች ላይ ተጽዕኖ ሊያርፍ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማለት ያስፈለገውም የተገኘው ውጤት ምንም እንኳን የአስተማማኝነት መወሰኛ ነጥቡን ያሟላ ቢሆንም ጉዳዩን ከተጠኚ ተማሪዎች ዳራ ጋር አያይዞ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡

በአጠቃላይ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና የጥናቱን መረጃዎች (ተላውጦዎች) ለመተንተን ይቻል ዘንድ መረጃዎቹ ማሟላት የሚኖርባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟሉ በመሆናቸው የትንተናው ሂደትም እንደሚከተለው ሊቀርብ ችሏል፡፡

#### 4.1.1.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ፓራሜትሪካዊ ስታትስቲክስ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ውስጥ በመረጃ መተንተኛነት ተግባር ላይ የዋለው ዘዴ ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲሆን ዘዴውን ለመጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ ጥናቱ በአንድ ተጠኚ ቡድን ላይ ተመስርቶ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችና የጽሁፍ መጠይቆች በሚሰበሰቡ መረጃዎች አማካኝነት የተጠኚዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ንጽጽራዊ ልዩነት ማረጋገጥ ዋነኛ አላማው በመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የመተንተኛ ዘዴውን በጥናቱ ውስጥ ለመጠቀም የጥናቱን አላማ ብቻ መመልከት በቂ አይሆንም፡፡ መተንተኛ ዘዴው የፓራሜትሪካዊ ስትስቲክስ እሙኖችን ሟማላት አለማሟላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከእሙኖች ውስጥ አንዱ የመረጃ ስርጭት ወጥነት (Normality) እንደመሆኑ መጠን በጥናቱ ውስጥ የቀረቡት ጥገኛ ተለዋዋጮች ማለትም ፡- ቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት፣ አረፍተ ነገር መጻፍ፣ አረፍተ ነገር ማቀናበር፣ ጅምር ሀሳብ መጨረስ፣ ስርዓተ ነጥብ መጠቀምና ድርሰት መጻፍ የሚሉት ንዑሳን የመጻፍ ክሂል ችሎታዎች ያላቸው የመረጃ ስርጭት ውጤት እንደሚከተለው ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.3. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የውጤት ስርጭት ወጥነት (Normality)**

| የመለኪያ ዓይነት | ናሙና | Kolomogorov-Smirnov. | | | Shapiro- Willk. | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Statistic | DF. | Sig. | Statistic | DF. | Sig. |
| አረፍተ ነገር መጻፍ | Pre | .298 | 7 | .060 | .840 | 7 | .099 |
| | Post | .298 | 7 | .200* | .913 | 7 | .416 |
| አረፍተ ነገር እንደገና ማዋቀር | Pre | .267 | 7 | .142 | .900 | 7 | .330 |
| | Post | .281 | 7 | .100 | .850 | 7 | .122 |
| ጅምር ሀሳቦችን አጠናቆ መጻፍ | Pre | .307 | 7 | .045 | .842 | 7 | .103 |
| | Post | .208 | 7 | .200* | .968 | 7 | .881 |
| ስርዓተ ነጥቦችን በመጠም መጻፍ | Pre | .119 | 7 | .200* | .968 | 7 | .984 |
| | Post | .237 | 7 | .200* | .871 | 7 | .188 |
| ድርሰት መጻፍ | Pre | .270 | 7 | .132 | .892 | 7 | .287 |
| | Post | .250 | 7 | .200* | .852 | 7 | .128 |
| ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት | Pre | .281 | 7 | .101 | .846 | 7 | .113 |
| | Post | .267 | 7 | .140 | .890 | 7 | .276 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየው በቅድመና በድህረ ፈተናዎቹ ላይ ጥገኛ ተለዋዋጭ ሆነው የቀረቡት አረፍተ ነገር መጻፍ፣ አረፍተ ነገር ማቀናበር፣ ጅምር ሀሳብ መጨረስ፣ ስርዓተ ነጥብ መጠቀም፣ ድርሰት መጻፍና አጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ የሚሉት ሲሆኑ ከእነዚህም አንጻር የተገኙ የኮልሞግሮቭ ሲሚኖርቭ እና የሻፒሮ ዊልክ ውጤቶች ከ0.05 በላይ ሆነው ተመዝግበዋል፡፡ በቅድመና በድህረ ፈተናዎቹ ጥገኛ ተለዋዋጭ ሆነው የቀረቡት የኮልሞግሮቭ ሲሚኖርቭ እና የሻፒሮ ዊልክ ውጤቶች ከ0.05 በላይ የሆነ የጉልህነት ውጤት የሚታይባቸው መሆናቸው ደግሞ የመረጃ ስርጭት ወጥነትን እሙን ማሟላታቸውን ሊያመለክት ችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ ጥናቱ የፓራሜትራዊ ህግን ያሟላ በመሆኑ በጥንድ ናሙና ቲቴስት እያንዳንዱ ጥገኛ ተለዋዋጭ እንዲተነተን ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የተጠኚ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመለካት በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ወቅት በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት መረጃዎች መሰብሰባቸውን ቀደም ሲል ለመግለጽ

ተሞክሯል። እነዚህም መረጃዎች በተመረጠው ዘዴ ከመተንተናቸው በፊት በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ እንደተደረገው የጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የመተንተኛ ዘዴ ወይም የፓራሜትሪካዊ ስትስቲክስ እሙኖች መሟላት አለመሟላታቸውን ለማረጋገጥ የስርጭት ወጥነታቸው እንዲፈተሽ ተደርጓል። ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም ይህንኑ የሚያሳይ ነው።

**ሰንጠረዥ 4.4. የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የውጤት ስርጭት ወጥነት**

**(Normality)**

| የጽሁፍ መጠይቅ | ኮልሞጎሮቭ- ሲሚርኖቭ (Kolmogorov-Smirnov) | | | ሻፒሮ ዊልክ (Shapiro- Wilk) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Df | Sig. | Statistic | Df | Sig. |
| ቅድመትምህርት የመማር ፍላጎት | .132 | 7 | .200* | .982 | 7 | .967 |
| ድህረ ትምህርት የመማር ፍላጎት | .117 | 7 | .200* | .987 | 7 | .986 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት መተንተኛ ዘዴ ፓራሜትሪካዊ ስትስቲክስ እሙኖችን የሚመለክት ሲሆን ይህም ተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ለመለካት በቅድመና በድህረ የጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ስልት መተንተን ስለመቻልን አለመቻላቸው አስቀድሞ የተፈተሸበት ነው። ከእነዚህ አንጻር የተገኙ የኮልሞግሮቭ ሲሚኖርቭ እና የሻፒሮ ዊልክ ውጤቶች ሲታዩ ከ0.05 በላይ ሆነው ተመዝግበዋል። በመሆኑም የጥናቱ መረጃዎች የስርጭት ወጥነታቸው (Normality) ተሰልቶ የፓራሜትራዊ ህግን ያሟሉ ሆነው በመገኘታቸው የተመረጠው ዘዴ ማለትም በጥንድ ናሙና ቲቴስት በጥናቱ ላይ በመተንተኛነት እንዲያገለግል ተደርጓል።

### 4.1.1.3. የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች ውጤት ትንተና

**ሰንጠረዥ 4.5. ጥቅልና ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች ትንተና**

| የመለኪያ ዓይነት | የፈተና ዓይነት | ናሙና | የነጻነት ደረጃ | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የT ዋጋ | የP ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አረፍተ ነገርመጻፍ | ቅድመ | 7 | 6 | 7.27 | 1.83 | 10.92 | 0.000 | 0.78 |
| | ድህረ | | | 14.09 | 3.26 | | | |
| አረፍተነገር እንደገና ማዋቀር | ቅድመ | 7 | | 7.4 | 1.75 | 8.23 | 0.000 | 0.73 |
| | ድህረ | | | 13.3 | 3.05 | | | |
| ጅምር ሀሳቦችን አጠናቆ መጻፍ | ቅድመ | 7 | 6 | 6.56 | 1.9 | 12.33 | 0.000 | 0.80 |
| | ድህረ | | | 12.04 | 2.9 | | | |
| ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም | ቅድመ | 7 | | 7.59 | 2.04 | 9.276 | 0.000 | 0.756 |
| | ድህረ | | | 12.83 | 3.01 | | | |
| ድርሰት መጻፍ | ቅድመ | 7 | 6 | 5.86 | 2.01 | 2.68 | 0.037 | 0.449 |
| | ድህረ | | | 6.93 | 2.76 | | | |
| ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት | ቅድመ | 7 | | 34.10 | 10.63 | 12.44 | 0.000 | 0.80 |
| | ድህረ | | | 62.07 | 13.5 | | | |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ የተካተቱት ንዑሳንና ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ያስመዘገቧቸው ናቸው፡፡ ሰንጠረዡ አጠቃላይ የጥናቱን መረጃዎች የትንተና አወቃቀር ለማሳየት የቀረበ እንጂ ዝርዝር ማብራሪያ የሚሰጥበት አይደለም፡፡ ነገር ግን በሰንጠረዡ ውስጥ የተዘረዘሩት ንዑሳንና ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤቶች ራሳቸውን ችለው በተናጠል መገለጽ ስላለባቸው ትንተናውን በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.6. አረፍተ ነገሮችን የመጻፍ ንዑስ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር**

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ"t" ዋጋ | የ"p" ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ አረፍተ ነገር መጻፍ | 7 | 7.27 | 1.83 | 6 | 10.92 | 0.000 | 0.78 |
| ድህረ አረፍተ ነገር መጻፍ | 7 | 14.09 | 3.26 | | | | |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ላይ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡትን ውጤት የሚያመለክት ነው፡፡ ከትንተናው መገንዘብ የሚቻለው በሁለቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ የሆነ የመጻፍ ችሎታ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ ይኸውም የቅድመ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት 7.27 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት ደግሞ 14.09 ነው፡፡ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነት ደግሞ 6.29 ነው፡፡ ይህም የቅድመ ትምህርት ፈተናው ከድህረ ትምህርት ፈተናው በ6.29 አማካይ ውጤት ያህል ዝቅ ብሎ መገኘቱን ያሳያል፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ መደበኛ ልይይትም የቅድመ ትምህርት ፈተናው 1.83 ሲሆን የድህረ-ፈተናው ደግሞ 3.26 ነው፡፡ይህም የሚያመለክተው ተጠኚዎች በወሰዱት የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል 1.43 ያህል የውጤት ልዩነት መታየቱን ነው፡፡

ነገር ግን የአማካይ ልዩነቱን ብቻ በማየት ጉልህ ልዩነት መጥቷል ማለት በቂ ስለማይሆን ሌሎች ስታትስቲክስ ውጤቶችን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በሰንጠረዡ እንደሰፈረው የተገኘው ውጤት (t(6)= 10.92፣ P=0.000) ሆኗል፡፡ በስሌቱ መሰረትም የቲ ዋጋ ከዜሮ የራቀ መሆኑንና በዚህም የተነሳ በ6 የነጻነት ደረጃ የተገኘው የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች ሆኖ መመዝገቡን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት ደግሞ ተጠኚ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ከሚማሩበት የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ይልቅ በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራቸው በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት እንደፈጠረላቸው ያመለክታል፡፡ሆኖም

የጉልህ ልዩነት ደረጃው ማስተማሪያ ዘዴው ተጽዕኖ እንደፈጠረ ቢያሳይም በምን ያህል ደረጃ ተጽዕኖ መፍጠር እንደቻለ ለማወቅ የዝምድና ጥንካሬ ማስላት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያም ተሰልቶ የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ውጤት 0.78 ሆኗል፡፡ የኢታ ካሬው ውጤት እንደሚመለከተው የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው ጠንካራ መሆኑን ነው፡፡በአጠቃላይ በኢታ ካሬው ውጤት መሰረትነት 78% ያህሉ የተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ እንዲሻሻልና በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተመዘገበውን 7.27 አማካይ ውጤት በድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ወደ 14.09 ከፍ እንዲል ያደረገው ዋነኛው ምክንያት ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማራቸው ነው ወደሚል ሀሳብ ያደርሳል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.7. አረፍተ ነገሮችን የማቀናበር ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር**

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ"t" ዋጋ | የ"p" ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ አረፍተነገር ማደራጀት | 7 | 7.4 | 1.75 | 6 | 8.23 | 0.000 | 0.73 |
| ድህረ አረፍተ ነገር ማደራጀት | 7 | 13.3 | 3.05 | | | | |

በሰንጠረዡ ላይ በቀረበው መረጃ መነሻነት አረፍተ ነገሮችን እንደገና አቀናብሮ በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ያስመዘገቡት ውጤት ልዩነት ማሳየቱን መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኘው አማካይ ውጤት 7.4 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 13.3 የሆነ አማካይ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነትም 5.9 ሲሆን ይህም የድህረ ትመህርት ፈተናው ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በአማካይ በ5.9 ያህል ልቆ መታየቱን ያስገነዝባል፡፡ እንደዚሁም በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለው መደበኛ ልይይት የቅድመ ትምህርት ፈተናው 1.75 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተና ደግሞ 3.05 ነው፡፡ይህም የድህረ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልይይት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልይይት

በ1.3 ከፍ ማለቱን ያመለክታል፡፡ ይሁንና በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ የተገኙትን የአማካይ ውጤት ልዩነቶችን ብቻ በማየት ጉልህ ልዩነት መጥቷል ማለት በቂ ስላልሆነ ሌሎች የማስያ ውጤቶችን ማመሳከር ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ከሰንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው በትንተናው የተገኘው ውጤት (t(6)= 8.23 ፣ P=0.000) ሲሆን ይህም የቲ ዋጋ ከዜሮ የራቀ መሆኑንና በዚህም የተነሳ በ6 የነጻነት ደረጃ የተገኘው የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች ሆኖ መመዝገቡን ያስረዳል፡፡ ይህ ደግሞ ተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማር ከጀመሩ በኋላ ያመጡት የመጻፍ ክሂል ችሎታ በዘዴው ሳይማሩ በፊት ከነበራቸው ጋር ሲነጻጸር ጉልህ ልዩነት ማሳየቱን የሚያመለክት ነው፡፡ ሌላው የጉልህ ልዩነት ደረጃውን በመመልከት የማስተማሪያ ዘዴው በተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ ተጽዕኖ እንደፈጠረ መግለጽ ቢቻልም የተጽዕኖው ደረጃ በምን ያህል መጠን እንዳለም ማወቅ ተገቢ ስለሚሆን የዝምድና ጥንካሬውን ማስላት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያም ተሰልቶ የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ውጤት 0.73 ሲሆን ይህም የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው ጠንካራ መሆኑን የሚያስመለክት ነው፡፡ በአጠቃላይ በኢታ ካሬው ውጤት መሰረትነት 73% ያህሉ የተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ እንዲሻሻልና በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው 13.3 አማካይ ውጤት በቅድመ ትምህርት ፈተናው ከተመዘገበው 7.4 አማካይ ውጤት በ5.9 ውጤት ያህል ልቆ እንደታይ ያደረገው ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማራቸው ምክንያት ነው ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.8. ጅምር ሀሳቦችን የመጨረስ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር**

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ”t” ዋጋ | የ“p” ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ጅምር ሀሳቦችን መጨረስ | 7 | 6.56 | 1.9 | 6 | 12.334 | 0.000 | 0.80 |
| ድህረ ጅምር ሀሳቦችን ማደራጀት | 7 | 12.04 | 2.9 | | | | |

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ የሚያመለክተው በአንቀጽ ውስጥ ጅምር ሀሳቦችን አጠናቆ በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረት ምህርት ፈተናዎች ላይ ያስመዘገቡትን ውጤት ንጽጽራዊ ልይይት ነው፡፡ ትንተናው የሚያሳየው በሁለቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ የሆነ የመጻፍ ችሎታ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ ይኸውም በቅድመ ትምህርት ፈተናው ላይ ተጠኚዎች ያገኙት አማካይ ውጤት 6.56 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 12.04 የሆነ አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያለ አማካይ ውጤት በ5.84 ያህል ልዩነት እንዲያሳይ ሆኗል፡፡ በሌላ አገላለጽ የቅድመ ትምህርት ፈተናው ከድህረ ትምህርት ፈተናው በ5.84 አማካይ ውጤት ያህል ዝቅ ብሎ መገኘቱን ያመለክታል ማለት ነው፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለውን መደበኛ ልይይት ስንመለከት የቅድመ ትምህርት ፈተናው 1.9 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 2.9 ነው፡፡ይህም ተጠኚ ተማሪዎች በወሰዱት የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል 1 ነጥብ ያህል የውጤት ልዩነት መታየቱን የሚያመለክት ነው፡፡

ይሁን እንጂ የአማካይ ልዩነቱ መምጣት ብቻውን ለጉልህ ልዩነት መገኘት በቂ ይሆናል ተብሎ ስለማይታሰብ ሌሎች ስታትስቲክስ ውጤቶችንም ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በሰንጠረዡ ላይ እንደተገለጸው በተጨማሪ ስሌቶች የተገኘው ውጤት (t(6)= 12.334፣ P=0.000) መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህም የቲ ዋጋ ከዜሮ የራቀ መሆኑንና በዚህም የተነሳ በ6 የነጻነት ደረጃ የተገኘው  የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች ሆኖ መመዝገቡን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት ደግሞ ተጠኚ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ከሚማሩበት የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ይልቅ በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራቸው በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት ያመጡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ሆኖም የጉልህ ልዩነት ደረጃው ማስተማሪያ ዘዴው ተጽዕኖ እንደፈጠረ ያሳይ እንጂ የተጽዕኖው ደረጃ በምን ያህል መጠን እንደተቀመጠ ስለማይገልጽ የዝምድና ጥንካሬውን በተጨማሪነት ማስላት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያም ተሰልቶ የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ውጤት  0.80 ሲሆን ይህም የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው ጠንካራ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በጥቅሉ በኢታ ካሬው ውጤት መሰረትነት የ80% ያህሉ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ እንዲሻሻልና በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተመዘገበው 6.56 ዝቅተኛ አማካይ ውጤት በድህረ ትምህርት ፈተናው ከተገኘው 12.04 አማካይ ውጤት ከፍ እንዲል ያደረገው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የተጠኚ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ወይም ፋይዳ የላቀ በመሆኑ ነው ወደሚል ሀሳብ ያደርሳል፡፡

ሰንጠረዥ.4.9. ስርዓተ ነጥቦችን የመጠቀም ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ”t” ዋጋ | የ“p” ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም | 7 | 7.59 | 2.04 | 6 | 9.276 | 0.000 | 0.756 |
| ድህረ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም | 7 | 12.83 | 3.01 | | | | |

በሰንጠረዡ የቀረቡት መረጃዎች በአረፍተ ነገርና በአንቀጽ አደረጃጀት ስርዓት ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው በመጠቀም ረገድ ተጠኚ ተማሪዎች ያላቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተጠኚዎች ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ በወሰዱት የቅድመ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 7.59 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ያመጡት አማካይ ውጤት ደግሞ 12.83 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያለውን አማካይ ውጤት ስንመለከትም የ5.24 ያህል ልዩነት ያሳየ ሲሆን ይህም የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በ5.24 አማካይ ውጤት መሻሻሉን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ የመደበኛ ልይይት እንደዚሁ በቅድመ ፈተናው 2.04 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ያለው ደግሞ 3.01 ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተጠኚዎች በወሰዱት ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል የ0.97 ውጤት ልዩነት መኖሩን ነው፡፡

ይሁንና የአማካይ ልዩነቱን ብቻ በማየት ጉልህ ልዩነት መጥቷል ማለት በቂ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ የስታትስቲክስ ውጤቶችንም ማየት ያስፈልጋል፡፡በመሆኑም በሰንጠረዡ እንደሚታየው በሌሎች ስሌቶች የተገኘው ውጤት (t(6)=9.276፣ P=0.000) ሆኗል፡፡ በስሌቱ መሰረትም የቲ ዋጋ ከዜሮ የራቀ መሆኑንና በዚህም የተነሳ በ6 የነጻነት ደረጃ የተገኘው የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች ሆኖ መመዝገቡን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት ደግሞ ተጠኚ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ከሚማሩበት የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ይልቅ

በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራቸው በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት እንደፈጠረላቸው ያመለክታል። ሆኖም የጉልህ ልዩነት ደረጃው ማስተማሪያ ዘዴው ተጽዕኖ እንደፈጠረ ቢያሳይም በምን ያህል ደረጃ ተጽዕኖ መፍጠር እንደቻለ ለማወቅ የዝምድና ጥንካሬ ማስላት ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያም ተሰልቶ የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ውጤት 0.756 ሆኗል። የኢታ ካሬው ውጤት እንደሚመለክተው የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው ጠንካራ መሆኑን ነው። በአጠቃላይ በኢታ ካሬው ውጤት መሰረትነት 75.6% ያህሉ የተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ እንዲሻሻልና በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተመዘገበውን 7.59 አማካይ ውጤት በድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ወደ 12.83 ከፍ እንዲል ያደረገው ዋነኛው ምክንያት ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማራቸው ነው ወደሚል ሀሳብ ያደርሳል።

**ሰንጠረዥ.4.10. ድርሰት የመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር**

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ"t" ዋጋ | የ"p" ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ድርሰት መጻፍ | 7 | 5.86 | 2.01 | 6 | 2.68 | 0.037 | 0.449 |
| ድህረ ድርሰት መጻፍ | 7 | 6.93 | 2.76 | | | | |

በሰንጠረዡ የቀረቡት መረጃዎች የሚያመለክቱት ድርሰት በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ላይ ያስመዘገቡትን ውጤት ነው። በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የትንተና ዘዴ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ላይ የድርሰት መጻፍ ችሎታቸው ላይ ልዩነቶችን አሳይተዋል። ይኼውም በቅድመ ትምህርት ፈተናው ላይ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 5.86 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ደግሞ 6.93 አማካይ ውጤት ሆኖ ተገኝቷል። በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነት 1.07 ሲሆን ይህም የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በ1.07 አማካይ ውጤት

በልጦ መታየቱን ያስገነዝባል፡፡ ሌላው በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ መደበኛ ልይይት በቅድመ ትምህርት ፈተናው 2.01 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 2.76 ነው፡፡በዚህም በሁለቱ መካከል የ0.76 የውጤት ልዩነት መኖሩን መረዳት ተችሏል፡፡

ይሁንና በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ የታዩ የአማካይ ውጤት ልዩነቶችን ብቻ በመመልከት ጉልህ ልዩነት መጥቷል ብሎ መደምደም ተገቢ ስለማይሆን በሌሎች ስሌቶች የተገኙ ውጤቶችም ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡በመሆኑም ከሰንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው በትንተናው የተገኘው ውጤት (t(6)= 2.68፣ P=0.037) ሲሆን ይህም የቲ ዋጋ ከዜሮ የራቀ መሆኑንና በዚህም የተነሳ በ6 የነጻነት ደረጃ የተገኘው የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች ሆኖ መመዝገቡን ያስረዳል፡፡ ይህ ደግሞ ተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማር ከጀመሩ በኂላ ያሳዩት ድርሰት የመጻፍ ክሂል ችሎታ በዘዴው ሳይማሩ በፊት ከነበራቸው ጋር ሲነጻጸር ጉልህ ልዩነት ማሳየቱን የሚያመለክት ነው፡፡ ሌላው የጉልህ ልዩነት ደረጃውን በመመልከት የማስተማሪያ ዘዴው በተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ ተጽዕኖ እንደፈጠረ መግለጽ ተችሏል፡፡ ነገር ግን የተጽዕኖው ደረጃ በምን ያህል መጠን እንዳለ ማወቅ ጠቃሚ በመሆኑ የዝምድና ጥንካሬውን ማስላት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያም ተሰልቶ የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ውጤት 0.449 ሲሆን ይህም የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው መካከለኛ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በአጠቃላይ በኢታ ካሬው ውጤት መሰረትነት 44.9% ያህሉ የተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ እንዲሻሻልና በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው 6.93 አማካይ ውጤት በቅድመ ትምህርት ፈተናው ከተመዘገበው 5.86 አማካይ ውጤት በ1.07 ውጤት ያህል ልቆ እንደታይ ያደረገው ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማራቸው ምክንያት ነው ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡

በአጠቃላይ በእያንዳንዱ ዝርዝር መለኪያ የተመዘገቡ አማካይ ውጤቶች ማሻሻልን ያሳዩ በመሆናቸው የቲ ዋጋቸው ከዜሮ እንዲርቅ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይኸውም በአረፍተ ነገር መጻፍ 10.9፣ በአረፍተ ነገር ቅንብር 8.23፣ በጅምር ሀሳብ መጨረስ 12.334 በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም 9.276 ፣ በድርሰት መጻፍ 2.68 እንዲሁም በአጠቃላይ ቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት 12.44 የቲ ዋጋዎች ተገኝተዋል፡፡ ከቅድመው ይልቅ በድህረ ፈተናው የተመዘገቡት አማካይ ውጤቶች ከፍ በማለታቸው እንዲሁም የቲ ዋጋቸው ጨምሮ በመታየቱ የተነሳ የጉልህነት ውጤታቸው ከጉልህነት መቁረጫ ነጥቡ (<0.05) በታች የሆኑ ውጤቶች እንዲመዘገቡ

ምክንያት ሆኗል፡፡ይህም በዝርዝር ሲታይ አረፍተ ነገር በመጻፍ፣ አረፍተ ነገር በማቀናበር፣ ስርአተ ነጥብ በመጠቀም፣ ጅምር ሀሳብ በመጨረስ፣ በአጠቃላይ ቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት 0.000 እንዲሁም ድርሰት በመጻፍ 0.037 የጉልህነት ውጤቶች እንደተመዘገቡ ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ ያሳያል፡፡

በየዝርዝር መስፈርቶቹ የተመዘገቡት ውጤቶች ጉልህ ልዩነት ያሳዩ በመሆናቸው፣ የጉልህነት ደረጃቸውን (የዝምድና ጥንካሬያቸውን) መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በአረፍተ ነገር በመጻፍ፣ በአረፍተ ነገር በማቀናበር፣ ጅምር ሀሳብ በመጨረስ፣ ስርዓተ ነጥብ በመጠቀምና በአጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤት የተመዘገቡት የጉልህነት ውጤቶች እንደ የቅደም ተከተላቸው 0.78፣ 0.73፣ 0.80፣ 0.756፣ 0.80 የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ ውጤቶች የተገኙ ሲሆን እነዚህም ውጤቶች ሲተረጎሙ ደረጃቸው ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ድርሰት በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል የተመዘገበው የዝምድና ውጤት 0.449 ሲሆን ይህም ጥንካሬው መካከለኛ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በሌላ አገላለጽ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች አረፍተ ነገር መጻፍ፣ አረፍተ ነገር በማቀናበር፣ ጅምር ሀሳብ በመጨረስ፣ ስርዓተ ነጥብ በመጠቀምና አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ችሎታን በማሻሻል ያለው ውጤታማነት ከፍተኛ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን እንደዚሁም ድርሰት በመጻፍ ረገድ ያለው ፋይዳም መካከለኛ መሆኑን ከተገኘው ውጤት መረዳት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ.4.11. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት ትንተና ንጽጽር**

በዚህ ጥናት ውስጥ አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤት ተደርጎ የተወሰደው ተጠኚ ተማሪዎች ከአረፍተ ነገር አጻጻፍ፣ አረፍተ ነገሮችን ከማደራጀት፣ ጅምር ሀሳቦችን አጠናቆ ከመጻፍ፣ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና ድርሰት ከመጻፍ አንጻር ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች ነው፡፡ የተጠኚዎችን አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤት ለማነጻጸርም የጥንድ ናሙና መተንተኛ ዘዴ ስራ ላይ ውሏል፡፡

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ"t" ዋጋ | የ"p" ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ የመጻፍ ክሂል ጥቅል ውጤት | 7 | 34.10 | 7.8 | 6 | 12.44 | 0.000 | 0.80 |
| ድህረ የመጻፍ ክሂል ጥቅል ውጤት | 7 | 62.7 | 13.5 | | | | |

በሰንጠረዡ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ተጠኚ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲሰላ የተገኘውን ውጤት ነው፡፡ ውጤቱ እንደሚመለክተውም ተማሪዎቹ ከልምምዱ በፊት የነበራቸው የቅድመ ፈተና አማካይ ውጤት 34.10 እንደነበር ነው፡፡ ሆኖም ከልምምዱ በኋላ ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት አማካይ 62.07 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ይልቅ ድህረ ትምህርት ፈተናው በ27.97 አማካይ ልዩነት ልቆ መታየቱን ይመለክታል፡፡ ነገር ግን የአማካይ ልዩነቱን ብቻ በማየት ጉልህ ልዩነት መጥቷል ማለት ስለማይቻል፣ ሌሎች ስታትስቲክስ ውጤቶችን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በተጨማሪ ስሌቶች (t(6) T= 12.44፣ P=0.000) Std. D= (10.63 and 13.5), Eta square = (0.80) የሆኑ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በስሌቱ መሰረትም የቲ ዋጋ ከዜሮ የራቀ መሆኑ፣ በዚህም የተነሳ በ6 የነጻነት ደረጃ የተገኘው የባለሁለት ጫፍ

የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ውጤት ተጠኚ ተማሪዎች ቀደም ሲል ከሚማሩበት የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ይልቅ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት እንደፈጠረ ያመለክታል፡፡ ሆኖም የጉልህ ልዩነት ደረጃው አቀራረቡ ተጽዕኖ እንደፈጠረ ቢያሳይም በምን ያህል ደረጃ ተጽዕኖ መፍጠር እንደቻለ ለማወቅ የዝምድና ጥንካሬ ማስላት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያም ተሰልቶ የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ውጤት 0.80 ሆኗል፡፡ የኢታ ካሬውም ውጤት እንደሚመለክተው የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው ጠንካራ መሆኑን ነው፡፡ ከስሌቱም በመነሳት፣ 80% ያህሉ የተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ እንዲሻሻል ያደረገውና በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው 62.07 አማካይ ውጤት በቅድመ ትምህርት ፈተናው ከተመዘገበው 34.10 አማካይ ውጤት ተሻሽሎ መገኘቱ ወይም የ27.97 ያህል አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማራቸው ምክንያት ነው ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡

#### 4.1.1.4. የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤቶች ትንተና

በጥናቱ ላይ የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ዋነኛ አላማ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በተጠኚ ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ሚያሳድረው ተጽዕኖ ካለ ለማረጋገጥ ሲባል ነው፡፡በመሆኑም በጥናቱ ሂደት የጽሁፍ መጠይቁ በቅድመና ድህረ ትምህርት ትግበራው ወቅት ለተጠኚዎች ቀርቦ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ምላሾችም ተጣርተው፣ተደራጅተውና በመቶኛ ተሰልተው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ በዚህም ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት የነበራቸው የመማር ፍላጎት በማስተማሪያ ዘዴው ከተማሩ በኋላ ካላቸው ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል ልዩነት እንዳሳየ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ሌላው በጽሑፍ መጠይቁ የተካተቱ ጥያቄዎችን አቀራረብ ስንመለከት በሁለት ፈርጅ የተከፈሉና በአሉታዊና በአዎንታዊ የሀሳብ አገላለጽ ስልቶች የተዋቀሩ ሲሆኑ እነዚህም የመጀመሪያዎቹ አስራ አንዱ ጥያቄዎች ተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ከሚቀርብበት መንገድ አንጻር ያላቸው የመማር ፍላጎት ምን እንደሚመስል የሚዳስሱ ናቸው፡፡ቀጣዮቹ አስራ ሁለት ጥያቄዎች ደግሞ የክሂሉን ጠቃሚነት አስመልክቶ ተማሪዎች ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ በተመሳሳይ ቅርጽ የቀረቡ ናቸው፡፡ይሁንና በሁሉም ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች አላማ አድርገው የተነሱት መስተጋብራዊ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ፍላጎት ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን መፈተሽ እንደመሆኑ

መጠን በትንተናው ሂደትም ተጠቃለው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ቀጥሎ ቀረበው ሰንጠረዥም ይህንኑ የሚያመለክት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ.4.12. የጽሑፍ መጠይቅ ውጤቶች ትንተና ንጽጽር**

| የጽሁፍ መጠይቅ | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ"t" ዋጋ | የ"p" ዋጋ | የዝምድና ጥንካሬ (Eta squared) [1] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት የመማር ፍላጎት | 7 | 45.86 | 2.79 | 6 | 15.547 | 0.000 | 0.838 |
| ድህረ ትምህርት የመማር ፍላጎት | 7 | 75.57 | 3.99 | | | | |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያመለክተው ተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ፍላጎታቸውን ለመለካት በቀረበላቸው ቅድመ እና ድኅረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከልምምዱ በፊት በሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ 45.86 አማካይ ውጤት ሲገኝ በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ከተማሩ በኋላ የተገኘው ውጤት ደግሞ 75.57 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቁ ይልቅ የድህረ የጽሑፍ መጠይቁ በ29.71 አማካይ ከፍ ማለቱን የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ ከተገኘውም አማካይ ልዩነት በመነሳት በ6 የነጻነት ደረጃ የተመዘገበው የ"t"ዋጋ 15.547 በመሆን ተመዝግቧል፡፡ ይህም ውጤት ከዜሮ የራቀ መሆኑ ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያመለክታል፡፡ በዚህም የተነሳ የጉልህነት ደረጃው 0.000 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ውጤት ጉልህ ልዩነት መኖሩን የሚጠቁም ነው፡፡ ጉልህ ልዩነት የታየ በመሆኑም የዝምድና ጥንካሬ ደረጃው እንዲሰላ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ 0.838 ሆኗል፡፡ ከተገኘው ውጤት መረዳት የተቻለው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት ለማሻሻል ያለው ሚና ወይም ውጤታማነት ጠንካራ መሆኑን ነው፡፡

#### 4.1.1.5. የአይነታዊ መረጃዎች ውጤት ትንተና

##### 4.1.1.5.1. የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ውጤት ትንተና

የቡድን ተኮር ውይይቱ ዋነኛ ዓላማ መስተጋብራዊ ዘዴ በተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎታቸው ላይ ለውጥ አምጥቷል ወይስ አላመጣም? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይቻል ዘንድ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ ለተገኙት መረጃዎች ማጠናከሪያ የሚሆን ሀሳብ ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡ በጥናቱ ሂደት ለውይይት የቀረቡት ጥያቄዎች ከመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴና ከመጻፍ ክሂል ጋር የተገናኙ ሲሆኑ ቁጥራቸውም ሰባት (7) ነው፡፡ የእያንዳንዱ ጥያቄ የያዘው ዝርዝር ሀሳብም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

1. የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ከመምህራችሁና ከጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በሚከናወኑ በቅደም ተከተላዊ ተግባራት መደራጀቱ፣ በምልክት ቋንቋና በእይታዊ መሳሪያዎች ታግዞ መቅረቡ የመጻፍ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ ረድቷችኋል? እንዴት?
2. በጽህፈት ልምምዱ ወቅት መምህራችሁ ሁሉንም ተግባር ራሳቸው ቢተገብሩት ወይስ እናንተ እንድትሰሩ ቢያደርጓችሁ ትመርጣላችሁ? ለምን?
3. በልምምዳችሁ ወቅት የጽሁፍ ስራችሁን ከጓደኞቻችሁና ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ወይም የእራሳችሁን ስራ በራሳችሁ ገምግማችሁ እንድታሻሽሉ ይረዳችሁ ዘንድ የተዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት ጠቃሚ ነው ትላላችሁ? ለምን?
4. መምህራችሁ የዕለት ተዕለት ለውጣችሁን ለመከታተል የሚሰጡት ተከታታይ ምዘናና ውጤታችሁ እየተመዘገበ የሚቀመጥበት የግል ማህደረ ምዘና መኖሩ የመጻፍ ክሂላችሁን ለማሻሻል ምን ያህል ጠቅሟችኋል?
5. በመጻፍ ክሂል ልምምዳችሁ ወቅት መምህራችሁ ተግባራትን በምልክት ቋንቋ እየተረጎሙ ያቀረቡበት መንገድ ትምህርቱን ለመገንዘብ ረድቷችኋል? ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡
6. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርታችሁን በተማራችሁበት ወቅት የገጠማችሁ ችግር ወይም መሻሻል አለበት የምትሉት ነገር አለ?

7. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራችሁ በመጻፍ ክሂል ችሎታችሁና በመማር ፍላጎታችሁ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

እነዚህ ጥያቄዎች የቀረቡት በጥናቱ ለተሳተፉት ለሰባቱ ተማሪዎች ሲሆን ውይይቱ የተከናወነው ደግሞ ጥናቱ ሊጠናቀቅ ሁለት ቀን ሲቀረው ወይም በስድስተኛው ሳምንት ነው። ሌላው በጥቂዎች ላይ ቅድመ ዝግጅት በማድረግና በምልክት ቋንቋ በመተርጎም ውይይቱን የመራችውም ሆነ ከተማሪዎች የሚሰጡትን ምላሾች ወደ ጽሁፍ በመቀየር የተባበረችው በትምህርት ቤቱ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች አማርኛ ቋንቋን የምታስተምር ሌላ መምህርት ስትሆን ይህም የመረጃውን ታዓማኒነት ለማስጠበቅ ሲባል የተደረገ ነው። ማለትም ውይይቱ የማስተማሪያ ዘዴውን በተገበረችው መምህርት ቢከናወን የሚሰበሰበው መረጃ ምናልባት በግላዊ ስሜት  ተጽዕኖ ስር ሊወደወቅ ይችል ይሆናል የሚል ስጋት ስለነበረ ነው። በአጠቃላይ በውይይቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከጥናቱን ዓላማዎች አንፃር በገላጭ የትንተና ስልት እንደሚከተለው ተተንተነው ቀርበዋል።

**ጥያቄ 1. የመጻፍ  ክሂል ትምህርቱ  ከመምህራችሁና  ከጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በሚከናወኑ በቅደም ተከተላዊ ተግባራት መደራጀቱ፣ በምልክት ቋንቋና በእይታዊ መሳሪያዎች ታግዞ መቅረቡ የመጻፍ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ ረድቷችኋል? እንዴት?**

ይህንን ጥያቄ በተመለከተ በሁሉም የውይይቱ ተሳታፊዎች የተሰጠው መልስ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል። ይሄውም ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎችም ሆነ የትምህርት ወቅቶች የመጻፍ ክሂል ትምህርትን አሁን በቀረበበት መንገድ ማለትም እራሱን ችሎ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶት፣ በልምምድ ጊዜዉም ከማቀድ እስከ መገምገም የሚደርሱ የክንውን ደረጃዎች ተደራጅተውለትና በዚያም ሂደት ዉስጥ ተማሪዎች እርስ በእርስ እየተማማሩና በመምህራቸው አማካኝነት በምልክት ቋንቋና ትምህርቱን በሚያቀሉላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች እየታገዙ ተምረው እንደማያውቁ በመግለጽ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከቀደመው የማስተማሪያ መንገድ የተለየ እንደሆነ አረጋግጠዋል። በሌላ በኩል እንደተጨማሪ የተነሳው ሀሳብ እነዚህ ተማሪዎች አብዛኛውን የክፍል ደረጃዎች እየተማሩ የመጡት መስማት በተሳናቸው መምህራን ሲሆን በዚህም ለክሂል ትምህርቱ ትኩረት ተሰጥቶት ባለመማራቸው ምክንያት አሁን ላይ ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችል ችሎታ ይቅርና ቃላትን አዋቅሮ ነጠላ አረፍተ ነገር የመመስረት አቅም እንዳጡ በመናገር በዕለት ተዕለት ህይወታቸውም በክሂሉ ለመገልገል ብዙ እንደከበዳቸው

በአንክሮ ገልጸዋል፡፡ ይሁንና በመስተጋብራዊ ዘዴ በተማሩበት በዚህ አጭር ቀን የአዳዲስ ቃላትን ጽንሰ ሀሳባዊ ፍቺ ከማወቃቸው ባሻገር በትንሹም ቢሆን ስሜታቸውን የሚገልጽ ጽሁፍ ጽፈው ከጓደኞቻቸው ጋር ሀሳብ መለዋወጥ መቻላቸው እንዳስደሰታቸውና ወደፊትም የመጻፍ ክሂልን ለማወቅ ፍላጎት እንዳደረባቸው ተናግረዋል፡፡

**ጥያቄ 2. በጽህፈት ልምምዱ ወቅት መምህራችሁ ሁሉንም ተግባር ራሳቸው ቢተገብሩት ወይስ እናንተ እንድትሰሩ ቢያደርጓችሁ ትመርጣላችሁ? ለምን?**

ይህ ጥያቄ በቀጥታም ባይሆን የመስተጋብራዊ ዘዴን አስፈላጊነት የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ለጥያቄው ከተሰጡ ምላሾች መካከል ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑትን ብናነሳ በአብዛኞቹ ተወያዮች ዘንድ እንደተነሳው በመስተጋብራዊ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የትምህርት ቆይታ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህራቸው በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የቀረቡ መልመጃዎችን እንዲገለብጡና የገለበጡትንም በዝምታ እንዲያነቡ ከማድረግ ያለፈ የጽሁፍ ልምምድ እንዲያደርጉ፣ተግባራትን በጥንድም ሆነ በቡድን እንዲያከናውኑና እርስ በእርስ እንዲማማሩ እንደማያበረታቷቸው፣ በመልመጃዎችም ላይ ቢሆን መምህራቸው የሚሰጧቸውን መልስ ከመቀበል ባሻገር እንዲመራመሩ፣ ሀሳብ እንዲያፈልቁ፣ እንዲጠይቁ፣ እንዲወያዩና እርስ በእርስ ተገማግመው ምግበ ምላሽ እንዲለዋወጡ የሚያደረጉበት እድል እንዳልተፈጠረላቸው ይህም በቋንቋ በችሎታቸው ላይ ከፍተኛ ውስንነት እንዳስከተለባቸው ልጸዋል፡፡ በመስተጋብራዊ ዘዴ መማር ከጀመሩ ጀምሮ ግን ቀደም ሲል በመምህሩ አዛዥነት ያከናዉኗቸው የነበሩትን ተግባራት ሀላፊነትን በመውሰድ እራሳቸው እንደሚሰሩ፣ባልተለመደ ሁኔታ የጽሁፍ ልምምድም በስፋት እንደሚያደረጉ፣ በእያንዳንዱ የልምምድ ተግባራቸውም ላይ ሂደቱን ለማቅለል በመምህራቸው የሚደረግላቸው ድጋፍና ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉት መስተጋብር ትምህርቱን እንዲወዱት እንዳደረጋቸው፣ ይህም ቀድሞ የነበራቸውን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በአንጻሩ ከፍ እንዳደረገላቸው በውይይቱ አብራርተዋል፡፡ በመሆኑም በመጻፍ ክሂል ልምምድ ወቅት ተግባራት በመምህራን የበላይነት የሚከናወኑ ከሆነና የተማሪዎችም ተሳትፎ ከተገደበ ተማሪዎችን ከጠያቂነትና ከፍላቂነት ወደ ጠባቂነት የሚያሻግር ከመሆኑም በላይ በመካከላቸው ሊኖር የሚገባውን የመቀራረብ፣ የመረዳዳት መንፈስ እንዳያጎለብቱ እንዲሁም ትምህርቱን እንዲሰለቹት እንደሚያደርጋቸው በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡

**ጥያቄ 3. በልምምዳችሁ ወቅት የጽሁፍ ስራችሁን ከጓደኞቻችሁና ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ወይም የእራሳችሁን ስራ በራሳችሁ ገምግማችሁ እንድታሻሽሉ ይረዳችሁ ዘንድ የተዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት ጠቃሚ ነው ትላላችሁ? ለምን?**

በጥያቄ ቁጥር ሶስት ላይ አብዛኞቹ ተወያዮች የሰጡት ምላሽ ተመሳይ ሲሆን ይሄውም በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ሲማሩ ልምምድ ከመጀመራቸው አስቀድሞ በቆይታቸው ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ? እነዚያ ተግባራትም እንዴትና በምን መንገድ እንደሚመዘኑ? ማለትም የጽህፈት ስራቸው በምን አይነት የመመዘኛ መስፈርት እንደሚመዘን? ከእነሱ የሚጠበቀው ሀላፊነት ምን ሊሆን እንደሚገባው? በመምህርታቸው አማካኝነት መገለጹና የሁለትዮሽ ስምምነት መፈጠሩ ትምህርቱ በከፍተኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የመጻፍ ክሂል ትምህርትንም እንደዚህ ራሱን ችሎ በታቀደና በተደራጀ ሁኔታ ቀርቦ መማራቸው በመማር ፍላጎታቸውና በችሎታቸው ላይ መሻሻልን እንዳመጣላቸው ገልጸዋል፡፡ በልምምዳቸው ወቅትም የጽሁፍ ስራቸውን የሚገመግሙበት መንገድ በተለምዶ ከሚሰጠው ጥቅል ፈተና የተለየና በስራቸው ያሳዩትን ድክመትና ጥንካሬ እለት በእለት በራሳቸው፣ በጓደኞቻቸውና በመምህራቸው አማካኝነት እየተመለከቱ የሚያሻሽሉበት እንደሆነና ይህም ለችሎታቸው ማደግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው አብራርተዋል፡፡ ይሁን እንጅ ከውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል ሁለት ተማሪዎች ያነሱትና ሌሎችም የተጋሩት ሀሳብ አለ፡፡ ይህም "የመመዘኛ መስፈርቶቹን በእጃችን ይዘን ጽሁፍን ስንለማመድ የአጻጻፍ ህጎችን የበለጠ እንድናውቅ፣ ስህተቶቻችንንም ነቅሰን እንድናወጣና በጥቅሉ ስርአቱን የጠበቀ ስራ እንድንሰራ እንደሚያደርገን ተረድተናል ነገር ግን ችግር የሆነብን በመስፈርቶቹ ላይ ያለን እውቀት ዝቅተኛ መሆኑ ነው" ብለዋል፡፡ የሰጡትን ሀሳብ ለማብራራት ለምሳሌ ከመስፈርቶቹ መካከል አንዱ ስለሆነው የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ብናነሳ ስርዓተ ነጥብን ጠብቆ ለመጻፍ አስቀድሞ ስለስርዓተ ነጥብ ዓይነቶችና ባህሪያቶቻቸው ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ያላወቁትን ህግ መጠበቅ ይከብዳልና፡፡ በመሆኑም እንደ ተማሪዎቹ አገላለጽ መምህራን መስፈርቱን በልምምዱ ወቅት እንዲጠቀሙባቸው ከማድረጋቸው በፊት ስለአይነታቸው፣ ጠባያቸውና አገባባቸው ወ.ዘ.ተ ሊያስረዷቸው ይገባል ማለት ነው፡፡ በርግጥ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው መጠን ካለባቸው የቋንቋ ችሎታ ውስንነት የተነሳ ሀሳቡ ሚዛን የሚደፋ እንደሆነ የተመራማሪዋም እምነት ነው፡፡

**ጥያቄ 4. መምህራችሁ የዕለት ተዕለት ለውጣችሁን ለመከታተል የሚሰጡት ተከታታይ ምዘናና ውጤታችሁ እየተመዘገበ የሚቀመጥበት የግለ ማህደረ ምዘና መኖሩ የመጻፍ ክሂላችሁን ለማሻሻል ምን ያህል ጠቅሟችኋል?**

በክለሳ ድርሳን ክፍል ለማብራራት እንደተሞከረው ግለ ማህደረ ምዘና (ፖርትፎሊዮ) ተማሪዎች እለት በእለት የሚያከናውኗቸው የመጻፍ ክሂል ተግባራት እየተመዘኑ የሚከማቹበት የውጤት ሰነድ ነው፡፡ ይህንንም በማስመልከት በተራ ቁጥር አራት ላይ ለተነሳው ሀሳብ ተወያዮች የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት በጽሀፈት ልምምዱ ሂደት በተከታታይ የሚሰጧቸው ምዘናዎችና ምገበ ምላሾች በችሎታቸው ላይ ከፍተኛ መሻሻል እንዲያመጡ ከማስቻሉም በላይ በስራዎቻቸው ሚያስመዘግቡት ውጤትም በማህደረ ምዘና (ፖርትፎሊዮ) ተሰንዶ መቀመጡ በመምህራቸውና በእነርሱ መካከል በመተማመን ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያደርግና ሀላፊነት ተሰምቷቸው የላቀ ስራ እንዲሰሩ ሚያበረታታ እንደሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት በነበረው የትምህርት ቆይታቸው ይህ ዓይነቱ አተገባበር አጋጥሟቸው ባለማወቁ በአጠቃቀሙ ረገድ ጥቂት ግርታን እንደፈጠረባቸው ሁለት የሚሆኑ ተማሪዎች ሀሳብ ዘንዝረዋል፡፡ በጥቅሉ ግን በምዘና ሂደቱ ላይ ሁሉም ተወያዮች በጋራ ያንጸባረቁት ሀሳብ ከዚህ በፊት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጡ ምዘናዎች በአጭር ጊዜ ታርመው በሚመለሱ በምርጫ ሰጪ፣ በአዛምድ፣ በክፍት ቦታ መሙላትና በሌሎች አቀራረቦች በመሆናቸው የተማሪዎችን ጊዜ፣ አቅምና ሀላፊነት እንባዛም የሚጠይቁ አልነበሩም፡፡ ይህም በጥናቱ ሂደት ከነበረው የመማር ማስተማር ተግባር ጋር ሲነጻጸር በብዙ መልኩ የሚለይ ሆኖ ማግኘታቸውን የገለጹ ሲሆን በተለይ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለብቻው ተለይቶ በተግባራዊ ልምድና ምዘናዎች መቅረቡ ምዘናውና ውጤቶችም እንድአፍታ ታይተው የሚወገዱ ሳይሆኑ ተሰንደው በመቀመጥ ሂደታዊ መሻሻላቸውን የሚያሳዩ መሆናቸው ለችሎታቸው መሻሻል አዎንታዊ ሚና እንዳለው በስፋት አንስተዋል፡፡

**ጥያቄ 5. በመጻፍ ክሂል ልምምዳችሁ ወቅት መምህራችሁ ተግባራትን በምልክት ቋንቋ እየተረጎሙ ያቀረቡበት መንገድ ጠቅሟችኋል? ምክንያታችሁን አቅርቡ፡፡**

በዚህ ጥያቄ ላይ ከሁሉም ተወያዮች የተነሱት ሀሳቦች ሙሉ ለሙሉ የማስተማሪያ ዘዴው ደጋፊ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል በነበራቸው የትምህርት ወቅት የመጻፍ ክሂልንም ሆነ ሌሎች

የቋንቋውን ክፍሎች በማስተማር ረገድ መምህራን የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ዘዴ የመማር ሁኔታቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑን የገለጹ ሲሆን በተለይ ደግሞ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ማስተማር አድካሚና ጊዜ የሚፈጅ ሆኖ ስለሚታሰብ በመምህራ እየተዘለለ በተማሪዎችም እየተረሳ ያለ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ይሁንና በመስተጋብራዊ ዘዴ የቀረበላቸው የመጻፍ ክሂል ትምህርት የምልክት ቋንቋ ትርጎማን እንደ አንድ የማስተማሪያ ስልት  የሚጠቀም መሆኑ በሚገባቸውና በቀላል መንገድ ተግባራትን እንዲያከናውኑ እንዳገዛቸው በመግለጽ ወደፊትም ትምህርቱ በዚህ መልኩ ቢቀጥል ያለችግር በክሂሉ መገልገል የሚያስችላቸውን ችሎታ እንደሚያስገኝላቸው ተናግረዋል፡፡

**ጥያቄ ቁጥር 6. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርታችሁን በተማራችሁበት ወቅት የገጠማችሁ ችግር ወይም መሻሻል አለበት የምትሉት ነገር አለ?**

በጥናቱ ትግበራ ሂደት ተጠኚዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን ሲማሩ የገጠሟቸውን ችግሮች እንዲገልጹ ተጠየቁት ጥያቄ ላይ የተወሰኑ ሀሳቦችን አንስተዋል፡፡ ተወያዮች እንደ ችግር ካነሱት አንዱ በመጻፍ ልምምዱ ወቅት የማስተማሪያ ዘዴው የሚከተላቸውን መርሆዎች ለመተግበር የሚያደርጉት ጥረት ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑ ሌሎች የትምህርቱ ክፍሎች ለመከወን የስራ ጫና የፈጠረባቸው መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማስተማሪያ ዘዴው በአብዛኛው በእርስ በርስ መማማር ላይ ባተኮሩ አቀራረቦች መመስረቱ በራስ የመተማመን ስሜታቸውንና የጋራ ግንኙነታቸውን በእጅጉ የጨመረላቸው እንደሆነ በእጅጉ የሚያምኑ ቢሆኑም በትምህርቱ ሂደት ግን በግላቸው ያከናወኗቸው የነበሩ ተግባራትን በምልክት ቋንቋና ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለመምህራቸውና ለጓደኞቻቸው እንዲገልጹና አስተያየቶችን እንዲለዋወጡ በሚደረጉበት ጊዜ አብሯቸው ከቆየው የፍርሀት ስሜት የተነሳ ጭንቀት ይገጥማቸው እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡

**ጥያቄ ቁጥር 7. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራችሁ በመጻፍ ክሂል ችሎታችሁና በመማር ፍላጎታችሁ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?**

መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመማር ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ያለውን ፋይዳ አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኚዎች የሰጡትን ምላሽ በቅደም ተከል ስንመለከት ሁሉም ተማሪዎች በጋራ ያነሷቸው የማስተማሪያ ዘዴው የመጻፍ ክሂል ተግባራትን ከመማር ሁኔታቸው ጋር በተስማሙ የእይታ መሳሪያዎች፣ ተዳሳሽ ቁሶችና አካላዊ ትዕይንቶች

ታጅበው እንዲቀርቡ እድል መስጠቱ ትምህርቱን ቀላል፣ተጨባጭና አይረሴ እንዲሆን ያደረገው መሆኑን በዋናነት ገልጸል፡፡ ሌላው በማስተማሪያ ዘዴው ያለው የምዘና አሰጣጥ ተከታታይ፣ መስፈርት ተኮርና አሳታፊ መሆኑ ስህተቶቻቸውን በቀላሉ እያረሙ እንዲሄዱና ከቀን ወደ ቀን አቅማቸውን እንዲገነቡ እንዳስቻላቸው ጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት አሰጣጡ ከቀላል ተግባራት ማለትም ከሆሄያትና ከቃላት ጀምሮ እስከ አረፍ ተነገሮች፣አንቀጾችና ድርሰት የመጻፍ ልምምዶች ላይ መድረሱ በእያንዳንዱ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ያለባቸውን ክፍተት እንዲሞሉ የረዳቸው መሆኑን ጭምር ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ አማካኝነት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ልምምዱ በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ተሳልጦ መቅረቡ ችሎታቸውን ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ለመማር ይፈሩትና ይጠሉት የነበረውን ስሜት አስወግዶ ትምህርቱን እንዲወዱት፣እንዲፈልጉትና አቅልለው እንዲመለከቱት እድል የፈጠረላቸው መሆኑን በውይይቱ ላይ በስፋት ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በአጠቃላይ በውይይቱ ተጠኚዎች የሰጡት ምላሽ በአጭሩ ሲገለጽ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ቀደም ሲል ከሚማሩበት መንገድ የተለየ እንደሆነና በዚህም ዘዴ በመማራቸው ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ማደጉን፣ የመጻፍ ክሂል ችሎታቸው በአንጻሩ መሻሻሉን፣ እንደዚሁም በራስ የመተማመን ስሜታቸው መጨመሩን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር አብሮ የመስራትና የመረዳዳት ባህላቸውን ያዳበረላቸውና ሀላፊነት እንዴት መወጣት እንደሚቻል ያስተማራቸው ከመሆኑም ባሻገር ለመጻፍ ክሂል ትምህርት የነበራቸውን አስተሳሰብ ከፍ እንዲል እንዳደረገላቸው ከምላሻቸው መገንዘብ ተችሏል::

### 4.1.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በዚህ ክፍል በዋና ጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን ጥናቱ አስቀድሞ ካስቀመጣቸው መላምቶችና ተመራማሪዎች ከደረሱባቸው ግኝቶች ጋር በማስተሳሰር ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ ማብራሪያው በጥናቱ ውስጥ ዋነኛ ትኩረት በሆኑት የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መገለጫዎች ማለትም አረፍተ ነገር በመጻፍ፣ በማደራጀት፣ ጀምር ሀሳቦችን በማጠናቀቅ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀምና ድርሰት በመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች እንዲሁም በተጠኚዎች የመጻፍ ትምህርት የመማር ፍላጎት አኳያ በተገኙ ውጤቶች ላይ በመመስረት የሚቀርብ ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ተጠናቅሯል፡፡

#### 4.1.2.1. ከንዑስ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች አንጻር

##### 4.1.2.1.1. አረፍተ ነገር መጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል

አረፍተ ነገር መጻፍ በዚህ ጥናት ውስጥ አንዱ የመገምገሚያ መስፈርት ሆኖ የቀረበ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም ተማሪዎች በመነሻነት በቀረቡላቸው ቃላት ላይ ተመርኩዘው የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን ምን ያህል መጻፍ ችለዋል በሚለው ላይ ነው፡፡ከዚህ አኳያ ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ አረፍተ ነገር የመጻፍ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ሲታይ የቅድመ አረፍተ ነገር መጻፍ ፈተና ውጤታቸው በድህረ አረፍተ ነገር መጻፍ ፈተና ካስመዘገቡት የተሻለ አማካይ ውጤት ታይቶበታል፡፡ ይኸውም የቅድመ ፈተናው አማካይ ውጤት 7.27 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት ደግሞ 14.09 ነው፡፡ የ "ቲ" ዋጋ 10.92 ፣ የ"P" ዋጋ 0.000፣ የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.78 ሆኖ መገኘቱ በተጠኚዎች አረፍተ ነገር የመጻፍ ንዑስ ክሂል ላይ ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያስረዳል፡፡ ከተፈጠረው ጉልህ ልዩነት በመነሳት የተገኘው የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ ሲታይ ዝምድናው ጠንካራ እንደሆነ አመላክቷል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት ከቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ውጤት ጋር በማስተሳሰር ደጋፊ ወይም የልዩነት ሀሳቦችን ማንሳት የውጤት ማብራሪያው አንዱ አካል መሆኑ ቢታወቅም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀገራዊ ጥናቶችን ማግኘት ባለመቻሉ ውጤቶችን ማነጻጸር አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በሁሉም መልኩ በማሻሻል ረገድ ያለው ጠቀሜታ የላቀ መሆኑን ከእንግሊዝኛ ቋንቋ አንጻር ፈትሸው ከገለጹ የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች ከነ Elizabeth (2009)፣ Wolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Wolbers et,al (2016) እና Wolbers et,al (2012) የጥናት ግኝት ጋር ዝምድና ያለው ውጤት እንደተገኘ መረዳት ተችሏል፡፡

##### 4.1.2.1.2.. አረፍተ ነገር እንደገና የማቀናበር ንዑስ የመጻፍ ክሂል

አረፍተ ነገሮችን እንደገና ማዋቀር የሚለው መስፈርት በንዑስ የመጻፍ ክሂል አላባውያንነት ከተካተቱት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ ንዑስ የመጻፍ ክሂል በአማርኛ ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት መሰረት በትክክለኛው መንገድ ያልተደራጁና በአሰላለፋቸው የተፋለሱ ሀሳቦችን የተሸከሙ ቃላትንና ሀረጋትን ተገቢውን የአጻጻፍ ስርዓት በመከተል እንደገና አደራጅቶ በጽሑፍ ማስፈርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ እሳቤ በመነሳት ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ የአረፍተ ነገር ማደራጀት ፈተናዎች ላይ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች በጥንድ

ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ በማስላት ልዩነቱን ለማነጻጸር ተችሏል፡፡ በዚህም የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኘው አማካይ ውጤት 7.4 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 13.3 የሆነ አማካይ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነትም 5.9 ሲሆን ይህም የድህረ ትመህርት ፈተናው ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በአማካይ በ5.9 ያህል ልቆ መታየቱን ያስገነዝባል፡፡ ይህም በሁለቱ ፈተናዎች ላይ ተጠኚ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ የውጤት ልዩነት ማምጣት መቻላቸውን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም የ"t" ዋጋ 8.23 የ"P" ዋጋ 0.000 የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.73 ሆኗል፡፡ ይህ ውጤት የተገኘበት ዋነኛ ምክንያት ተጠኚዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ስለታላሚውን ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት በተደጋጋሚ በመማራቸውና በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መርህ መሰረትም ሰፊ ልምምዶችን በማድረጋቸው ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለ፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማጎልበት ረገድ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ያለው አዎንታዊ ተጽዕኖ ጉልህ እንደሆነ ያረጋገጠ በመሆኑ ከWolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Elizabeth (2009)፣ Wolbers et,al (2016) እና Wolbers et,al (2012) የጥናት ውጤቶች ጋር ተቃርኖ የሌለው እንዲሆን አድርጎታል፡፡

#### 4.1.2.1.3. ጅምር ሀሳቦችን የመጨረስ ንዑስ የመጻፍ ክሂል

ጥሩ ድርሰት ለመጻፍ በጥሩ ሀሳቦች የተገነቡ አንቀጾች የማስፈለጋቸውን ያህል ጥሩ አንቀጾችን ለመገንባትም እንደዚሁ የቃላት፣ የሀረጋትና የአረፍተ ነገሮች አገባብና አደረጃጀት እውቀት አስፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡ ሀሳቦችን በመገንባት ሂደት ተፈላጊውን ቃል፣ ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር በተገቢው አውድ መጠቀም የሚጻፈው ድርሰት የተዋጣለት እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም የተጠኚ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለመለካት አንዱ መመዘኛ ተደርጎ የተወሰደው ጅምር ሀሳቦችን የማጠናቀቅ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ከተቀመጠው መስፈርት አንጻር ተጠኚዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ያስመዘገቡትን ውጤት ተተንትኖ ልዩነቱ ተመላክቷል፡፡ ይኼም በቅድመ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 6.56 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 12.04 የሆነ አማካይ ውጤት አምጥተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያለ አማካይ ውጤት በ5.84 ያህል ልዩነት እንዲታይ ሆኗል፡፡ እንዲሁም የ"t" ዋጋ 12.334፣ የ"P" ዋጋ 0.000 ፣የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.780 ሆኖ ተመዝገቧ፡፡ ይህም ተጠኚዎች በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ከመማራቸው በፊት የነበራቸው የመጻፍ ችሎታ ከትምህርቱ በኋላ እንደተሻሻለ

የሚያመለክት ነው፡፡ምክንያቱም በጥናቱ ትግበራ ሂደት በነበረው የመጻፍ ክሂል ልምምድ ተማሪዎች ሀሳባቸው በተጓደሉ የአንቀጽ/ የድርሰት ናሙናዎች ላይ ተንተርሰው የራሳቸውን ሀሳብ እየጨመሩና እየቀነሱ በመጻፍ ስራቸው ተነባቢ እስኪሆን ድረስ ያከናወኗቸው ተግባራት ውጤቶች ይሆናሉ የሚል አስተሳሰብ በመኖሩ ነው፡፡

ከተቀመጠው መስፈርት አኳያ የተገኘውን ውጤት ከቀደምት ተዛማጅ የጥናት ውጤቶች ጋር ለማነጻጸር ሁኔታዎች ባይፈቅዱም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለውን አዎንታዊ ሚና ካመለከቱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የውጪ ጥናቶች Elizabeth (2009)፣ Wolbers et,al (2016) Wolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014) እና Wolbers et,al (2012) ጋር ቅርበት አለው፡፡

**4.1.2.1.4. ስርዓተ ነጥቦችን የመጠቀም ንዑስ የመጻፍ ክሂል**

በአራተኛ ደረጃነት የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መመዘኛ ሆኖ የቀረበው የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ሲሆን የዚህ መስፈርት ዋነኛ ትኩረትም ተማሪዎች በሚጽፏቸው አረፍተ ነገሮች፣ አንቀጾችና ድርሰቶች ውስጥ የታላሚው ቋንቋ የአጻጻፍ ስርዓት በሚፈቅደው መልኩ ስርዓተ ነጥቦችን እንዴት ባለ ሁኔታ ይጠቀማሉ? የሚለውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንንም ንዑስ የመጻፍ ክሂል ለመለካት በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ላይ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ተግባራት የቀረቡ ሲሆን ተግባራቱም በሶስቱ አራሚዎች ታርመው የተገኘው ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የትንተና ዘዴ እንዲሰላ ተደርጎ ልዩነቱን ማሳየት ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ተጠኚዎች በቅድመ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ንዑስ የመጻፍ ክሂል ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 7.59 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ያመጡት አማካይ ውጤት ደግሞ 12.83 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ መካከል ያለውን አማካይ ውጤት ስንመለከትም የ5.24 ያህል ልዩነት ያሳየ ሲሆን ይህም የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በ5.24 አማካይ ውጤት መሻሻሉን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ሌላው የ"t" ዋጋ 9.276፣ የ"P" ዋጋ 0.000፣ የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.756 ሆኖ ተመዝግቧ፡፡ ይህም ተጠኚዎች በመስተጋብራዊ ዘዴ ከተማሩ በኋላ ያመጡት የመጻፍ ክሂል ችሎታ በዘዴው ከመማራቸው በፊት ከነበራቸው ጋር ሲነጻጸር ጉልህ ልዩነት ማሳየት መቻሉን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ለተማሪዎች የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም መሻሻል ዋነኛው ምክንያት መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ለዚህም ማረጋገጫ በጥናቱ ትግበራ ሂደት የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መርህ መሰረትነት ሲቀርብ የስርዓተ ነጥብ ዓይነቶችን፣ ቅርጻቸውንና አገባባቸውን በተመለከተ

በጥልቀት የሚያስረዱ ልምምዶች በአስረጅ ምሳሌዎችና በእይታዊ መሳሪያዎች ታግዘው መካሄድ መቻላቸው ነው፡፡

ከስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም አኳያ የተገኘውን ውጤት ከቀደምት የጥናት ውጤቶች ጋር በቀጥታ ማነጻጸር ባይቻልም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸውን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በጠቅሉ ካመለከቱ የውጪ ጥናቶች Elizabeth (2009)፣ Wolbers et,al (2016) Wolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014) እና Wolbers et,al (2012) ጋር ተዛማጅነት ያለው ውጤት በጥናቱ እንደተገኘ መገንዘብ ይቻላል፡፡

#### 4.1.2.1.5. ድርሰት የመጻፍ ንዑስ ክሂል

በመጨረሻ ደረጃ ከንዑስ መጻፍ ክሂሎች አንጻር መመዘኛ ሆኖ የቀረበው አጭር ድርሰት መጻፍ የሚል ነው፡፡ ይህ የመጻፍ አላባ በዚህ ጥናት ውስጥ እንደ አንድ ንዑስ ክሂልነት ተካትቶ ይቅረብ እንጅ በብዙ ጥናቶች ዘንድ ግን ብቸኛ የመጻፍ ክሂል መመዘኛ ተደርጎ እንደሚተገበር ከድርሳናት መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና በጥናቱ የተለያዩ ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎችን በመመዘን ረገድ ድርሰት የመጻፍ ተግባርን በብቸኝነት መርጦ መጠቀሙ የጥናቱን አላማ እንደማምከን ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የታቀፉትን ተማሪዎች ብንመለከት እንኳን የድርሰት አጻጻፍ መርሆዎችን ተምረው ድርሰት እንዲጽፉ የሚታዘዙበት አቅም ወይም ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም፡፡ የመጻፍ ክሂል ችግራቸው የሚጀምረው ሆሄያትን በትክክለኛው ቅርጻቸው ከመጻፍ ነው፡፡ ጥናቱ የሚካሄድበት አላማም የተማሪዎች የመጻፍ ችግር ምን እንደሆነ ለይቶ መፍትሄ መፈለግ እስከሆነ ድረስ ትምህርቱም ሆነ ምዘናው በዋናነት ማተኮር ያለበት በችግሮቻቸው ዙሪያ ነው፡፡ በዚህም በጥናቱ ትግበራ ሂደት በነበረው የመማር ማስተማር ክንውን ችግሮችን ለመቅረፍ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ ድርሰት መጻፍ  የችሎታው አንዱ መመዘኛ መስፈርት ሆኖ ሲቀርብ ትኩረት የነበረው በተመረጡ ርዕሶች መነሻነት ተጠኚዎች ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አንቀጾች አንድ አጭር ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ላይ ተማሪዎች የጻፏቸው ድርሰቶች ታርመው የውጤት ንጽጽር ተደርጎባቸዋል፡፡ ንጽጽሩ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የትንተና ዘዴ የተሰላ ሲሆን በተገኙት ውጤቶች መካከልም ጉልህ የሆነ ልዩነት እንዳለ ተረጋግጧል፡፡

ይኼውም በቅድመ ትምህርት ፈተናው ላይ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 5.83 ሲሆን በድህረ ትምህርት ፈተናው ላይ ደግሞ 6.93 አማካይ ውጤት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች

መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነት 1.07 ሲሆን ይህም የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በ1.07 አማካይ ውጤት በልጦ መታየቱን ያስገነዝባል፡፡ በተጨማሪም የ"t" ዋጋ 2.68፣ የ"P" ዋጋ 0.037፣ የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.449 ሆኗል፡፡ ይህም ተጠኚ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ ያላቸው ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በዘዴው ከመማራቸው በፊት ከነበራቸው ጋር ሲነጻጸር ተሻሽሎ መገኘቱን የሚያመለክት ሲሆን የተተኳሪ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድም  መስተጋብራዊ ዘዴ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ሊያሳይ በሚያስችል ሁኔታ Wolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Elizabeth (2009)፣ Wolbers et,al (2016) እና Wolbers et,al (2012) ካጠኗቸው ጥናቶች ጋር ተዛማጅነት ያለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

#### 4.1.2.2. ከጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር

ከተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አኳያ ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚገቡ አምስት ዝርዝር ዓላማዎች (አረፍተ ነገር መጻፍ፣ ማደራጀት፣ ጅምር ሀሳብ ማጠናቀቅ፣ ስርዓተ ነጥብ መጠቀምና ድርሰት መጻፍ) የሚሉት የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም በአማራጭና በአልቦ መላምትነት ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ በጥናቱ ውስጥ አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤት ተደርጎ የተወሰደው ተጠኚ ተማሪዎች በሁሉም ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች ማለትም አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ፣ አረፍተ ነገሮችን እንደገና በማዋቀናበር፣ ጅምር ሀሳቦችን አጠናቆ በመጻፍ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀምና ድርሰት በመጻፍና ያስመዘገቧቸው የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች ሲሆኑ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የትንተና ዘዴ ተሰልተው ልዩነታቸውም በጥቅል እንዲነጻጸር ተደጓል፡፡

ጥናቱ በአንድ የሙከራ ቡድን ላይ ተመስርቶ የተከናወነ በመሆኑ የተጠኚዎች ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤት የተነጻጸረው በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ማለትም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ባስመዘገቧቸው ውጤቶች መካከል ነው፡፡ በተደረገው ንጽጽር መሰረትም በሁለቱ ፈተናዎች መካከል በተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ውጤት ላይ ልዩነቶች ተንጸባርቀዋል፡፡ የውጤት ሰንጠረዦቹ እንዳመለከቱት ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመ ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 34.10 ሲሆን በድህረ ፈተናው ላይ ደግሞ 62.07 ነው፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለ የአማካይ ውጤት ልዩነትም 27.97 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሌላው የ "t" ዋጋ ፣12.44፣ የ"P" ዋጋ 0.000፣ የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.80 በመሆን የተመዘገበ ሲሆን ይህ ደግሞ መስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ መዳበር አዎንታዊ

ተጽዕኖ ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብና በውጪ ሀገር እንግሊዝኛ ቋንቋን መሰረት አድርገው ከተጠኑ የWolbers (2008)፣ Dostal and Wolbers (2014)፣ Elizabeth (2009)፣ Wolbers et,al (2016) እና Wolbers et,al (2012) ጥናቶችም ጋር የሚዛመድ ውጤት መገኘቱን የሚያመላክት ነው። ከተገኘው ውጤት በመነሳት ጥናቱ ካስቀመጣቸው መላምቶች መካከል "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት የለም" የሚለው አልቦ መላምት ውድቅ ሆኖ በተቃራኒው "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት አለ" የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነትን ሊያገኝ ችሏል።

#### 4.1.2.3. ከተማሪዎች የመማር ፍላጎት አንጻር

ይህ ጥናት ከሚመልሳቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የተጠኚዎችን የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት ሲሆን ይህንንም ለመመለስ በጥናቱ ትግበራ ሂደት ተጠኚ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። በዚህም የተገኘው ምላሽ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ እንዲነጻጸር የተደረገ ሲሆን ንጽጽሩም በፈተናዎቹ ላይ እንደተደረገው የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ ምላሽ ከድህረ የጽሁፍ መጠይቁ ምላሽ ጋር በሚኖረው ልዩነት ላይ ተኮረ ነው። በዚህም ተጠኚዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ ዘዴ ከመማራቸው አስቀድሞ ከሞሉት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ በዘዴው ከተማሩ በኋላ ከተገኘው ጋር ሲነጻጸር በሁለቱ ምላሾች መካከል ጉልህ ልዩነት ተንጸባርቋል። የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየውም ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ ያስመዘገቡት የፍላጎት ማሳያ አማካይ ውጤት 45.86 ሲሆን በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ከተማሩ በኋላ የተገኘው ውጤት ደግሞ 75.57 ነው። ይህም ውጤት ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቁ ይልቅ የድህረ የጽሑፍ መጠይቁ በ29.71 አማካይ ከፍ ማለቱን ያመለክታል። ሌላው የ"t" ዋጋ 15.547፣ የ"P" ዋጋ 0.000፣ የዝምድና ጥንካሬው ደግሞ 0.838 ሆኗል። ይህም ተጠኚዎች በተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል ትምህርት የመማር ፍላጎትና ከትምህርቱ በኋላ ባሳዩት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን የሚያስገነዝብ ነው። ወይም በሌላ አገላለጽ ተጠኚዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት ለመጻፍ ክሂል ትምህርት የነበራቸው ዝቅተኛ ፍላጎት በዘዴው ከተማሩ በኋላ ጨምሮ(ከፍ ብሎ) ተገኝቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መሰረታዊ የአተገባበር መርሆዎቹ ተጠብቀውና አስፈላጊ የትምህርት

ግብዓቶች ተሟልተው መተግበር ከቻለ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያለው መሆኑን ነው፡፡

ከተገኘው ውጤት በመነሳትም ጥናቱ ካስቀመጣቸው መላምቶች "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎትና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት የለም" የሚለው አልቦ ውድቅ ሆኖ በአንጻሩ "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎትና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት አለ" የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በሌላ በኩል በቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘው የዓይነታዊ መረጃ ውጤትም በፈተናና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውን ውጤት የሚደግፍ ሆኗል፡፡ የትንተና ውጤቱ እንደሚያመለክተው ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን መማራቸው በክሂሉ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ችሎታና ፍላጎት እንዲያጎለብቱ የረዳቸው ከመሆኑም ባሻገር በመካከላቸው የመቀራረብ፣ የመረዳዳት መንፈስ እንዲኖርና በራስ የመተማመን ስሜታቸው እንዲዳብር ጭምር እድል የፈጠረላቸው መሆኑን ከገላጭ የትንተናው ውጤት መገንዘብ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ፣ የመፍትሄ ሀሳቦችና ወደፊት ሊጠኑ የሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች

## 5.1. ማጠቃለያ

*በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ለማሻሻል የሚኖረውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው። ይህንንም መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችንና ሁለት አበይት መላምቶች በአማራጭና በአልቦ መላምትነት ያስቀመጠ ሲሆን የጥናቱ  የመጀመሪያው መሰረታዊ ጥያቄ "መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት በተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ የሚያሳድረው  ተጽዕኖ አለ? የተጽዕኖው ዓይነት ምንድን ነው?" የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ በመመለስ ረገድም ጥናቱ አማራጭና አልቦ መላምቶችን ነድፏል። አማራጭ መላምቱ "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት አለ" የሚል ሲሆን አልቦ መላምቱ ደግሞ  "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት የለም" የሚል ነው።*

*ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ "መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በተጠኚ ተማሪዎች የመማር ፍላጎት  ላይ ያመጣው ለውጥ አለ? ለውጡስ ምን ይመስላል?" የሚል ሲሆን መሰረታዊ ጥያቄውን በመመለስ ረገድም እንደዚሁ አልቦና አማራጭ መላምቶች አስቀድመው ተቀምጠዋል።አልቦ መላምቱ "ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመማር ፍላጎትና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት የለም" የሚል ሲሆን አማራጭ መላምቱ ደግሞ"ተጠኚ ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በነበራቸው የመማር ፍላጎትና በዘዴው ከተማሩ በኋላ ባላቸው መካከል ልዩነት አለ" የሚል ነው። ከላይ በተጠቀሱት መልኩ ጥናቱ ሊመልሳቸው ያቀዳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎችም ሆነ ሊያረጋግጥ የተነበያቸውን መላምቶች ለማሳካት በሂደቱ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል።*

*በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ጥናት ሙከራዊ  እንደመሆኑ መጠን ወደ ትግበራ ከመገባቱ አስቀድሞ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት፣ በተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴ መሰረትነት*

የማስተማሪያ ግብዓቶችን ማጠናቀር፣ ዘዴውን ለምትተገብረው መምህርት ማሰልጠኛ የሚሆን ረቂቅ መንደፍና ሌሎች በርከት ያሉ የቅድመ ትግበራ ክንውኖች አስፈላጊ በመሆናቸው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ ቀጥሎም ለመረጃ መሰብበሰቢያነት፣ ለማስተማሪያና ለማሰልጠኛ የተዘጋጁት ግብዓቶች ትክክለኛነታቸውን አስተማማኝነታቸው በአማካሪዎችና በባለሞያዎች እንዲሁም በናሙና ጥናት ተፈትሾ ከተረጋገጠ በኋላ በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ አማካኝነት በተመረጠው አልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት ዋናው ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ ጥናቱ ያተኮረበት የክፍል ደረጃ ሰባተኛ ክፍል ሲሆን ይህም በአላማ ተኮር ተመርጧል፡፡ በክፍል ደረጃው የሚማሩት ተተኳሪ ተማሪዎች እንደዚሁ ሰባት ሲሆኑ ካላቸው የቁጥር ውስንነት የተነሳም ጠቅላይ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ሁሉም በጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በመቀጠል ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ ፈተናዎቹን እንዲፈትኑና የጽሁፍ መጠይቁን እንዲያስሞሉ የተመረጡትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የተሰጣቸው ሁለት መምህራን የቅድመ ትምህርት ፈተናውንና የጽሁፍ መጠይቁን ትግበራ በሚገባ አከናውነው የመጀመሪያው ዙር መረጃ ስብሰባ ስራ ተጠናቋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የማስተማሪያ ዘዴውን (መስተጋብራዊ ዘዴ) እንድትተገብር አስቀድሞ የሰባት ቀን ስልጠና በተመራማሪዋ በኩል የተሰጣት መምህርት የማስተማር ስራውን እንድትጀምር ተደርጎ ትምህርቱ ለስምንስት ተከታታይ ሳምንታት እየተሰጠ ከቆየ በኋላ በቅድመ ትምህርቱ ወቅት ተጠኚዎች ቀርቦላቸው የነበረውን ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ  በሁለቱ መምህራን በድጋሜ እንዲፈተኑና እንዲሞሉ ተደርጎ እንዲሁም የድህረ ትምህርት የቡድን ተኮር ውይይቱን በተመረጠችው መምህርት አማካኝነት በማከናውን በትምህርት ቤት ያለው የዋናው ጥናት ስራ ተቋጭቷል፡፡

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለጸው የፈተናው አላማ የተጠኚዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለመለካት፣ የጽሁፍ መጠይቁ ደግሞ የመማር ፍላጎታቸውን መጠን ለማወቅ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች የተጠኚዎችን የመጻፍ ችሎታና የመማር ፍላጎት በሚያረጋግጡ መልኩ በጥንድ ናሙና ቲ- ቴስት ስልት ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን በዚህም የጥናቱን መሰረታዊ አላማዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹን በጥንድ ናሙና-ቴስት ዘዴ ለመተንተን ሲታሰብም አስቀድሞ የተሰራው በዘዴው ለመጠቀም የሚያስችሉ የቅድመ ሁኔታ መርሆዎችን የመፈተሽ ተግባር ሲሆን በዚህም በፈተናዎቹና በጽሁፍ መጠይቁ የተሰበሰቡት መረጃዎች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የመተንተኛ ዘዴ ቢተነተኑ በቅድመ ሁኔታው

ላይ የተቀመጠውን ህግ የማይጥሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል (ሰንጠረዥ4.2.ን ይመልከቱ)፡፡

በዚህም መሰረት በትንተናው የተገኙትን ውጤቶች ስንመለከት በቅድመ ትምህርት ፈተናው ላይ ተጠኚ ተማሪዎች ከጥቅል የመጻፍ ውጤትም ሆነ ከንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች አንጻር ያስመዘገቡት ውጤት ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን ከሀያ ሁለት (22) የመጻፍ ትምህርት ተግባራት ወይም ከስምንት ሳምንታት የጽህፈት ልምምዶች በኋላ በድህረ ትምህርት ፈተናው ያሳዩት የችሎታ መሻሻል ግን ከፍተኛ የሚባል እንደነበር መረዳት ይቻላል (ሰንጠረዥ4.10.ን ይመልከቱ)፡፡

በሌላ በኩል ከተጠኚ ተማሪዎች የመማር ፍላጎት አንጻር ጥናቱ ይዞት የተነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ  በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ወቅት ተጠኚዎች የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጎ መረጃዎች መሰብሰባቸውን ከፍ ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ከትንተና ውጤት መመልከት የተቻለው የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ በመስተጋብራዊ ዘዴ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ተጠኚ ተማሪዎች ለትምህርቱ የነበራቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑንና በማስተማሪያ ዘዴው ከተማሩ በኋላም በፊት የነበራቸው የመማር ፍላጎት ተለውጦና ከፍ ብሎ መገኘቱን ነው (ሰንጠረዥ4.11.ን ይመልከቱ)፡፡ በተጨማሪም በቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘው የአይነታዊ የመረጃ ትንተና ውጤትም በፈተናዎቹና በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውን ውጤት የሚደግፍ ሆኖ ነው የተገኘው፡፡ በአጠቃላይ በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት ከተገኙት የመጠናዊና የአይነታዊ መረጃዎች የትንተና ውጤት መገንዘብ የተቻለው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሻሻልም ሆነ የመማር ፍላጎታቸውን በማሳደግ  ረገድ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ያለው አዎንታዊ ፋይዳ (አስተዋጽኦ) የላቀ መሆኑን ነው፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

ጥናቱ ይዟቸው ከተነሳቸው አላማዎችና ካሳካው ግብ በመነሳት  የተለያዩ መደምደሚያዎች ላይ መደረስ ተችሏል፡፡ቀደም ባሉት ክፍሎች በስፋት ለመዳሰስ እንደተሞከረው በዚህ ጥናት ውስጥ በተፈታሽነት የቀረበው መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ በውጤትና ሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ቅንጅታዊ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ ለማስተማር ሲባል በፈለቀ አዲስ አስተሳሰብ የተፈጠረ ነው፡፡ የማስተማሪያ ዘዴው ለመጻፍ ችሎታ መጎልበት መማር ማስተማሩ ውጤትን ብቻ ግብ ሳያደርግ በሂደት ላይ ተመስርቶ መከናወን አለበት ብሎ የሚያምን ወይም ተግባራት የሰዋስው ህጋጋትን ከማሳወቅ ባሻገር በተግባቦት ላይ አተኩረው እንዲቀርቡ የሚፈልግ ነው፡፡ በመሆኑም በመጻፍ ክሂል ትምህርቱ የሚከናወኑ ተግባራት ቅድመ ጽህፈት፣

ጊዜ ጽህፈትና ድህረ ጽህፈት በተባሉ ሶስት ደረጃዎች ውስጥ እንዲያልፉ ይደረጋል። በእነዚህ ደረጃዎችም ተማሪዎች ስለሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ እንዲያቅዱ፣ ሀሳብ እንዲያሰባስቡና እንዲያደራጁ፣ የመጀመሪያ ረቂቃቸውን እንዲጽፉ፣ እዲከልሱና እንዲያርሙ እድል ይሰጣቸዋል። በሂደቱ መጨረሻም የታላሚውን ቋንቋ የሰዋስው አጠቃቀም ህግጋትና የአጻጻፍ ስርዓት የጠበቀ ትክክለኛ የጽሁፍ ስራ ከተማሪዎች ይጠበቃል። እነዚህና መሰል መርሆዎች የማስተማሪያ ዘዴው አይነተኛ ባህሪያት እንደመሆናቸው መጠን በጥናቱ ትግበራ ወቅትም በነበረው የመማር ማስተማር ሂደት ተግባራዊ ሆነዋል። በተለይ ደግሞ የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች መስማት የተሳናቸው ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ትምህርቱን ከመማር ሁኔታቸው ጋር አስማምቶ ለማቅረብ በተደረገው ጥረት በርካታ ተግባራት የተከናወኑና ተግባራቱም ያስገኙት ጥቅም ቀላል የማይባል ነው።በዚህም መሰረት፦

- የመጻፍ ክሂል ትምህርት በተለያዩ ደረጃዎች ተከፋፍለው በሚቀርቡና በተከታታይ በሚመዘኑ የጽህፈት ተግባራት ላይ ተመስርቶ መቅረቡ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎትን በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው እንደሆነ ከድምዳሜ ላይ ተደርሷል።ምክንያቱም በማስተማሪያ ዘዴው ትግበራ ወቅት እንደተስተዋለው በእያንዳንዱ የጽህፈት ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ከአንድ ጫፍ ተነስተው ወደ ሌላ ጫፍ የሚደርሱ ብቻ ሳይሆኑ ወደ ኋላና ወደፊት በመመላለስ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚያሳልጡ ናቸው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ተደጋጋሚ ልምምዶችን እንዲያደርጉ፣ እርስ በእርስ እንዲወያዩ፣ ስህተታቸውን በጥልቀት እንዲመለከቱና እንዲያርሙ እንዲሁም በክሂሉ በትክክል መጠቀም እስከሚችሉ ድረስ በርካታ የጽህፈት ተግባራትን እንዲያከናውኑ ሰፊ እድል የሰጣቸው ሆኖ ተገኝቷል።
- በመስተጋብራዊ ዘዴ አማካኝነት መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚቀርብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ስኬታማ የሚሆነው ከተግባራት አደረጃጀቱ ባለፈ ተግባራቱ በሚቀርቡበት የማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይም በእጅጉ መጨነቅ ሲችል እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል። እንደሚታወቀው የመጻፍ ክሂል ችሎታ የሚጀምረው የሚጻፍበትን ቋንቋ ሆሄ በትክክለኛ ቅርጽ ከመጻፍ ነው።ቀጥሎም ቃላትን መገንባት፣ አረፍተ ነገሮችን ማዋቀር፣ አንቀጾችን ማደራጀትና ድርሰትን ወደ መጻፍ እያደገ ይሄዳል።መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በማስተማር ረገድም እነዚህን አላባውያን ያሟላ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማግኘት በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊተኮርባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህ መካከል ደግሞ የማስተማሪያ መሳሪያዎች

አቅርቦት አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ጽህፈትን መረዳት ወይም መከወን የሚችሉት እንደሌሎች ተማሪዎች ቀለል ባሉ ምሳሌዎችና መመሪያዎች ሳይሆን በእይታዊ፣ በተዳሳሽ መሳሪያዎችና በተግባራዊ ትዕይንቶች ወ.ዘ.ተ አማካኝነት ነው፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ ተማሪዎች አጋዥ የማስተማሪያ ቁሶች ያላቸውን ዋጋ በቀላሉ ማየት አይገባም፡፡ በአጠቃላይ ለእያንዳንዱ የጽህፈት ይዘት/ተግባር በሚፈልገው መጠን የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ ሂደቱን ቀልጣፋና ቀላል፣ትምህርቱን አይረሴ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር በተማሪዎች ላይ የሚኖረውን የስራ ጫና በብዙ እጥፍ በመቀነስ ለትምህርቱ ፍላጎት እንዲኖራቸው የሚያደርግ እንደሆነ በጥናቱ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ ተችሏል፡፡

- በመስተጋብዊ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ የሚመዘነው የትምህርት ማጠናቀቂያ ጊዜያት ተጠብቀው በሚዘጋጁ ፈተናዎች ሳይሆን ዕለት በዕለት በሚከናወኑ የጽህፈት ተግባራት መሰረትነት ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ የጎላ ድርሻ ያለው ሆኖ እንደተገኘ በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ምክንያቱም በጥናቱ ሂደት ተማሪዎች የሚያከናውኑት እያንዳንዱ የጽህፈት ተግባር በተደጋጋሚ ይገመገምና አስተያየት ይሰጥበት የነበረው በመምህራቸው፣ በራሳቸውና በጓደኞቻቸው ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች ስህተታቸውን በፍጥነት ተረድተውና አርመው ስርዓታዊና ትክክለኛ ጽሁፍ እንዲጽፉ የረዳቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የእርስ በእርስ የመማማር መንፈሳቸው እንዲጎለብት፣ በራስ የመተማመን ስሜታቸው እንዲጨምርና ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ከፍ እንዲል ያገዛቸው መሆኑን ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡
- መስተጋብራዊ ዘዴ  በውጤትና ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል አቀራረቦች ቅንጅታዊ የማስተማሪያ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ የሚተገበር እንደመሆኑ መጠን የቋንቋውን መዋቅር ከማሳወቅ ባሻገር ለአጠቃቀሙ/ ለተግባቦት ትኩረት ይሰጣል፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች የአጻጻፍ ስርዓቱን ያሟላ አረፍተ ነገር፣ አንቀጽና ድርሰት እንጽፉ እድል የፈጠረላቸው እንደሆነ ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳቦች

እንደሚታወቀው የመጻፍ ክሂል ትምህርት በቀላሉ የሚለመድ ሳይሆን በበርካታ ሂደታዊ ልምምዶች ውስጥ አልፎ የሚገኝ ነው። ይህንን ችሎታ ለማምጣትም በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። ከእነዚህ ጥረቶች መካከል ደግሞ አንዱ ትምህርቱን ሊያቀሉ የሚችሉና ከተማሪዎች የመማር ሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባር ላይ ማዋል ነው። ምክንያቱም ለአንድ የትምህርት አላማ መሳካትና መክሸፍ የማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና የላቀ በመሆኑ ነው። ከዚሁ ጋር በተገናኘም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መቀነስ ይቻል ዘንድ በተለይ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው በውጪ ተመራማሪዎች ተጠንቶ የተመሰከረለትን መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ፋይዳ ከአማርኛ ቋንቋና በሀገራችን ካለው የትምህርት አሰጣጥ ወይም አውድ አንጻር በዚህ ጥናት መመርመር ተችሏል። በተካሄደው ሙከራዊ ጥናትም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት ከማሳደግ አንጻር ያለው ፋይዳ አዎንታዊ ሆኖ ተገኝቷል። በጥናቱ ውጤት መሰረትም ተመራማሪዋ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ቢደረጉ ይጠቅሙ ይሆናል በሚል እሳቤ ቀጥሎ የቀረቡትን የመፍትሄ ሀሳቦች ለመምህራን፣ ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች፣ ለትምህርት የምልከታ ባለሞያዎችና ለተማሪ ቤተሰቦች ለማጋራት አቅርባለች።

- ለመምህራን፡- ከሁሉም በላይ የመማር ማስተማር ሂደቱን በበላይነት የሚዘውሩት መምህራን እንደሆኑ ይታወቃል። ይህ ሲባል የትምህርቱን ይዘቶች/ ተግባራት በማደራጀት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት፣ የምዘና ስልቶችን በመንደፍ፣ የመማሪያ ክፍሎችን በማመቻቸትና ሌሎች ተግባራትን በማከናወን ትልቅ ሀላፊነት አለባቸው። ወይም በሌላ አገላለጽ የማስተማሪያ ዘዴውን የሚተገብሩ ዋነኛ አካላት መምህራን ናቸው። በመሆኑም መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ያለውን አዎንታዊ ፋይዳ ተገንዝበው በተቻለ መጠን ዘዴው በሚከተላቸው የአተገባበር መርሆዎች መሰረት የመጻፍ ክሂል ትምህርቱን ቢያቀርቡ ለተማሪዎች የውጤት ከፍታ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

- ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች፦ እንደሚታወቀው የመርሃ ትምህርት አዘጋጆች አንድን ትምህርት ለተመረጠው የክፍል ደረጃና በዚያው ውስጥ ይማራሉ ተብለው ለሚታሰቡ ተማሪዎች በሚመጥን መልኩ በበላይነት የሚቀርጹ ናቸው፡፡ በመሆኑም የማስተማሪያ ግብዓቶችን በሚያዘጋጁበት ወቅት አነስተኛ ቁጥር ያላቸውንና ልዩ ድጋፍ የሚሹ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ባይዘነጉና በተለይ የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ችሎታቸውን ለማሳደግ ጥቅም እንዳለው በዚህ ጥናት የተረጋገጠውን መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ እንዲካተት ቢያደርጉ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተማሪዎች ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ችግር ይቀርፋል የሚል እምነት አለ፡፡ መስተጋብራዊ ዘዴ ለጽህፈት ማስተማሪያነት ሲቀርብ ተግባራት፣ ማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ ምዘናዎች ወ.ዘ.ተ እንዴት ሆነው መዘጋጀት፣ መደራጀትና መቅረብ እንደሚገባቸው በጥናቱ ትግበራ ወቅት በማስተማሪያነት ባገለገሉት ማለማመጃ ተግባራት ውስጥ በከፊል ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ተግባራት ጋር የተዛመዱ አቀራረቦችን በመማሪያ መጽሀፎች ውስጥ በግብዓትነት ቢጠቀሙ ትምህርቱ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች አሳታፊ እንዲሆን ከማስቻሉም ባሻገር እንደ አጠቃላይ ሲታሰብም ለክሂሉ ማደግ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡
- ለትምህርት ምልከታ ባለሞያዎች፦ በስነ ትምህርት አተገባበር ስርዓት ሂደት ውስጥ የሚታቀዱ አላማዎች ግባቸውን የሚመቱት በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት የሚጠበቅባቸውን የስራ ሀላፊነት መወጣት ሲችሉ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ የትምህርት ባለድርሻ አካላት መካከል የምልከታ ባለሞያዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከስራቸው አንዱም በየትምህርት ቤቶች እየተዘዋወሩ የትምህርት አተገባበሮችን መገምገምና ድጋፍ መስጠት እንደመሆኑ መጠን በየጊዜው በጥናት እየተፈተሹ ከሚወጡ አዳዲስ የትምህርት አስተሳሰቦች ጋር በመተዋወቅ ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና ለአስተዳደሮች ስልጠናዎች ተደራሽ የሚሆኑበትን መንገድ ቢያመቻቹ ለአጠቃላይ የትምህርት አቀራረቦች መጎልበት የላቀ ጥቅም ይኖረዋል የሚል እምነት አለ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ባለሞያዎች በተለይ መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች አንጻር የሚታየውን የትምህርት አሰጣጥ ክፍተትና ልጆቹ የሚፈልጉትን ልዩ እገዛ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂላቸውን በማሳደግ ረገድ ጥቅም እንዳለው በዚህ ጥናት ተፈትሾ የተረጋገጠውን መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን

እንዲጠቀሙበት ስልጠና እንዲሰጥ የማመቻቸት ስራ ቢሰሩ ለተማሪዎችም ሆነ ለክሂሉ መበልጸግ የጎላ ድርሻ አለው፡፡

- ለተማሪ ቤተሰቦች፦ መስማት የተሳናቸውም ሆነ ሌሎች ተማሪዎች በትምህርት ቤት ከሚያሳልፉት ጊዜ ይልቅ በቤት ውስጥ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚኖራቸው እጅግ ይሰፋል፡፡ የቤተሰቦች ትልቁ የስራ ድርሻም ልጆቻቸውን በጥናት ማበረታትና የትምህርት ግብዓቶችን በማቅረብ መደገፍ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች ከሌሎች በላቀ ሁኔታ ትልቅ ሀላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፦ ከመማሪያ ክፍል ውጪ የሚሰጧቸውን የመጻፍ ክሂል ተግባራት በምልክት ቋንቋ እየተረጎሙ ማለማመድ፣ ትምህርቱን ሊያቀሉላቸው የሚችሉ እይታዊ ማስተማሪዎችን፣ ተዳሳሽ ቁሶችንና የመሳሰሉትን ግብዓቶች በማቅረብ መርዳትና በክሂሉ መጠቀም የሚያስችሏቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት በራስ የመተማመን ስሜታቸውን መገንባ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 5.4. ወደፊት ሊጠኑ የሚገቡ የትኩረት አቅጣጫዎች

የማስተማሪያ ዘዴዎችን አቀናጅቶ የማስተማር አዲስ ስነ ትምህርታዊ አስተሳሰብ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያነት መጠቀም በውጪዎች ዘንድ እየተለመደ የመጣና ፋይዳውም በጥናቶች እየተፈተሸ ያለ መሆኑን ከድርሳናት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ጥናት የተካሄደበት ትልቁ አላማም የተተኳሪ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎት በማሳደግ ረገድ መስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ ያለውን ፋይዳ ከአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አንጻር ፈትሾ ትምህርቱን የሚደግፍ አስተዋጽኦ ማበርከት ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ጥናት ለመዳሰስ የተሞከረው ጥቂት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች የመማር ሁኔታና ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንጻር ወደፊት ሊጠኑ የሚገባቸው ሌሎች መሰረታዊ ነጥቦችም ያሉ መሆናቸውን አጥኚዋ ስለምታምን ቀጥሎ ባጭሩ የተቀመጡ ሀሳቦችን በትኩረት አቅጣጫነት አቅርባለች፡፡

- በዚህ ጥናት ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል የመማር ሁኔታ በመፈተሽ ሂደት ሌሎች የቋንቋው ክሂል ውሱንነቶችም እንዳሉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይኼውም ተማሪዎች ካለባቸው የመጻፍ ክሂል ችግር ባሻገር የማንበብ ክሂል ክፍተትም አለባቸው፡፡ እንደዚሁም ለንግግር ተግባቦት በሚገለገሉበት የምልክት ቋንቋና በአማርኛ

ቋንቋ የጽሁፍ ስርዓት መካከል ያለው የአጠቃቀም ልዩነት የመጻፍ ክሂል ችሎታቸው እንዳያድግ በእጅጉ እየጎዳው እንዳለ መመልከት ተችሏል፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ጉዳዮችም ሰፊ ጥናትና መፍትሄ የሚፈልጉ በመሆናቸው በተቻለ መጠን የተመራማሪዎች ትኩረት ቢሆኑ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመማር ችግሮች መቅረፍ ይቻላል፡፡

- መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያነት ለማዋል የሚያስችል የሙከራ ጥናት ውጤት ማግኘት የዚህ ጥናት አላማና ግብ ሆኖ የተከናወነ ቢሆንም የማስተማሪያ ዘዴውን ለሌሎች ክሂሎች፣ቋንቋዎችና ተማሪዎች ማስተማሪያነት መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ ስለሚታመን በተጠቆሙት ሀሳቦች ዙሪያ ተጨማሪ ጥናቶች ቢደረጉ ለመማር ማስተማር ሂደቱ መጎልበት የጎላ ድርሻ ይኖረዋል፡፡
- በዚህ ጥናት መዳሰስ የተቻለው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከማስተማሪያ ዘዴ አኳያ የሚደርስበትን ተጽዕኖ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በጥናቱ ሂደት የተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል ችግሮች ከሌሎች ተለዋዋጮችም አንጻር የሚመነጩ እንደሆነ መመልከት ተችሏል፡፡ለምሳሌ፡- ከምልክት ቋንቋው የአጠቃቀም ስርዓት፣ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከተካተቱ የማስተማሪያ ይዘቶች/ተግባራት፣ ከመምህራን አቅም ውሱንነት ማለትም በሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት የሰለጠኑና የተመረቁ አለመሆን ወ.ዘ.ተ ችግሮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በተማሪዎች ላይ ለሚታየው የመጻፍ ችሎታ ችግር የሚኖራቸው ተጽዕኖ ቀላል አይሆንም፡፡ ለዚህም የናሙና ጥናቱ በ2011 ዓ.ም. በተከናወነበት ቪክትሪ እና የዋናው ጥናት በ2013 ዓ.ም በተደረገበት አልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት የነበረውን የመምህራን ምደባ ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ተመርቀው የሚያስተምሩ መምህራን እጅግ ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ በአብዛኞቹ የክፍል ደረጃዎች ትምህርቱ የሚሸፈነው በሌሎች የትምህርት አይነቶች በተመረቁና የምልክት ቋንቋን በትክክል በማያውቁ እንዲሁም መስማት በተሳናቸው መምህራን መሆኑን ተመራማሪዋ ተመልክታለች፡፡ ይህ ዓይነቱ የትምህርት አተገባበርም በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመማር ፍላጎታቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የሚያመጣው ችግር እንዳለ በመገመት ተያያዥ ጥናቶች ቢደረጉ ጠቃሚ ይሆናል የሚል እምነት አለ፡፡

- በመጨረሻም በዚህ ጥናት የመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ ፋይዳ ሲመረመር ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ ሰባተኛ ሲሆን ተጠኚ ተማሪዎች ደግሞ መስማት የተሳናቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከድርሳናት መረዳት እንደሚቻለው የማስተማሪያ ዘዴው በዝቅተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የትምህርት እርከኖች ለሚገኙ ተማሪዎችም ሆነ የመጀመሪያ ወይም የሁለተኛ ቋንቋቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ መዳበር ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ ስለሆነም የማስተማሪያ ዘዴውን ተጽዕኖ ከሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ወደፊት በጥናት መፈተሽ ቢቻል ጠቃሚ ስነ ትምህርታዊ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሰሎሞን ተሰማ፡፡ (1987)፡፡ የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ባየ ይማም፡፡ (2000)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

አለማየሁ ተመስገን፡፡ (2007)፡፡ በጽህፈት ትምህርት ወቅት ሰዋስዋዊ ስህተቶች ላይ የሚሰጥ እርማት ለክሂሉ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፡፡ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

አማረ ተሾመ፡፡ (2010)፡፡ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ፡፡ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

እንዳለ ተስፋዬ፡፡ (1992)፡፡ በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሚና፡፡ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)

ክፍሌ ሀብተማርያም፡፡ (1986)፡፡ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ፡፡ ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ጌታሁን አማረ፡፡ (1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ* ፡፡ አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት ፡፡

ግርማ ገብሬ፡፡ (1990)፡፡ በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብራዊ ስልት (Intractive Approach) ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፡፡ ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)

የሽጥላ መንግስቴ፡፡ (2008)፡፡ በጽሕፈት አውድ የሚቀርብ ሰዋስዉ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አካዳሚያዊ ጽሕፈት ሰዋስዋዊ ስልጠት በማሻሻል ያለው ውጤት፡፡ በዘጠነኛ ክፍል የቤንችና የካፊኛ አፍፊት ተማሪዎች ማሳያነት፡፡ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2001)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡ አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Adrienne Anne, R,. (2012). *An analysis of Teaching methods for Children who are Deaf with multiple Disabilities.* Washington University.MA thesis.

Almayehu Teklemariam. (2003). Communication Experiences of Pre-Language Deaf Students in the Special Classes the Ethiopian. *Journal of Education*.Vol.XXIIINo.1.

Andreas.K, (1999). Interest Motivation and Learning an Educational, Psychological Perspective European. *Journal of Psychology of Education*.Vol.XIV.

Anne Gray L, (2003). *Academic and Social integration of Deaf and Hard- of-Hearing Students.*In a Carnbridg Research .Uk University.

Aragon, J. Claudia, E., Mira, b., Dalia, C., Rodrigue, z., Cloria, S, (2013). *an analysis of the Writing skill difficulties of the English Composition Students the Foreign Language.* Department of the University of Elsatvador.

Brand, A. (1991). Social cognition, emotions, and the psychology of writing. *Journal of Advanced Composition,* 11, 395-407.

Brookes, A. & Grundy, P, (1990). *Writing for Study purposes*. Cambridge: Cambridge University Press.

Brown, H.D. (2001). *Teaching by Principles: An Interactive Approach to Language Pedagogy*. Longman: San Francisco State University.

Button K, Johnson, M.J., & Furgerson, P, (1996). *Interactive Writing in aprimary class room.* Boston: Pearson Education.

Byrne, D,.(1988). *Teaching Writing Skills*. Long man: Hong Kong: Group Ltd.

Byrne, D,.(1996). *Teaching Writing Skill*. Longman: hand books for Language Teachers.

Campbell, D, Cook, J (2006). *Experimental and quasi-experimental designs for research.* London: Longman ltd.

Cazden, C.,(1996). *Selective Traditions Reading of Vygotsky in Writing Pedagogy*.In Hicks (Ed). Discourse, Learning and Schooling. (PP 165-185) Cambridge: Cambridge University Press.

Celece-Muricia,M,.(1985). Making Informed Decisions about the role of Grammar in Language.*In TESOL Newsletter*.V.29.No,1

Christen, S., Lori. L,. Nicholas.G,. (2013). Critical Needs of Student who are Deaf Hard of hearing. *Laurent Clerc National Deaf Education. APublic Imput Summary Center clerccenter gallaudet. Edu*. Gallaudet Universiy Washington D.C.

Cizek.M, &Grerory.B,.(2011). *Standar Setting, Aguide to Establishing and Evaluating Performance Standards on Tests*. Oxford: Oxfored Universiy Press.

Cohen, L,.(2000). *Research Methods in Education.* (5th ed.) London and New York: Routledg Falmer.

Creswell, J, W,. (2009). *Research Design. Qualitative, Quantitative& Mixed Method Approach*.

(3rd ed.) London: Sage Publication Inc.

Dagne Belachew. (200). “Vocational Education skill training needs of Hearing Impaired Students.” Addis Abeba University, MA thesis.

Dewey, J. (1913). *Interest and effort in education*. Cambridge, Massachussets: Riverside Press.

Deginesh Desalegn (2016). “Acadamic Challenges of Deaf Students in Inclusive class and Peception of Their Inclusion in Primary School” Arbaminch University. MA thesis.

Dornyei, Z,.(2007). *Research Methods in Applied Linguistics.Qualitative, Quantitative &Mixed Methodologies.* Blackwell Publishing.UK: OUP

Dostal, H., and Wolbers, K,.(2014). Developing Language and Writing Skills of Deaf and Hard of Hearing Students, a Simultaneous Approach.*Literacy Research and Instruction*, Taylor Francis Group Vol.53.

Elizabeth, G,. (2009). Teaching written language to students who are deaf or hard of Hearing. *Independent Studies and Capstones.*Paper 186.Program in Audiology and Communication Sciences, Washington University Schoo of Medicine.http://digitalcommons.wustl.edu/pacs_capstones/186.

Ellis, R. (1990). *Instructed Second Language acquisition*. Oxford: Black well Publishers.

Emma, M., and Carole, J.T,. (2012). Single group, Pre- Post- test Research designs.Some Methodological Concerns.*Review of Education*. Oxford: University of York UK. (Vol.38NO.5).

Ferris, D., and Roberts, B., (2001).Error feed back in L2 writing classes. How explicit does it need to be? *Journal of Second Language Writing*.

Ferris, Dana R,.(2003).*Response to Student writing.Implications for Second Language Students.* London: Lawrence Erlbaum Associates Inc.

Flo. B, and Bill. P. (2009).Writing Strategies for Learners who are Deaf. *Center for Ecellence in Learning Supports*.Nor Quest College.

Folling-Albers, M., & Hartinger, A. (1998). Interest of boys and girls in elementary school. In L. Hoffmann, A. Krapp, K. A. Renninger & J. Baumert (Eds.), *Interest and learning: Proceedings of the Seeon Conference on interest and gender* (pp. 175-183). Kiel: IPN.

Fountas, I. C., McCarrier, A., and Pinnell, G. S. (2000).*Interactive Writing.How language and Literacy come together.* K-2.Portsmouth, NH: Heinemann.

Frick, R. W. (1992). Teaching mind in society: Teaching, schooling and literate discourse. *In L. C. Moll (Ed.), Vygotsky and education: Instructional implications and applications of Sociohistorical psychology* (pp. 175-205).Cambridge UK: Cambridge University Press.

Girima, Wossenie. (2008) "Effects of Instrumental Enrichment and Meditated Learnig Experience on EFL Vocabulary Task Performance of Student with Hearing Impairments" Addis Abeba University. Phd Dissertation.

Graziano M, Raulin, L (1998). *Research Methods*: *A Process of Inquiry*. New York: Harper Collins College Publishers

Habibullah.P, Rafique. M, Shumaila. M, Ali. R. K, & Illahi B, (2018). Acritical Review Vygotsk's Socio-Cultural Theory in Second Language Acquisition, *international Journl Of English Lingustics*, Vol, 8.No.4.

Harmer, J,. (1996). *The practice of English Language Teaching*. London: and New York: Long Man ltd.

Harmer, J,.(2004). *How to Teach Writing?* England: Pearson Educational Limited.

Harp, S. F., & Mayer, R. E. (1997). The role of interest in learning from scientific text and illustrations: On the distinction between emotional interest and cognitive interest. *Journal of Educational Psychology*, *89*(1), 92-102.

Heaton, J.B,. (1988). *Writing English Language Tests.* London & New York: Long Man ltd.

Heaton, J. B. (1991). *Writing English Language Tests.* New York: Longman UK. Ltd

Hedg, T,.(1988). *Mistakes and Erros*: London: Longman ltd.

Hedge, T,.(2001).*Teaching and Learning in the Language Classroom*. Oxford: Oxford University press.

Hidi, S., & Berndorff, D. (1998). Situational interest and learning. In L. Hoffmann, A. Krapp, K. A. Renninger & J. Baumert (Eds.), *Interest and learning: Proceedings of the Seeon Conference on Interest and Gender.* Kiel: IPN

Hillocks, G., Jr,.(1986). Research on Writing Composition, New Directions for teaching .*Urbana III: NCRE/ ERIC.*

Hinkel, E,. (2011) .*What Research on Second Language Writing tells us and what it does not.*In Hinkel, Eli (ed.) Hand Book of Research in Second Language Teaching Learning Vol. II (pp.542). New York & London: Rutledge.

Hpelin, K,. (2017). *Writing skills of Hearing Impaired Students who Benefit from services at Public Schools in Turkey*. Andolu University.

Hussni, M., (2014). *The Effectiveness of Using Interactive Writing Strategyon Developing Writing Skills among 7th Graders and their Attitudes towards Writing.* Islamic University of Gaza. MA thesis.

Hyland, K.(2003). ***Second Language Writing***. Cambridge; CUP

Jacobs, H,L.,Zinkgraf, S.A., Wormuth, D. R., Hartfiel, V.F., & Hughey, J. B,. (1981).*Testing ESL composition: A practical approach*. Rowley, MA: Newbury House.

John.T,R. (2004). The Communicative Approach to Language Teaching. *International Journal of English* .University of Essex Murica.

Joseph. P, (2010). *Student Interest in Teaching Learning Conceptualizing Student Model of Teacher Communication Student Imotional and Cognitive Interest and Ingagement*. Ohio University.

Kaplan, R, Grabe.B,. (1996). *Theory and Practice of Writing*. London: Longman.

Keys, C.W,. (2000). Investigating the thinking processes of eighth grade writers during the composition of a scientific laboratory report. *Journal of Research in Science Teaching.*

Kroll, B,. (1990). What does time buy? ESL Student Performance on home versus class Compositions. *In Kroll, Barbara (ed.) Second Language Writing*. Research Insight for the Class Room.Cambridge: CUP.

Kroll, B,.(1993). *Teaching Writing in the ESL Context*. In M. Celce-Murcia (Ed. 2nd Ed). Teaching English as a Second or Foreign Language.Oxford: Oxford University press.

Linda,.F &John,.R.H,. (1981).Cognitive Process Thorey of Writing, *Journal of WritingResearch*. Universty of South Run Calfornya, Lossangels

Margret A.(2006). *Confronting difference an excursion through the History of Special Education, Helsinki*: Usimaao.MA thesis.

Marsden, E. and J. Torgerson, C. (2012).Single group, pre- and post-test research designs, some methodological concerns. Oxford: *Review of Education* Vol. 38, No. 5

McCarrier, A, and Pinnell, G.S,.(1994). *Interactive writing Atransition tool for assisting children in learning to read and write***.**In E. Hiebert & Taylor (Eds.), Getting reading right from the start: Effective early literacy interventions Boston.

McLaughlin,B.(1991). *Theories of Second Language Learning*. London: Edward Arnold.

Mohammed Hayata Ebrahim (2013). "Status of Inclusive Education of Hearing Impaired Students in primary schools" Addis Ababa University MA thesis.

Moore, K. (1995). *Classroom Teaching Skills.* New York: McGraw-Hill, Inc.

Muijs,D,.(2004). *Doing Quantitative Research in Education with SPSS.*London: Sage Publications.

Neorgious,S.N,.(1999). Parental attributions as predictor of involvement & influences on Child Achievement.*British Journal of Educational Psychology*.

NICHCY (2010). *Deafness and hearing Loss*. Chicago: University press.

Norrish, J. (1983). *Language Learners and Their Errors.* London: McMillan Publisher Ltd.

Nunan, D, (1989). *Designing Tasks for the Communicative Class Room.* Cambridge: CUP.

Oshima, and, Hougue, A, (1981). *Writing Academic English*. Second Edition. Cambridge: Person Education Ltd.

Paul.O, (2013). Functional Writing Skill for Effective Communication. The English Language Classroom in Kenya. *Journal of Emerging Frends in Educational Research and Policy Studies.*

Pincas, A,. (1982). *Teaching English Writing.* Hong Kong: Macmillan Publishers Ltd.

Rachell.M,F. (2013). *The Use and Implementation of Intractive Writing as an International Method for primary Teachers in Texas Educational service Center*, University of Corpus Chrisiti.

Raimes,A,.(1983). *Techniques in Teaching Writing.* Oxford: Oxford University Press.

Richads, J. C,.(1990). *The Language Teaching Matrix*. Cambridge: UniversityPress.

Richards, J.C,.& Rodgers, T,. (2001). *Approaches and methods in language teaching* (2nd ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Rick, JB,.(2006). *Research Methodology and Techniqes*. (2nd ed.). New Delhi India: New age in Ternajonal Ltd Publishers

Robin B,.(2009). *Research Methods & Experimental Design*. Cambridge: CUP.

Romana H, (2012). *Deaf Students Learning English as a foreign Language*. Masaryk University BURNO Faculty of Education Department of English.

Ronald,T. K, (2008). Training Writing Skill.Acognitive Developmental Perspective. Saint Louis University.USA, *Journal of Writing Research.*

Rumsey, T.A, (1998). *Improving the Writing Skills of At-Risk Students Through the Use of Writing Across the Curriculum and Writing Process Instruction*. Grand Valley State University.M.AThesis.

Salah, M.A. (2010). *A Suggested Program for Developing Teaching Writing Skills of Secondary School Teachers.* Khan Younis Governorat Islamic University- Gaza. M.A Thesis.

Saur, K, (2012). The Impact of Student Interest and Instructor Effectiveness on Student Performance. *Journal of Education Fisher Digital Publication*.

Seow, A, (2002). The Writing Process and Process Writing.In Richards, Jack C. and Renandya Willy A.(ed.) *Methodology in Language Teaching An Anthology of Current Practice*. *(PP.315).*Cambridge: Cambridge: University Press.

Slavin, R.E. (1990). Comprehensive cooperative learning methods: Embedding cooperative learning in the curriculum and the school. *In S. Sharan (Ed.) cooperative learning theory and practice. New York.*

Sheilla, B, W,. (2011). Teaching of Reading and Writing to Deaf Learners in Primary School is in Uganda University of Oslo Norway. *The Journal if Deaf Education.* vol.13.

Silva, T, (1990**).** *SecondLanguage Composition Instruction:* Developments, Issues, and Directionsin ESL in Second Language Writing. Research Insights for the Classroom, Barbara Kroll (Ed.), 11-23. Cambridge: CUP.

Smith .R (2010) *Strategies of Social Research*. p101 London Prentice Hall International

Smoke, T,.(1987). *AWriter's Workbook.An Interactive Writing Text for ESL Students*. New York: ST. Martin's Press.

Steven M, R,. (2015). *Experimental Research Methods*.The systematic design of instruction (4th ed.). New York: Harper Collins College.

Tammie, L. S. (2003). Interactive and Independent Writing Instruction in a First Grade Classroom**.** *Mid-Western Educational Researcher .Volume 25, Issue 3.*

Tesfay, Solomon. (1995) "The effectiveness of Learner Self-Correction of Written Errors in the EFL Class room" In Partial fulfillment of the requirements for the Degree of Master of Art in TEFL.School of Graduate Studies.Addis Ababa University .MA thesis.

Tesfaye Basha. (2014). Signed Language proficiency and Reading comprehension skill of Deaf Children in special and integrated Primary School in Adis Aabeba *international Journal of Research.*Vol 1,

Troxka, L.Q, (1990). *Hand book for writers,* Engle wood cliffs, New Jersey: Prentice Hall, Inc

Twodros. (2014). "Educational opportunities and challenges of students with Hearing Impairment Inliimat Behibret Primary School Assela" Addis Ababa University MA. Thesis

Vygotsky, L,.(1978). *Mind in society: The development of higher psychological processes*. Cambridge: Harvard University Press.

White, R. & Arndt, S,.(1996). *Process Writing fifth impression.Hand books for Language teachers*.Longman: Cambridge University Press.

White, R.V,.(1988). *Acadamic writing process and product.* ETL Document*:* HongKong: Modern English Publication and the British Council.

Williams, C,.(2011). Best Practice in Mainstream Education of deaf and Hard-of-Hearing Student *Education forum*.Universty of cinciinnati.

Winzer, M.A. (1986). *Early Development in Special Education some aspects of Enlightenment Thought.* Faculty of Education.Cambridge University.

Wolbers, K. (2008). Strategic and Interactive Writing Instruction (SIWI): Apprenticing deaf students in the construction of English text.*ITL International Journal of AppliedLinguistics*, Vol. 156,

Wolbers, K., Dostal, H. & Graham, S, (2016*). "*Final Research Performance Report Development of Strategic and Interactive Writing Instruction for deaf and hard o fhearing students" Washington D.C: Institute of Education Sciences.

Wolbers, K., Dostal, H. & Stephenson, B,. (2012).Strategic and Interactive Writing Instruction (SIWI), A two-year focus on the language and literacy development of deafand linguistically diverse students.Nashville, Tennessee: *Tenness Higher Education Commission.*

World Health Organization (WHO).(2019). Deafness and Hearing Loss.Retrieved on March 20. 2019 from Httpsi// www.who.int.

## አባሪ ሀ

## በአልፉ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች የቀረበ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና (ዋና ጥናት)

**የተሰጠው ሰዓት 2፡00** **ፈተናው የሚይዘው ውጤት 100%**

**የትምህርት ዓይነት አማርኛ**

**መለያ ቁጥር--------- ዕድሜ--------- ጾታ------------**

**ማሳሰቢያ፡-** ከመለያ ቁጥር፣ ከዕድሜና ከፆታ ውጪ በፈተናው ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

**አጠቃላይ መመሪያ ፦ውድ ተማሪዎች ከዚህ በታች የጽህፈት ችሎታችሁን የሚለኩ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ለቀረቡት ጥያቄዎችም የአሰራር መመሪያዎች ተሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም በተሰጡት መመሪያዎች መሰረት ሁሉንም ጥያቄዎች ስሩ፡፡**

### ክፍል አንድ ውስን ጽሕፈት

**መመሪያ አንድ፦ ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ላይ በመመስረት ተገቢውን የአጻጻፍ ስርዓት የተከተሉና የተሟላ መልዕክትን ማስተላለፍ የሚችሉ አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፦ ጥያቄ- ተሸለመ**

**መልስ-** <u>ዳንኤል በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ስላመጣ ተሸለመ፡፡</u>

1.1 ነጋዴ -------------------------------------------------------------------------------

1.2 ዝናብ -------------------------------------------------------------------------------

1.3 ሄደ -------------------------------------------------------------------------------

1.4 ተማሪ -------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ ሁለት፡*** ቀጥሎ በቀረቡት የአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ተዘበራርቀው የተቀመጡን ቃላት እንደገና በማስተካከል ሰዋስዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁና ትርጉም የሚሰጡ አረፍተ ነገሮች አድርጋችሁ ጻፏቸው፡፡

**ምሳሌ፡ ጥያቄ- ትፈራለች ሰላም በሰው ፊት ማወራት**

**መልስ- ሰላም በሰው ፊት ማውራት ትፈራለች፡፡**

2.1 ይሰራል ከእንጨት ወንበር፡፡

----------------------------------

2.2 መትከል ይከላከላል ዛፍ ድርቅን ፡፡

------------------------------------------

2.3 ጸሃይ ትወዳለች ማንበብ መጽሃፍ ፡፡

------------------------------------------

2.4 የገዛው አበበ መኪና ያምራል በጣም፡፡

--------------------------------------------

2.5 ያጠና ጠንክሮ ተማሪ ጥሩ ያመጣል ውጤት፡፡

-------------------------------------------------

2.6 ወላጆቹን ልጁ ያከብራል ፡፡

--------------------------------------------------

2.7 ይሄዳሉ ብዙ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት፡፡-------------------------------------------

2.8 በምሰራቅ ጸሀይ የምትወጣው ነው ፡፡-----------------------------------------

***መመሪያ ሶስት፡*** **ከዚህ በታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ በተጓደሉ ቃላት ምትክ ቁጥሮች ሰፍረዋል፡፡ በቁጥሮቹ ቦታ መግባት ያለበትን ቃል ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በትክክለኛ ቅርጹ አስተካክላችሁ ፃፉ ፡፡**

| ይወድቃል፣ ይተሳሰራል፣ ይረበሻል፣ መገላገል፣ይጥራል |
|---|

ሱስ አካልና መንፈስን ያዳክማል፡፡ በአኗኗሩ ጠንቃቃ፣ በአስተሳሰቡ በሳል፤በስራውም ክቡር የሆነ አንድ ሰው በአጉል ሱስ የተጠመደ ከሆነ የለመደውን ባላገኘ ጊዜ መንፈሱ -----1----፤አካሉ ይዝላል፤ ምላሱ -------2----፡፡ ሱሱ የፀና ከሆነም እግሮቹ ተዝለፍልፈው መሬት ላይ ---3----፡፡ ተሸናፊ ሆኖ ላለመታየትም ለመነሳት ----4----፡፡ ሱስ ሰዎችን ሲቆጣጠር የሚያስከትለው ችግር ከዚህ ከፍ ብሎ ቢገኝም በፍላጎታቸው ላይ አስቀድመው ከወሰኑ ከዚህ አይነቱ ጣጣ-------5-----እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**ምሳሌ፦ መልስ-** 1.<u>ይረበሻል</u> 2. ------------ 3 ---------------- 4 -------------- 5---------------

***መመሪያ አራት፦ ከዚህ በታች የቀረቡት አረፍተ ነገሮች የስርዓተ ነጥብ ጉድለት ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም በሰንጠረዡ ውስጥ ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ለክፍት ቦታዉ ተስማሚ የሆነውን ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አረፍተ ነገሮቹን እንደገና ጻፉ፡፡***

| ፦ | / | ፡፡ | “ ” | ? | ! | ፣ |
|---|---|---|---|---|---|---|

4.1. ዳንኤል ለቤተሰቦቹ የመጀመሪያ ልጅ ነው ----

4.2. ከበደ-----ሰለሞን-----ሳራና ሰላም የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

4.3. እሰይ----ስፈልግሽ መጣሽ፡፡

4.4. የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበር መቼ ተመሰረተ----

4.5. አልማዝ ከገበያ ብረቱኳን----- ሎሚ----ቲማቲምና ቃሪያ ገዝታ መጣች፡፡

## ክፍል ሁለት መር ጽሕፈት

**መመሪያ አምስት፦ የሚከተለውን ጅምር ፅሁፍ በጥሞና አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኋላ፣ እያንዳንዳቸው ከሰላሳ አምስት እስከ አርባ የሚሆኑ ቃላትን በያዙ ሁለት አንቀጾች ጅምሩን ሀሳብ ጨርሳችሁ ጻፉ ።**

የተፈጥሮ ሀብቶች ከሚባሉት መካከል ውሀ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል።ውሀ የኤልክትሪክ ሃይልን ለማመንጨት፣ ለመጓጓዣነት ይጠቅማል። ውሀ ለሰው ልጆችም ሆነ ለሌሎች ህይወት ላላቸው ነገሮች የሚሰጠው ጥቅም ይህ ብቻ አይደለም።ለምሳሌ -------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------::

## ክፍል ሶስት ነፃ ጽሕፈት

**መመሪያ ስድስት፦ ከዚህ በታች ከቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥ በመቶ ቃላት ባለሁለት አንቀጽ ገላጭ ድርሰት ጻፉ።**

- የትምህርት ጥቅም
- የስፖርት አስፈላጊነት እና አይነቶች
- የትራፊክ አደጋ መንስኤና የሚያስከትለው ጉዳት

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------- ::


------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ::**

**መመሪያ ሰባት፦ ቀጥሎ በቀረበው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ውስጥ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ሀሳቦች በማስፋፋት የህይወት ታሪካችሁን ጻፉ፡፡**



## አባሪ ለ

# በቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች የቀረበ የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ (ናሙና ጥናት)

**ውድ ተማሪዎች፡-**የዚህ የፅሁፍ መጠይቅ ዓላማ ለጥናቱ የተመረጡ መስማት የተሳናቸው የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ከመማራቸው በፊትና በኋላ በችሎታቸውና በመማር ፍላጎታቸው ላይ የሚታይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመግለጽ የሚያስችል ጠቃሚ መረጃ ማግኘት ነው፡፡

**በመሆኑም ጊዜያችሁንና ጉልበታችሁን በመስጠት መጠይቁን ለመሙላት ለምታደርጉት ትብብር አጥኚዋ አስቀድማ ለማመስገን ትወዳለች፡፡**

**ክፍል አንድ አጠቃላይ መመሪያ፡-**

ከዚህ በታች የተለያዩ ጥያቄዎች በሁለት ክፍሎች ቀርበዋል፡፡ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በትክክል የእናንተን ፍላጎት ወይም ባህሪ ይወክላል የምትሉትን ከምርጫዎቹ ፊትለፊት በሚገኘው ክብ ውስጥ የ “x” ምልክት በማድረግ መልሱ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል ወይም ስህተት የሚባል መልስ የለውም፡፡ ትክክለኛ መልሱ የራሳችሁን ሀሳብ ያንፀባርቃል የምትሉት ምርጫ ነው፡፡

ማሳሰቢያ፡፡ከመለያ ቁጥር፣ ከዕድሜና ከፆታ ውጪ በፅሁፍ መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

መለያ ቁጥር---------- ዕድሜ------------ ጾታ---------------------

**ክፍል ሁለት፡- የፍላጎት ጥያቄዎች**

በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡት ምርጫዎች እንደሚከተለው ይወከላሉ፡፡

4 =በጣም እስማማለሁ 3= እስማማለሁ 2 = አልስማማም 1= በጣም አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ **ከመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዉ ጋር በተያያዘ ለመማር ያላቸውን ፍላጎት የሚዳስሱ** | | | | |
| 1 | የመጻፍ ክሂል ትምህርት መማር ደስ የሚለኝ በስዕላዊ መግለጫዎች ታግዞ ሲቀርብ ነው፡፡ | | | | |
| 2 | በመጻፍ ክሂል ልምምድ ወቅት እያንዳንዱ ተግባር በምልክት ቋንቋ ሲገለጽልኝ ስለሚገባኝ ለመማር እነሳሳለሁ፡፡ | | | | |
| 3 | የመጻፍ ክሂል የሚቀለኝ ከጓደኞቼ ጋር ስወያይ በመሆኑ ሀሳቤን በማካፈልና የእነሱን በመቀበል መማር ያስደስተኛል፡፡ | | | | |
| 4 | በመጻፍ ልምምድ ጊዜ በመምህራን የሚሰጡ ተከታታይ ተግባራት ስለሚያደክሙኝ ትምህርቱን እንድጠላው አድርጎኛል፡፡ | | | | |
| 5 | በመጻፍ ትምህርት ወቅት መምህራን በተደጋጋሚ የሚሰጧቸው ምዘናዎች ስህተቶቼን እያሻሻልኩ እንድሄድ ስለሚያደረጉኝ እንዲቋረጡ አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 6 | በፅህፈት ልምምድ ወቅት መምህሬ ፅሁፌን ወዲያውኑ አርመዉ ሲመልሱልኝ የበለጠ መስራት እፈልጋለሁ ፡፡ | | | | |
| 7 | በመጻፍ ትምህርት ወቅት ሁሉም የክፍል ውስጥ ተግባራት በመምህራን ሲሸፈኑና ከስራ ነጻ ስሆን ያስደስተኛል፡፡ | | | | |
| 8 | መምህሬ የጽሁፍ ስራየን ካረሙልኝ በኋላ እንደገና አስተካክዬ እንድፅፍ ሲያዝዙኝ ደስ አይለኝም፡፡ | | | | |
| 9 | በመጻፍ ልምምድ ወቅት የጽሁፍ ስራዬን ለጓደኞቼ ማሳየትም ሆነ የእነሱን ማየት አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 10 | በመጻፍ ልምምድ ጊዜ በምሰራቸዉ ስህተቶች ላይ ከመምህሬና ከጓደኞቼ ጋር መወያየቴ የበለጠ እንደማር ያደርገኛል፡፡ | | | | |
| | **ለመጻፍ ክሂል ከሚሰጡት ዋጋ አኳያ ለመማር ያላቸውን ፍላጎት የሚዳስሱ** | | | | |
| 11 | የመጻፍ ትምህርት በተማሪዎች ፍላጎትና ምርጫ መመስረት አለበት | | | | |
| 12 | ሀሳቤን መለዋወጥ የምችለው የምልክት ቋንቋ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ብቻ ነው ብዬ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለማምን የመጻፍ ክሂልን ለማወቅ አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 13 | ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለመማር የመጻፍ ክሂል ችሎታ መኖር ጠቃሚ በመሆኑ ትኩረት ልሰጠው እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |
| 14 | ከጓደኞቼ ጋር ሀሳቤን በነጻነት እንድገልጽ ዕድል ስለሚፈጥርልኝ የመጻፍ ክሂል ልምምድ ሲኖረን እደሰታለሁ፡፡ | | | | |
| 15 | የመጻፍ ክሂል የምልክት ቋንቋን ያህል ሀሳቤን ለመግለጽ ስለሚያስችለኝ ለመማር ያለኝ ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ | | | | |
| 16 | መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ መኖር አስፈላጊ ባለመሆኑ መማር አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 17 | የጽሁፍ ክህሎትን መማሬ የፈጠራ ችሎታዬን ስለሚያዳብርልኝ ለልምምዱ ትኩረት እሰጣለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | የመጻፍ ክሂልን የምማረው ለህይወቴ ስለሚጠቅመኝ ሳይሆን ተገድጄ ነው፡፡ | | | | |
| 9 | እውቀትን ለማግኘትም ሆነ ለሌሎች ለመስጠት የመጻፍ ክሂል ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቼ እማራለሁ፡፡ | | | | |
| 20 | መስማት ባልችልም የጽሁፍ ችሎታ ካለኝ ጎበዝ ደራሲ መሆን እንደምችል ስለማዉቅ መማር እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |
| 21 | በመጻፍ ክሂል ትምህርት የማገኘው እውቀት ብዙ በመሆኑ ለረጅም ሰዓት ስማር ብቆይ አይሰለቸኝም፡፡ | | | | |
| 22 | ከምልክት ቋንቋ በስተቀር በጽሁፍ ከጓደኞቼ ጋር የምግባባ ስለማይመስለኝ ትምህርቱ ደስ አይለኝም፡፡ | | | | |
| 23 | የመጻፍ ክሂል የምልክት ቋንቋ ከማይችሉ ሰዎች ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ ችሎታው እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |

24. የመጻፍ ክሂል ትምህርትን መማራችሁ ለህይወታችሁ ጠቃሚ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? አስረዱ፡፡

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

25. የመጻፍ ክሂል ትምህርትን መማር የምትፈልጉት በምን አይነት መንገድ

ሲቀርብላችሁ ነው?አብራሩ፡፡

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ መ

# በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች ተሻሽሎ የቀረበ የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ (ዋና ጥናት)

**ውድ ተማሪዎች፡-** የዚህ የፅሁፍ መጠይቅ ዓላማ ለጥናቱ የተመረጡ መስማት የተሳናቸው የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ከመማራቸው በፊትና በኋላ በችሎታቸውና በመማር ፍላጎታቸው ላይ የሚታይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመግለጽ የሚያስችል ጠቃሚ መረጃ ማግኘት ነው፡፡

**በመሆኑም ጊዜያችሁንና ጉልበታችሁን በመስጠት መጠይቁን ለመሙላት ለምታደርጉት ትብብር አጥኚዋ አስቀድማ ለማመስገን ትወዳለች፡፡**

**ክፍል አንድ አጠቃላይ መመሪያ፡-**

ከዚህ በታች የተለያዩ ጥያቄዎች በሁለት ክፍሎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በትክክል የእናንተን ፍላጎት ወይም ባህሪ ይወክላል የምትሉትን ከምርጫዎቹ ፊትለፊት በሚገኘው ክብ ውስጥ የ "x" ምልክት በማድረግ መልሱ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል ወይም ስህተት የሚባል መልስ የለውም፡፡ ትክክለኛ መልሱ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ **ከመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዉ ጋር በተያያዘ ለመማር ያላቸውን ፍላጎት የሚዳስሱ** | | | | |
| 1 | የመጻፍ ክሂል ትምህርት መማር ደስ የሚለኝ በስዕላዊ መግለጫዎች ታግዞ ሲቀርብ ነው፡፡ | | | | |
| 2 | በመጻፍ ክሂል ልምምድ ወቅት እያንዳንዱ ተግባር በምልክት ቋንቋ ሲገለጽልኝ ስለሚገባኝ ለመማር እነሳሳለሁ፡፡ | | | | |
| 3 | የመጻፍ ክሂል የሚቀለኝ ከጓደኞቼ ጋር ስወያይ በመሆኑ ሀሳቤን በማካፈልና የእነሱን በመቀበል መማር ያስደስተኛል፡፡ | | | | |
| 4 | በመጻፍ ልምምድ ጊዜ በመምህራን የሚሰጡ ተከታታይ ተግባራት ስለሚያደክሙኝ ትምህርቱን እንድጠላው አድርጎኛል፡፡ | | | | |
| 5 | በመጻፍ ትምህርት ወቅት መምህራን በተደጋጋሚ የሚሰጧቸው ምዘናዎች ስህተቶቼን እያሻሻልኩ እንድሄድ ስለሚያደረጉኝ እንዲቋረጡ አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 6 | በፅህፈት ልምምድ ወቅት መምህሬ ፅሁፌን ወዲያውኑ አርመዉ ሲመልሱልኝ የበለጠ መስራት እፈልጋለሁ ፡፡ | | | | |
| 7 | በመጻፍ ትምህርት ወቅት ሁሉም የክፍል ውስጥ ተግባራት በመምህራን ሲሸፈኑና ከስራ ነጻ ስሆን ያስደስተኛል፡፡ | | | | |
| 8 | መምህሬ የጽሁፍ ስራየን ካረሙልኝ በኋላ እንደገና አስተካክዬ እንድፅፍ ሲያዝዙኝ ደስ አይለኝም፡፡ | | | | |
| 9 | በመጻፍ ልምምድ ወቅት የጽሁፍ ስራዬን ለጓደኞቼ ማሳየትም ሆነ የእነሱን ማየት አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 10 | በመጻፍ ልምምድ ጊዜ በምሰራቸዉ ስህተቶች ላይ ከመምህሬና ከጓደኞቼ ጋር መወያየቴ የበለጠ እንደማር ያደርገኛል፡፡ | | | | |
| | **ለመጻፍ ክሂል ከሚሰጡት ዋጋ አኳያ ለመማር ያላቸውን ፍላጎት የሚዳስሱ** | | | | |
| 11 | የመጻፍ ትምህርት በተማሪዎች ፍላጎትትና ምርጫ መመስረት አለበት | | | | |
| 12 | ሀሳቤን መለዋወጥ የምችለው የምልክት ቋንቋ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ብቻ ነው ብዬ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለማምን የመጻፍ ክሂልን ለማወቅ አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 13 | ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለመማር የመጻፍ ክሂል ችሎታ መኖር ጠቃሚ በመሆኑ ትኩረት ልሰጠው እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |
| 14 | ከጓደኞቼ ጋር ሀሳቤን በነጻነት እንድገልጽ ዕድል ስለሚፈጥርልኝ የመጻፍ ክሂል ልምምድ ሲኖረን እደሰታለሁ፡፡ | | | | |
| 15 | የመጻፍ ክሂል የምልክት ቋንቋን ያህል ሀሳቤን ለመግለጽ ስለሚያስችለኝ ለመማር ያለኝ ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ | | | | |
| 16 | መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ መኖር አስፈላጊ ባለመሆኑ መማር አልፈልግም፡፡ | | | | |
| 17 | የጽሁፍ ክህሎትን መማሬ የፈጠራ ችሎታዬን ስለሚያዳብርልኝ ለልምምዱ ትኩረት እሰጣለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | የመጻፍ ክሂልን የምማረው ለህይወቴ ስለሚጠቅመኝ ሳይሆን ተገድጄ ነው፡፡ | | | | |
| 19 | እውቀትን ለማግኘትም ሆነ ለሌሎች ለመስጠት የመጻፍ ክሂል ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቼ እማራለሁ፡፡ | | | | |
| 20 | መስማት ባልችልም የጽሁፍ ችሎታ ካለኝ ጎበዝ ደራሲ መሆን እንደምችል ስለማዉቅ መማር እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |
| 21 | በመጻፍ ክሂል ትምህርት የማገኘው እውቀት ብዙ በመሆኑ ለረጅም ሰዓት ስማር ብቆይ አይሰለቸኝም፡፡ | | | | |
| 22 | ከምልክት ቋንቋ በስተቀር በጽሁፍ ከጓደኞቼ ጋር የምግባባ ስለማይመስለኝ ትምህርቱ ደስ አይለኝም፡፡ | | | | |
| 23 | የመጻፍ ክሂል የምልክት ቋንቋ ከማይችሉ ሰዎች ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ ችሎታው እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |

## አባሪ ሠ

# በቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች የቀረበ የቡድን ተኮር ውይይት (ናሙና ጥናት)

ቀን -----/------/2011 ዓ/ም ሰዓት፦ 1፡00

**ዓላማ**፡- የዚህ የቡድን ውይይት ዋና ዓላማ ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚገኙ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በመጻፍ ክሂል ችሎታቸውና በመማር ፍላጎታቸው ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደታየ ለማወቅ የመማር ማስተማር ሂደቱን ሁለንተናዊ ክንውን አስመልክቶ ከተጠኚዎች በሚሰነዝሩት ሀሳቦች መሰረትነት ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ነው፡፡

**ክፍል አንድ፡- የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ከመምህራችሁና ከጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በሚከናወኑ በቅደም ተከተላዊ ተግባራት መደራጀቱ፣ በምልክት ቋንቋና በእይታዊ መሳሪያዎች ታግዞ መቅረቡ የመጻፍ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ ረድቷችኋል? እንዴት?
2. በጽህፈት ልምምዱ ወቅት መምህራችሁ ሁሉንም ተግባር ራሳቸው ቢተገብሩት ወይስ እናንተ እንድትሰሩ ቢያደርጓችሁ ትመርጣላችሁ? ለምን?
3. በልምምዳችሁ ወቅት የጽሁፍ ስራችሁን ከጓደኞቻችሁና ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ወይም የእራሳችሁን ስራ በራሳችሁ ገምግማችሁ እንድታሻሽሉ ይረዳችሁ ዘንድ የተዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት ጠቃሚ ነው ትላላችሁ? ለምን?
4. መምህራችሁ የዕለት ተዕለት ለውጣችሁን ለመከታተል የሚሰጡት ተከታታይ ምዘናና ውጤታችሁ እየተመዘገበ የሚቀመጥበት የግል ማህደር መኖሩ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ምክንያታችሁን አቅርቡ፡፡
5. በመጻፍ ክሂል ልምምዳችሁ ወቅት መምህራችሁ ተግባራትን በምልክት ቋንቋ እየተረጎሙ ያቀረቡበት መንገድ ጠቅሟችኋል? ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡

## አባሪ ረ

# በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ለሚማሩ ተጠኚዎች ተሻሽሎ የቀረበ የቡድን ተኮር ውይይት (ዋና ጥናት)

ቀን -----/------/2013 ዓ/ም ሰዓት፦ 1፡30

**ዓላማ**፡- የዚህ የቡድን ውይይት ዋና ዓላማ ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚገኙ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የመጻፍ ትምህርታቸውን በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኂላ በመጻፍ ክሂል ችሎታቸውና በመማር ፍላጎታቸው ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደታየ ለማወቅ የመማር ማስተማር ሂደቱን ሁለንተናዊ ክንውን አስመልክቶ ከተጠኚዎች በሚሰነዝሩት ሀሳቦች መሰረትነት ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ነው፡፡

**ክፍል አንድ፡- የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ ከመምህራችሁና ከጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በሚከናወኑ በቅደም ተከተላዊ ተግባራት መደራጀቱ፣ በምልክት ቋንቋና በእይታዊ መሳሪያዎች ታግዞ መቅረቡ የመጻፍ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ ረድቷችኋል? እንዴት?
2. በጽህፈት ልምምዱ ወቅት መምህራችሁ ሁሉንም ተግባር ራሳቸው ቢተገብሩት ወይስ እናንተ እንድትሰሩ ቢያደርጓችሁ ትመርጣላችሁ? ለምን?
3. በልምምዳችሁ ወቅት የጽሁፍ ስራችሁን ከጓደኞቻችሁና ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ወይም የእራሳችሁን ስራ በራሳችሁ ገምግማችሁ እንድታሻሽሉ ይረዳችሁ ዘንድ የተዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት ጠቃሚ ነው ትላላችሁ? ለምን?
4. መምህራችሁ የዕለት ተዕለት ለውጣችሁን ለመከታተል የሚሰጡት ተከታታይ ምዘናና ውጤታችሁ እየተመዘገበ የሚቀመጥበት የግል ማህደር መኖሩ የመጻፍ ክሂላችሁን ለማሻሻል ምን ያህል ጠቅሟችኋል? ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡
5. በመጻፍ ክሂል ልምምዳችሁ ወቅት መምህራችሁ ተግባራትን በምልክት ቋንቋ እየተረጎሙ ያቀረቡበት መንገድ ትምህርቱን ለመገንዘብ ረድቷችኋል? ምክንያታችሁን አቅርቡ፡፡
6. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርታችሁን በተማራችሁበት

ወቅት የገጠማችሁ ችግር ወይም መሻሻል አለበት የምትሉት ነገር አለ?

7. በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ መማራችሁ በመጻፍ ክሂል ችሎታችሁና

   በመማር ፍላጎታችሁ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

## አባሪ ሰ

## የናሙናና የዋና ጥናቱን ቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች ለማረም ተግባር ላይ የዋለው የJacobs et.al (1981) እና የHeaton (1988) መስፈርት

| ይዘት | |
|---|---|
| 30-27 (ከእጅግ በጣም ጥሩ - በጣም ጥሩ) | በርዕሱ ዙሪያ የተሟላ ዕውቀት ያለው፣ በተፈለገው መልኩ የተብራራ፣ ወዘተ… |
| 26-22 (ከጥሩ - አማካይ) | ስለርዕሱ መጠነኛ ዕውቀት ያለው፣ በመካከለኛ ደረጃ የቀረበ፣ ወዘተ… |
| 21-17 (ከበቂ-ዝቅተኛ) | ስለርዕሱ ውስን ዕውቀት ያለው፣ ጥቂት ፍሬ ነገርን ብቻ ያካተተ፣ ወዘተ… |
| 16-13 (በጣም ዝቅተኛ) | ስለርዕሱ ምንም ዕውቀት ያላዘለ፣ ከርዕሱ ጋር ያልተዛመደ፣ ወዘተ… |
| **አደረጃጀት** | |
| 20-18 (ከእጅግ በጣም ጥሩ - በጣም ጥሩ) | ርቱዕ የሆነ አገላለጽ የሚታይበት፣ ሀሳቦች በግልጽ የሰፈሩበት፣ ወዘተ… |
| 17-14 (ከጥሩ - አማካይ) | በተገቢው መልኩ ተደራጅቶ ያልቀረበ፣ ሆኖም ዋና ዋና ሀሳቦች ተለይተው የቀረቡበት |
| 13-10 (ከበቂ-ዝቅተኛ) | ርቱዕ አገላለጽ የሌለው፣ የሀሳቦች አሻሚነት የሚስተዋልበት ወይም የሀሳቦች ተያያዥነት የማይታይበት፣ ወዘተ… |
| 9-7 (በጣም ዝቅተኛ) | ምንም ዓይነት መልዕክት የማያስተላልፍ፣ የሀሳብ አደረጃጀት የማይታይበት፣ ወዘተ… |
| **ቃላት** | |
| 20-18 (ከእጅግ በጣም ጥሩ - በጣም ጥሩ) | ብስለት የሚታይበት፣ የተዋጣለት የቃላት መረጣ/አባባል እና አጠቃቀም የሚታይበት፣ ወዘተ… |
| 17-14 (ከጥሩ - አማካይ) | በበቂ ደረጃ መቅረብ የቻለ፣ አልፎ አልፎ ከቃላት መረጣ/አባባል እና ከአጠቃቀም አኳያ ስህተት ቢታዩበትም ምን ለማለት እንደተፈለገ ለመገመት የሚያስችል፣ ወዘተ… |
| | |
| 9-7 (በጣም ዝቅተኛ) | በጣም ዝቅተኛ የሆነ የቃላት እውቀት የሚስተዋልበት |
| **የቋንቋ አጠቃቀም** | |

| | |
|---|---|
| 25-22 (ከእጅግ በጣም ጥሩ - በጣም ጥሩ) | ትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀም፣ በተገቢው መልኩ ተዋቅሮ የቀረበ፣ ወዘተ… |
| 21-18 (ከጥሩ - አማካይ) | የተሻለ የቋንቋ አጠቃቀም የሚታይበት ሆኖም ተራ በሆነ መልኩ ተዋቅሮ የቀረበ |
| 17-11 (ከበቂ-ዝቅተኛ) | ከትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀምም ሆነ ከተራ ቋንቋ አጠቃቀም አኳያ የጎላ ችግር የሚታይበት፣ ወዘተ… |
| 10-5 (በጣም ዝቅተኛ) | የዐረፍተ ነገር አመሰራረት ህግጋትን በተገቢው ሁኔታ መለየት ያልቻለ፣ ወዘተ … |
| **ሥርዓተ አጻጻፍ** | |
| 5 (ከእጅግ በጣም ጥሩ - በጣም ጥሩ) | የአጻጻፍ ሥርዓቱ ከፍተኛ የሆነ፣ ወዘተ… |
| 4 (ከጥሩ - አማካይ) | ከሆሄያት አጻጻፍ እና ከሥርዓተ ነጥብ አኳያ አልፎ አልፎ ስህተት የሚስተዋልበት፣ ወዘተ… |
| 3 (ከበቂ-ዝቅተኛ) | ከሆሄያት አጻጻፍ እና ከሥርዓተ ነጥብ አኳያ ተደጋጋሚ ስህተት የሚስተዋልበት፣ ወዘተ… |
| 2 (በጣም ዝቅተኛ) | የአጻጻፍ ስርዓቱ ትልቅ ድክመት የሚስተዋልበት፣ ከሆሄያት አጻጻፍ እና ከሥርዓተ ነጥብ አኳያ ስህተት በስፋት የሚስተዋልበት፣ ወዘተ… |

Jacobs, H.L., Zinkgraf, S.A., Wormuth, D. R., Hartfiel, V.F., & Hughey, J. B. (1981) *Testing ESL composition: A practical approach*. Rowley, MA: Newbury House.

Heaton,J.D.(1988) Writing English Language Tests(2nd Ed.).London:Longman.

## አባሪ ሸ

## የናሙናና የዋና ጥናቱን ቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች

## ለማረም ተግባር ላይ የዋለው የChrstopher Gordon (2001)

**የመገምገሚያ ሞዴል ከ**Elizabeth (2009፡31) **የተወሰደ**

| **የቅድመ አዋቂነት ጊዜ /Convectional/ ከ3-5 ዕድሜ** | **የዝንባሌመታያጊዜ /Emerging age / ከ4-6 ዕድሜ** | **የመጎልበቻ ጊዜ /Developing age/ ከ5-7 ዕድሜ** |
|---|---|---|
| -በዚህእድሜ (ደረጃ) የቃላትን ትርጉም በስዕል ታግዘው እንዲረዱ ይጠበቃል፡፡<br><br>-ስዕሎችንም በአቻቃል ይወክላሉ፡፡<br><br>-የራሳቸውን ስም እንዲጽፉይጠበቃል<br><br>-ቃላትን በመለያ ፊደሎች የሚወክሉበት ጊዜ ነው <u>ለምሳሌ፡-</u><br>ከ - ከበሮ<br>አ- አበባ<br><br>-ለሚያውቁት ነገር ትርጉምየሚሠጡበ ት ነው፤<br><br>-ስዕል ስለው ወደ ቃል ይተረጉማሉ፤ | -ለሚያዩት ስዕል አቻ ቃል ይሰጣሉ፡፡<br><br>-ስለሚያዩት ስዕል ከአቻ ቃል ባለፈ ደጋፊ ገለጻም ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ምልክቶችን፣ቃላት ስሞችንና ሌሎች ቀላል ፅሁፍችን አስመስለው ይገለብጣሉ፡፡<br><br>-በሆሄያትናቅርጽመካከል ያለውን ልዩነት ይለያሉ፡፡ <u>**ምሳሌ**</u> በእንግሊዘኛው ካፒታልና ስሞልን፣<br>-አናባቢናተነባቢ ድምፃችን ይለያሉ፡፡<br><br>-የራሳቸውንፁሁፍ የሚያነቡበትና ራሳቸውን እንደፀሀፊ የሚቆጥሩበት ጊዜ ነው፡፡<br><br>-በጽህፈትስራቸው ለሚፈፅሙትስህተት ሀላፊነትየሚወስዱበት ደረጃ ነዉ፡፡ | -ከአንድ እስከ ሁለት የሚደርሱ ዐ.ነገሮችን ይገነባሉ፡፡<br><br>-ተራና የተለመዱ ስሞችን ይፅፋሉ፡፡<br><br>-በፅሁፋቸው መጀመሪያና መጨረሻሊኖር የሚገባውን ህዳግ ይጠብቃሉ፡፡<br><br>-በቃላት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የፊደላት ስደራ ይጠብቃሉ፡፡<br><br><u>ለምሳሌ</u> በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያሉ ቃላትን ለመፃፍ ካፒታልና ስሞል ሆሄያትን እንዴትና የት መጠቀም እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡<br>-በቃላትመካከልሊኖር የሚገባውንክፍተት አልያም ስርዓተ ነጥብ ጠብቀው ይጽፋሉ፡፡<br>-ድምፅንከሆሄ ጋር ዋህደው ቃላትንይጽፋሉ፡፡ማለትምእያንዳንዱድም ፅየሚቆምለትንየሆሄ ውክልና ይለያሉ፤ |

| | | |
|---|---|---|
| **የጅማሮጊዜ /Begningage/ 6-8 ዕድሜ** | **የተስፋፎትጊዜ /Expandingage/<br>ከ7-9 ዕድሜ** | **የሽግግርጊዜ /Transitionalage/<br>ከ8-10ዕድሜ** |
| -በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተመርኩዘው ከሁለት በላይ የሆኑ ዐ.ነገሮች ይጽፋሉ፡<br><br>-ያዩትንናበአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተመርኩዘው ከሁለት በላይ የሆኑ ዐ.ነገሮች ይጽፋሉ፡፡<br><br>ያዩትንናያለፉበትን ልምድበዘገባ መልክ ይጽፋሉ፡፡<br><br>መፃፍስለሚፈለጉት ነገር ርዕስ ይመርጣሉ፡፡<br><br>-ለራሳቸው የፅሁፍ ስራ አርትኦትና ክለሳየሚያደርጉበት ጊዜ ነዉ፡፡<br><br>-ያለመሰልቸት ቃላትንክፍተታቸው ንጠብቀውይጽፋሉ፡፡<br><br>-ፊደላትንተነባቢ አድርገው በተገቢ ቅረፃቸውየሚጽፉበት ደረጃ ነው፡፡<br><br>-ከባድየሚባሉቃላትን | -ከመምህራቸውጋር ሆነው አጭርታሪኮችን ናግጥሞችን የሚፅፋበት ጊዜ ነዉ፡፡<br><br>-በሚያውቁት እውነታ ላይ ተመርኩዘው በመምህራቸው በሚሠጣቸው ርዕስ ላይ መፃፍ ይጀምራሉ፡፡<br><br>-በሚያውቁት እውነታ ላይ ተመርኩዘውበመምህራቸው በሚሠጣቸው ርዕስ ላይ መፃፍ ይጀምራሉ፡፡<br><br>-ጅምርዐ.ነገሮችንበራሳቸው አገላለጽአሟልተው ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ዕከላዊሀሳብን (ሀይለቃል) መሠረትአድርገው ይፅፋሉ፡፡<br><br>-ለቃላት ምርጫና ለሀሳብ አደረጃጀትትኩረት የሚሠጡበት ጊዜ ነው፡፡<br><br>-የቅድመ ፅሀፈትተግባራትን ማከናወን ይጀምራሉ፡፡<br><br>-በራሳቸውና በጓደኞቻቸው ፅሁፍ ላይ ምግበ ምላሽ የሚለዋወጡበት ጊዜ ነው፡፡ | -ግላዊስሜታቸውን መነሻ አድርገው የሚፅፉበት ጊዜ ነው፡፡<br><br>- መግቢያ ሁተታናመደምደሚያ የተባሉ የፅሁፍን ክፍሎችን ጠብቀው ይጽፋሉ፡፡<br><br>-መግቢያሁተታና መደምደሚያ የተባሉ የፅሁፍን ክፍሎችን ጠብቀው ይጽፋሉ፡፡<br><br>የተመረጡቃላትንበመጠቀምግጥምን፡፡ዘገባዎችን፣ ደብዳቤዎችን ወዘተ ይጽፋሉ፡፡<br><br>-አንቀጽንአደራጅተው ይፅፋሉ፡፡<br><br>-ለፅሁፋቸው ተነባቢነት ምግበምላሽ የሚሹበትና ክለሳ የሚያደርጉበት ጊዜ ነው፡፡<br><br>-የሰዋሠውና የስርዓተነጥብ ግድፈቶችን ለማረም የሚጥሩበት ነው፡፡<br><br>እንደየባለቤት አፀፋ አመልካች ያሉ ምዕለዶችን ለይተው ይጽፋሉ፡፡<br><br>ምሳሌ ቤታቸው /ኣቸው/ |

| | | |
|---|---|---|
| መፃፍ የሚጀምሩበት ነው፡<br><br>-ሆኄያት በቃል መጀመሪያመካከልና መጨረሻ ሲመጡ የሚይዙትን ቅርፅ ይለያሉ፡፡<br>-የራሳቸውን ጽሁፍ ከጓደኞቻቸው ጋር ማናበብየሚጀምሩበት ጊዜ ነው፡፡ | -የራሳቸውን የአፃፃፍ ስልት በመከተል ከሰዋስው ስህተት በከፊል የፀዳ ፁሁፍ ይጽፋሉ፡፡ | |
| **የቅልጥፍና ጊዜ /Fluentage/ ከ9-11 ዕድሜ** | **ብቁየመሆኛ ጊዜ /Proficientage/ከ10-13ዕድሜ** | **የማገናኛጊዜ/Connectingage/ ከ11-14 ዕድሜ** |
| -የተደራጀ ልብ-ወለድም ሆነ ኢ-ልብ ወለዳዊ ታሪኮችን በምሪት በመምህራቸው እገዛ ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ለፅሁፋቸው ውበት የተመረጡ ቃላትን መጠቀም ይጀምራሉ፡፡<br><br>-ውስብስብ ዐ.ነገሮችን መረዳት ይችላሉ፡፡<br><br>-የሚፅፉት ነገር ላይ ጥልቅ ገለፃና ትንታኔ ይሠጣሉ፡፡<br><br>-በሚጽፉት ርዕስ ጉዳይ ላይ | -የራሳቸውንስሜትና አስተያየትሀሳብ አመንጭተው ያለ መምህራቸው ድጋፍ ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ለችግሮችመፍትሄየሚሆኑ ሀሳቦችንአፍልቀዉ የሚጽፋበት ጊዜ ነው፡፡<br><br>-አጫጭር የልብወለድ ታሪኮች ሲጽፉ ዋናና ንዑስ ገፀባህሪያትን ለይተው ይጽፋሉ፡፡<br><br>-የተደራጁና ፍሰታቸውን የጠበቁ ፅሁፎችን በዋቢ መረጃዎች አስደግፈው ይጽፋሉ፡፡<br><br>-በአመክዩና በምሳሌዎች የተጠናከሩ ሀሳቦችን | -የተደራሲያንን ፍላጎት ያገናዘቡ ፅሁፎችን ራሳቸውን ችለው ይጽፋሉ፡፡<br><br>-በዋቢየተደገፉ የተደራጁና ፍሰታቸውን የጠበቁ ጥልቅ ሀሳቦችን የያዙ አጫጭር ታሪኮችን ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ገላጭ፣ሳቢና ማራኪ በሆነ ቋንቋ ሀሳባቸውን በፅሁፍ ይገልፃሉ፡፡<br><br>-ስለሚጽፉት ታሪክ ታማኒነት ከራሳቸው ጋር ሙግት የሚጀምሩበት ጊዜ ነው፡፡<br><br>- ለሀሳባቸው ማጉያ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ስዕሎችን ሠንጠረዦችንና ሌሎችመግለጫዎችን በመጠቀም መፃፍ የሚችሉበት ደረጃ ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ከመምህራቸው ጋር መወያየት የሚጀምሩበት ጊዜነው፡፡<br><br>-ለአቀዷቸው ርዕሰጉዳዮች ተገቢውን የአፃፃፍ ስልትየሚቀይሱበት ነው፡፡<br><br>-አለማና ተደራሲ ተኮር ፁሁፎችን ይጽፋሉ፡፡<br><br>-መዝገበ ቃላትና ሌሎች ደጋፊ ስራዎችንለፅሁፋቸው መጠቀም ይችላሉ፡፡<br><br>-በሚፅፉት ፁሁፍ እያንዳንዱ አንቀፅ መያዝ ያለበትን ሀሳብ መወሰን ይችላሉ፡፡ | ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ከአንድ በላይ የሆኑ አንቀፆችን በተገቢመሸጋገሪያ /አያያዥ/ቃላት ተጠቅመው ይጽፋሉ፡፡<br><br>-መግቢያ፣ ሀተታ መደምደሚያን የጠበቀና በተዛማጅ ስራዎች የተመሳከረ ፁሁፍ ይጽፋሉ፡፡<br><br>-ስርዓተነጥቦችንና የሠዋሠውህግጋትን በራሳቸው ያርማሉ፡፡ | - ለጠንካራ አገላለፆችና ከበድ ያሉ ስርዓተ ነጥቦችን የሚጠቀሙበት እድሜነው፡፡<br><br>- የራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን ስራ ገምግመው ማጠናከሪያ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡ |
| **የነጻነት ጊዜ** /Independent age/ **ዕድሜ ገደብ የለውም** | | |
| - የተደራጁ ፍሰታቸውን የጠበቁ ጥልቅ ፁሁፎችን ከትክክለኛ የዋቢ አጠቃቀስ ጋር አዋህደው ይፅፋ፡፡<br>- መሸጋገሪያ ሀሳቦችን ያሟሉ ሰንሰላታማ አንቀፆችን በተገቢ ይጽፋሉ፡፡<br>- ምናባዊ ፅንስ ሀሳቦችን ተጠቅመው ይጽፋሉ፡፡<br>- የራሳቸውን የአፃፃፍ ስልትና መርህ መርጠው የሚፅፉበት ጊዜ ነው፡፡<br>- ለሚፅፉበት ርዕስ ጉዳይ አፅመ ታሪክ /ቢጋራ/ ቀድመው ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡<br>- በአጠቃላይ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ያለመምህር ቁጥጥር በነፃነት በሚፈልጉት ርዕስ ጉዳይ ላይ ተመርኩዘው ከስህተት የፀዳ የፅሁፍ ስራን ይጽፋሉይጠበቃል፡ | | |

# አባሪ ቀ

# በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለተተኳሪው የክፍል ደረጃ (7ኛ ክፍል) ለምታስተምር ወይም ለሚያስተምር መምህር (ርት) የተዘጋጀ የስልጠና መመሪያ

## መግቢያ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳዉን አብይ አላማ ለማሳካት የተለያዩ ተግባራት በየደረጃው ተከናውነዋል፡፡ ከእነዚህም አንዱ የማስተማሪያ ዘዴውን በተግባር ለሚፈትሸው መምህር በቂ ስልጠና መስጠት ነው፡፡በመጀመሪያ ይህ ስልጠና የሚሰጠው ለሁለት ጊዜና (ለዋናውና ለናሙና ጥናት) እንዲሁም ለሁለት የተለያዩ መምህራን(ዋናውንና የናሙና ጥናቱን ለሚተገብሩት) ሲሆን በዚህ ክፍል የቀረበው የግንዛቤ ማስጨበጫ መመሪያም የናሙና ጥናቱን በቪክትሪ መስማት የተሳናቸው አንደኛና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤት ለተገበረችው መምህርት ነው፡፡

የስልጠናው መመሪያ ዋና አላማ መምህርቷ በማስተማሪያ ዘዴው ምንነትና ባህሪይ ዙሪያ እውቀት እንዲኖራት ማስቻል፣ ዘዴው የሚከተላቸውን መርሆዎች ማለትም ክሂሉን በማስተማር ሂደት እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግና ትምህርቱ የሚፈልጋቸው ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ ማሳወቅ፣ እንዲሁም የመጻፍ ክሂልን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች በመስተጋብራዊ ዘዴ አማካይነት ማስተማር ፋይዳው ምን ያህል እንደሆነ ወ.ዘ.ተ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው፡፡ በዚህም የጥናቱ አጋር የሆኑትእኚህ መምህርት ስለ ማስተማሪያ ዘዴው ምንነት፣ መሰረታዊ ባህሪያቱን፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ አተገባበሩን፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹንና ሌሎችንም መሰረታዊ ጉዳዮች ይገነዘባሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

### የስልጠናው መመሪያ ያካተታቸው ይዘቶች

ይህ የስልጠና መመሪያ በሚከተሉት መሰረታዊ ነጥቦች ያተኮረ ነው፡፡

- በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነትና ባህሪያት፣
- በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ፣
- በማስተማሪያ ዘዴው የአተገባበር መርሆች፣

**የስልጠናው ዓላማ**

ከፍ ሲል እንደተጠቀመው የዚህ ስልጠና ዋና አላማ ዘዴውን የምትተገብረው መምህርት፦

- በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነት፣ ባህሪይ፣ ጠቀሜታ ዙሪያ ያላትን እዉቀትና ክህሎት ከፍ በማድረግ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በልበ ሙሉነት ለመተግበር እንድትችል ማብቃት ሲሆን

- ሌላው ደግሞ የማስተማሪያ ዘዴው ሲተገበር ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ማለትም የመጻፍ ክሂል ትምህርቱ በዘዴው ሲቀርብ ሊኖር የሚገባው የመምህርቷና የተማሪዎች ሚና፣ትምህርቱ የሚያልፍባቸው መሰረታዊ ደረጃዎችና በማስተማሪያ መሳሪያነት የሚያስፈልጉ ግብኣቶች እንዲሁም ተጠኚ ተማሪዎቹ እንዳላቸው ልዩ የመማር ሁኔታ ግምት ዉስጥ ሊገቡ በሚችሉ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ እንዲኖር ማስቻል ነዉ።

**የስልጠናው ቅደም ተከተላዊ አተገባበር መግለጫ**

ስልጠናው የሁለት ሰዓት ርዝማኔ ላለው ተከታታይ ሰባት ቀናት የተሰጠ ሲሆን በሂደቱም የተመራማሪዋ ገለጻና የሁለትዮሽ ዉይቶች ተግባራዊ ተደርገዋል። ስልጠናው ያለፈባቸውን የየዕለት ተግባራት ባጭሩ ለመግለጽ ያህል፦

**በስልጠናው የመጀመሪያ ቀን**

እንደሚታወቀው ይህ ቀን የስልጠናው የመጀመሪያ ቀን እንደመሆኑ መጠን ስለማስተማሪያ ዘዴው ምንነት ከመገለጹ አስቀድሞ የጥናቱን አላማና አስፈላጊነት እንዲሁም ዋነኛ ግቡምምን እንደሆነ ለማስተዋወቅ ተሞክሯል። ይሁን እንጂ ጥናቱ ይዞት ለተነሳዉ አላማ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የተመራማሪዋ ሩጫ ብቻ ሳይሆን በምርምሩ የሚሳተፉት ተማሪዎችና መምህረቷ መሆናቸውን በአደራ መልክ ጭምር በማሳወቅ ኃላፊነት እንዲወስዱ ተደረገ።በዚህም መስማማት ላይ ከተደረሰ በኋላ ወደቀጣዩ የስልጠናው ተግባር ተገብቷል።በመጀመሪያ ሊፈተሽ ስለታሰበው የማስተማሪያ ዘዴ ማለትም መስተጋብራዊ ዘዴ ምንነነትና መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሳደግ ያለዉን ፋይዳ አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን የሰጡአቸውን ብያኔዎች መነሻ በማድረግ በተመራማሪዋ የቃል ገለጻና የሁለትዮሽ ውይይት ተደርጓል። እነዚህ የመወያያ ሀሳቦች በጥናታዊ ጽሁፉ የክለሳ ድርሳን ክፍል (በምዕራፍ 2)

ከተካተቱት ለዉይይት በሚያመቹ መልኩ አጥረው የተወሰዱ ሲሆኑ በሰልጣኚዋ መምህርት በኩልም በማስታወሻ መልክ የተወሰዱ ናቸው፡፡ለምሳሌ

- የመስተጋብራዊ ማስተማሪያ ዘዴ ታሪካዊ አጀማመር፣ ከሌሎች የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር የሚጋራው ባህሪ (ከሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር)፣መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን በማስተማር ረገድ ያስገኘዉ አዎንታዊ ፋይዳና የታዩበት ድክመቶች የሚሉ ሀሳቦች ምርምሮችን ዋቢ በማድረግ ለውይይቱ ቀርበዋል፡፡

**በስልጠናው ሁለተኛ ቀን**

በዚህ ቀን የተነሱ ሀሳቦች በስልጠናዉ የመጀመሪያ ቀን ከቀረቡት ሀሳቦች ጋር ተያያዥና ቀጣይ የሆኑ ሲሆኑ በተለይ የማስተማሪያ ዘዴዉን ባህሪና ጠቀሜታ በተመለከተ በይደር በታለፉ ሀሳቦች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህ ዕለት ሰልጣኝ መምህርቷ የምታቀርባቸዉ የይብራራልኝ ጥያቄዎች ሚዛን የደፋበት ነበር፡፡ ከተነሱት ጥያቄዎች መካለከል ጥቂቶቹ ብንጠቅስ፦

- የማስተማሪያ ዘዴዉ ጥቅም እንዳለው የተረጋገጠዉ በእንግሊዝኛ ቋንቋና ባደጉ ሀገራት ሆኖ ሳለ በእኛ ሀገርና በአማርኛ ቋንቋ ሲፈተሽ ችግር አያመጣም?
- የማስተማሪያ ዘዴው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ከማሻሻሉ ባሻገር ለሌሎች ተጓዳኝ ክሂሎች ማለትም (ለማዳመጥ፣ለመናገርና ለማንበብ) መዳበር ያለው ጠቀሜታ ምንድ ነው?
- የማስተማሪያ ዘዴዉ ከትምህርቱ ባለፈ በማህበራዊ የተግባቦት ክሂላቸው ላይ ምን አይነት አዎንታዊ ገጽታ አለዉ? ወ.ዘተ ሲሆኑ ጥያቄዎችም አግባብነት ባለው ምሳሌና እዉነታ እየተደገፉ ምላሽ ተሰቷቸዋል፡፡

**በስልጠናው ሶስተኛ ቀን**

በዚህ ጥናት መስተጋብራዊ የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ መስማት ለተሳናቸዉ ተማሪዎች ማስተማሪያ ሆኖ ሲቀርብ ሌሎች ተማሪዎችን ለማስተማር ከሚውልበት አዉድ በተለየ ከብዙ አማራጭ ስልቶችና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ጋር ተቀናጅቶ ነዉ፡፡ በመሆኑም ዘዴው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በማስተማሪያነት ከመቅረቡ አስቀድሞና በኋላ በመምህራን ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ለሰልጣኝ መምህረቷ ሰፊ ገለጻ ተደረጓል፡፡ከተነሱት ሀሳቦች መካከል

- በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚከናወን የመጻፍ ክሂል ትምህርት በሂደቱ የሚከተላቸው ደረጃዎች አሉ፡፡ እንዲሁም ሂደቱን ያቀላጥፉ ዘንድ አስቀድመው የሚዘጋጁ ግብኣቶችም ይኖራሉ፡፡ እነዚህም ቅድመ ትምህርት፣ጊዜ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ተግባራት ናቸው፡፡ የቅድመ ትምህርት ተግባራት የሚባሉት ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚከናወኑ ሲሆኑ ለምሳሌ የመጻፍ ትምህርቱን አላማ መንደፍ፣ በትምህርቱ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ መለየት፣ በየተግባራቱ ላይ የመምህሩና የተማሪዎች ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባ መወሰን፣ ለየተግባራቱ የሚሰጠውን ሰዓትና ምቹ ቦታ ማዘጋጀት፣ ተማሪዎችን ማደራጀት፣ ተግባራቱ በምን ዓይነት መመዘኛ እንደሚመዘኑ መወሰን ለዚህም ለእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ የሚሆን ማህደረ ምዘና (ፖርትፎሊዮ) ማዘጋጀት፣ ለምዘናው መስፈርት ሆነዉ የሚያገለግሉ ነጥቦችን ማጠናቀር፣እንዲሁም ተጠኚዎች መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው መጠን በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊያጋጥማቸው የሚችልን የተረድኦት ችግር ይቀርፋሉ ተብለዉ የሚታሰቡ ረዳት ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ሞዴል ጽሁፎችን ማዘጋጀት በአጠቃላይ በመጻፍ ልምምዱ ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆኑ ተግባራትን መርጦ ማቀድና እቅዱንም ለተማሪዎች በማሳወቅ ለትምህርቱ እንዲዘጋጁ መቀስቀስ እንደሆኑ ምርምሮችን ዋቢ በማድረግ ለሰልጣኝ መምህርቷ ተገልጿል፡፡ በዚህም መነሻነት የሁለትዮሽ ውይይቱ ከተከናወነ በኋላ ተከታዩ ሀሳብ ወደ ቀጣዩ የስልጠና ቀን ተሸጋግሯል፡፡

**በስልጠናው አራተኛ ቀን**

በዚህ ቀን መወያያ ሆነው የቀረቡት ሀሳቦች ከቀደመው ቀን ብዙም የተለዩ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በቅድመ ትምህርቱ ጊዜ ይከናወናሉ ተብለው የተዘረዘሩት ተግባራት ከገለጻ ባለፈ እንዴት በተግባር መሰራት እንደሚችሉ መታወቅ ስላለበት መምህርቷ ሀሳቡን ወደተግባር በምትለውጥበት ዘዴ ላይ ውይይት ተደረገዋል፡፡ ለምሳሌ

- ማህደረ ምዘና (ፖርትፎሊዮ) እንዴትና ከምን እንደምታዘጋጅ፣
- ተማሪዎችን በየስንት ጊዜ እንደምትመዝንና መመዘኛ መስፈርቶችን ከየት እንደምታጠናቅር፡፡
- ለየተግባራቱ የሚዘጋጁ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ፣ ከምን እንደሚዘጋጁና ሞዴል ጽሁፎችን እንዴትና መቼ መጠቀም

እንደሚያስፈልግ፣ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እቅዱ የተሻለዉን መንገድ መምረጥ እንደሚገባ፣ ይህ ሲባል የመስተጋብራዊ ዘዴ አንዱ መርህ በመምህሩ የበላይነት የሚመራን የመጻፍ ክሂል ትምህርት በማስቀረት ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው እየተማማሩ እራሳቸዉን የሚያበለጽጉበትን መንገድ መፍጠር ነዉ፡፡ በመሆኑም በአንድ ክፍል ዉስጥ የሚማሩ ተማሪዎች እንዳላቸዉቁጥር ፣ጾታ፣ ዳራዊ ማንነት ወ.ዘ.ተ ከፋፍሎ ለማስተማር ማቀድ የቅድመ ትምህርቱ አንዱ ተግባር ስለሆነ ፡፡ የየቡድኑ አባላት ብዛት ስንት ይሁን? አንድ ዓይነት አባላትን ወይስ ቅይጥ አባላትን የያዘ ቡድን ይመስረት?ቡድኖቹስ በማን አማካይነት (በተማሪዎች ምርጫ፣ ባላቸው ውጤት፣ መምህሩ ባወጣው መስፈርት ወይስ በእጣ) ይመስረቱ? በሚለው ሀሳብ ላይ በመወያየት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

**በስልጠናው አምስተኛና ስድስተኛ ቀን**

ቀድመው በነበሩት የስልጠናው ቀናት ቀርበው ሀሳብ በተሰነዘረባቸው የመወያያ ርዕሶች ላይ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ስለነበሩ ሰልጣኝ መምህርቷ ባቀረበቻቸው ጥያቄዎች ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ በማስተማሪያ ዘዴው አተገባበር ላይመነሳት ያለባቸው ሀሳቦች ቀጥለዋል፡፡ በዚህም በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚቀርብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት በጊዜ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ትግበራው ምን እንደሚመስል ድርሳናትን በማጣቀስ በተመራማሪዋ ከተገለጸ በኋላ የሁለትዮሽ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በጽሁፉ ምዕራፍ 2 በስፋት እንደተነሳው መስተጋብራዊ ዘዴ የዉጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ቅይጥ እንደመሆኑ ሲተገበርም የሚከተሉቸው ደረጃዎች አሉ፡፡እነዚህ ደረጃዎች በጽህፈት ልምምዱ ወቅት ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የሚያልፉባቸው ሲሆኑ ስለሚጽፉበት ጉዳይ ርዕስ ከመምረጥና ከማቀድ ጀምሮ የጻፉትን እስከመከለስ ድረስ

ያለውን ተግባር የሚወጡበት እንደሆነ በውይይቱ በስፋት ተነስቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል **በማቀድ** የጽህፈት ደረጃመስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ተማሪዎችም ቢሆኑ ስለሚፅፉት ነገር ርዕስ የሚመረጡበትና ርዕሳቸውን ሊያጎሉላቸው የሚችሉላቸውን ጠቃሚ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰቡበት እንዲሁም ለጽሁፍ ተግባሩ እራሳቸውን የሚያዘጋጁበት እንደሆነ ይታወቃል (Oshima&Houghu1981 ፣Harmer 2004:4-6)፡፡ ይሁን እንጂ ተግባሩ መስማት በተሳናቸውና በሚችሉት ተማሪዎች ዘንድ ሲታይ ደግሞ እኩል የቀለለ

ላይሆን ይችላል፡፡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ብንመለከት ካለባቸው የቋንቋ ችሎታ ውስንነት የተነሳ በአብዛኛው የክፍል ደረጃ በሚባል መልኩፊደላትን በትክክለኛው ቅርጻቸው ለይቶ ከመጻፍ ጀምሮ ዐረፍተ ነገሮችን እስከ ማዋቀር ድረስ ከፍተኛ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ይህንን ችግር ለመለየትም ሆነ ለመፍታት መምህራን የተለያዩ ተግባራን ሊያከናውኑ ይገባል፡፡ለምሳሌ በእያንዳንዱ ተማሪ የተመረጠውን ርዕስ እየዞሩ አልያም ጽሁፋቸውን ሰብስቦ በማንበብ ወይም ሠሌዳ ላይ በመፃፍ ትክክለኛነታቸውን ማሳየት፣ከመሰሎቻቸውም ሆነ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ጥንድ ሆነው በርዕሶቻቸው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፣ በርዕሶቻቸው ስር ስለሚያነሷቸው ሀሳቦች አንድ በአንድ እየዘረዘሩ እንዲፅፉ እድሉን መስጠት፣ መሪ ሀሳቦችንም ማቅረብ፣ የፃፉትን ገምግሞ ምግበ ምላሽ መስጠት እንደሚገባ ተነስቷል፡፡ ሌላው ብዙ ጊዜ በሀሳብ ነደፋቸው ወቅት የቃላት ፍቺ ሊፈትናቸው ስለሚችል እንግዳ ሆነው ለሚከብዷቸው ቃላት መምህሩ ተመሳሳይ፣ ተቃራኒና አውዳዊ ፍቺ እየሰጠ በቻርት መልክ ሊያሳውቃቸው ይገባል፡፡ የማያውቁትን አዲስ ቃል በሌላ መልኩ ከሚያውቁት ፍቺ ጋር በማዛመድ አልያም በማቃረን ማሳየት ወይም እንደተመራማሪዎች አጠራር (BuldConcept Vocabulary Webs or Chat model) መጠቀም እንደሚገባ ምክክር ተደርጓል፡፡

Raimes (1983:7) Button.et.al (1996:445) እንደገለጹትም መስተጋብራዊ ዘዴ የውጤትና ሂደት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ቅይጥ እንደመሆኑ በአተገባበር ሂደቱ ላይም በሞዴል ጽሁፎች የሚጀምር፣ በማስተማሪያ መሳሪያነት ደግሞ የስዕል ወረቀቶችን በዓይነት በቀለም የሚጠቀም፣ ማርከሮችን፣መቅረጸ ድምጾችን፣ የተቆራረጡና ሊለጠፉ የሚችሉ የሆሄያትና የቃላት ከርዶችን፣ ነጭ ሰሌዳ፣ መጠቆሚያ ቀስት፣ ሰንጠረዦችን ወዘተ. የሚፈልግ ነው፡፡መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ሲውል ደግሞ ከዚህ በላቀ ሁኔታ ተጠናክሮ መቅረብ አንደሚገባው ለሰልጣኝ መምህርቷ ለማስገንዘብ ተሞክሯል፡፡

ሌላው የጊዜ ትምህርተቱ ተግባር ማደራጀት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ግልጽ ባለ መልኩ ወደ ጽሁፍ እንዲቀይሩት የሚረዳቸውን የድርጊት ማህቀፍ የሚነድፉበትና ለትግበራው የሚዘጋጁበት እንደሆነ Wolbers (2008)፣ Williams (2011) ያስረዳሉ፡፡ይህ ሲባል ለጽሁፍ ስራቸው የሰበሰቧቸው ፍሬ ሀሳቦች በዝተው እንዳያስቸግሩና የጽሁፉን አቅጣጭ እንዳያስቱ እንደጠቃሚነት ደረጃቸው የሚመርጡበት ነው፡፡ስለሆነም በማደራጀት ሂደት ተማሪዎች ርዕሳቸውን ሊያጎሉላቸው የሚችሉ ሀሳቦች እንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል

እንዲመርጡና እንዲለዩ መምህሩ የሚያበረታተበት ተማሪዎችም በንቃት የሚሳተፉበት እንደሆነ በውይይቱ ተነስቷል፡፡

ቀጣዩ ተግባርደግሞ መግለጽ፣መጻፍ ነው፡፡ደረጃው በሁሉም አይነት ተማሪዎች ዘንድ ለሚከናወን የፅህፈት ትምህርት በተመረጠ አንድ ርዕስ ላይ የተሰሰበቡ መረጃዎች በመጀመሪያ ረቂቅነት የሚተነተኑበት ነው (Smoke1987:70)፡፡ በሂደቱ የሚከናወኑት ተግባራት አድማስ ግን እንደተማሪዎቹ የመማር ሁኔታ የተለያዩ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መጻፍን ሲማሩ በየደረጃው የሚያጋጥማቸው ችግርና ሊደረግላቸው የሚገባ እገዛ ፈረጀ ብዙ ነው፡፡ በዚህ ደረጃም የፅህፈት ልምምድን ሲያደርጉ ከስነ ዘዴው ጋር ተዋህደው ሊተገበሩ የሚችሉ ስልቶች አሉ፡፡ እነዚህ ስልቶች እንደሚፃፈው የፁሁፍ አይነት የተለያዩ ናቸው፡፡እንደሚታወቀው መምህራን ቃላትን፣ዐረፍተ ነገሮችን፣ አንቀፆችንና ሰፋፊ ሀተታዎችን ሲያጽፉ የሚጠቀሟቸው መንገዶች አንድ አይነት አይሆኑም፡፡ ስለሆነም መምህርቷ እያንዳንዱን የመጻፍ ንዑስ ክሂል ስታሰተምር እንዴት ያሉ አይነት ስልቶችን መከተል እንዳለባት በክለሳ ድርሳኑ የተገለጹትን ሀሳቦች ተመራማሪዋ እያብራራች ውይይት ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም ለተሻለ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሀሳቡን በወረቀት በማስፈር እንድታነብ ተሰቷታል፡፡

ሌላው የጊዜ ትምህርቱ ተግባር መተርጎም ሲሆን በዚህ የጽህፈት ደረጃ ተተኳሪ ተማሪዎች ከሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ ውጪ እንዳይወጡ ወይም ይዘታቸውን ለቀው ስላልተፈለገ ነገር ሲጽፉ እንዳይገኙ መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ስራ እየተመለከተ በምልክት ቋንቋቸውም ሆነ ሌላ መንገድ ተጠቅሞ በመተርጎም ግንዛቤ የሚያስጨብጥበት ነዉ፡፡ ይህም የመጻፍ ክሂልን ከማንበብ፣ ከንግግር (ከምልክት ቋንቋ) ጋር አገናኝቶ የማስተማር አንዱ የመስተጋብራዊ ዘዴ ጠንካራ ጎን መገለጫ ነው፡፡ በዚህም ሰልጣኝ መምህርቷ የምልክት ቋንቋን አቀላጥፋ የምታውቅ በመሆኗ በትርጎማ የጽህፈት ትምህርት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የልምምዱ ጊዜ የምልክት ቋንቋውን እንዳስፈላጊነቱ አስማምታ ብትጠቀም ሂደቱ ለተማሪዎች የበለጠ ግልጽ እንደሚሆንላቸው በውይይቱ ተነስቷል፡፡

ቀጣዩ ተግባር አርትኦት ማድረግ ነው፡ ፡ በአርትኦት የጽህፈት ደረጃ በመጀመሪያ ረቂቅ የቀረበው ፅሁፍ ከሰዋሰው ህግጋት አጠባበቁ፣ ከሀሳብ አደረጃጀቱ፣ ከይዘት ግልፅነቱ፣ከተደራሲያን ሁኔታና ከሌሎች መሰል ስርዓቶች አንፃር ትክክለኛነቱ ምን ያህል እንደሆነ? የሚገመገምበት ነው፡፡ ደረጃው ተማሪዎች በጥንድም ይሁን በግል የፃፉትን ጽሁፍ ደጋግመው እንዲያነቡ ዕድል ስለሚፈጥርላቸው የውስጣቸውን የጽሁፍ ችሎታ /inner voice/

ለማውጣት ያስችላቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ስለሆነም በዚህ ደረጃ መምህርቷ የጽሁፍ ስራቸውን በራሳቸው አሊያም በጥንድ ሆነው እርማት እንዲሰጣጡ ማመቻቸትና የእነሱንም ተከትሎ ምግበ ምላሽ ለእያንዳንዱ መስጠት እንደሚገባ እንዲሁም ምግበ ምላሹ ጽሁፋዊ ቢሆንና ይህም ተማሪዎችን የበለጠ ሊያበረታ እንደሚችል Wolbers (2008)፣ Williams (2011) የሙህራንን ሀሳብ ዋቢ በማድረግ ከስምምነት ተደርሷል፡፡

የመጨረሻው <u>የመከለስ</u> ተግባር ሲሆን ይህም በአርትኦቱ ወቅት ተገምግመው ችግር ያለባቸው ሀሳቦች የሚወገዱበት አልያም ማስተካከያ የሚደረግባቸው ደረጃ ነው፡፡የጥናቱ ተተኳሪዎች መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው ብዙ ጊዜ የሰዋስው አጠቃቀም ችግር ስለሚታይባቸውና የምልክት ቋንቋውም ይህንን በግልጽ ስለማያሳያቸው በዚህ ወቅት መምህርቷ አስፈላጊውን እገዛ ልታደርግላቸው እንደሚገባ ተገልጾላታል፡፡ስለሆነም ተማሪዎች የጽሁፍ ስራቸውን በሚከልሱበት ወቅት በራሳቸውና በመሰላቸዉ መንገድ እንዲሄዱ ከመፍቀድ መስተጋብራዊ ዘዴ በሚከተለው መርህ መሰረት በቅድመ ትምህርት ተግባሩ ጊዜ በተዘጋጀው የማረምያ መስፈርት መሰረት እንዲከልሱ ማድረግና ለዚህም መስፈርቱን ለሁሉም ተማሪዎች አባዝቶ መስጠት ተገቢ መሆኑን በማስገንዘብ የሁለቱ ቀን የ4 ሰዓት ዉይይት ተጠናቋል፡፡

**በስልጠናው ሰባተኛ ቀን**

በዚህ እለት ለውይይት የቀረበው ሀሳብ እንደቀደመው ሁሉ በድህረ ትምህርቱ ትግበራው ወቅት መምህርቷ ምን አይነት ስራዎችን ማከናወን እንደሚገባት ማሳወቅ ነዉ፡፡እንደሚታወቀው በዚህ ጊዜ በቅድመና ድህረ ትምህርት ትግበራው ጊዜ ታቅዶ የተከናወነው የጽህፈት ልምምድ የነበረው ጠንካራና ደካማ ጎን በጥልቀት ሚገመገምበት፣ የተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት ተጠናቅሮ የሚገለጽበትና ለቀጣይ የትምህርቱ ተግባር የሚበጁ ተሞክሮዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ጊዜ ነዉ፡፡ ስለሆነም መምህርቷ ይህንን ተገንዝባ በሂደቱ መጀመሪያ አዘጋጅታ በልምምዱ ወቅት የተማሪዎችን እያንዳንዱን የጽሁፍ ስራ እየመዘነችና ውጤት እየሰጠች ወረቀታቸውን ስትሰንድበት በነበረው የምዘና ማህደር(በፖርትፎሊዮ) መሰረትነት አጠቃላይ ዉጤታቸዉን መግለጽና ቅሬታ ካላቸው መስማት፡፡እንዲሁም ማስተካከያ የሚፈልጉ አሰራሮች ካጋጠሙ ማሻሻያ ማድረግ እንሚጠበቅባት ከአደራ ጋር ጭምር በማሳሰብ ስልጠናው ተጠናቆ ወደስራ ተገብቷል፡፡

## አባሪ በ

## መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ የማድረጊያ መርህ፡፡

ይህ የአተገባበር መመሪያ የማስተማሪያ ዘዴዉን የምትተገብረው ወይም የሚተገብረው መምህርት ምህርቱን በምን ዓይነት መንገድና ሁኔታ ለተጠኚ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ማከናወን እንደሚገባቸው የሚያግዝ ነው፡፡ መርሆው በማስተማሪያ ዘዴው ባህሪ ላይ የተመሰረተና ሌሎች ተመራማሪዎች ዘዴውን በፈተሹበት ጊዜ የተከተሉትን መንገድ ወደ ታላሚው ቋንቋና ተተኳሪ ተማሪዎች አስማምቶ በማምጣት የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ቀጥሎ በቀረቡት ሂደታዊ ክንውኖችላይ ማተኮር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ የክንውን ደረጃዎች በቅድመ-ትግበራ፣ በጊዜ-ትግበራና በድህረ-ትግበራ አፈጻጸም የሚታዩ ናቸው፡፡

1. **ቅድመ-ትግበራ**

መስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴን በመማሪያ ክፍል ዉስጥ ለመተግበር ሲታሰብ ሂደቱን ሊያቀለጥፉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይማተኮር እንደሚገባ የዘርፉ ተመራማሪዎች ያስረደሉ (Dostal & Wolbers2014፣ Elizabeth 2009፣ Wolbers.et.al 2012 እና 2016) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በትምህርት እቅዱ ስር የሚጠናቀሩ ሲሆኑ ለምሳሌእንደሚቀርበዉ የትምህርትይዘትና እንደታለመው አላማ የማስተማሪያ ግብዓቶችን ማደራጀት፣ ማለትም ስዕሎች፣ መጻፊያ ቻርቶችና ፓልከሮች፣ ካርዶችና በጥቅሉ የተጠኚዎችን የተረድኦት ችግር ሊቀንሱ የሚችሉ ሌሎች እይታዊ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ሌላው ተጠኚ ተማሪዎች መስማት የተሳናቸው እንደመሆናቸው መጠን ያላቸውን የቁጥር ውስንነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በጾታ ቀይጦ በቡድን በመከፋፈል የሚያከናውኑትን ተግባርና የስራ ሀላፊነታቸውን መለየት፣ይህ ሲባል በመስተጋብራዊ ዘዴ ተማሪዎች ስለሚማሩት ነገርም ሆነ ስለሚመዘኑበት መንገድ ቀድመው እንዲያውቁ ማድረግ አንዱ የመምህሩ ተግባር መሆኑ በክለሳው ክፍል ተገልጿል፡፡ስለሆነም የጽህፈት ልምምዱ በምን አይነት ተግባራት ላይ እንደሚያተኩር፣ልምምዱ ለምን ያህል ሰዓታት እንደሚቆይ፣ ምዘናው በየስንት ጊዜ እንደሚሰጥና በምን ላይ እንደሚያተኩር ማለትም የመገምገሚያ መስፈርት በማዘጋጀት እንዲሁም ምዘናዉ በፖርትፎሊዮ (በግል ማህደር) መልክ በእነርሱና በመምህራቸው እየተሰነደ ከተቀመጠ በኋላ ለአጠቃላይ ውጤት እንደሚበቃ ለማሳወቅ ማቀድ Flobrokop &Bill Persall (2009)፡፡ ምቹ

የመማሪያ ክፍልን ለመፈጠር ማቀድ፣ ለአብነት ያህል የተማሪዎችን ውይይትና የጽሁፍ ስራ እንደልብ ለመከታተል የሚያስችል ቦታ እንዲኖር ማመቻቸት፡፡ በዚህም ተጠኚዎች መስማት የተሳናቸው በመሆናቸው ከሰሌዳና ከመምህራቸው እይታ ውጭ ባልሆነ መልኩ በቡድናቸዉ እንዲቀመጡ ማድረግ፡፡ለልምምዱ የሚያስፈልጉና ተተኳሪ ተማሪዎቹን ሊያግዙ የሚችሉ የእይታ መሳሪያዎችን ማስቀመጫ ቦታ ማዘጋጀት፡፡ በአጠቃላይ ስለመስተጋብራዊ ዘዴ አዎንታዊ ገጽታና ስለሚያስገኝላቸው ጥቅም የሚገልጽ ጽሁፍ ለእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ እንዲደርስ አድርጎ ማዘጋጀት ትምህርቱን ለማቀልጠፍ የሚረዳ ነዉ፡፡

2. **ጊዜ-ትግበራ**

በቅድመ- ትግበራው ታቅደው የተዘጋጁት የጽህፈት ልምምዱ ተግባራት በመማሪያ ክፍል ዉስጥ የሚከናወኑት በዚህ ደረጃ ነው፡፡ በኋላ በቀጣይ ወደ ትግበራ ይገባል፡፡ አስቀድሞ እንደተገለጸው በመስተጋብራዊ የማስተማሪያ ዘዴ የመማር ማስተማሩን ሂደት በበላይነት የሚመሩት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከሚጠበቁባቸው ተግባራት መካከል ለአብነት ያህል ከመምህራቸው የተሰጣቸውን ስራ በግል፣ በጥንድና በጋራ መስራት፣ በሰሩት ስራ ላይ ምግበ ምላሽ ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ፣ ተመዝነው ውጤት የተሰጣቸው የጽሁፍ ስራዎቻቸውን እየተከታተሉ በግል ማህደራቸው ማስቀመጥ፣ በአጠቃላይ ዕለት በዕለት በሚሰጣቸው ተግባራት ላይ በንቃት በመሳተፍ ችሎታቸውን ለማሳደግ መትጋት ይጠቀሳሉ፡፡ በአንጻሩ የመምህሩን ሚና ስንመለከት፡-በመስተጋብራዊ ዘዴ መምህሩ እንደአመቻች ሆኖ ስለሚቀርብ በተማሪዎች የልምምድ ተግባር ላይ በክፍል ውስጥ እየተንቀሳቀሰ የሁሉንም ቡድኖች ስራ ይቃኛል፡፡ ይህንንም ማድረጉ ምናልባት ለአሰራር የከበዳቸውና ግልጽ ያልሆነላቸዉ ነገር ካለ ለመለየትና መፍትሄ ለመስጠት ነው፡፡ የባህሪ ሆነ ሌሎች ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ በቀላሉ ለይቶ በማወቅ ወዲያው መፍትሄ ለማፈላለግ ይረዳዋል፡፡በእርግጥ በልምምድ ወቅት የሚደረግ የመምህራን እንቅስቃሴን በበጎና በጥሩ መልኩ የሚመለከቱ ምሁራን እንዳሉ ድርሳናት ይጠቁማሉ (Moore1995)፡፡ ለምሳሌ ጉዳቱ ምናልባት እንቅስቃሴው የበዛ ከሆነ የተማሪዎችን ትኩረት ይስብና በሚያከናውኑት ተግባር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ከሚችል ስጋት የመነጨ ሲሆን ጥቅሙ ግን ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው በልምምዱ ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን በመለየትና እልባት በመስጠት ትምህርቱን ማቀልጠፍ ነው፡፡

ሌላው ትምህርቱ ከተፈታሹ የማስተማሪያ ዘዴና ክሂል ሳያፈነግጥ እየተተገበረ መሆኑን መገምገምና ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ የተማሪዎችን ስራ መከታተልና ምግበ ምላሽ መስጠት፣ በእያንዳንዱ የቡድን ስራ ተማሪዎች የደረሱበትን ውጤት በማህደረ ተግባራቸው (ፖርትፎሊዮ) እንዲሰንዱና እራሳቸውን እየገመገሙ እንዲያሻሽሉ ማድረግና በመጨረሻም የምዘና ውጤታቸውን መግለጽ ናቸው፡፡

3. ድህረ-ትግበራ

በቅድመና ድህረትግበራው ጊዜ ታቅዶ የተከናወነው የጽህፈት ልምምድ የነበረው ጠንካራና ደካማ ጎን በጥልቀት ሚገመገምበትና ለቀጣይ የትምህርቱ ተግባር የሚበጁ ተሞክሮዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ጊዜ ነው፡፡

## አባሪ ተ

# ተጠኚ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለማስተማር የተዘጋጁ የጽህፈት ትምህርት ተግባራት

የናሙና ጥናቱን ለማካሄድ ከዚህ በታች በዘጠኝ ክፍልና በአስራ ስምንት ተግባራት ተከፋፍለው በማስተማሪያነት የቀረቡት ይዘቶች እያንዳንዳቸው እለታዊ የትምህርት እቅድ ሚዘጋጅላቸው ሲሆን የሚመሰረቱትም በመስተጋብራዊ ዘዴ ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ የጽሁፍ ክፍልም ለየተግባራቱ የሚቀርቡትን እለታዊ የትምህርት እቅዶች ማቅረብ ጽሁፉን ከመመጠን አኳያ አስፈላጊ ባለመሆኑ በክፍል ሁለት ከቀረቡት ሁለት አብይ የመጻፍ ተግባራት ለአንዱ(ለተግባር ሀ.) የእለታዊ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር መመሪያ በማቅረብ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በእርግጥ በክፍል ሁለት ለተግባር ሀ. የተዘጋጀው ትምህርት ዕቅድና ክንውን መመሪያ በክፍሉ ከቀረበው ይዘት አንጻር የተቃኘ ይሁን እንጅ በሌሎች ክፍሎች ለቀረቡት የመጻፍ ተግባራት ለሚዘጋጁት ዕለታዊ ዕቅዶችም ዓብይ ምሳሌ(ሞዴል) በመሆን ያገለግላል፡፡

## ክፍል አንድ፦የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያትን መጻፍና ቃላትን መመስረት

ከዚህ በታች ተሟልተው ያልተጻፉ የአማርኛ ፊደላት ቀርበዋል፡፡በመሆኑም ተማሪዎች ፊደላቱን ከመነሻቸው እስከመድረሻቸው ድረስ በትክክለኛ ቅርጻቸው ለመጻፍ የሚያስችላቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ሌሎች የተጓደሉ ፊደላትን አሟልተው እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡በእርግጥ በዚህ ንዑስ ክፍል (በክፍል አንድ) የቀረቡት ተግባራት በተመረጠው የክፍል ደረጃ (7ኛ ክፍል) ለሚቀርብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከደረጃ በታች እንደሆነ ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ነገር ግን የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ያለባቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ችግር የሚጀምረው ፊደላትን በትክክለኛ ቅርጻቸው ካለመጻፍ መሆኑን በናሙና ጥናቱ ወቅት ማረጋገጥ ስለተቻለ የጽህፈት ማስተማሪያ ይዘቶቹ ላይ ማሻሻያ በማድረግ ትምህርቱ ከዝቅተኛ የመለማመጃ ተግባራት እንዲጀምር ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት ሆሄያትንና ቃላትን በመጻፍ ረገድ ተማሪዎች ያላቸው ችሎታ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተግባራቱ ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊትና በኋላ በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ምዘና መልክ ለተማሪዎች እንዲቀርቡላቸው ተደርጓል፡፡ይህ ዓይነቱ አካሄድ የተለያዩ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ አጥኝዋ ታምናለች፡፡ ለምሳሌ ተጠኚዎች ከትምህርቱ በፊት የነበራቸው የሆሄያትና የቃላት ምስረታ አቅም ከልምምዳቸው በኋላ ከሚኖራቸው ጋር ተነጻጽሮ የሚገኘው ልዩነት በጥቂቱም ቢሆን የማስተማሪያ

ዘዴውን(መስተጋብራዊ) ተጽዕኖ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን የተማሪዎችን የመስራት ችሎታ አስቀድሞ በመለየት በትምህርቱ ሂደት የሚቀርቡ ተጨማሪ ተግባራትን ለማደራጀት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡ በመሆኑም በክፍል አንድ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ተከታይ ክፍሎች የቀረቡ የመጻፍ ተግባራትም በአብዛኛው በቅድመና ድህረ ልምምድ እንዲሁም በቅድመና ድህረ ምዘና ክንውኖች ተቃኝተው በሙከራ ጥናቱ ትግበራ ወቅት ተከናውነዋል፡፡

**ተግባር ሀ. ሆሄያትን በትክክለኛው ቅርጻቸው መጻፍ፡፡ በቅድመ ትምህርት ተግባር እና ምዘናነት የቀረበ፡፡**

ምሳሌ፦ ሀ ሁ --- ሃ --- ህ ሆ (ሂ እና ሄ) በባዶ ቦታው ላይ የሚገቡ ፊደላት ናቸው፡፡

ለ --- ሊ --- ሌ ል --- (ሉ፣ላ እና ሎ በባዶ ቦታው ላይ መጻፍ ያለባቸው ፊደላት ናቸው)

ሐ ሑ ሒ ሓ ሔ ሕ ሖ (ፊደላት ከመነሻቸው እስከ መጨረሻቸው ድረስ በትክክለኛ ቅርጻቸው ተሟልተው ሲጻፉ)

ቀጥሎ የቀረቡትን ደግሞ በምሳሌው መሰረት በትክክል ጻፉ

መ --- --- ማ --- --- ሞ

ሠ ሡ ሢ --- --- ሥ ሦ

ረ --- --- ራ --- ር ---

--- ሱ ሲ --- --- ስ ---

ሸ ሹ --- ሻ --- --- ሾ

ቀ --- ቂ ቃ --- --- ቆ

በ ቡ --- --- ቤ --- ቦ

ተ --- --- --- ቴ --- ቶ

ቸ --- --- ቻ --- ች ቾ

ኍ ኊ ኋ ኌ ኅ ኆ

ነ --- --- ና --- --- ኖ

ኘ ኙ --- --- ኜ --- ኞ

አ --- ኢ --- --- እ ---

ከ --- --- --- ኬ --- ኮ

ኸ ኹ ኺ ኻ ኼ ኽ ኾ

ወ ዉ --- --- ዌ --- ዎ

ዐ ዑ ዒ ዓ ዔ ዕ ዖ

ዘ ---- ---- ዛ --- ዝ ዞ

ዠ ዡ ዢ ዣ ዤ ዥ ዦ

የ ዩ ዪ --- ዬ --- ዮ

ደ ዱ --- ዳ --- --- ---

ጀ --- ጂ --- ጄ --- ---

ገ ጉ --- --- ጌ --- ጎ(ጐ)

ጠ --- --- ጣ --- ጥ ---

ጨ ጩ --- ጫ --- --- ጮ

ጰ --- ጲ --- ጴ --- ጶ

ጸ --- --- --- --- ጽ ጾ

ፀ ፁ ፂ ፃ ፄ ፅ ፆ

ፈ --- --- ፋ ፌ --- ---

ፐ ፑ --- --- ፔ --- ፖ

**ተግባር ለ. ውድ ተማሪዎች፦ ከዚህ በታች የተለያዩ ፊደላትን መነሻ በማድረግ የተመሰረቱ ቃላትና ቃላቱ የሚወክሏቸውን ፍቺ በስዕል በማቅረብ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ እናንተም ምሳሌዎችን መሰረት በማድረግ በተሰረዘሩት ፊደላት አማካኝነት ትርጉም የሚሰጡ ቃላትን በመጻፍ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡**

**ምሳሌ ፦ <u>መነሻ ስዕል</u> <u>መነሻ ፊደል</u> <u>ምስርት ቃል</u>**




ጫ ጫማ



አ አንበሳ



ባ ባርኔጣ



ሰ ሰዓት



ብ ብርቱን



ጃ ጃንጥላ



ወ ወፍ




እ እንቁላል



ተ ተሸከመች (ች)



ተ ተሸከመ



መ መተባበር

| <u>መነሻ ስዕል</u> | <u>መነሻ ፊደል</u> | <u>ምስርት ቃል</u> |
|---|---|---|
| | ሀ | |
| | ለ | |
| | ቀ | |
| | ሸ | |
| | ከ | |
| | ሩ | |
| | ዶ | |
| | ግ | |
| | ን | |
| | ጠ | |

ውድ ተማሪዎች መነሻ ፊደላትን መሰረት በማድረግ የጻፋችኋቸውን ቃላት  ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተለውን መገምገሚያ መስፈርት በመከተል ስራችሁን እንደገና ከልሱ፡፡

ሀ.ቃላትን ስመሰርት ፊደላትን በትክክለኛ ቅርጻቸው ምን ያህል

ጽፌአለሁ?

ለ. የመሰረትኳቸው ቃላት ትርጉም የሚሰጡ ናቸው?

መ. ከቀረቡልኝ መነሻ ፊደላት ውጭ የጻፈኳቸው ቃላት አሉ?

ሠ. የጻፍኳቸውን ቃላት ትርጉም በስዕል ምን ያህል ገልጫለሁ?

ረ. ፊደላትን መነሻ አድርጌ የመሰረትኳቸውን ቃላት ትርጉም በምልክት

ቋንቋ  ለሌሎች መገለጽ እችላለሁ?

ሠ. የጻፍኳቸው ቃላት አረፍተ ነገር ለመመስረት የሚያስችሉ ናቸው?

**ተግባር ሐ. የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መጻፍ**

**አቀራረብ**

**መምህሩ(ሯ)** ፦ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መጽሀፍ ገጽ 6 ላይ መምህሩ ቃላትን እንዲያነብ ተማሪዎች ደግሞ አዳምጠው እንዲጽፉ ያዝዛል፡፡ነገር ግን ተጠኚዎች መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች እንደመሆናቸው በንባብ ምትክ የምልክት ቋንቋን አሊያም ወካይ ስዕሎች በማቅረብ ቃላቱን በግላቸው እንዲጽፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

| ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|

ሀ. ጠገበ

ለ. ወፈረ

ሐ. ደረቅ

መ. መደሰት

ሠ. ጠንካራ

ረ. ብርድ


ሰ. ብርሀን

**ተማሪዎች**፦መምህራቸው በምልክት ቋንቋ ከሚነግራቸው ወይም በቃላት መግለጫ ካርታ ከቀረበላቸው በመነሳት ቃላትን በየግላቸው ይጽፋሉ፡፡

**መምህሩ(ሯ)**፦ተማሪዎች ለጻፏቸው ቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ለመፈለግ ብዙ ከመድከማቸው በፊት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ለመፈለግ በሚያስችሉ መርሆች ላይ በመመስረት ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ ደግሞ ቃላት ያላቸው ሚና በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ ምሁራን ጠቃሚ የቃላት ማስተማሪያ ሞዴል ናቸው ብለው ከገለጿቸው መካከል አንዱን ለዚህ ንዑስ ክፍል በምሳሌነት በማቅረብ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

በተለይ በመስተጋብራዊ የማስተማር ዘዴ አተያይ መሰረት ለምሳሌ፦ ተማሪዎች ቃላትን እንዲማሩ ሲደረግ መምህራን ሊከተሉት የሚገባው ስልት ሌሎች ተማሪዎች ከሚማሩበት

መንገድ በተለየ መልኩ የየቃላቱን ፍቺና አገባብ የሚያሳውቁ አስረጅ ስዕሎችን፣ አማራጭ ትርጉሞችን፣ የሰንጠረዥ መግለጫዎችን ወዘተ. ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም መስማት የሚችሉት ተማሪዎች ለቃላት የሚኖራቸው እውቀት በሚናገሩት ቋንቋ ችሎታ ልክ ይወሰናል፡፡ ቀድመው በሚያውቁት ቋንቋ ላለ አንድ ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ለመስጠት ቢፈልጉ የቃሉን ትርጉም የሚያሳይ ተጨማሪ ስዕላዊ መግለጫ እና ሌሎች አገናኝ ፅንስሀሳቦች ላያስፈልጓቸው ይችላል፡፡ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚቀርብ የአንድ ቃል ትርጉም ምንነት ግልፅ የሚሆንላቸው በስዕል ተደግፎ አልያም ቃሉ ባለው ልዩ ልዩ ገጽታዎች ተብራርቶ መቅረብ ሲችል እንደሆነ Elizabeth (2009) ''Knowledge modell of vocabulary acquisition" ብለው ካቀረቡት ሀሳብ መገንዘብ ይችላል፡፡




ከቀረበው የቃላት ፍቺ ማስተማሪያ ስልት መረዳት የሚቻለው ለእነዚህ ተማሪዎች አንድን አዲስ ቃል ለማስተማር ቃሉን በፈረጀ ብዙ ትርጓሜዎች መግለፅና በተለያዩ የዐረፍተ ነገር ምስረታዎች ውስጥ በማስገባት የላቀ ተረድኦት መፍጠር መቻሉን ነው፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች በሚጽፏቸው ቃላት ላይ ምን ያህል እንደተሳሳቱና ትክክል እንደሆኑ ለማረጋገጥ የእያንዳንዱን ተማሪ ስራ መመልከት፣ እርስ እርስ እንዲተራረሙ ማመቻቸትና ምግበ ምላሽ በመስጠት ትምህርቱን ማጠቃለል ያስፈልጋል፡፡

***ማስተማሪያ መሳሪያ*** ፡ ከለር ቾክ፣ የቃላት ካርታ፣ ወካይ ስዕሎች

***ግምገማ፡*** ተማሪዎች በየጽህፈት ልምምዱ የሚሰሯቸው ስራዎች የምዘናው አካል ናቸው፡፡ በመስተጋብራዊ ዘዴም የጽህፈት ትምህርት ምዘናዎች የሂደቱ አንድ አካል ከመሆናቸው በተጨማሪም የእያንዳንዱን ተማሪ የባህሪ ለውጥ ለመከታተል ያመች ዘንድ ግለ ማህደረ ተግባር (Portfolio) እንዲሁም የቅድመ ምዘና ተግባር ንድፍ (Rubrics) ማዘጋጀት ይጠበቃል፡፡ በዚህም ተማሪዎች በየእለቱ የሚጽፏቸው ጽሁፎች በራሳቸዉና በመምህራቸው እየተገመገሙና እየታረሙ ይሰነዳሉ፡፡

## ክፍል ሁለት፡ አረፍተ ነገር መመስረትና ማዋቀር

በክፍል አንድ ሆሄያትን መሰረት አድርገው ተማሪዎች በመሰረቷቸው ቃላት ላይ ሰፊ የሆነ የእርስ በእርስ ውይይት የተደረገና የመምህርቷም ምግበ ምላሽ የተሰጠ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንዲሁም ተግባራቱ ተከታታይነት እንዲኖራቸው በማሰብ ቀደም ሲል በጻፏቸው ቃላት ላይ ተመርኩዘው አረፍተ ነገር እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ልምምዱን ለማስፋት በሚደረገው ሂደትም በሌሎች ቃላት ላይ በመመስረት ሰዋስዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁና ትርጉም አዘል የሆኑ አረፍተ ነገሮችን ተማሪዎች እንዲመሰርቱ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ፡ ሰበሰበ፣ መጣ፣ ሮጠ፣ ተማረች፣ ጎበዝ፣ ጨለማ፣ ዘፈነ፣ በረረ፣ ጨካኝ፣ ለመነ የሚሉት ቃላት ይገኙበታል፡፡

***ተግባር ሀ. መመሪያ፡ በክፍል አንድ መነሻ ፊደላትን መሰረት በማድረግ በስዕላዊ መግለጫ የቀረቡላችሁን ቃላት ትክክለኛ ትርጉም የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ ለመምህራችሁ እና ለጓኞቻችሁ አስረዱ፡፡***

ምሳሌ፡ “ጫማ” የሚለውን ቃል ትርጉም ከአንድ በላይ የሆኑ አረፍተነገሮች በመመስረት ማሳየት ይቻላል፡፡

1. አበበ ጫማ ገዛ፡፡
2. ጫማ ከእንስሳት ቆዳ ይሰራል፡፡

3. ለምለም ያደረገችው ጫማ ያምራል።

4. የእግርን ደህንነት ለመጠበቅ ጫማ ማድረግ ያስፈልጋል።

5. ዳንኤል ጫማ ማድረግ አይወድም።

ውድ ተማሪዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በእያንዳንዱ ቃል ሁለት ሁለት አረፍተ ነገሮችን ጻፉ።

ሀ. አንበሳ      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

ለ. ባርኔጣ      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

መ. ሰዓት      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

ሠ. ብርቱካን      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

ረ. ጃንጥላ      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

ሰ. ወፍ      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

ሸ. እንቁላል      አረፍተ ነገር 1.
               አረፍተ ነገር 2.

ቀ ተሸከመች      አረፍተ ነገር 1.

               አረፍተ ነገር 2

በ. ተሸከመ        አረፍተ ነገር 1.

አረፍተ ነገር 2.

ተ. መተባበር     አረፍተ ነገር 1.

አረፍተ ነገር 2.

ውድ ተማሪዎች ቃላትን መሰረት በማድረግ የጻፋችኋቸውን አረፍተ ነገሮች  ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተለውን መገምገሚያ መስፈርት በመከተል ስራችሁን እንደገና ከልሱ፡፡

1. እያንዳንዱን ቃል መሰረት በማድረግ የጻፍኳቸው አረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉት መልዕክት ምን ያህል ትክክለኛ ነው?
2. በአረፍተ ነገሮች ውስጥ የተካተቱት ፊደላትን በትክክለኛ ቅርጻቸው መጻፍ ችያለሁ?
3. የእያንዳንዱን አረፍተ ነገር መልዕክት በምልክት ቋንቋ ለሌሎች ማስረዳት እችላለሁ?
4. በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢውና በትክክለኛ ቅርጻቸው ተጠቅሜያለሁ?
5. በጻፍኳቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት እና ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ) ተሟልተው ይገኛሉ?
6. በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ አላስፈላጊ የሆነ የሀሳብ ድግግሞሽ ይታያል?
7. የጻፍኩት አረፍተ ነገር መሰረት ያደረኩትን ቃል ትክክለኛ ትርጉም መግለጽ ይችላል?
8. በአረፍተ ነገሮቼ ውስጥ ያካተትኳቸውን ቃላት ምን ያህል በትክክለኛ አሰላለፋቸው መጻፍ ችያለሁ?
9. በጻፍኳቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ ጾታን፣ቁጥርን ወዘተ. ለመግለጽ የተጠቀምኳቸው ቃላት ትክክለኛውን የአጻጻፍ ስርዓት የተከተሉ ናቸው?
10. በሁሉም አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት፣ ተሳቢ እና ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ) ተገቢ ቦታቸውን ይዘው ይገኛሉ?

**አቀራረብ**

**መምህሩ(ሯ)** ፦ተማሪዎች በቀረቡላቸው ቃላት ላይ አረፍተ ነገሮችን መመስረት እንዲችሉ ፍንጭ ይሆናቸው ዘንድ ስለ አረፍተ ነገሮች አመሰራረት ባህሪ ማለትም አንድ አረፍተ ነገር ሊያሟላ የሚገባቸውን መሰረታዊ ክፍሎች ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ  እንዲሁም

መሰረታዊ ትርጉም በምልክት ቋንቋ በመታገዝ ማስረዳት። እንዲሁም ተግባራቱን ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት መልክ እንዲሰሯቸው ማድረግ፣ ስራቸውን በንቃት መከታተልና አርማትና ምግበ ምላሽ መስጠት ይጠበቃል።

ምሳሌዎች ሀ. ካሳ ሄደ= ባለቤት+ ግስ

ካሳ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ= ባለቤት+ ተሳቢ +ግስ

ለ. ለምለም መጣች = ባለቤት+ ግስ

ለምለም ዛሬ መጣች= ባለቤት +ተሳቢ +ግስ

**ተማሪዎች፦** ከመምህራቸው በተሰጣቸው ማብራሪያ መሰረት በቀረቡላቸው ቃላት ላይ በመመስረት አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ።ለጓደኞቻቸውና ለመምህራቸው በማሳየትም ምግበ ምላሽ ይቀበላሉ።

**ተግባር ለ. በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃላት አገባብ መዋቅር ችግር ያለባቸውን በማስተካከል ትክክለኛ አረፍተ ነገር መጻፍ።**

**አቀራረብ**

**መምህሩ(ሯ)**፦ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የቃላት አገባብ ችግር ያለባቸው አረፍተ ነገሮችን እንደገና አዋቅረው እንዲጽፉ ማድረግና ባልገባቸው ነገር ላይ ማብራሪያ መስጠት።

- አየለ ገዛ መኪና
- ጸሃይ ትመጣለች ነገ
- አልማዝ ናት ጎበዝ ተማሪ
- መጽሃፍ ዳንኤል እያነበበ ነው
- ሰላምና ሉሊት እየተጫወቱ ነው ኳስ

**ተማሪዎች**፦ ከነስህተታቸው የተጻፉ አረፍተ ነገሮችን አስተካክለው በመጻፍ በምልክት ቋንቋ ታግዘው የጻፉትን ይገልጻሉ። ምግበ ምላሽም ይወስዳሉ።

***ማስተማሪያ መሳሪያ*** ፦ ከለር ቾክ፣ የቃላትና የአረፍተ ነገር መወቅር ማመላከቻ ካርታ፣

ወካይ ስዕሎች

***ግምገማ*** ፦ ተማሪዎች የሰሯቸው አረፍተ ነገሮች ትክክለኛነታቸው ተገምግሞ ውጤት

ይሰጠዋል።

## ክፍል ሶስት፦አንድ አንቀጽ መጻፍ

***ተግባር ሀ. መመሪያ፦ ከታች ስለ አንቀጽ ምንነትና ባህሪ የሚገልጸውን አጭር ጽሁፍ ተማሪዎች እንዲያነቡ ከተደረገ በኋላ ኢትዮጵያ ወንዞች፣ የአፈር ጥቅም፣ ሱሰኝነት፣ ያለ እድሜ ጋብቻ ከሚሉት ርዕሶች አንዱን በማስመረጥ አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ማገዝ ያስፈልጋል።***

### አንቀጽ

አንቀጽ ማለት አንድ ዋና ሀሳብን ለመግለጽ ሲባል በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሃሳብ አንድነታቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮች ተቀናጅተው የሚቀርቡበት የድርሰት ክፍል ነው። አንቀጽ በባህሪው አንድ ሃይለ ቃል (መንደርደሪያ አረፍተ ነገር) እና ሌሎች በሃይለ ቃሉ የተገለጸውን ሃሳብ ሊያጎለብቱ የሚችሉ ዝርዝር ሃሳቦችን የያዙ አረፍተ ነገሮችን ይይዛል።ለአብነትም የሚከተለውን ምሳሌ እንመለከታለን።

የተመጣጠነ ምግብ ገንቢ፣ ሀይል ሰጪና በሽታ ተከላካይ የሆኑትን ያካትታል። እነዚህ የምግብ ዓይነቶችም ከእንስሳትና ከአትክልት ተዋጽኦዎች የሚገኙ ናቸው። ገንቢ ምግቦችን ብንመለከት ከስጋ፣ ከቅቤ፣ ከእንቁላል፣ ከአኩሪ አተርና ከመሳሰሉት ይገኛሉ። ሃይል ሰጪ ደግሞ ማርን፣ ጥራጥሬን፣ ሸንኮራ አገዳን፣ ዳቦንና ሌሎች ተዋጽኦዎችን ያካትታል። እንደ ካሮት፣ ቆስጣ፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ሎሚ ያሉት እንደዚሁ በበሽታ ተከላካይ ምግብነታቸው ይታወቃሉ።

ከላይ ባጭሩ ከቀረበው ጽሁፍ አስረጂ ጽሁፍ መረዳት እንደሚቻለው የአንቀጹን ዋና ሃሳብ (ሃይለ ቃል) የያዘው "የተመጣጠነ ምግብ ገንቢ፣ ሀይል ሰጪና በሽታ ተከላካይ የሆኑትን ያካትታል" የሚለዉ ነው። የእያንዳንዱን የምግብ አይነት መገኛ ለማመልከት ተከትለው የመጡት ሃሳቦች ግን ዝርዝር ወይም ደጋፊ ሃሳቦች ናቸው። በመሆኑም ሃይለ ቃሉ ከእርሱ በኋላ በመጡት ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ሊብራራ መቻሉን መገንዘብ ያስፈልጋል።ከቀረበው ምሳሌ በመነሳት ሃይለ ቃሉ በአንቀጹ መጀመሪያ እንደሚገኝ ይገለጽ እንጅ በሌላ መልኩ ግን የአንቀጽ ሃይለ ቃል ዝርዝር ጉዳዮችን አስቀድሞ በማቅረብ በስተመጨረሻ እና በአንቀጹ ውስጥ ከሰፈሩት ከመጀመሪያዎቹ ጥቂት አረፍተ ነገሮች በኋላና ከመጨረሻዎቹ ጥቂት አረፍተ ነገሮች በፊት ወይም በመካከል ለመጣ ይችላል።

**አቀራረብ**

***መምህሩ(ሯ)*** ፦ትምህርቱን ለመጀመር የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ ምቹ ሁኔታዎችን ካረጋገጠ(ች) በኂላ ሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ በሚሆኑበት መልኩ ስለ አንቀጽ የሚገልጸውን ጽሁፍ በወረቀት አባዝቶ(ታ) መስጠት አልያም በከለር ቾክ ሰሌዳ ላይ መጻፍ፡፡

***መምህሩ(ሯ)***፦ተማሪዎች ጽፈው መጨረሳቸውን ማረጋገጥና ቁጥራቸውን ባገናዘበ መልኩ

በቡድን በመክፈል በርዕሰ ጉዳዩ ላይ እንዲወያዩ ማድረግና ተጨማሪ ገለጻ

መስጠት፡፡

***ተማሪዎች*** ፡ ስለአንቀጽ የሚያትተውን ማስታወሻ መጻፍ ወይም ማንበብ እንዲሁም

በሀሳቡ ላይ መወያየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

***መምህሩ (ሯ)*** ፦ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ላይ ተመስርተው በጋራ አንድ አንቀጽ

እንዲጽፉ ማድረግ፣ በጽህፈት ልምምዳቸው ወቅትም ስራቸውን በንቃት መከታተልና ማገዝ፡፡

***ተማሪዎች*** ፡ ተገቢውን የአንቀጽ አጻጻፍ ስልት የተከተለ ማለትም ሃይለቃልና ዝርዝር

ሀሳቦችን ያካተተ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ ስራቸውንም ለመምህራቸው በማሳየት ምግበ ምላሽ ይቀበላሉ፡፡

***ማስተማሪያ መሳሪያ፦***

***ግምገማ*** ፡

## ቀጥሎ ተግባር ሀ. ላይ የቀረበውን የትምህርት ክንውን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለመተግበር መምህሩ እለታዊ እቅዱን ሲያዘጋጅ ሊያተኩረባቸው የሚገቡ ነጥቦችን እንመልከት፡፡

## እለታዊ የትምህርት እቅድ 1.

## የትምህርት ዓይነት- አማርኛ

**የዕለቱ አብይ የትምህርት ርዕስ-** ተፈጥሮን ማድነቅ

**የዕለቱ ንዑስ የትምህርት ርዕስ-** መስቦቻችን

**ተግባር-** አንቀጽ መጻፍ፦ አላማውም ተማሪዎች በእድሚያቸውና በክፍል ደረጃቸው ልክ ነገሮችን ተረድተዉ ሀሳባቸውን በጽሁፍ በመግለጽ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ችሎታ እንዲያጎለብቱ ማድረግ ነው፡፡

**የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ-----**

**የክፍል ደረጃ- 7ኛ**

**የትምህርት ወሰን-** አንደኛ ሴሚስተር

**የትምህርት ዘመን-** 2011 ዓ.ም

**ትምህርት ቤት-** ቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤት

**የትምህርቱ አላማ-** ተማሪዎች ቀላል ቃላትን፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀርንና ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው በመጠቀም አንድ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

**እቅዱ ያካተታቸዉ ነጥቦች፦** የመምህሩ ተግባር፣ የተግባራቱ ገለጻዎች፣ **የመተግበሪያ ጊዜ ርዝማኔ፣** የማስተማሪያ ዘዴና መሳሪያዎች፣ የምዘና ስልት ናቸው፡፡

**የመምህሩ ተግባር-** 1. **<u>በቅድመ ጽህፈት ወቅት</u>፦**መምህሩ(ሯ) በተቻለ መጠን ከተማሪዎች የቀደመ እውቀት ወይም የኋላ ታሪክ መነሳት ስለሚያስፈልጋቸው ከእለታዊ ትምህርቱ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎችን በማንሳት የተማሪዎችን አቅም በመገምገም ክፍተታቸውን መለየት፡፡

ለምሳሌ፦ አንቀጽ ምንድን ነው? አንድ አንቀጽ ሲጻፍ ሊሟሉ የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? የሚሉትና ሌሎች ተያያዥ ሀሳቦችን በማንሳትከተማሪዎች ሚሰነዘሩትንም ሆነ ተጨማሪ ምሳሌዎችን በሰሌዳ ላይ በመጻፍና በምልክት ቋንቋ በመታገዝ ማስረዳት፡፡

3. **<u>በጊዜ ጽህፈት ወቅት</u>፦**በቀደመ እውቀት ቅስቀሳው ጊዜ ከተደረጉት የጋራ ውይይቶች በመነሳት የዕለቱን የትምህርት ተግባር ማስተዋወቅና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ማብራሪያ መስጠት፡፡ ከተማሪዎችም ሀሳብ መቀበልና የስህተት ማጣሪያ (proof read) ማድረግ፡፡ለምሳሌ፦ ስለአንቀጽ ምንነትና የአጻጻፍ ስልቱን በሚመለከት ስለ አደረጃጀቱ (ሀይለ ቃለ፣ዝርዝር ሀሳቦች) አወቃቀር፣ የቃላት መረጣው ወ.ዘ.ተ አስረጂ ሞዴል ጽሁፎችን ለእያንዳንዱ ተማሪ በወረቀት አባዝቶ መስጠት፣ ማስታወሻውንም ፣በግልና በጥንድ እየሆኑ እንዲያነቡት ማድረግ፡፡ በጽሁፉ ውስጥ አሻሚ ለሚሆኑ ቃላት ቻርቶችን (Diagram) እይታዊ መግለጫዎችን ማቅረብ፡፡ ቀጥሎም የጽሁፉን ሀሳብ በተረዱበት መንገድ እንዲገልጹ በማበረታታት ለጋራ ውይይት አቅርቦ የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት፡፡ተማሪዎች የጽሁፍ ልምምዳቸዉን ከመጀመራቸው በፊት በሚጽፉት ነገር ላይ የሚኖራቸው እዉቀት ወሳኝ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን መምህሩ (ሯ) የእያንዳንዱን ተማሪ የግንዛቤ ደረጃ መገምገም ይገባቸዋል፡፡

- ቀጣዩ የጊዜ ጽፈት ተግባር የሚሆነው ተማሪዎች የጽሁፍ ልምምዳቸውን እንዲያደረጉባቸው በመምህሩ (ሯ) በቀረቡ ርዕሶች ላይ ዉይይት ማድረግ ሲሆን በዚህም ተማሪዎች ከተገለጹላቸው ርዕሶች መካከል የወደዱትን አንዱን እንዲመርጡ ይጠበቃል፡፡
- ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርዕስ ከመረጡ በኋላ የመጀመሪያ ሙከራቸውን ያከናውናሉ፡፡ በዚህም በርዕሳቸው ስር ይካተታሉ የሚሏቸውን ሀሳቦች ይዘረዝራሉ፣ ዋናና ንዑስ ሀሳቦችን ያዋቅራሉ፣ ቀጥሎም በዘፈቀደ ያሰፈሯቸዉን ሀሳቦች በቅደም ተከተላቸው በማደራጀት ትርጉም ያለው አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡
- በመስተጋብራዊ ዘዴ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ሲተገበር ወይም ተማሪዎች የጽሁፍ ልምምዳቸውን ሲያደርጉ መምህሩ (ሯ) ሊከተሉት የሚገባቸው ደረጃዎች አሉ፡፡እነዚህም

ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መጻፍ (መግለጽ)፣ መተርጎም (በምልክት ቋንቋ መጠቀም)፣ አርትኦት ማድረግና መከለስ ናቸው፡፡ ስለሆነም በጊዜ ጽህፈቱ ወቅት ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሀሳቦችን ነድፈውና አደራጅተው የመጀመሪያ ረቂቃቸዉን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ የሚሸጋገሩት አርትኦትና ክለሳ ወደ ማድረጉ ስራ ነው፡፡

- በመሆኑም መምህሩ (ሯ) ተማሪዎች እንደ ጸሀፊ ሀያሲም ሆነው የራሳቸውን ስራ እንዲገመግሙ እድል ይሰጣል፡፡ይሁንና ተማሪዎች በልምምዳቸው ወቅት ጽሁፋቸውን ይገመግማሉ ሲባል በምን መስፈርትነት? የሚለዉ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ለዚህም መምህራኑ ቀድመው የሚያዘጋጁቸው የመከለሻ መመሪያ ቅጽ (Revising guide line check list) ጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ መገምገሚያ መስፈረቶች አንድ ጥሩ ጽሁፍ ሊያሟላቸው ከሚገቡ ጉዳዮች የሚመነጩ ናቸው፡፡

ለምሳሌ- በጽሁፉ ላስተላልፍ የፈለኩትን ሀሳብ ግልጽና የተደራጀ በሆነ መልኩ መግለጽ ችያለሁ?

- በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ ሊነሱ የሚገቡና አንባቢ የሚጠብቃቸውን አብይ ጉዳዮችማካተት ችያለሁ? አላስፈላጊ አገላለጾችንስ ተጠቅሚያለሁ?
- ሆሄያትንና ቃላትን በተገቢዉ ቅርጻቸዉና ቦታቸዉ አስፍሪያቸዋለሁ?
- የሰዋስው ህጎችን ጠብቄአለሁ?
- ስርዓተ ነጥቦችን በትክክል ተጠቅሜያለሁ?
- ጽሁፌ መስመሮችን ጠብቆ በተገቢው ተቀምጧል?
- አንባቢዎች የጻፍኩትን ይረዱልኛል? የመሳሰሉት ናቸው (Whit 1993)::

ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን መገምገሚያ መስፈርቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ አባዝቶ መስጠትና ስለትኩረታቸው ማብራራት ሌላዉ የመምህሩ (ሯ) ዓብይተግባር ነው፡፡

4. <u>**በድህረ ጽህፈት ወቅት**</u>፡-ተማሪዎች በጊዜ ጽህፈት ወቅት የመጀመሪያ ረቂቃቸውን ከመጻፍ ተግባራቸዉ አንስቶ እስከ ክለሳ ድረስ በርካታ ስራዎችን አከናው ነው ከጨረሱ በኋላ ቀጣይ ስራዎች የሚሆኑት ስለጻፉት ነገር ለሌሎች ጓደኞቻቸው መግለጽና ለመምህራቸው በማሳየት ምግበ ምላሽ ወይም አስተያየት መቀበልይሆናል፡፡ለምሳሌ- በዚህ የትምህርት ዕቅድ ተማሪዎች እንዲጽፉ የተፈለገው አንድ ገላጭ አንቀጽ

እንደመሆኑ ከቀረቡላቸው አራት ርዕሶች መካከል በአንዱ ላይ ተመርኩዘው የጻፉትን አንቀጽ ከይዘት ተኮርነቱ፣ ከቃላት አጠቃቀሙ፣ ከሰዋስው ህግ ጠባቂነቱ፣ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀሙ፣ ከሀሳብ አደረጃጀቱ (ዋናና ዝርዝር ሀሳብ አወቃቀሩ) ወ.ዘ.ተ አንጻር ምን ያህል ደካማና ጠንካራ እንደሆነ አስተያየት እንዲሰጥበት ይደረጋል ማለት ነው፡፡

በዚህ ጊዜ በተማሪዎች መካከል የሚደረጉት የእርስ በርስ ግምገማዎች ትምህርቱ በጋራና በአብሮነት መንፈስ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ከመሆናቸዉ በተጨማሪ ተማሪዎችን ከጸሀፊነት ወደ ተችነት የሚያሻግር ክህሎትን እንደሚሰጣቸዉ ስለሚታመን በሁሉም የልምምዱ ተግባራት በሚዘጋጁ ዕለታዊ ዕቅዶች ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡

- የመምህሩ (ሯ)ን ግምገማ በተመለከተ ግን የእያንዳንዱን ተማሪ የጽሁፍ ስራ በተደራጀ የመገምገሚያ መስፈርት መመዘን ይጠበቃል፡፡ ለዚህም በዘፈቀደ ከሚከናወኑት ይልቅ ምሁራን የተማሪዎችን የጽሁፍ ስራ ለማረም ጥቅም ላይ ቢውሉ ይበጃሉ ብለው ከገለጿቸው መካከል አመችውን መርጦ መጠቀም እንደሚገባ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡
- የመስተጋብራዊ ዘዴ አንዱ አላማም ተማሪዎች በሚሰሩት ስራ ብቻ ሳይሆን ስራቸው በሚመዘንበት ጉዳይ ላይ ከመምህራቸው ጋር ቀድሞ ስምምነት መፍጠር እንደመሆኑ የጽሁፍ ስራቸው ምን ምን ነጥቦችን መያዝ እንዳለበት? እንዴትና ከምን አንጻር እንደሚታረም? ወ.ዘተ የሚገልጽ የመገምገሚያ ቅጽ (Rubric) ለእያንዳንዳቸው ተባዝቶ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ መገምገሚያው ባካተታቸው ጽንሰ ሀሳቦች ላይም ግልጽ ማብራሪያ በመምህሩ ይሰጣል፡፡
- በዚህ የናሙና ጥናት ላይ የሚከናወኑ የተማሪዎች የጽሀፈት ልምምድ ተግባራት የሚመዘኑትም በዘርፉ ምርምር ያደረጉ ምሁራን ቀጥሎ ካስቀመጧቸው ሀሳቦች አንጻር ይሆናል፡፡ በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ዉስጥ የታዩ ግድፈቶችን ለይቶ ለማመልከትና ተማሪዎችም ስህተታቸውን ተረድተው በቀላሉ ለማስተካከል እንዲችሉ መምህሩ የሚከተሉት ምልክቶችና ትርጉሞችን ይጠቀማል፡፡
-

| ምልክት | ትርጉም | ምሳሌ |
|---|---|---|
| ሆ | የ ሆሄያት አጻጻፍ ችግር | - ዳንኤል ደከመ ነው |
| ቃ | የቃላት አጠቃቀም ችግር | - ጸሃይ ጎበዘችልናት |

ዐ/ነ		የአረፍተ ነገር አወቃቀር ችግር		- ለምለም ዛሬ <u>መጣ</u>

(የባለቤትናየግስ አለመስማማት)

የሰዋስውግድፈት

ሰዋስ		(የነጠላናብዙቁጥርችግር)		- እኔ ሶስት <u>ወንድም</u> አሉኝ

አያያ		አያያዦችን በተገቢው አለመጠቀም		- ሉሊት <u>የ</u>ሰሎሞን ሄዱ

ስ/ነ/ብ		የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር		- መቼ መጣሽ<u>።</u>

ይዘት		ጽንሰ ሀሳቦችን ያለመረዳት ችግር		- የሚጽፉበትንጉዳይ አለመረዳት

በድህረ ልምምዱ ወቅትም መምህሩ (ሯ) የተማሪዎችን ስህተት በዚህ መልኩ ከለየ (ች) በኋላ አሻሽለው እንዲጽፉ እድል ይሰጣል። ተማሪዎችም በተሰጣቸው አስተያየት ላይ በመመስረት እንደገና ከልሰው የጽሁፍ ስራቸውን ለመምህራቸው ያስረክባሉ። በመጨረሻም ውጤታቸው በመጠን መገለጽ ስላለበት ቀጥሎ የቀረበዉን የውጤት መወሰኛ ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል።

| ውጤት | መገለጫ ባህሪ |
|---|---|
| እጅግ በጣም ጥሩ | ጽሁፉ በተገቢው ሁኔታ የተደራጀና የሀሳብ ፍሰቱን የጠበቀ ከሆነ፣ ጥሩ የቃላት ምርጫ ካለው፣ ጥቂት (ከ2) ያልበለጠ የሚጠበቅ ስህተት ያስተናገደ፣እንዲሁም ጥሩ የፊደል አጣጣልና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ከታየበት። |
| በጣም ጥሩ | ዋና ሀሳቡ ጥሩ ሆኖ ከተገለጸና የሀሳብ ፍሰቱ ከተጠበቀ በተጨማሪም (ከ3) ያልበለጠ የሰዋስው ስህተትና በአንጻሩ የሆሄያትና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀሙ ጥሩ ሆኖ የተገኘ ጽሁፍ ሲሆን |
| ጥሩ | ዋናው ሀሳብ ተገልጾ ነገር ግን የግልጽነትና የአደረጃጀት ችግር በተወሰነ መልኩ ካለበት፣የሰዋስው ስህተቱ (ከ4) ያልበለጠና በከፊል የሆሄያትና የስርዓተ ነጥብ ግድፈት የታየበት ከሆነ |
| አጥጋቢ | ዋናውን የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ ለመለየት ካስቸገረና አንቀጾቹ በተደጋገሙና ግልጽ ባልሆኑ ቃላቶች ከተደራጁ የሰዋስውና የስርዓተ ነጥብ ችግሮች በብዛት ካጋጠሙ |
| ዝቅተኛ | የጽሁፉ ፍሬ ሀሳብ ጭራሽ ግልጽ ያለሆነ፣ ያልተደራጀ፣ የሰዋስዉና የስርዓተ ነጥብ ችግሮችን በስፋት የያዘ ሲሆን |

## ክፍል አራት፡ከሁለት በላይ አንቀጾችን መጻፍ፦ አስተዋጽኦ

## (ቢጋርመንደፍ)

**ተግባር ሀ.** ከዚህ በታች ስለ ቢጋር ምንነት፣ ጠቀሜታና የአጻጻፍ መመሪያ የሚገልጸውን ጽሁፍ ተማሪዎች ካነበቡ በኋላ ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ ቢጋር እንዲነድፉ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ የትራፊክ አደጋ መንስኤዎች፣ የደን ጥቅም፣ ድርቅ፡፡

**ቢጋር (አስተዋጽኦ)**

አንድ የድርሰት ስራ ከመጀመሩ በፊት ሶስት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከልም ቀዳሚዉን ቦታ የሚይዘዉ ርዕስ መረጣ ነው፡፡ አንድ ጸሃፊ ስለሚጽፍበት ጉዳይ ርዕስ ከመረጠ በኋላ ቀጥታ ወደ ጽሁፍ አይገባም፡፡ በተመረጠው ርዕስ ላይ ማሰብ ያስፈልገዋል፡፡ ርዕሱ ሰፍቶ መንዛዛት እንዳይፈጠር አሊያም ጠቦ መነሳት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይነሱ እንዳይቀሩ መመጠን ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሁለተኛው ተግባር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሌላው በተመረጠዉና በተመጠነው ርዕስ መሰረትነት ቢጋር (አስተዋጽኦ) መንደፍ ሶስተኛው ተግባር ነው፡፡

የቢጋርን ጠቀሜታ ባጭሩ ስንመለከት አላማን ግልጽ ለማድረግ፣ ሀሳብን ከአላማ ጋር ለማዛመድ፣ የድርሰቱን ሃሳብ በቅደም ተከተል ለማደራጀት፣ ጽሁፉ ከርዕሰ ጉዳዩ እንዳያፈነግጥ ለማድረግ ወ.ዘ.ተ ያግዛል፡፡ ስለቢጋር ሲነሳ ሌላዉ ሊተኮርበት የሚገባው ነገር የአጻጻፍ መርሆው ነው፡፡ እንደተገለጸው ቢጋር የድርሰት ሀሳብ ማደራጃ እንደመሆኑ ለዋናና ንዑሳን ሀሳቦች ተዛምዶና ክትትሎሽ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን ምሳሌዎች መመልከት ይቻላል፡፡

1. የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መስፋፋት
    1.1. ጎጂ ልማዶች
        1.1.2. እንጥል ማስቆረጥ
        1.1.3. ግርዛት
        1.1.4. ሀገወጥ ዉርጃ
    1.2. ጥንቃቄ የጎደለው ግብረ ስጋ ግንኙነት

1.3. የ “መ” ህግ የሚባሉትን አለማክበር

1.3.1. አለመታቀብ

1.3.2. አለመወሰን

1.3.3. አለመጠቀም

1.4. በአጋላጭ ሱሶች መጠመድ

1.4.1.መጠጣት (መስከር)

1.4.2. አነቃቂ መድሀኒቶችን መዉሰድ

1.4.3. መቃም

2. የአየር ንብረት መዛባት መንስኤዎች

2.1. የደን መጨፍጨፍ

2.1.1. በተቆረጡ ዛፎች ምትክ አለመትከል

2.2.2. ዛፎችን ማቃጠል

2.2.3. ዛፎችን ለማገዶ መጠቀም

2.2. ጪስ ያላቸው ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት

2.2.1. የሲሚንቶ ፋብሪካዎች

2.2.2. የድንጋይ ከሰል ማምረቻዎች

2.2.3. የተሽከርካሪ መሳሪያዎች ማምረቻዎች

2.3. መሬትን ልቅ ለሆነ ግጦሽ መጠቀም

**አቀራረብ**

***መምህሩ(ሯ)፦*** አስረጂ ጽሁፉን በወረቀት አባዝቶ በመስጠት ወይም በከለር ቾክ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በማስገልበጥ እያንዳንዳቸው ተማሪዎች በጥሞና እንዲያነቡት ማድረግ፡፡ ሲጨርሱም በቢጋር ምንነት፣ ጠቀሜታና አጻጻፍ ስልቱ ላይ በምልክት ቋንቋ የተደገፈ ሰፋ ያለ ገለጻናሁሉን አቀፍ ውይይት ማድረግ፡፡

***ተማሪዎች፦***አስረጂ ጽሁፉን በጥሞና ማንበብ፣ የመምህራቸውን ገለጻ ማዳመጥ፣ በውይይቱ በንቃት መሳተፍ፣ እንዲሁም ያልገባቸውን መጠየቅ፡፡

***መምህሯ(ሩ)፦*** ከቀረቡት ሶስት ርዕሶች መካከል አንዱን መርጠዉ እንዲጽፉ ለእያንዳንዱ ተማሪ እድል መስጠት፤ በመረጡት ርዕስ ላይ ከተለያዩ ምንጮች ማለትም ቤተ መጻህፍት

በማስገባት ተዛማጅ ጽሁፎችን በማቅረብ ሀሳብ እንዲያሰባስቡ ማድረግ፣ ባገኙት ሀሳብ መሰረትነትም ቢጋር እንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡ በዚህም የእያንዳንዱን ተማሪ ስራ መከታተልና አስተያየት እየሰጡ ማረም የመምህሩ(ሯ) ዋነኛ ተግባራት ናቸው፡፡

***ተማሪዎች፦***የመረጡትን ርዕስ ለመምህራቸው በማሳየት እንደሚሰሩበት በጋራ ይወስናሉ፡፡ ቀጥሎም በርዕሳቸው ዙሪያ ከተለያዩ ምንጮች ሀሳቦችን በማሰባሰብ በተማሩትና በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት ቢጋር (አስተዋጽኦ) ይነድፋሉ፡፡ በመጨረሻም ስራቸውን ለመምህራቸውና ለጓደኞቻቸው አቅርበው እርማትና ማበረታቻ ይቀበላሉ፡፡

**የአጻጻፍ ስርኣት፦ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ**

**ተግባርለ.** ካሳ እየተንደረደረ መጣ፡፡ አልማዝ የገዛችዉ ቦርሳ ያምራል፡፡ ሰላም በትምህርቷ ጎበዝ ናት፡፡ ዳንኤል የቡድናችን መሪ ነው፡፡ ሉሊትና ጂዎን ጓደኞሞች ናቸው፡፡

**አቀራረብ.**

***መምህሩ(ሯ)፦***በክፍል አንድ እንደታየው ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መጽሀፍ ገጽ 19 ላይ መምህሩ አረፍተ ነገሮችን አዘጋጅቶ እንዲያነብ ተማሪዎች ደግሞ አዳምጠው

እንዲጽፉ ያዝዛል፡፡ ነገር ግን ተጠኚዎች መስማት የሳናቸው ተማዎች እንደመሆናቸው

በንባብ ምትክ የምልክት ቋንቋን አሊያም ቻርቶችን በማቅረብ አረፍተ ነገሮችን በግላቸው እንዲጽፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

***ተማሪዎች፦*** መምህራቸው በምልክት ቋንቋ ከሚነግራቸው ወይም በቻርት ከተመለከቱት በመነሳት አረፍተ ነገሮችን በየግላቸው ይጽፋሉ፡፡

***መምህሩ(ሯ)፦***ተማሪዎች በጻፏቸው አረፍተ ነገሮች ላይ ምን ያህል እንደተሳሳቱና ትክክል እንደሆኑ ለማረጋገጥ ሰሌዳ ላይ እየጻፉ እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ማመቻቸትና ምግበ ምላሽ በመስጠት ትምህርቱን ማጠቃለል፡፡ በአረፍተ ነገር አጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ከሚሰጣቸው ለምሳሌ የቃላት፣ የሆሄያት አቀማመጥ፣ የባለቤትና የግስ ስምምነት እንዳስፈላጊነቱ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ወ.ዘ.ተ ይጠቀሳሉ፡፡

***ማስተማሪያ መሳሪያ*** ፦ ከለር ቾክ፣ ቻርት ፣ የተለያዩ ሞዴል ጽሁፎች

***ግምገማ*** ፦ በክፍል አንድ ላይ በተገለጸው መልኩ ይከናወናል፡፡

## ክፍል አምስት፦ከሁለት የበለጡ አንቀጾችን መጻፍ

***ተግባር ሀ.*** ቀደም ሲል በክፍል ሁለት ስለቢጋር አነዳደፍ ከተማሩ በኂላ ከተሰጧቸው ርዕሶች አንዱን በመምረጥ አስተዋጽኦ መጻፋቸው ይታወሳል፡፡ በዚያም መነሻነት የትምህርቱን ቅደም ተከተላዊ እድገት በጠበቀ ሁኔታ ማለትም እንደ መስተጋብራዊ ዘዴ መርህ ሂደቱን ከቀላል ወደ ከባድ በማደራጀት በዚህ ክፍል ባለሁለት አንቀጽ ድርሰት እንዲጽፉ ማበረታታት ይጠበቃል፡፡

**አቀራረብ**

***መምህሯ (ሩ)፦*** ከፍ ሲል እንደተገለጸው በመጻፍ ትምህርት ልምምድ ወቅት ከቅድመ ጽህፈት እስከ ድህረ ጽህፈት ባለዉ ክንዉን ሂደቱ ሊያልፍባቸው የሚገቡ እንደ ማቀድ፣ማደራጀት፣ መጻፍ፣ መተርጎም፣ መከለስና አርትኦት ማድረግ የተባሉ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህ ተግባራትም በዚህ የትምህርት ክፍል እንዲከናወኑ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ***መምህሩ(ሯ)*** ተማሪዎች በእያንዳንዱ የጽህፈት ደረጃ ምን መስራት እንዳለባቸው? ማሳወቅ፣ ያልገባቸውን በትርጎማ (በምልክት ቋንቋ) ማስረዳት፣ ባጠቃላይ ስራቸውን በትጋት እየተከታተሉ ማገዝ ይገባል፡፡ለምሳሌ **ድርቅ** በሚለው ርዕስ ሊጽፍ የፈለገ አንድ ተማሪ ***በቅድመ ጽህፈት ደረጃ*** ከሚጠበቅበት ተግባር የመጀመሪያው ስለድርቅ የሚያወሱ መረጃዎችን በመምህሩ ታግዞ ከተለያዩ

ምንጮች መረጃዎችን ማሰባሰብ ነዉ፡፡ ቀጥሎም የሰበሰበውን መረጃ እንደአስፈላጊነታቸው መጠን በቅደም ተከተል ያደራጃል፡፡ ይህ ሲባል የተገኙ መረጃዎች ሁሉ ለጽሁፍ ስራ አይውሉም በዝተዉ እንዳያስቸግሩ አንሰውም ሊባል የተፈለገው ሀሳብ እንዳይቀር ጠቃሚና የማይቀሩትን መምረጥ ይገባል፡፡ የድርቅ ምንነት፣ አጋላጭ ነገሮች፣ የሚያስከትለው ጉዳት፣ መከላከያ መንገዶቹ ወ.ዘ.ተ ጉዳዮች በርዕሱ ላይ ለሚጽፈው ተማሪ ማተኮሪያ ሃሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ መልኩ በቅደም ተከተል ተደራጁትን ዋናና ንዑስ ሀሳቦችን በቢጋር ቅርጽ ማስቀመጥ የተማሪው ቀጣይ ተግባር ይሆናል፡፡**ይህ በመስተጋብራዊ ዘዴ የማቀድና ማደራጀት የጽህፈት ትምህርት ደረጃ ይባላል፡፡**

የቅደመ ጽህፈት ተግባሩን በዚህ መልኩ ያለፈው ተማሪ **በጊዜ ጽህፈቱ ወቅት** ደግሞ

ከሚያከናውናቸው ተግባራት የመጀመሪያው **ድርቅን** በተመለከተ በቢጋር ቅርጽ አስይዞ

የዘረዘራቸውን ዋናና ንዑስ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ረቂቁን ይጽፋል፡፡ በጽሁፍ ልምምዱ ላይ የሚያስፈልገውን የመምህሩን እረዳታ ለማግኘት የሚልክት ቋንቋ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡**ይህ ደግሞ የትርጎማ ደረጃ ተብሎ ይጠራል፡፡** ሌላው በጊዜ ጽህፈት የተማሪዉ የሚያከናው ነው ተግባር ሃሳብ እንደመጣለት **ስለድርቅ** በጻፈው የመጀመሪያ ረቂቅ ላይ የእርማት ስራ መስራት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የጽሁፍ ስራቸውን እንዲገመግሙበት በመምህራቸው ተዘጋጅቶ የሚሰጣቸዉ መስፈርት ጥቅም ላይ ይዉላል ማለት ነዉ፡፡ ደረጃው ደግሞ **እርትኦት** ይባላል፡፡ የመጨረሻው የተማሪው የጊዜ ጽህፈት ተግባር የሚሆነው በየደረጃው በድርቅ ዙሪያ ያነሳቸው ሃሳቦች ተገቢውን ያጻጻፍ ስርኣት ተከትለው ምን ያህል? እንደተጻፉና ማስተላለፍ የተፈለገውን መልእክት በማስተላለፍ ረገድምን ምን ያህል? ግባቸውን እንደመቱ ለማረጋገጥ የጽሁፍ ስራውን ማስገምገምና ምግበ ምላሽ ተቀብሎ በማሻሻል የመጨረሻ ረቂቁን መጻፍ ነው፡፡ይህም **የክለሳ ደረጃ** በመባል ይጠራል፡፡

***ተማሪዎች፡-*** ከምሳሌው ወጥተን ተግባሩ ከአጠቃላይ ተማሪዎች አንጻር ሲገለጽ በክፍል ሁለት ትምህርታቸው መርጠው ቢጋር በነደፉለት ርዕስ ላይ በመመስረት ባለ ሶስት

አንቀጽ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡ በልምምዳቸው ወቅትም በየደረጃው ለሚያከናውኑት ተግባር

የሚረዷቸው መረጃዎችን ሲፈልጉ መምህራቸውንና ጓደኞቻቸውን እንዲጠይቁ ይጠበቃል፡፡

**መምህሩ (ሯ)፦** የተማሪዎችን የመጨረሻ የጽሁፍ ስራ ሰብስቦ በማረም ምግበ ምላሽ ከሰጠ በኋላ እንደገና አሻሽለው እንዲጽፉ እድል ይሰጣል፡፡ ተግባራትን መደጋገም ደግሞ በአንጻሩ በተማሪዎች ችሎታ ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊ ተጽዕኖ ስላለ ሊዘነጋ አይገባም፡፡

**ተማሪዎች-፦**ከመምህራቸው የተሰጣቸውን አስተያየት በመቀበል ከቀደሙ የተሻለ ጽሁፍ ለመጻፍ ይተጋሉ፡፡

**የአጻጻፍ ስርዓት፦ ስርአተ ነጥቦች**

**ተግባር ለ.** ተማሪዎች ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ስርአተ ነጥቦች በስም ከለዩ በኋላ አገልግሎታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡

ሀ. ሀሎ! እንደምን አለሽ? እኔ ደህና ነኝ፡፡

ለ. ከፊቴ ጥፊ!

መ. "የተማረ ሰው ወድቆ አይወደወቅም" አሉ አቶ ሀምዛ፡፡

ሠ. እሰይ! ደግ አደረግህ!

**አቀራረብ**

**መምህሯ (ሩ)-፦** ተማሪዎች በስርአተ ነጥቦች ላይ ያላቸዉ እውቀት ምን ያህል እንደሆነ? ለማወቅ እያንዳንዳቸው የሚያዉቁትን የስርኣተ ነጥብ አይነትና አገልግሎት ስሌዳ ላይ እንዲጽፉ ማድረግና ማወያየት እንዲሁም ለጋራ ግንዛቤ እንዲሆናቸው የስርአተ ነጥቦች አይነትና አገልግሎትን የሚያሳይ ዕይታዊ መግለጫ ማቅረብ፡፡ ቀጥሎም ጥንድ ጥንድ ሆነው

የተሰጣቸውን ተግባር እንዲያከናዉኑ ማድረግና ስራቸውን እየተከታተሉ መደገፍ፡

በመጨረሻም ከሌሎች ጥንድ አቻ ተማሪዎች ጋር ስራቸዉን ተቀያይረዉ እንዲተራረሙ

ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

**ተማሪዎች፦** ከዚህ ቀደም የሚያዉቋቸዉን ስርአተ ነጥቦችና አገልግሎታቸው ጽፈው

ለመምህራቸውና ለጓደኞቻቸው ያሳያሉ፡፡ መምህራቸው የሚስረዳቸውንም

ይከታተላሉ፡፡የተሰጣቸዉን ተግባርም ጥንድ ሆነዉ በመስራት ስራቸዉን ያስገመግማሉ፡፡

የሚሰጣቸዉን ምግበ ምላሽም ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

***ማስተማሪያ መሳሪያ፦*** ቻርቶች፣ ማርከር፣ ፍላሽ ካርዶች

***ግምገማ*** ፦ በየጽህፈት ልምምዱ ተማሪዎች የሚያከናውኑት የጽሁፍ ስራዎች እየታረሙና እየተከለሱ በእያንዳንዱ ተማሪ የግል ማህደረ ተግባር (Portfolio) ሲሰነዱ ጎን ለጎንም ውጤት እየተሰጣቸው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይሁንና የትምህርቱ ዋና አላማ

የተማሪዎችን ችሎታ ወደ ተሸለ ደረጃ ማድረስ እንደመሆኑ ውጤትን ከማከማቸት ይልቅ

በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ተማሪዎች በሚያደረጓቸው ልምምዶች ላይ ከፍተኛ

ትኩረት ይሰጣል፡፡

## ክፍል ስድስት፦ የዋናና ዝርዝር ሀሳቦች አወቃቀር

***ተግባር ሀ.*** ከታች የቀረበውን ሀሳብ ተማሪዎች በጥሞና እንዲያነቡት ከተደረገ በኋላ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲለዩና በዚያም ዙሪያ ከመምህራችሁና ከጓደኞቻችሁ ጋር እንዲወያዩ ማመቻቸት የመምህሩ ተቀዳሚ ተግባር ይሆናል፡፡ህይወት ላላቸው ነገሮች ከሚያስፈልጉ ንጥረነገሮች ዋነኛዉ ዉሃ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሰዎች፣ እንስሳትና ዕጽዋት በህይወት ለመኖር ውሀ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሰዎች ውሀን ለመጠጥ፣ የግልን ጽህናን ለመጠበቅ፣ ምግብ ለማብሰልና ቁሳቁሶችን ለማጽዳት ይገለገሉበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ውሀ ለሃይል ምንጭነት፣ ለመስኖ፣ ለደን ልማት፣ ለእርሻ ሰብልና ለመሳሰሉት በጣም ጠቃሚ

ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ውሀ ለሰው ልጆችና ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ እንደትልቅ ሃብት

ይቆጠራል፡፡

**አቀራረብ**

***መምህሯ*** (ሩ)፦በክፍል አንድ አንቀጽ በመጻፍ ሂደት የዋናና ዝርዝር ሃሳቦች መገኛ ቦታና

አገልግሎታቸው የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን

መጀመር፡፡ ለበለጠ ግንዛቤም በቻርት ላይ የተጻፉ ሞዴል ጽሁፎችን (አንቀጾችን) በማቅረብ የዋናና ዝርዝር ሃሳቦች መገኛ ቦታን በከለር እያሰመሩ ማሳየትና አገልግሎታቸውንም በምልክት ቋንቋ በማስረዳት ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

**ተማሪዎች፡-**ስለዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ጠቀሜታና መገኛ ቦታቸው ቀደም ሲል የተማሩትን መሰረት በማድረግ ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡በምልክት ቋንቋ ታግዞ የሚደረግላቸውን ገለጻና በእይታ የቀረበላቸውን ሃሳብ ለመረዳት ይሞክራሉ፡፡

**መምህሩ (ሯ)፡-**ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል በተሰጣቸው አንቀጽ ላይ ተወያይተው ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡

**ተማሪዎች** ፡-በአንቀጹ ላይ ከተወያዩ በኋላ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ወስነው በቡድን መሪያቸው አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡

**መምህሯ(ሩ)፡-** ተማሪዎች በሚያቀርቡት ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ ምግበ ምላሾችንና ከክፍል ውጪ ሊለማመዱባቸው የሚችሉ ተመሳሳይ ተግባራትን መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ስለሆነም መምህር(ት) ከዚህ በታች የቀረበዉን ተግባር ተማሪዎች እንዲያከናውኑ አዝዟቸው፡፡**

**የቤት ስራ**

የሚከተለውን አጭር የቢጋር ንድፍ በመጠቀም <u>ስደት</u> በሚል ርዕስ አራት አንቀጾች ያሉት ድርሰት ጻፉ፡፡

የአንቀጽ አንድ ዋና ሀሳብ፡- **የስደት ምንነት**

የአንቀጽ ሁለት ዋና ሀሳብ፡- **የስደት መንስኤዎች**

የአንቀጽ ሶስት ዋና ሀሳብ፡- **የሚያስከትላቸዉ ችግሮች**

የአንቀጽ አራት ዋና ሀሳብ፡- **መፍትሔዎች**

**ተማሪዎች፡-**ለእያንዳንዱ ዋና ሀሳብ አበልጻጊ ዝርዝር ሃሳቦችን በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም የተሟላ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ ስራቸውንም ለጓደኞቻቸውና ለመምህራቸው ያስገመግማሉ፡፡

**የአጻጻፍ ስርኣት፦ ስርኣተ ነጥብ**

**ተግባር ለ.** ተማሪዎች የሚከተሉትን ስርአተ ነጥቦች በአግባቡ በመጠቀም አንቀጹን እንደገና እንዲጽፉ ማበረታታት፡፡

| | |
|---|---|
| ፡፡ አራት ነጥብ<br>“ ” ትምዕርተ ጥቅስ<br>. አንድ ነጥብ | ! ትምዕርተ ስላቅ<br>- ንዑስ ጭረት |

የአለም ቲቢ ቀን በየአመቱ የሚከበረው የተለያዩ መሪ ቃላትንና መፈክሮችን በማንገብ ነው፡፡ለምሳሌ እአአ ከ2010 2011 እንደ መሪ ቃል የተመረጠው በአዲስ አስተሳሰብና ፍጥነት ቲቢን እንግታ የሚል ነው ይህ የጸረ ቲቢ እንቅስሴ ዘመናዊና ቀልጣፋ የላቦራቶሪ ምርመራ ዘዴዎች በስራ ላይ መዋል እንዳለባቸውም ይጠቁማል

**አቀራረብ**

***መምህሩ (ሯ)፦***ተማሪዎችን በጥንድ በማደራጀት የአንቀጹን ሃሳብ ከስርኣተ ነጥብ አጠቃቀም አንጻር ያለበትን ግድፈት እንዲለዩና አርመው እንዲጽፉ ማደረግ፡፡ እንዲሁም እርስ በእርሳቸው እንዲማማሩ ይረዳ ዘንድ ስራቸውን ተቀያይረው አስተያየት እንዲሰጣጡ ማመቻቸት፡፡

***ተማሪዎች፦***ጥንድ ጥንድ በመሆን በአንቀጹ ሃሳብ ላይ በመወያየት የስርኣተ ነጥብ አጠቃቀም ግድፈቱን በመለየት እንደገና አሻሽለው ይጽፋሉ፡፡ ቀጥሎም ከሌሎች የቡድን አባላት ጋር ስራቸውን በመቀያየር ይገማገማሉ፡፡

***የማስተማሪያ መሳሪያዎች፦*** ከለር ቾክ፣ ቻርቶች፣ ባጠቃላይ እይታዊ መሳሪያዎች ጥቅም ላይይዉላሉ

***ግምገማ፦***በሌሎች ክፍሎች የተገለጹት በዚህም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሰባት ፦ በምክንያትና ውጤት ስልት አንቀጽ መጻፍ

**ተግባር ሀ.** ተማሪዎች በምክንያትና በዉጤት ዙሪያ የቀረበውን የማብራሪያ ጽሁፍ

እንዲያነቡ ማድረግና ተጨማሪ ገለጻና ምሳሌ በምልክት ቋንቋ መስጠት፡፡

# ማስታወሻ

በማንኛውም ጉዳይ ቢታይ ውጤት ከእርሱ በፊት ቀድመው በሚመጡ ምክንያቶች ወይም መንስኤዎች ሊመጣ የሚችል ሲሆን በአንጻሩ መንስኤዉ ደግሞ ለውጤቱ መምጣት ሰበብ የሚሆነው ነው፡፡ በድርሰት ውስጥም ይህ ሁኔታ ይነሳል፡፡ የድርሰት ውጤት በታሪክ ሂደት ምን ተከሰተ? ምን ሆነ? ሚለውን ጥያቄ ይዘን ስንነሳ የምናገኘው መልስ ሲሆን መንስኤው ደግሞ ለተከሰተው ወይም ለሆነው ነገር መነሻው ምንድነው? ለሚለው መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ መንስኤና ውጤት ተነጣጥለው የማይኖሩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደመሆናቸው ተጓድለው በተገኙበት አውድ የሚነገረውን ሀሳብ ሲሸርፉት ይስተዋላል፡፡

**ለምሳሌ 1፦**

| <u>መንስኤ</u> | <u>ውጤት</u> |
|---|---|
| ➢ የአልኮል መጠጥ ሱስ | - ምጣኔ ሀብትን ያናጋል፡፡ |
| | - ለአደገኛ ወንጀሎች |
| | - ለሞት ይዳርጋል |

❖ ከላይ ስለመንስኤና ውጤት ምንነትና ተዛምዶ የቀረበውን ሀሳብ ሊያጠናክርላቸው የሚችል የተለያዩ ምሳሌዎችን እንዲመለከቱ ከተደረገ በኋላ ርእሶችን በማቅረብ በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡

**ምሳሌ 2፦** ጫት መቃም በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ በአእምሮ ላይ ከፍተኛ መነቃቃትን ፈጥሮ እንደገና ወደ ድብርት በመክተት መረበሽና አለመረጋጋትን ያመጣል፡፡ በሂደትም የሆድና የአንጀት ድርቀትን ያስከትላል፡፡ በተዋስያን ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን በማዳከም ለተለያዩ ጉዳቶች ያጋልጣል፡፡ የምግብ ፍላጎት እንዲቀንስ ከማድረጉም በተጨማሪ ጉበትና ቲቢ ለተባሉ ከባድ በሽታዎች ይዳርጋል፡፡

| <u>መንስኤ</u> | <u>ውጤት</u> |
|---|---|
| **- ጫት መቃም** | **- ድብርት** |
| | **- የሆድ ዕቃ ድርቀት** |
| | **- የመከላከል አቅም ማዳከም** |

**አቀራረብ**

***መምህሯ*** (ሩ)፦ተማሪዎች መንስኤና ውጤት በድርሰት ውስጥ እንዴት እንደሚመጡ? ቅደም ተከተላዊ ስርአታቸውን፣ አስፈላጊነታቸውን ወ.ዘ.ተ በተለያዩ ምሳሌዎችና አስረጂ ጽሁፎች በመጠቀም ማስረዳት ይጠበቃል፡፡ ትምህርቱን አሳታፊ ለማድረግም ለምሳሌ እያንዳንዱን ተማሪ በተናጥል በማስነሳት በምክንያትና በውጤት የተጋመዱ አረፍተ

ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡ በሂደትም መዋቅሩን እያሳደጉት እንዲሄዱ መረዳት፡፡

***ተማሪዎች፦*** በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ መምህራቸው በምልክት ቋንቋ የሚሰጧቸውን ገለጻና ማስታወሻ መቀበል፡፡ ያልገባቸውን መጠየቅ፡፡ ምክንያትና ውጤትን የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች ምስረታው ላይም በንቃት መሳተፍ፡፡

**የክፍል ስራ ፦**

***መምህር ተማሪዎች*** **"ጦርነት"** የሚለውን ርዕሰ መነሻ አድርገው በምክንያትና ውጤት ስልት ሁለት አንቀጽ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

**የአጻጻፍ ስርአት፦ የቃላት አወቃቀር ስርአት በአረፍተ ነገር ውስጥ**

**ተግባር ለ.** የቃላትን ቅደም ተከተል እንደገና በማዋቀር አረፍተ ነገሩን በትክክል መጻፍ፡፡

ሀ. ያዛባል የአእምሮ ስርአት ጫት፡፡

ለ. በግብርና ስራ ቢሰማሩ ውጤታማ ይሆናሉ የተማሩ ሰዎች፡፡

ሐ. የስራ ባህልን ስለሚጎዳ ለሃገርም ሆነ ለግለሰብ እድገት ጸር ነው ጫትመቃም፡፡

መ. ያጋልጣል የአልኮል መጠጥ ስካር ስለሚያስከትል ለጠብ፣ ለስርቆትና ለሌሎች አደገኛ ወንጀሎች፡፡

ሠ. ሁለት ሰዓት ብቻ ነው ሳይጨርሱ መቆየት የሚችሉት ሱስ ያለባቸው ሰዎች፡፡

**አቀራረብ**

**መምህሩ (ሯ)**፦ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በማደራጀት ከላይ በቀረቡላቸው አረፍተ ነገሮችላይ እንዲወያዩ በማድረግ በአወቃቀራቸው ላይ የታየውን ስህተት ነቅሰው እንዲያወጡ ማድረግ፡፡ ቀጥሎም በዉይይታቸው ተስማምተው እንደገና በትክክለኛ የአጻጻፍ ስርአታቸው የጻፏቸውን አረፍተ ነገሮች ለመምህራቸውና ለሌሎች ተማሪዎች በምልክት ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በምልክት ቋንቋ ታግዘው እንዲያስረዱ ማድረግ፡፡ በምክንያትና ውጤትስልት ድርሰት እንዲጽፉ

**ተማሪዎች**፦ ከቡድን አባላቶቻቸው ጋር በመሆን ተወያይተውና ተስማምተው አስተካክለው የጻፏቸውን አረፍተ ነገሮች ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለመምህራቸውና ለጓደኞቻቸው ያስረዳሉ የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብለውም ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች**፦ የተማሪዎችን ግንዛቤ ሊያፋጥኑ የሚችሉ ዕይታዊ ክንውኖችና መጻፊያ ማርከሮች፣ ማንበቢያ ቻርቶች ወይም የወረቀት ጽሁፎች

**ግምገማ**፦ተማሪዎች በልምምዳቸው ወቅት የሚያከናውኗቸው ተግባራት እንዳስፈላጊነታቸው በተከታታይ ይመዘናሉ፡፡

## ክፍል ስምንት፦የግጥም ስንኞችን አሟልቶ መጻፍ

**ተግባር ሀ.** ቀጥሎ ለቀረቡት ስንኞች ለእያንዳንዳቸው ተስማሚ የሚሆኑ ሌሎች ስንኞችን ተማሪዎች ከራሳቸው እያፈለቁ እንዲጽፉ ማገዝ፡፡

**ትምህርት ቤቴ**

ሀ. ትምህርት ቤቴ ፍቅሬን ልግለጽልሽ፣

---------------------------------------------

ለ. ራዕየን ላሳካ በትምህርት ገበታ፣

--------------------------------------------

ሐ. የህይወቴ ለዋጭ ፍጹም መድሃኒቴ፣

-------------------------------------------

መ. መሰረት ሆነሽኝ ጠንክሬ እንድሰራ፣

-------------------------------------

ሠ. ታሪክን አዉቄ ህዝቦችን እንዳከብር፣

--------------------------------------------

ረ. ፍቅርሽን መግለጫ ቃላት ቢያጥረኝም፣

--------------------------------------------

ሰ. እጠብቅሻለሁ ኑሪልኝ እናቴ ------------------------------------------

**አቀራረብ**

***መምህሩ*** **(ሯ)፦** ከዚህ በፊት ተማሪዎች ስለ ግጥም የአጻጻፍ ስልቶች ከሚያውቁት ለመነሳት ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲያስታውሱ ማድረግና ተጨማሪ ማጠናከሪያ ገለጻ በምልክት ቋንቋ መስጠት፡፡

***ተማሪዎች*****፦**ስለግጥም አጻጻፍ የሚያውቁትን ለማስታወስ በቡድን በመወያየት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡ በኋላም የመምህራቸውን ገለጻ በመከታተል እዉቀታቸውን ያጠናክራሉ፡፡

***መምህሯ*** **(ሩ)፦**ተማሪዎችን በጥንድ ጥንድ ማደራጀትና ለጽህፈት ልምምዱ ከቀረቡት መልመጃዎች መካከል አንዱን ወይም ሁለቱን በምሳሌነት በማሳየትና የሚሰሩት ተግባር ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ሌሎች አስረጂዎችን በማከል ማለትም የግጥምን የአጻጻፍ ስርኣት የሚያስረዱ ሞዴል ጽሁፎችን በማቅረብ ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

***ተማሪዎች*****፦**ሁለት ሁለት ሆነው መምህራቸው እንዲያነቡ በሚሰጧቸው ሞዴል ጽሁፎች ላይ ስለግጥም የአጻጻፍ ባህሪይ ይወያያሉ፡፡ ያልገባቸው ነገር ካለ ይጠይቃሉ፡፡ በመቀጠልም ሚልተው እንዲጽፏቸው የቀረቡላቸውን የግጥም ስንኞች በመጻፍ ለመምህራቸውና ለክፍል ጓደኞቻቸው በማሳየት ምግበ ምላሽ ይቀበላሉ፡፡

**የአጻጻፍ ስርአት፦ የግጥም ስንኞችን ማደራጀት**

**ተግባር ለ. መምህር** ቀጥሎ ተዘበራርቀው የተቀመጡ ስንኞችን በማቀናጀትና ተገቢ ስርአተ ነጥቦችን በማሟላት እንደገና እንዲጽፉ ተማሪዎችን አበረታቷቸው፡፡

**ጽጌሬዳና ዳመና**

አንዲት ጽጌሬዳ ቃሏን አስተዛዝና

የጸሃይ ንዳድ ያቃጠላት በብዙ

እንዲህ ተናገረች ለሰማይ ዳመና

ጠውልጎ የሚታይ የቅጠሏ ወዙ

እባክህ ጣልልኝ የዝናብ ጠብታ

ምንም ተስፋ የለኝ መሞቴ ነውና

ቶሎ ካላራስከኝ ጉልበቴ እንዲጠና

ድርቀት በጣም ጎድቶኝ እየኝ ስንገላታ

እዘንብልሻለሁ ጠብቂኝ እያለ

ምንም ሳይጥልላት መንገዱን ቀጠለ

አሁን መሄዴ ነው ለትልቅ ጉዳይ

ስመለስ መጥቼ ሳልፍ ባንቺ ላይ

(ከበደ ሚካኤል፣1999፡፡ታሪክና ምሳሌ ፩ኛ መጽሀፍ፡፡፩ኛ መጽሀፍ ፪ኛ እትም፣ገጽ33 በከፊል የተወሰደ፡፡)

**አቀራረብ**

**መምህሩ (ሯ)፦**ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል በመጀመሪያ በግጥሙ ሃሳብ ላይ እንዲወያዩ ማድረግና እንዴት አድርገው አደራጅተው መጻፍ እንዳለባቸው ማስረዳት፡፡ ልምምዳቸውንም እየተዘዋወሩ መመልከት፣ ሲጨርሱም ስራቸውን ተቀያይረው አስተያየት እንዲሰጣጡና እንዲተራረሙ ማድረግ፡፡ በየትኛውም መልኩ ተማሪዎች እርስ በእርስ እንዲገማገሙ ሲደረግ አላማው አቅጣጫውን እንዳይስት በማረሚያ መስፈርቱ ላይ የጋራ ቅድመ ስምምነት ሊደረግ ይገባል፡፡

**ተማሪዎች፦** በቡድን በመሆን የግጥሙን ሃሳብ ለመረዳት መወያየት፡፡ ሀሳቡን እንደተረዱ ካረጋገጡ በኋላ ወደ ቀጣዩ የማደራጀት ስራቸው መሸጋገር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የማደራጀቱን ስራከጨረሱም በኋላ ከሌሎች የቡድን አባላት ጋር ጽሁፋቸውን በመቀያየር አስተያየት ይቀባበላሉ፡፡ በመጨረሻም ለመምህራቸው አሳይተው ትክክለኛውን ምግበ መላሽ ይወስዳሉ፡፡

**ማስተማሪያ ዘዴ፦** እይታን ያማከሉ የጽሁፍ መሳሪያዎችና ሞዴል ጽሁፎች

**ግምገማ፦** ተማሪዎች እርስ በእርስ የሚያደረጓቸዉ የሃሳብ ልውውጦችና መምህራኑ በተከታታይ እያረሙና ምግበ ምላሽ እየሰጡ የሚሰንዷቸው የጽሁፍ ስራዎች የምዘናው አካል ናቸው፡፡

## ክፍል ዘጠኝ፦ ግለ ታሪክ መጻፍ

**ተግባር ሀ.** ቀጥሎ ስለ ግለ ታሪክ አጻጻፍ የሚገልጽ አጭር ጽሁፍ አለ፡፡ ይህንን ጽሁፍ ተማሪዎች በእርጋታ እንዲያነቡት ማድረግና ባገኙት ፍንጭ ላይ ተመስርተዉ የራሳቸውን ማንነት (ግለ ታሪክ) የሚገልጽ ተራኪ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማገዝ፡፡

**ማስታወሻ**

ግለ ታሪክ ከህይወት ታሪክ ብዙ የተለየ አይደለም፡፡ የሚለየው ግለሰቡ የራሱን የህይወት ታሪክ በመጻፉ ነው፡፡ ግለ ታሪክ በቅደም ተከተል በተደራጁ የጸሀፊው የህይወት ገጠመኞች ትርክት ከመሆኑ ባሻገር በዉስጡም ሊያካትታቸው የሚገቡ ቁም ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም ለምሳሌ የባለታሪኩ ስም፣ የትውልድ ቀንና ስፍራ፣ የአስተዳደግ ሁኔታና የትምህርት ቤት ቆይታ፣ የህይወት ገጠመኝ፣ የግል አመለካከት፣ የቤተሰብ ሁኔታ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

(ምንጭ፣ በ2007 ዓም ከተሻሻለው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ የተማሪው መጽሀፍ የተወሰደ፡፡)

**አቀራረብ**

***መምህሩ (ሯ)፦*** የህይወት ታሪክ እንዴት እንደሚጻፍ መግለጽና ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስላላቸው የአጻጻፍ ልምድ መወያየት፡፡ ቀጥሎም በተለያዩ ግለሰቦች ላይ የተጻፉ ግለ ታሪኮችን እንዲያነቡ ሞዴል ጽሁፎችን መስጠት፡፡በንባብ ካገኙት እውቀት በመነሳትም የራሳቸውን ግለታሪክ እንዲጽፉ ማበረታታት፡፡ በእያንዳንዱ የጽህፈት ልምምድ ደረጃ የሚያከናውኑትን ተግባር በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም ስራቸውን በመገምገም ምግበ ምላሽ መስጠት ይጠበቃል፡፡

***ተማሪዎች፦*** ለስራቸው ይረዷቸው ዘንድ በአስረጂነት በቀረቡት ሞዴል ጽሁፎች ላይ ጥልቅ ንባብ ማካሄድና ከጨበጡት እውቀት በመነሳት የራሳቸውን ግለ ታሪክ ይጽፋሉ፡፡ በሂደቱም ለሚያጋጥማቸው ችግር ከመምህራቸው ጋር መፍትሄ እየሰጡ ያልፋሉ፡፡ በልምምዱ ያረቀቁትን፣ የከለሱትንና አርትኦት የሰጡበትን የጽሁፍ ስራ ለመምህራቸው በማሳየት ምግበ ምላሽ ይቀበላሉ፡፡

***የአጻጻፍ ስርአት፦   በአረፍተ ነገር አወቃቀር ውስጥ የሆሄያት አጻጻፍ ስርአት***

***ተግባር ለ. መምህር*** ተማሪዎች ቀጥሎ በተሰጡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የፊደላት ግድፈት (ስህተት) የሚታይባቸውን ቃላት በማረም አስተካክለው እንዲጽፉ ብታደርጉ፡፡

ሀ. በደሮው ጊዜ የነበረውን የአገራችንን የትምህርት ስርዓት አብርታችሁ ግለጹ፡፡

ለ. አገራችን ምጣኔ ሀብታዊዋን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለዩ የማዕድን
   አይኖች አሏት፡፡

ሐ. ተማሪ በምን አይነት ሁኔታ ሊሳተፍ እንዲችል ተናገሩ፡፡

መ. ውሀን በግብ አጠራቅሞ ማቆየት፣ ማጣራትን ማራጨት ከፍተኛ ወጪ
   ይጠይቃል፡፡

**አቀራረብ**

***መምህሯ*** (ሩ)፦ተማሪዎችን በጥንድ በማጣመር በተሰጣቸው ተግባር ላይ እንዲወያዩ ማስተባበርና ስራቸውን እየተከታተሉ ማረምና ምግበ ምላሽ መሰጠት፡፡ ሆሄያትን በተመለከተ እንግዳ ሊሆኑባቸው የሚችሉ አወቃቀሮች ያሉ ከሆነ የፊደል ገበታ በመጠቀም ማስረዳት፡፡

***ተማሪዎች፦*** የተሰጣቸውን ተግባር ለሁለት በመቀናጀት መከወን፡፡ በልምምዳቸው ወቅት ያልገባቸው ነገር ካለ መምህራቸውን መጠየቅና ስራቸውን ሲያጠናቅቁ በመጀመሪያ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተቀያይረው ይተራረማሉ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ለመምህራቸው በማቅረብ ማጠቃለያ አስተያየት ይወሰወዳሉ፡፡

***የማስተማሪያ*** **ዘዴ፦** ከለር ቾክ፣ የፊደል ገበታ፣ ሞዴል ጽሁፎች

***ግምገማ*** ፦ ተማሪዎች እርስ በእርስ የሚያደረጓቸዉ የሃሳብ ልውውጦችና መምህራኑ በተከታታይ እያረሙና ምግበ ምላሽ እየሰጡ የሚሰንዷቸው የጽሁፍ ስራዎች የምዘናው አካል ናቸው፡፡

## ክፍል አስር፦ የደብዳቤ አጻጻፍ

***ተግባር ሀ. መምህር*** ከዚህ በታች የስራ ደብዳቤ ምንነትንና የአጻጻፍ ስልቱን በተመለከተ አስረጂ ጽሁፍ ቀርቧል፡፡ በአጻጻፍ መመሪያው ላይ ተማሪዎች ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር ተወያይተው ከተረዱ በኋላ ራሳቸውን በአንድ መስሪያ ቤት በጸሀፊነት ለመቀጠር እንደሚያመለክት ስራ ፈላጊ በማሰብ የስራ ቅጥር ማመልከቻ እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡

**የስራ ደብዳቤ አጻጻፍ**

ብዙ የደብዳቢ አይነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የስራ ደብዳቤ አንዱ ነው፡፡ የስራ ደብዳቤ በተለያዩ የግልም ሆነ የመንግስት ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች ወ.ዘ.ተ ይጻፋል፡፡ የስራ ደብዳቤ ለተለያዩ አላማዎች ሊጻፍ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ዓቢይ ጉዳይ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ለመስጠት፣ የስራ ወይም የይለፍ ፈቃድ ለማስተላለፍ፣ ቅጥር ለመፈጸም፣ ቅጣት ለማሳለፍና ለመሳሰሉት ተግባር ላይ ይውላል፡፡ በአጻጻፍ ስርአቱም የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ሊያሟላ ይገባል፡፡

ሀ. የተጻፈለት ሰው ወይም ክፍል አድራሻ

ለ. የጸሃፊዉ ሰው ስም ወይም ክፍል አድራሻ

ሐ. የተጻፈበት ቀን

መ. የተጻፈበት ርዕሰ ጉዳይ

ሠ. ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት (ሃሳብ)

ረ. የመዝጊያ (ማጠቃለያ) ቃል፡፡ **ምሳሌ ከሰላምታ ጋር! ቃላችንን እንጠብቅ!**

**አቀራረብ**

***መምህሩ(ሯ)፡-*** የስራ ደብዳቤ አጻጻፍ ስልትን ሊያስረዱ የሚችሉ የተለያዩ መልክ ያላቸው ሞዴል ደብዳቤዎችን በወረቀት አባዝቶ ለተማሪዎች በመስጠት በግልና በቡድን እንዲያነቡ ማበረታታት፡፡ ተጨማሪ ገለጻዎችን በማድረግም ሃሳቡን ግልጽ ማድረግ፡፡ ተሰጣቸውን ተግባር ለመተግበር የሚያስችል ደረጃ ላይ እንደደረሱ በመምህሩ ከተረጋገጠ ሁሉም ተማሪዎች የራሳቸው የስራ ደብዳቤ እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡ ስራቸውን ካጠናቀቁ በኂላም ለአቀራረብና ሁሉን አቀፍ አስተያየት ለመቀበል ይችሉ ዘንድ ጽሁፉን ከወረቀት ወደ ቻርት መገልበጥ ይሆናል፡፡ በዚህም እያንዳንዱ ተማሪ የጻፈውን ይዞ በመቆም በምልክት ቋንቋ እየታገዘ ንባብ ያደርጋል ማለት ነው፡፡

***ተማሪዎች፡-*** የስራ ደብዳቤ አጻጻፍ ስልትን በተመለከተ ከመምህራቸው የተሰጣቸውን ማስታወሻና አስረጂ ጽሁፎችን በግልና በቡድን በመሆን እያነበቡ ይወያያሉ፡፡ ማብራሪያዎችን በመከታተል ያልገባቸውን ይጠይቃሉ፡፡ የአጻጻፍ ዘዴውን በደንብ ከተረዱና ለመጻፍ ዝግጁ መሆናቸውን በኂላ በታዘዙት መልኩ ደብዳቤ መጻፍ ይጀምራሉ፡፡ ጽሁፋቸዉን ካጠናቀቁ በኂላም የእያንዳንዳቸውን ስራ ለውይይት ማቅረብ ስለሚያስፈልግ ቅርጹን ከወረቀት ወደ ቻርት መቀየር ይጠበቃል፡፡ ጽብረቃው እንዳለቀም በተሰጣቸው አስተያየት መሰረት የማሻያ ስራ ያከናውናሉ፡፡

**የአጻጻፍ ስርአት፡- የቃላት ሰዋስዋዊ አጠቃቀም በአረፍተ ነገርአውድ ውስጥ**

**ተግባር ለ. መምህር** ተማሪዎች በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በማስተካከል አረፍተ ነገሮችን አስተካክለው እንዲጽፉ አድርጋቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቤተሰቦቹ አቅማቸው (የፈቀደ) እያደረጉለት ነው፡፡

መልስ፡- ቤተሰቦቹ አቅማቸው የፈቀደውን እያደረጉለት ነው፡፡

ሀ. እሷ የሃያ (ዓመታት) ወጣት ናት፡፡

ለ. ትምህርቱን በሚገባ (የማይከታተል) የፈተና ውጤቱ ሁሉ ዝቅተኛ ሆነ፡፡

ሐ. ሰዎች በስራና በእውቀት አራሳቸውን ካላሻሻሉ (ኑሮ) መለወጥ አይችሉም፡፡

መ. የጫት ቤት ባለቤቶች ጫት ቃሚ (ደንበኛ) ይወዷቸዋል፡፡

ሠ. የእሷ ከትምህርት ቤት መቅረት (ጓደኞቿ) ሆነ መምህሮቿን ግራ (ማጋባት) መጣ፡፡

**አቀራረብ**

**መምህሯ(ሩ)፡-**ቃላት በአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርአት ውስጥ ያላቸውን ሚና በተመለከተ

በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻ ማድረግና የተሰጧቸውን መለማመጃ ጥያቄዎች በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ማመቻቸት፡፡ ስራቸውን ምን ያህል ተረድተው እየሰሩ እንዳለም በመከታተል እገዛ መስጠት፡፡ተወያይተው ከጨረሱ በኋም የተስማሙበትን በቡድን መሪያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በማቅረብ ሃሳብና አስተያየት እንዲቀበሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ተማሪዎች፡-**በአረፍተ ነገር ዉስጥ ቃላትን የሰዋሰው ስርአት ሳይፋለስ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ከመምህራቸው የሚሰጣቸውን ገለጻ ይከታተላሉ፡፡ በዚህም ዙሪያ እንዲሰሩ የተሰጣቸውን መልመጃ በቡድን በመሆን ያከናዉናሉ፡፡ በመጨረሻም አስተካከለው የጻፉትን አረፍተ ነገር በቡድን መሪያቸው አማካኝነት ለሌሎች ተማሪዎች በማሳየት አስተያየት ይቀበላሉ፡፡

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-** እይታን የሚያጎሉ ከለር የጽህፈት መሳሪያዎች ፣ ቻርቶች

***ግምገማ፡*** ተማሪዎች እርስ በእርስ የሚያደረጓቸው የሃሳብ ልውውጦችና መምህራኑ በተከታታይ እያረሙና ምግበ ምላሽ እየሰጡ የሚሰንዷቸው የጽሁፍ ስራዎች የምዘናው አካል ናቸው፡፡

## አባሪ ቸ

## በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ የአጠቃላይና የንዑሳን የመጻፍ ክሂል ውጤቶች (የናሙና ጥናት- ቪክትሪ መስማት የተሳናቸው አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት)

- **በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኙ አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች**

| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አማካይ ዉጤት |
|---|---|---|---|
| 01 | 32 | 30 | 31.5 |
| 02 | 44 | 46 | 45 |
| 03 | 21 | 19 | 20 |
| 04 | 49 | 47 | 48 |
| 05 | 31 | 31 | 31 |
| 06 | 20 | 23 | 21.5 |
| 07 | 33 | 30 | 31.5 |

- **በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኙ የንዑስ ክሂሎች ውጤቶች**

| መለያ ቁጥር | ዐ.ነ 20% | አደ.20% | ጅዐ.20% | ስነ.20% | ድር.20% | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 6.5 | 7.5 | 7 | 7 | 3.5 | 31.5 |
| 02 | 3.5 | 10 | 17 | 6 | 8 | 4.5 |
| 03 | 2 | 6 | 0.5 | 7.5 | 4 | 20 |
| 04 | 7 | 11 | 5 | 16 | 9 | 48 |
| 05 | 5.5 | 7.5 | 5 | 8 | 5 | 31 |
| 06 | 2.5 | 4 | 5.5 | 4 | 5.5 | 21.5 |
| 07 | 6 | 7 | 6.5 | 6 | 6 | 31.5 |

- **በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኙ አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች**

| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አማካይ ዉጤት |
|---|---|---|---|
| 01 | 49 | 52 | 50.5 |
| 02 | 55.5 | 56.5 | 56 |
| 03 | 29 | 27 | 28 |
| 04 | 57 | 59 | 58 |
| 05 | 41 | 39 | 40 |
| 06 | 24 | 24 | 24 |
| 07 | 36 | 38 | 37 |

- **በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኙ የንዑስ ክሂሎች ውጤቶች**

| መለያ ቁጥር | ዐነ.20% | አደ.20% | ጅዐ.20% | ሰነ.20% | ድር.20% | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 7.5 | 8.5 | 15 | 15 | 4.5 | 50.5 |
| 02 | 4.5 | 12.5 | 20 | 8 | 11 | 56 |
| 03 | 3 | 5.5 | 5.5 | 9.5 | 4.5 | 28 |
| 04 | 11 | 13 | 7.5 | 16 | 10.5 | 58 |
| 05 | 7.5 | 9.5 | 7 | 10 | 6 | 40 |
| 06 | 3.5 | 5.5 | 5 | 5 | 5 | 24 |
| 07 | 5.5 | 8.5 | 8 | 8 | 7 | 37 |

## አባሪ ጎ

## በቅድመና ድህረ ትምህርቱ ከተጠኚ ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች (የናሙና ጥናት- ቪክትሪ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት)

➢ በቅድመ ትምህርቱ በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች

| መለያ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 4 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 46 |
| 02 | 4 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 47 |
| 03 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 50 |
| 04 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 43 |
| 05 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 42 |
| 06 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 48 |
| 07 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 45 |

➢ በድህረ ትምህርቱ በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች

| መለያ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 1 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 70 |
| 02 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 77 |
| 03 | 4 | 4 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 74 |
| 04 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 77 |
| 05 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 1 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 71 |
| 06 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 73 |
| 07 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 72 |

## አባሪ ነ

## ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ላይ ያስመዘገቡት የአጠቃላይና የንዑሳን የመጻፍ ክሂል ውጤቶች (ዋና ጥናት- አልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት)

### በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ የተገኙ አጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ውጤቶች

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ | መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ |
| 01 | 21 | 17 | 17 | 18.3 | 01 | 35 | 36 | 35 | 35.3 |
| 02 | 34 | 33 | 31 | 32.6 | 02 | 58 | 61 | 59 | 59.3 |
| 03 | 37 | 36 | 35 | 36 | 03 | 66 | 64 | 63 | 64.3 |
| 04 | 43 | 40 | 39 | 40.6 | 04 | 79 | 76 | 77 | 77.3 |
| 05 | 37 | 37 | 37 | 37 | 05 | 66 | 70 | 65 | 67 |
| 06 | 43 | 41 | 41 | 41.6 | 06 | 75 | 72 | 70 | 72.3 |
| 07 | 32 | 35 | 31 | 32.6 | 07 | 59 | 57 | 61 | 59 |

### በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ የተገኙ የንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች ውጤቶች

| | ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አረፍተ ነገር መጻፍ | አረፍተ ነገር ማደራጀት | ጅምር ሀሳብ መጨረስ | ስርዓተ ነጥብ መጠቀም | ድርሰት መጻፍ | አማካይ | መለያ ቁጥር | አረፍተ ነገር መጻፍ | አረፍተ ነገር ማደራጀት | ጅምር ሀሳብ መጨረስ | ስርዓተ ነጥብ መጠቀም | ድርሰት መጻፍ | አማካይ |
| 01 | 3.6 | 4 | 3 | 4.3 | 3.3 | 18.3 | 01 | 8 | 8 | 7 | 7 | 5.3 | 35.3 |
| 02 | 7.3 | 7 | 7.3 | 6 | 5 | 32.6 | 02 | 12 | 11 | 13 | 13.3 | 10 | 59.3 |
| 03 | 8 | 8.3 | 7 | 7 | 5.6 | 36 | 03 | 15 | 15 | 12.3 | 11 | 11 | 64.3 |
| 04 | 9 | 7 | 8.3 | 10.3 | 6 | 40.6 | 04 | 17.6 | 16 | 16 | 15.6 | 12 | 77.3 |
| 05 | 7 | 8.3 | 7.3 | 9.3 | 5 | 37 | 05 | 15 | 15.6 | 12 | 15.3 | 9 | 67 |
| 06 | 9 | 9.6 | 8 | 8.6 | 6.3 | 41.6 | 06 | 17 | 15.6 | 14 | 14.6 | 11.3 | 72.3 |
| 07 | 7 | 7.6 | 5 | 7.6 | 5.3 | 32.6 | 07 | 14 | 12 | 10 | 13 | 10 | 59 |

### ተጠኚ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ላይ በእያንዳንዱ ንዑስ የመጻፍ ክሂል ያስመዘገቡት ዝርዝር ውጤት

- አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ | መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ |
| 01 | 4 | 3 | 4 | 3.6 | 01 | 9 | 8 | 7 | 8 |
| 02 | 8 | 7 | 7 | 7.3 | 02 | 12 | 13 | 11 | 12 |
| 03 | 7 | 9 | 8 | 8 | 03 | 15 | 16 | 14 | 15 |
| 04 | 10 | 9 | 8 | 9 | 04 | 18 | 17 | 18 | 17.6 |
| 05 | 8 | 7 | 6 | 7 | 05 | 15 | 16 | 14 | 15 |
| 06 | 10 | 9 | 8 | 9 | 06 | 18 | 17 | 16 | 17 |
| 07 | 7 | 8 | 6 | 7 | 07 | 13 | 14 | 15 | 14 |

- አረፍተ ነገሮችን በማደራጀት(በማቀናበር) ንዑስ የመጻፍ ክሂል በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ | መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ |
| 01 | 5 | 4 | 3 | 4 | 01 | 7 | 8 | 9 | 8 |
| 02 | 7 | 6 | 8 | 7 | 02 | 11 | 10 | 12 | 11 |
| 03 | 10 | 8 | 7 | 8.3 | 03 | 16 | 14 | 15 | 15 |
| 04 | 8 | 7 | 6 | 7 | 04 | 16 | 15 | 17 | 16 |
| 05 | 8 | 9 | 8 | 8.3 | 05 | 14 | 16 | 17 | 15.6 |
| 06 | 8 | 11 | 10 | 9.6 | 06 | 15 | 16 | 16 | 15.6 |
| 07 | 8 | 8 | 7 | 7.6 | 07 | 12 | 11 | 13 | 12 |

- ጅምር ሀሳብ በመጨረስ ንዑስ የመጻፍ ክሂል በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ | መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ |
| 01 | 4 | 2 | 3 | 3 | 01 | 8 | 6 | 7 | 7 |
| 02 | 7 | 8 | 7 | 7.3 | 02 | 13 | 12 | 14 | 13 |
| 03 | 7 | 6 | 8 | 7 | 03 | 12 | 11 | 14 | 12.3 |
| 04 | 9 | 8 | 8 | 8.3 | 04 | 17 | 16 | 15 | 16 |
| 05 | 7 | 7 | 8 | 7.3 | 05 | 12 | 13 | 11 | 12 |
| 06 | 9 | 7 | 8 | 8 | 06 | 14 | 15 | 13 | 14 |
| 07 | 4 | 6 | 5 | 5 | 07 | 10 | 9 | 11 | 10 |

- ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም ንዑስ የመጻፍ ክሂል በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ | መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ |
| 01 | 5 | 4 | 4 | 4.3 | 01 | 6 | 8 | 7 | 7 |
| 02 | 6 | 7 | 5 | 6 | 02 | 13 | 15 | 12 | 13.3 |
| 03 | 8 | 7 | 6 | 7 | 03 | 13 | 11 | 9 | 11 |
| 04 | 10 | 11 | 10 | 10.3 | 04 | 15 | 16 | 16 | 15.6 |
| 05 | 8 | 9 | 11 | 9.3 | 05 | 15 | 16 | 15 | 15.3 |
| 06 | 10 | 8 | 8 | 8.6 | 06 | 16 | 14 | 14 | 14.6 |
| 07 | 7 | 8 | 8 | 7.6 | 07 | 13 | 14 | 12 | 13 |

- ድርሰት በመጻፍ ንዑስ የመጻፍ ክሂል በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | ድህረ ትምህርት ፈተና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ | መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሶስት | አማካይ |
| 01 | 3 | 4 | 3 | 3.3 | 01 | 5 | 6 | 5 | 5.3 |
| 02 | 6 | 5 | 4 | 5 | 02 | 9 | 11 | 10 | 10 |
| 03 | 5 | 6 | 6 | 5.6 | 03 | 10 | 12 | 11 | 11 |
| 04 | 6 | 5 | 7 | 6 | 04 | 13 | 12 | 11 | 12 |
| 05 | 6 | 5 | 4 | 5 | 05 | 10 | 9 | 8 | 9 |
| 06 | 6 | 6 | 7 | 6.3 | 06 | 12 | 11 | 11 | 11.3 |
| 07 | 6 | 5 | 5 | 5.3 | 07 | 11 | 9 | 10 | 10 |

# አባሪ ኘ

## በቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች (ዋና ጥናት- በአልፋ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ትምህርት ቤት)

- ቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ

| መለያ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 4 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 46 |
| 02 | 4 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 47 |
| 03 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 50 |
| 04 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 43 |
| 05 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 42 |
| 06 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 48 |
| 07 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 45 |

- ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ

| መለያ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 76 |
| 02 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 77 |
| 03 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 78 |
| 04 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 79 |
| 05 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 74 |
| 06 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 69 |
| 07 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 73 |